# ራእየ ፡ ዮሐንስ ።

ራእዩ ፡ ለዮሐንስ ፡ ዘዮሐንስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘቍስጥንጥንያ ፡ መጥሮጶሊስ ፡
አመ ፡ ሀለዎ ፡ ይሰደድ ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ዮሐንስ ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ ተናግሮታል ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ያስተማራቸውን ፡ ገድፈውበት ፡ ለመገሠጽ ፡ መዓርገ ፡ ካህናት ፡ ተሰጥቶት ፡ ወበዐውዱ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ እሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ብሎ ፡ ኋላ ፡ የሚያመጣው ፡ ነው ። የጥጦስ ፡ የሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ የምጽአት ፡ ኋላም ፡ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወምድረ ፡ ሐዳሰ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣው ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ ጥንተ ፡ ነገሩስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኖኅ ፡ ከማየ ፡ አይኅ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የሦስቱ፡ ልጆቹን ፡ ስም ፡ በቅፋፍ፡ ጽፎ ፡ መልአኩን ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ አድርጎ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ቀኝ ፡ ቀኙን ፡ ለያፌት ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ መካከሉን ፡ ለሤም ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ግራ ፡ ግራውን ፡ ለካም ፡ አካፍሏቸዋል ። ያፌት ፡ ይህያንን ፡ ይህያን ፡ ዮትራስስን ፡ ዮትራስስ ፡ እስያን ፡ እስያ ፡ ሰባቱን ፡ ዮናናውያን፡ ይወልዳል ፡ ዮትራስስንስ ፡ ዘውእቱ፡ እስያ ፡ ይለዋል ፡ ብሎ ፡ ያፌት ፡ ይህያንን ፡ ይህያን ፡ እስያን ፡ እስያ ፡ ሰባቱን ፡ ዮናናውያን ፡ ይወልዳል ። በቋንቋቸው ፡ በዮናኒ ፡ ዮናናውያን ፡ ተብለዋል ። ይህስ ፡ ቋንቋ ፡ በሰው ፡ ይጠራል ፡ እንጅ ፡ ሰው ፡ በቋንቋው ፡ አይጠራም ፡ ብሎ ፡ ባባታቸው ፡ በይህያን ፡ ዮናናውያን ፡ ተብለዋል ። በሳዶቅ ፡ ሰዱቃውያን ፡ በይሁዳ ፡ አይሁድ ፡ በኤቦር ፡ ዕብራውያን ፡ በፋሬስ ፡ ፈሪሳውያን ፡ እንደ ፡ ተባሉ ። አንድም ፡ በፀሐይ ፡ ይቆጥሩ ፡ በፀሐይ ፡ ያመልኩ ፡ ነበርና ፡ ዮናናውያን ፡ ተብለዋል ፤ ጥንተ ፡ ዮን ፡ ንድቀተ ፡ ዮን ፡ እንዲል ። አንም ፡ ይላል ፡ ከሰባቱ ፡ ዮናናውያን ፡ በኵሩ ፡ ኤፌሶን ፡ ነው ። ከኤፌሶን ፡ መልክ ፡ ከደም ፡ አስተባብራ ፡ የያዘች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተወለደች ፡ ስሟን ፡ አርጤምስ ፡ አላት ፤ አካለ፡መጠን ፡ ባደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ ትዕቢት ፡ አሳድሮባት ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ ሲላት ፡ መልክህ ፡ ቢያምር ፡ ጥበብ ፡ የለህ ፡ ድሀ ፡ ነህ ፡ ትለዋለች ። ባለጸጋ ፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ ሲላት ፡ ብዕል ፡ ቢኖርህ ፡ ጥበብ ፡ የለህ ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ነህ ፡ ትለዋለች ። ጥበብ ፡ ያለው ፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ ሲላት ፡ ጥበብ ፡ ቢኖርህ ፡ ድሀ ፡ ነህ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ነህ ፡ ትለዋለች ። እንዲህ ፡ እያለች ፡ ስትኖር፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚባል፡ አንድ ፡ ሥራየኛ ፡ ላግባሽ ፡ አላት፡ ለብዙ፡ ባለጸጋ ፡ ለብዙ ፡ ጥበበኛ ፡ ለብዙ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ያልሆነለት ፡ ለአንተ ፡ እንደምን ፡ ይሆንልሃል ፡ አለችው ። መቸስ ፡ አንቺ ፡ የምትሺው ፡ መከበሩን ፡ አይደለምን ፡ እንድትከበሪ፡ ላድርግልሽ ፡ እንጅ፡ ምን ፡ ዕዳሽ ፡ አላት፡ በል ፡ እስቲ ፡ አድርገውና ፡ ልይህ ፡ አለችው ። ዘኢሰገደ ፡ ለአርጤምስ ፡ ይትበርበር ፡ ቤቱ ፡ ወይትህየድ ፡ ንዋዩ ፡ ብሎ ፡ በቅፋፍ ፡ ጽፎ ፡ አጋንንትን ፡ በምስሐቡ ፡ ጠርቶ ፡ ሰው ፡ ሰብስቤ ፡ በማስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ድምፅ ፡ እያሰማችሁ ፡ አምጥታችሁ ፡ ጣሉልኝ ፡ አላቸው ፡ ሕዝቡን ፡ ሰብስቦ ፡ በሚያስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ ድምፅ ፡ እያሰሙ ፡ መጡ ፤ እስቲ ፡ አሻ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ የምሰማው ፡ ድምፅ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ተነሥ

www.ethiopianorthodox.org

ቶ ፡ ቆመ ፡ ጣሉለት ፡ አንሥቶ ፡ አንቦ ፡ ለመቤቴ ፡ ለአርጤምስ ፡ አምላክነቷን ፡
የሚመሰክር፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ከወረደላት ፡ ለመቤቴ ፡ ለአርጤምስ ፡ ሰገድሁ ፡ ብሎ ፡
ሰግዷል ፤ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ሁሉም ፡ ሰግደውላታል ። አንድም ፡ እብ
ነ ፡ መንገኒጦስ ፡ የሚሉት ፡ እንደ ፡ ቆርበት ፡ ሐሊም ፡ ያለ ፡ ነው ። ሰብቆ ፡ ሣር ፡
ሲያሳዩት ፡ ይዞ ፡እንዲነሣ ፡ ያሳዩትን ፡ ሁሉ ፡ የሚያወጣ ፡ ነው ፤ ሲወጣ ፡ አይታ
ይም ፡ ሲወርድ ፡ ይታያል ፡ በዚያ ፡ አንሥቶ ፡ ጥሎለታል ፡ ያን ፡ አንሥቶ ፡ አንቦ ፡
ለእመቤቴ ፡ ለአርጤምስ ፡ አምላክነቷን ፡ የሚመሰክር ፡ ከሰማይ ፡ ከወረደላት ፡ እሰ
ግዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ሰገደላት ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ሰግደውላታል ። እሷን ፡
አግብቶ ፡ ዜውስን ፡ ወልዷል ። ዜውስንም ፡ የአምላክ ፡ ጅል ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡
ሰግደውለታል ። ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ተነሡ ፡ እንዳረጉ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያቸዋል፤
ሥዕላቸውን ፡ ሥለው ፡ ምስላቸውን ፡ መስለው ፡ የሚኖሩ ፡ ሁነዋል ። ያዛቆነ ፡ ሰይ
ጣን ፡ ሳያቀስ ፡ አያርፍም ፡ እንዲሉ ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ሰባቱን ፡ ከዋክብት፡
ፀሓይ ፡ ጨረቃን ፡ ሲያመልኩ ፡ ኑረዋል ፤ ሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ እልሽምሽ ፡ እልቀ
መር ፡ መሪህ ፡ መሸተሪ ፡ ዙሃል ፡ አጣርድ ፡ ዝሑራ ፡ ይባላሉ ፡ ዛሕራም ፡ ይላል ፡ እ
ንዲህ ፡ ሲኖሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልብ ፡ የመከረውን ፡ በነቢያት ፡ ያናገረውን ፡ ለመ
ፈጸም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፡ ብለህ፡ እንደ ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት፡ ተርክ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ሑሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ያለውን ፡ ያውቃሉና ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ዕጣ፡ በዕጣ ፡ ተካፍለው፡ ለ
ማስተማር ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ ምድረ ፡ ዕርአ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ደርሳዋለች ፤
ውጣ፡ አስተምር ፡ አሉት። እኔስ ፡ ብዙ፡ ጣዖት ፡ ከሚመለክበት፡ ሀገር ፡ አልሄድም ፡
አለ ፡ የወትሮ ፡ ፈራሁ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ አንተም ፡ እንጅ ፡ ፍቁረ ፡ እግዚኡ ፡ ለጥ
ብዓት ፡ አብነት ፡ ትሆናለህ ፡ ስንልህ ፡ ለፍርሃት ፡ ለበጎ ፡ አብነት ፡ ትሆናለህ ፡ ስን
ልህ ፡ ለክፋት ፡ አብነት ፡ ትሆናለህን ፡ በዚያውስ ፡ ላይ ፡ ኢትፍርህዎሙኬ ፡ ለእለ ፡
ይቀትሉ ፡ ሥጋክሙ ፡ ያለው ፡ በምን ፡ ይፈጸምልናል ፡ ብሎ ፡ አጸናንቶ ፡ ወስዶ ፡ ከ
ዚያው ፡ አድርሶት ፡ ተመልሷል ፤ እሱም ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ሃይማኖታችሁን፡
ልቀቁ ፡ አይላቸውም ፡ አስቀድሞ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ነገር ፡ ያስተምራቸዋል ፡ ዜ
ውስ ፡ አርጤምስ ፡ ቢሏችሁ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ናቸው ፡ ጥንቱንም ፡ የዕለት ፡ ዐ
ርብ ፡ ፍጥረታት ፡ ናቸው ፤ ዛሬም ፡ ሥጋቸው ፡ በመቃብር ፡ ነፍሳቸው ፡ በገሃነም ፡
ተይዟል ፡ ፀሓይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ ቢሏችሁ፡ ቀድሞም ፡ የዕለተ ፡ ረቡዕ ፡ ፍጥረ
ታት ፡ ናቸው ፡ ኋላም ፡ ኀላፍያን ፡ ናቸው ፤ ሰማዩን ፡ ምድሩን ፡ የብሱን ፡ ባሕሩን ፡
የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ ጌታ ፡ ከፅንስ ፡ ጀምሮ ፡ ያደረገ
ውን ፡ ተአምራት ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራውን ፡ ትሩፋት ፡ ቢነግራ
ቸው ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አም
ልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ ፡ ትምህርት ፡ ካልደረሰበት ፡
ለማዳረስ ፡ በሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ በሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ አንጻር ፡ ሰባት ፡ መንፈሳው
ያን ፡ ከዋክብት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ሹሞላቸው ፡ ሂዷል ። አንጾኪያን ፡ አስተምሮ ፡
ሶርያ ፡ ሶርያን ፡ አስተምሮ ፡ አንጾኪያ ፡ ሲመላለስ ፡ በባሕረ ፡ ሱላግያ ፡ መርከብ ፡



ተሰብሮበት ፡ እሱ ፡ ባንድ ፡ ስባረ ፡ ሐመር ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ አብሮኮርስ ፡ ባንድ ፡
ስባረ ፡ ሐመር ፡ ሁነው ፡ ፍጥሞ ፡ ከምትባል ፡ ደሴት ፡ ገብተዋል ። አንድም ፡ አን
ጾኪያን ፡ አስተምሮ ፡ ሶርያ ፡ ሶርያን ፡ አስተምሮ ፡ አንጾኪያ ፡ ሲመላለስ ፡ በባሕረ ፡
ሱላግያ ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ ተነሥቶበት ፡ መርከቡ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ተንከረተተች ፡
ከማዕበሉም ፡ ጽንዓት ፡ የተነሣ ፡ እስከ ፡ ውቅያኖስ ፡ እየተከፈተ ፡ ይታየው ፡ ነበር፤
በጭንቅ ፡ ፍጥሞ ፡ ከምትባል ፡ ደሴት ፡ ደርሰዋል ፡ (ገብተዋል) ። ከዚያ ፡ ሁኖ ፡
ወንድሞቼ ፡ ሁሉ ፡ በየሀገረ ፡ ስብከታቸው ፡ ጸንተው ፡ ያስተምራሉ ፡ የእኔ ፡
ማስተማር ፡ ፈቃድህ ፡ ባይሆን ፡ ነው ፤ ብሎ ፡ ቢያመለክት ፡ የበለጠ ፡ የጥጦስ ፡
የሐሳዌ፡ መሢሕ፡ የምጽአት፡ ነገር፡ ተገልጾለት፡ ጽፏል፡ ጌታ፡ ጥቂት፡ ሲሹ፡ ብዙ፡
መግለጽ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ኋላም ፡ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወምድረ ፡
ሐዳሰ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣው ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ ጽፏል ፡
ዳንኤል፡ የሚጠትን ፡ ነገር ፡ ሲሻ ፡ ቀኖና፡ ቢገባ ፡ የበለጠ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገል
ጾለት፡ መቅደስ ፡ ትትሐነፅ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ እንዳለ ። ጽፎ ፡ ለሰባቱ ፡
መንፈሳውያን ፡ ከዋክብት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ሰዶላቸዋል ። መዋዕለ ፡ ጽሕፈት ፡
ጌታ ፡ ባረገ ፡ ባንድ ፡ በሁለት ፡ በዘጠኝ ፡ ወዝንቱ ፡ ሣልሱ፡ እሙን ፡ ውእቱ ፡ እንዲ
ል። በዘጠኝ፡ ነው፡ እንደምን፡ አድርገው፡ ይመለከቱታል፡ ቢሉ፡ አንዱ፡ ተመልክቶ፡
ለአንዱ፡ይሰድለታል፡ (ጥቅ)፡ ወአንቢበክሙ፡ዛተ፡መልእክተ ፡ ፈንውዋ፡ ሎዶቅያ ፡
ያንብብዋ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወካዕበ፡ አንትሙ ፡ አንብብዋ ፡ ለመልእክት ፡ እን
ተ ፡ ጸሐፍኩ ፡ እምሎዶቅያ ፡ እንዲል ። ይህስ ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ መምህሩ ፡ ከባቴ ፡
አበሳ ፡ እንጅ ፡ ያይደለ ፡ ያንዱን ፡ ኃጢአት ፡ ላንዱ ፡ አይገልጽለትም ፡ ብሎ ፡
ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ኆኅተ ፡ ርኁተ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ በየራሱ ፡ አድ
ርጎ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ያለውን ፡ ቃሉን ፡ አንድ ፡ እያደረገ ፡ ሰባት ፡ ቀለምሲስ ፡
ጽፎ ፡ ሰዶላቸዋል ፡ በአጼ ፡ ዘድንግል ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰባት ፡ ቀለምሲስ ፡
ይዞ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለሐዋርያትም ፡ ጽፎ ፡ ሰዶላቸዋል ፡ ሐዋርያትም ፡
ከሰማንያ፡ አሐዱ፡ መጽሐፍ፡ አንዱ ፡ ራእየ፡ ዮሐንስ፡ ነው፡ ብለው፡ ለቀሌምንጦስ ፡
ሰደውለታል፡ሰጥተውታል፡ይህም፡ሲነበብ፡ሲተረጎም፡ ሁለት፡ መቶ፡ ሰባ፡ስድስት፡ዘ
መን ፡ኑሯል፡ በሁለት፡ መቶ፡ ሰባ፡ ስድስት፡ ዘመን፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡መክስምያኖስ ፡
የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ አላውያን ፡ ነገሥታት ፡ ተነሥተው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይ
ትዐጸዋ ፡ አብያተ ፡ ጣዖታት ፡ ይትረኀዋ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲ
ያናት ፡ ተተኮሱ ፡ መጻሕፍት ፡ ፈለሱ ፤ ከምእመናንም ፡ የሚሞቱት ፡ ሞቱ ፡ የሚ
ሰደዱትም ፡ ተሰደዱ ፡ ዘመኑም ፡ አርባ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተ
ነሣ ፡ ዘመነ ፡ ሰማዕታት ፡ ብለውታል ፤ ተባርዮ ፡ የማያስቀር ፡ ጌታ ፡ ራትዕ ፡
ንጉሥ ፡ መፍቀሬ ፡ ሃይማኖት ፡ ቈስጠንጢኖስን ፡ አነገሠ ፡ አዋጁን ፡ ባዋጅ ፡ መ
ለሰ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይትረኀዋ ፡ አብያተ ፡ ጣዖታት ፡ ይትዐጸዋ ፡ ብሎ ፡
አዋጅ ፡ ነገረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አርዮስ ፡ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ በባሕርዩ ፡ መለኮቱ ፡
ብሎ ፡ ተነሣ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጉባኤ ፡ በኒቅያ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሦስት ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሊቃውንት ፡ ተሰብስበው ፡ አርዮስን ፡ አውግ
ዘው ፡ ሃይማኖት ፡ መልሰው ፡ በሚለያዩበት ፡ ጊዜ ፡ ለመጻሕፍቱ ፡ ሁሉ ፡ አርእ
ስት ፡ ሰጥተዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስን ፡ አጥተውታል ፤ ከሰማንያ ፡ አ
ሐዱ ፡ መጻሕፍት ፡ አንዱ ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስ፡ ነበረ ፡ ጠፋ ፡ ብለው ፡ በአርእስት ፡
ጽፈውታል ፤ በምን ፡ አውቀው ፡ ቢሉ ፡ ሐዋርያት ፡ በአርእስት ፡ ጽፈውት ፡ አግኝ
ተው ። አንድም ፡ ከሐዋርያት ፡ ሲያያዙ ፡ የመጡ ፡ እለ ፡ አቡሊዲስ ፡ እለ ፡ ዲዮናስ
ዮስ፡ ነግረዋቸው፡ ይህ፡ በሆነ፡ በመቶ፡ አምሳ፡ ዘመን፡ ዮሐንስ፡ አፈ፡ ወርቅ፡ በቍስ
ጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ተሾመ ፤ ንጉሡ ፡ አርቃድዮስ ፡ ይባላል፡ ንግሥቲቱም ፡
አውዶክስያ፡ ትባላለች፡ መፍቀሪተ፡ ንዋይ፡ ገፋኢተ፡ ነዳይ፡ ነበረች፡ ይኸውም ፡ ሊ
ታወቅ ፡ ዐጸደ ፡ መበለት ፡ ነሣች፡ (ቀማች)፡ከዮሐንስ ፡አፈ፡ ወርቅ፡ ዘንድ ፡ሂዳ ፡ ተ
ማጠነች ፡ ርስቴን ፡ ቀማችኝ ፡ ብላ ፡ ዛሬ ፡ የተበደለ ፡ ድሀ፡ ከአቡን፡ ከዕጨጌ፡ እንዲ
ማጠን ፡ ርስቴን ፡ ቀማችኝ ፡ ትልሻለች ፡ በምን ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የቀማሻት ፡ መልሽ
ላት ፡ አላት ፡ እንዲያው ፡ እንጅ ፡ አይደለም ፡ ርስቱን ፡ ብትይ ፡ መሰሉን ፡ ልስጥሽ ፡
ዋጋውን ፡ ብትይ ፡ ወርቁን ፡ ልስጥሽ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለችው ፡ እንዲህ ፡ ትልሻ
ለችሳ ፡ አላት ፡ ለምኔ ፡ የኔ ፡ ርስት ፡ ለከተማ ፡ አቅራቢያ ፡ ነው ፡ በዚያውም ፡ ላይ ፡
ከዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ያፈራል ፡ ልጆቼን ፡ ርስት ፡ ነቅያቸው ፡ አልሞትም ፡
አለችው ፡ ርስተ ፡ ምድር ፡ ርስተ ፡ ሰማይ ፡ ነውና ፡ አይሆንም ፡ ብላለች ፡ መልሽ
ላት ፡ አላት ፡ አይሆንም ፡ ትል ፡ ዘንድማ፡ መንግሥቱ፡ የኔ ፡ ነው፡ እንጅ ፡ የሷ ፡ ነው፡
ብላ ፡ አይሆንም ፡ አለች ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አትግቢ ፡ ከምእመናን ፡ አትገ
ናኝ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ አትቀበይ ፡ ብሎ ፡ አወገዛት ፤ ቆጵሮስ ፡ ከኤጲፋንዮስ ፡
ዘንድ ፡ ልካ ፡ አስመጥታ ፡ ትነግረዋለች ፡ እይልኝ ፡ በዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በማ
ይገባ ፡ ነገር ፡ ሲያወግዘኝ ፡ እንግዲህ ፡ ጣዖት ፡ እንዳቆም ፡ ያደርገኛል ፡ ያን ፡
የቀደመውን ፡ ዘመነ ፡ አላውያን ፡ መልሼ ፡ አመጣዋለሁ ፡ አለችው ፡ እሱም ፡ ወን
ድሜ ፡ ለምን ፡ አወገዘሃት ፡ የምግባርማ ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ እየቀደመ ፡ ይሆናል ፡ ፍ
ታት ፡ በዚያውም ፡ ላይ ፡ ጣዖት ፡ አቆማለሁ ፡ ያን ፡ የቀደመ ፡ ዘመነ ፡ አላው
ያን ፡ መልሼ ፡ አመጣዋለሁ ፡ ትላለች ፤ በምእመናን ፡ መከራው ፡ ተመልሶ ፡ ቢመ
ጣባቸው ፡ ደግ፡ ነውን ፡ አለው ፡ ጣዖት ፡ ብታቆም ፡ ለራስዋ ፡ ይባሳት ፡ እሷ ፡ በገ
ሃነም ፡ ስትቃጠል ፡ ትኖር ፡ እንጅ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ጌታም ፡ በየርስቱ ፡ ይኑር ፡
ብሏል ፡ ርስተ ፡ ምድር ፡ የሰማያዊ ፡ ርስት ፡ አንጻር ፡ ነው ፡ ርስተ ፡ ምድር ፡ ነቅሎ ፡
ርስተ ፡ ሰማይ ፡ መውረስ ፡ ይገኛልን ፡ አይሆንም ፡ አለው ፤ ለመሰነባበት ፡ ገብቶ ፡
ሳለ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ታስወራለች ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ነውር ፡ ተገኝቶበት ፡
በሹመቱ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ገባ ፡ እያለች ፡ ታስወራ ፡ ዠመር ፡ ይህን ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡
ወርቅ ፡ ሰምቷል ፡ ተመልሶ ፡ ሄድሁልህ ፡ አለው ፡ በሰው ፡ መዓርግ ፡ ገብተህ ፡ ወዴ
ት ፡ ትሄዳለህ ፡ መሄድማ ፡ እንዳይሄዱን ፡ አለ ፡ ወይም ፡ እንጅ ፡ በመንገድ ፡ ትሞት፡
ይሆናል ፡ አለው ፡ አንተም ፡ እንጅ ፡ ታሥረህ ፡ ተግዘህ ፡ ትሞት ፡ ይሆናል ፡ አለው፤
አሁን ፡ በሁለቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ተቃሕዎ ፡ ኑሮባቸው ፡ አይደለም ፡ እንደ ፡ ተገለጸ



ላቸው ፡ መናገር ፡ ነው ፤ ኤጲፋንዮስ ፡ ሲሄድ ፡ በመንገድ ፡ አንበሳ ፡ ሰብሮት ፡ ሙ
ቷል። (የባሕር፡ ምታት ፡ መቶትም ፡ ቢሉ) ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ በነውር ፡ የሻ
ራቸው፡ ኤጲስ፡ ቆጶሳት፡ ነበሩ፤ ስምንት፡ ያህል፡ ናቸው፤ እሊያን፡ ሰብስባ፡ ፍረዱኝ ፡
አለቻቸው ፤ ንጉሥ ፡ ንግሥት ፡ ሲዘልፍ ፡ የማያፍር ፡ አንደበት ፡ ይጋዝ ፡ በቃ ፡ ብ
ለው፡ ፈርደውበታል፤ አሥራ፡ ደሴተ፡ አጥራክያ ፡ አግዛዋለች፡ የዮሐንስ፡ አፈ ፡ ወር
ቅ፡ ተግባሩ፡ መጽሐፍ፡ መመልከት፡ ጊዜያት፡ ማድረስ፡ ማስተማር ፡ ነውና ፡ መጽሐ
ፍ፡ ሲመለከት፡ ራእየ ፡ዮሐንስን ፡አግኝቶታል። ማን ፡ አግብቶት፡ ቢሉ፡ በሁለቱ፡ አላ
ውያን ፡ ነገሥታት ፡ ጊዜ ፡ ገብቶ ፡ በሀገራችን ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ መጻሕፍት ፡ ዳጋ ፡
ምጽሌ ፡ ዝዋይ ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ምጽዋም ፡ ይላል ። አንድም ፡ ከሰማንያ ፡
አሐዱ፡መጽሐፍ ፡ አንዱ ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ይ
ቅር ፡ ብሎ ፡ ቢያመለክት ፡ ንባቡ ፡ ከነትርጓሜው ፡ ተገልጾለት ፡ ጽፏል ፡ በዚ
ህም ፡ ሐዲስ ፡ ዳንኤል ፡ ተብሏል ፤ ዳንኤል ፡ የናቡከደነጾር ፡ ሕልም ፡ ከነትርጓ
ሜው ፡ ተገልጾለት ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ የኋላ ፡ ሰዎች ፡ አርእስት ፡ ለዮሐንስ ፡ አፈ ፡
ወርቅ ፡ ሰጥተዋል ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ አርእስት ፡
ሰጥቷል ፡ ዲያቆን ፡ ለማር ፡ ይስሐቅ ፡ የኋላ ፡ ሰዎች ፡ ለዲያቆን ፡ አርእስት ፡ እንደ ፡
ሰጡ ፡ መጥሮጶሊስን ፡ ጶሊሰ ፡ መጥራ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የተዛወረ ፡ ነው። ጶሊስ፡ ሊቅ ፡
መጥራ ፡ መዲና ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የመዲናይቱ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ መ
ምህሩ ፡ ዮሐንስ ፡ ከርስቱ ፡ ከጉልቱ ፡ ከዘመዱ ፡ ከነገዱ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ያገኘው ፡
ዮሐንስ፡ ወንጌላዊ ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ። አንድም ፡ መጥራም ፡ ጶሊስም ፡
መዲና ፡ ማለት፡ ነው ። (ጥቅ) ፡ ቆሮንቶስ፡ ሊቅ፡ አካይያ፡ ወይእቲ፡ መዲና፡ መጥራ ፡
ዘውእቱ ፡ መዲና ፡ እንዲል ። የመዲናይቱ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ መምህሩ ፡ ዮሐ
ንስ ፡ ያገኘው ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፤ ራእዩ ፡ ለዮሐንስ ፡ ዘከመ ፡ ርእዮ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንዳየው ፡ መጠን ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወማእከለ ፡ ስብዑ ፡ መኃትው ፡ ይነብር ፡ ከመ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ብሎ ፡ ኋላ ፡ እንዲያመጣው ። አንድም ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንዳየው ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያርእዮሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፡

ዮሐንስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸለት ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ ኢኮንከሙኑ ፡ አንትሙ ፡ ግብርየ ፡ በእግዚእነ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ አግብርቲሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ይነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ የነገረው ።

ዘሀለዎ ፡ ይኩን ፡ ፍጡነ ፡

ፈጥኖ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡

ወዘይከውን ፡ እምድኅረ ፡ ዝ ፡

ኋላ ፡ የሚደረገውን ፡ ወዘይመጽእም ፡ ይላል። አንድም፡ ዘሀለወ ፡ ይኩን ፡ ፍጡነ ፡ የጥጦስ፡ ወዘይመጽእ፡ የሐሣዌ፡ መሢሕ ። አንድም ፡ ዘሀለወ ፤ የሐሣዌ ፡ መሢሕ ። ወዘይከውን፡የምጽአት።አንድም፡ዘሀለወ ፡ ይኩን፡ ፍጡነ፡ የምጽአት፡ ምነው፡ ዛሬስ ፡ እንኳ ፡ ገና ፡ እንጅ ፡ ያይደለ ፡ ዘሀለወ ፡ ይኩን፡ ፍጡነ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ፈጥኖ ፡ ይታየዋልና፡ እንዳይቀር ፡ ያውቃልና ፡ እንደ ፡ ቀረበ፡ ሁኖ ፡ ይታየዋልና ። ወዘይመጽእ ፡ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወምድረ ፡ ሐዳሰ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣው ። እንድም ፡ ዘይመጽእ ፡ የጥጦስ ፡ ዘሀለወ ፡ ይኩን፡ ፍጡነ ፡ የሐሳዌ፡ መሢሕ ፡ ዘይመጽእ ፡ የሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ዘሀለወ ፡ የምጽአት ፡ ዘይመጽእ ፡ የምጽአት ፡ ዘሀለወ፡ ይኩን ፡ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወምድረ ፡ ሐዳሰ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣው።

ወፈነወ ፡ ምስለ ፡ መልአኩ ፡ ኀበ ፡ ዮሐንስ ፡ ገብሩ ፡

በመልአኩ ፡ ባልደረብነት ፡ በእደ ፡ መልአኩ ፡ ይላል ፡ በመልአኩ ፡ ቃለ ፡ አጽነት ፡ ለባለሟሉ ፡ ለዮሐንስ ፡ የነገረው ። አንድም ፡ ፈነወ ፡ መልአኮ ፡ ወደ ፡ ባለሟሉ ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ የሰደደውን ፡ መልአኩን ፡ ሰዶ ፡ የነገረው ፡ ቍ ፡ ፲፱ ፡ ም ፡ ፳፱ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

፪ ፤ ዘኮነ ፡ ስምዐ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ። ወበእንተ ፡ ስምዑ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የመሰከረውን ፡ የጻፈ ፡ እምቅድመ ፡ ይትወለድ ፡ አብርሃም ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ብኋል ፡ ብሎ ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ የህልውናውን ፡ የጌትነቱን ፡ የቅድምናውን ፡ ነገር ፡ የመሰከረ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ ውእቱ ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ፣ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ብሎ ። አንድም ፡ (ዘኮነ ፡ ስምዐ) ፡ የወንጌልን ፡ ነገር ፡ የመሰከረ ፡ (ወበእንተ ፡ ስምዑ) ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የምስክሩንም ፡ ነገር ፡ የጻፈ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ የመሰከረውን ፡ ዮሐንስ ፡ ሰማዕቱ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከልሐ ፡ ወይቤ ፡ ነዋ ፡ በግዑ ፡ ብሎ ።

ወበእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእየ ።

ስላየውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የመሰከረ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አንድም፡ ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእየ፡ ባየው ፡
ማየት ፡ ላይ ፡ ራእዩ ፡ ምን ፡ አይቷል ፡
ቢሉ ፡ ከጎኑ ፡ ትኩስ ፡ ምደ ፡ ጥሩ፡ ውኃ ፡
ሲፈስ ፡ አይቷል ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፱ ።

፫ ፤ ወብፁዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘያነብቦ ፡

የሚደግመው፡ ሰው፡ ንዑድ፡ ክቡር፡ ነው ፡

ወዘይሰምዕ ፡ ቃለ ፡ ተነብዮቱ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡

ድጋሙን ፡ የሚሰማው ፡

ወዘየዐቅብ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስቴቱ ፡

ምስጢሩን ፡ የሚያስተውለው ፡ ንዑድ ፡
ክቡር ፡ ነው ።

እስመ ፡ ቅሩብ ፡ ዘመኑ ።

ከጠፋ ፡ የተገኘበት ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጥበት፡
ዘመኑ ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፡ ከጠፋ ፡ የተገኘበ
ት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ዕሜት ፡ የሚያሰጥበት፣
እንደ፡ ዐቃብ፡ ሰዓት፡ አበሞ፡ ሰባ፡ አንድ፡
ጊዜ ፡ ደግሜ፡ ብጠጣው ፡ ውኃውን ፡ ምስ
ጢር፡ ገለጸልኝ፡ ብለዋል፣ እሳቸውስ፡ ይህ
ን፡ብለው፡ እመንና፡ ከመን፡ ከማጋጠም ፡
በቀር ፡ ያደረጉት ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡
ዲያቆን ፡ ብእሲተ ፡ መኰንን ፡ ወዳጅ ፡
ነበረችው ፤ ታማሚ ፡ ናት ፡ ከፊቷ ፡ ቁሞ ፡
ሲደግምላት ፡ በጎ ፡ ትሆናለች ፡ ወንድ ፡
ከሴት ፡ ከደረሰ ፡ መታማት ፡ ልማድ ፡
ነውና ፡ አንተ ፡ በሌለህበት ፡ ጊዜ ፡ የሚ
ገባ ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ ከዕ
ለታትም ፡ ባንድ ፡ ዕለት ፡ ቢገባ ፡ ከፊቷ ፡
ቁሞ ፡ ሲደግምላት ፡ አገኘው ፡ ለካ ፡ የነገ
ሩኝ፡ ሉሁ፡ሐሰት፡አይደለምሳ፡ ብሎ፡ከነመ
ጣፉ ፡ አስጠቅሎ ፡ ከባሕር ፡ አስጥሎታል፤
ወዲያው ፡ ብሩህ ፡ ብእሲ ፡ ተቀብሎ ፡ በደ
ሴት ፡ አኑሮታል ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡
ነው ፡ እየጸናባት ፡ ሂደ ፡ ከቶ፡ማን ፡ ባዳ
ነልኝ ፡ እያለ ፡ ሲጠይቅ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡

ከዚያ ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚያድ ፡
ልህ ፡ የለም ፡ አለው ፡ እሱንማ ፡ ከባሕር ፡
አስጥየው ፡ የለምን ፡ አለው ፡ ላንተ ፡
ይመስልሃል ፡ እንጅ ፡ እሱስ ፡ እንዲህ ፡
ካለ ፡ ቦታ ፡ አለልህ ፡ አለው ፡ ሰው ፡ ልኮ ፡
አስመጥቶት ፡ ቢደግምላት ፡ ድናለች ፡
አንተ ፡ እንደምን ፡ ዳንህ ፡ አለው ፡ ባስ
ጣልኸኝ ፡ ጊዜ ፡ ብሩህ ፡ ብእሲ ፡ ተቀ
ብሎ ፡ በደሴት ፡ አኖረኝ ፡ አለው ፡ ተካሶ ፤
በሀገሩ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ አሹሞታል ።
አንድም ፡ (ወብፁዕ ፡ ዘያነብቦ) ፡ የሚተ
ረጕመው ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡
(ወዘይሰምዕ ፡ )ትርጓሜውን፡ የሚሰማው፡
ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። (ወዘየዐ
ቅብ) ፡ ራእዩን ፡ የሚያስተውለው ፡ ሰው ፡
ንዑድ፡ክቡር፡ነው፡ይህ፡ቀረ፡ይህ፡ተደረገ፡
እያለ ። ጥቅ፡ እሙሰ ፡ ተዐቅብ ፡ ዘንተ፡ ነ
ገረ ፡ወትወድዮ፡ ውስተ፡ ልባ፡ እንዲል።
(እስመ ፡ ቅሩብ) ፡ ከዐረገ ፡ የተጻፈበት ፡
ራእዩ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ዘመኑ ፡ ቅርብ ፡
ነውና ፡ ምነው ፡ ዛሬስ ፡ እንኳ ፡ ገና ፡ እ
ንጅ ፡ ያይደለ ፡ ቅሩብ ፡ ዘመኑ ፡ አለ፡ቢሉ፡
ፈጥኖ ፡ ይታየዋልና ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡
ሁኖ ፡ ይታየዋልና ፡ እንዳይቀር ፡ ያው
ቃልና ። ካረገ፡ የተጻፈበት፡ በ፰፡ በ፪፡ በ፱ ፡
ወዝንቱ፡ ሣልሱ ፡ እሙን ፡ ውእቱ ፡ እንዲ
ል ፡ በ፱ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፯ ። ም ፡ ፳፪ ፡ ፲ ።

፬ ፤ ዘጸሐፈ ፡ ዮሐንስ ፡ ለሰብዑ ፡ አብያተ፡ ክርስቲ
ያናት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ እስያ ፡

ዘጸሐፈ ፡ ወጸሐፈ ፡ ጸሐፈ ፡ ይላል ፡ ጸሐ
ፍኩ፡ ሲል፡ (ጥቅ)፡ ይጽሕፍ፡ አቡሊዲስ ፡
ለእግዚኡ፡ ወለፍቁሩ፡ በርደጊስ፡ ወአመ ፡
ይመጽእ፡ እንዲል። እስከዚህ ፡ አርእስት ፡
ነው ፡ እሱ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ብሎ፡ ይዠምራል ፤
በእስያ ፡ በሰባቱ ፡ አህጉር ፡ ላሉ ፡ ምእ
መናን ፡ የጻፍሁት ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡
ይህን ፡ ራእይ ፡ ጻፍሁ ።



ሞገሱ ፡ ለክሙ፡

ሃይማኖት ፡ ይጽናላችሁ ። (ጥቅ)፡ ኢትግ
ድፉ ፡ሞገሰክሙ ፡ እንዲል ።

ወሰላሙ ፡

ምግባር ፡ ይፈጸምላችሁ ፡ ባንድ ፡ ዘይ
ቤስ ፡ ሁለት ፡ ንባብ ፡ አያስፈታም ፡ ብሎ፡
ሞገሱ። ባለሟልነት ። ወሰላሙ ፡ ፍቅር ፡
አንድነት ፡ ይደረግላችሁ ፡ (ጥቅ) ፡ እምድ
ኅረ ፡ ሰላመ ፡ ርእሱ ፡ ባልሐነ ፡ ወሰላመ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንተ ፡ ኵሉ ፡ ባቲ ፡ እን
ዲል ፡

እምኀበ ፡ ዘሀሎ ፡

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከነበረ ፡ ከአብ ፡

ወይሄሉ ፡

ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ ከሚኖር ፡ ከአብ ፡

ዘመጽአ ፡

ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ ከመጣ ፡ ከወልድ ፡

ወዘይመጽእ ፡

ዓለሙን ፡ ለማሳለፍ፡ ከሚመጣ ፡ ከወልድ ።
አንድም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ቅድመ ፡ ዓለም፡
ከነበረ ፡ ከወልድ ። ወይሄሉ ፡ ዓለሙን ፡
አሳልፎ ፡ ከሚኖር ፡ ከወልድ ። ዘመጽአ ፡
ለኵነተ ፡ ሥጋ ፡ ከመጣ ፡ ከወልድ ፡
ወዘይመጽእ ፡ ዳግመኛ ፡ ዓለሙን ፡ ለማ
ሳለፍ ፡ ከሚመጣ ፡ ከወልድ ፡ ይደረግላ
ችሁ ፡

ወእምነ ፡ ሰብዐቱ ፡ መንፈስ ፡ ዘቅድመ ፡ መንበሩ ፡
ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ህልውና፡ ካለ ፡ ከመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይደረግላችሁ፡ ሐተታ፡ ሰብ
ዐቱ ፡ አለ ፡ ስለ፡ ፍጹም፡ ሀብቱ ፡(ጥቅ)፡እስ
መ ፡ ኍልቍ ፡ ሰብዐቱ ፡ በኀበ ፡ ዕብራው
ያን ፡ፍጹም፡ ውእቱ ፡ እንዲል ። ወእምነ ፡
ሰብዐቱ ፡ መኃትው ፡ ዘቅድመ ፡ መንበሩ ፡

ብሎ ፡ ኋላ ፡ ያመጣዋል ። አንድም ፡ ፍጹ
ም ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከጌትነቱ ፡
ከሚሰጥ ፡ ከወልድ ፡ ይደረግላችሁ ፡ ዘመ
ጽአ ፡ ወዘይመጽእ ፡ ብሎ፡ ሁለት ፡ አርእ
ስት ፡ ተናግሯል ፡ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ፡
ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ። ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፰ ። ም ፡
፫ ፡ ፩ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ።

፭ ፤ ዘውእቱ ፡ ስምዕ ፡ መሃይምን ፡

ዘመጽአ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡ የታመነ ፡ ምስ
ክር ። አንድም ፡ ስምዕ ፡ ምስክር ፡ ወመሃ
ይምን ፡ የታመነ ። አንድም ፡ ስምዐ ፡ መሃ
ይምናን ፡ ይላል ፡ ምእመናን ፡ አምልኮ
ቱን ፡ የሚመሰክሩለት፡(ጥቅ) ፡ ወእነግር ፡
ስምዐከ ፡ በቅድመ ፡ ነገሥት ፡ እንዲል ።

ወውእቱ ፡ ቀደመ ፡ በኵረ ፡ ከዊነ ፡ እምነ ፡ ምውታን ፡
ዘተንሥአ ፡

በኵር ፡ መሆንን ፡ የገረመረ ፡ ወዘእሙ
ታን ፡ ከሙታንም ፡ ተለይቶ ፡ የተነሣ ።
አንድም ፡ በኵር ፡ ሁኖ ፡ ቀደመ ፡ ከዊነ ፡
ከዊንን ፡ የገረመረ ፡ ከዊንም ፡ ያልሁት ፡
ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የተነሣው ፡ መነ
ሣት ፡ ነው ።

ወውእቱ ፡ መኰንኖሙ ፡ ለነገሥተ ፡ ምድር ፡

ዘመጽአ ፡ ላለው ፡ ተናግሮ ፡ ወዘይመ
ጽእ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡
ነገሥታት ፡ ከፈረሱ ፡ ከበሰበሱ ፡ በኋላ ፡
አስነሥቶ ፡ የሚገዛ ፡ ይህንስ ፡ አሁን ፡
ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ በደመና ፡ ሰማይ ፡ ብሎ ፡
ያመጣዋል ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ዘመ
ጽአ ፡ ላለው ። አንድም ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡
ነገሥታት ፡ እየሾመ ፡ እየሸለመ፡ የሚገዛ፡
(ጥቅ)፡ አእምር ፡ ከመ፡ ልዑል ፡ ይኬንን ፡
መንግሥተ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡
ወለዘፈቀደ ፡ ይሁብ ፡ እስመ ፡ ኢይሠ
የም ፡ መኰንን ፡ ዘእንበለ ፡ እምኀበ ፡ እግ

www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ፡ እንዲል ። አንድም ፡ የዚ
ህን ፡ ዓለም ፡ ነገሥታት ፡ የሚነቅፍ ፡
የሚዘልፍ ፡

ውእቱ ፡ ዘአፍቀረክሙ ፡

የሞተላችሁ ፡ እሱ ፡ ነው ፡

ወኀፀበክሙ ፡ እምኃጣውኢክሙ ፡ በደሙ ፡

ተሰቅሎ ፡ ባፈሰሰው ፡ ደሙ ፡ ከኃጢአታ
ችሁ ፡ የለያችሁ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ም ፡ ፫፡፲፬።
ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፯። ቍ ፡ ፲፫ ። ቆላ ፡ ፩ ፡ ፲፫።
ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ። ም ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። ዕብ ፡ ፱፡፲፬ ።

፮ ፤ ወረሰየክሙ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ቅድሳተ ፡
አቡሁ ፡ እግዚአብሔር ፡

አንድነቱ ፡ ሦስትነቱ ፡ ተለይቶ ፡ በሚታ
ወቅባት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ። አን
ድም ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡
በሚመሰገንባት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
እንድትኖሩ ፡ ያደረጋችሁ ፡ እሱ ፡ ነው ።
አንድም ፡ ውስተ ፡ ቅድስተ ፡ አቡሁ ፡ ይ
ላል ፤ አባቱ ፡ በሚያድላት ፡ በክብርት ፡
ልጅነት ፡ እንድትጸኑ ፡ ያደረጋችሁ ፡ እሱ፡
ነው ።

ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡

ክብር ፡ ምስጋና ፡ ያለው ።

ወኃይል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ከሀሊነት ፡ ያለው ፡ ለዘላለሙ ፡ በእውነት፡
ያለሐሰት ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲ ። ፩፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡
ዘፀአ ፡ ፲፱ ፡ ፯ ።

፯ ፤ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ በደመና ፡ ሰማይ ፡

ወውእቱ ፡ መኰንኖሙ ፡ ለነገሥተ ፡ ም
ድር ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡
አለ ፡ በበኀ ፡ በኀዎቹ ፡ መምህራን ፡ አድሮ፡
ክፉ ፡ ክፉዎችን ፡ ነገሥታት ፡ ለመዝለፍ ፡
ለመንቀፍ፡ይመጣል፡በኤልያስ፡አድሮ፡አክ
አብን ፡በዮሐንስ፡አድሮ፡ ሄሮድስን፡እንደ ፡
ዘለፈ ፡ ደመና ፡ አላቸው ፡ በጎ ፡ በጎዎችን ፡
መምህራን ፡ ደመና ፡ ከውቅያኖስ ፡ ዝና
ም ፡ ቋጥሮ ፡ ወጥቶ ፡ እየዞረ ፡ እያዘነመ ፡
ለብዙ ፡ አዝርዕት ፡ አትክልት ፡ ይጠ
ቅማል ፡ እሊህም ፡ ዞረው ፡ አስተምረው ፡
ያልተመሰለውን ፡ መስለው ፡ የተመሰለ
ውን ፡ ተርጕመው ፡ ብዙ ፡ ምእመናንን ፡
ይረባሉ ፡ ይጠቅማሉና ። አንድም ፡ ነገ
ሥታትን ፡ ብቻ ፡ መምህራንንሳ ፡ ትሉኝ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በክፉዎችም ፡ መምህራን ፡
በመዓት ፡ ይመጣባቸዋል ፤ በጴጥሮስ ፡
አድሮ ፡ በሐናንያ ፡ በጳውሎስ ፡ አድሮ ፡
በበርያሱስ ፡ በመዓት ፡ እንደ ፡ መጣባ
ቸው ፡ ደመና ፡ አላቸው ፡ ክፉ ፡ ክፉዎ
ችን ፡ መምህራን ፡ ደመና ፡ ዝናም ፡ እየ
ቋጠረ ፡ ወጥቶ ፡ ካዘነመ ፡ በኋላ ፡ እንዳይ
ቆም ፡ ወዲያው ፡ እንዲበተን ፡ እሊህም ፡
መንፈሳውያን ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ሥጋው
ያን ፡ ሰማያውያን ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ምድ
ራውያን ፡ ሁነዋልና ። አንድም ፡ ዘመጽአ፡
ወዘይመጽእ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ አርእስት፡
ተናግሮ ፡ ነበረና ፡ ዘመጽአ ፡ ላለው ፡ ተና
ግሮ ፡ ዘይመጽእ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡ በባ
ሕርይ ፡ ክብሩ ፡ ይመጣል ፡ የምጽአት ፡
የዕርገት ፡ የታቦር ፡ ደመና ፡ የባሕርይ ፡
ክብሩ ፡ ነውና ። አንድም፡ ደመና፡ ሥጋ ፡
ሰማይ ፡ እመቤታችን ፡ ናት ፡ ሰማይ ፡ ዳግ
ሚት ፡ እንዲላት ፡ በሥጋ ፡ ማርያም ፡ በ
ክበበ ፡ ትስብእት ፡ ይመጣል ።

ወትሬእዮ ፡ ዙላ ፡ ዐይን ፡

ፍጥረት፡ ሁሉ፡ በርእይ፡ ታየዋለች፡ (ጥቅ)፡
ፍጥረትኒ፡ ትሬእዮ፡ ለፈጣሂሪ ፡ ከዊኖ ፡ በ
አካለ ፡ ቆማ ፡ እንዲል ፡

ወእልክቱሂ ፡ እለ ፡ ወግዕዎ ።

ጎኑን ፡ የወጉትም ፡ ሁሉ ፡ ይሬእይዎ ፡



ያለበት፡ነው፡ ያዩታል፡ሐተታ፡ ምነው፡የወ
ጋው ፡ አንድ ፡ ሐራዊ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡
ወግዕዎ ፡ አለ ፤ ቢሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፡
ካልጠራ ፡ ማብዛት፡ ልማዱ፡ ነውና ፡ (ጥቅ)
አየ ፡ ገቦ ፡ ረገዙ ፡ ሐራሁ ፡ ለጲላጦስ ፡
እንዲል ። አንድም ፡ አንድ ፡ በወረወር ፡
ሽሕ፡ በመከር ፡ እንዲሉ፡ ፈቃድ፡ ለሁሉ፡
ከሆነ ፡ ብሎ። አንድም ፡ በቀኖት ፡ የወጉ
ትን ፡ ጨምሮ ፡ ቆጥሮ ፡ ያውስ ፡ ቢሆን ፡
ትሬእዮ ፡ ያለው ፡ አይበቃም ፡ ቢሉ ፡
አስተያየቱ ፡ ልዩ ፡ ነውና ፡ ንጉሥ ፡ ለጠ
ላቱ ፡ እሳት ፡ ስለት ፡ ለወዳጁ ፡ ሹመት ፡
ሽልማት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ወይክዩ ፡ በእንቲአሁ ፡

ጽኤል ፡ በሱ ፡ ነገር ፡ ያለቅሳሉ ፡

ወዙሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ምድር ፡

አሕዛብም ፡ ያለቅሳሉ ፡

እወ ፡

እስራኤል ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡
ደረት ፡ ተወስነህ ፡ ብታስተምረን፡ አንቀ
ቀበልህ ፡ ብለን ፡ ሰቅለን ፡ የገደልንህ ፡
አንተ ፡ ነህን ፡ ይሉታል ፡ እወ ፡ ይላቸዋ
ል ፡ ይበክዩ ፡ ያለቅሳሉ ።

ወአማን ፡

አሕዛብ ፡ ሐዋርያት ፡ ያንተን ፡ ነገር ፡
ቢያስተምሯቸው ፡ እስራኤል ፡ አንቀበላ
ቸው ፡ ብለው ፡ አሳልፈው ፡ ለኛ ፡ ይሰ
ጡን ፡ የነበረ ፡ የነዚያ ፡ አምላክ ፡ ነህን ፡
ይሉታል ፡ አማን ፡ ይላቸዋል ፡ ይበክዩ ።
አንድም ፡ እወ ፡ እስራኤል ፡ናቸው ፤ ሐዋ
ርያት ፡ የአንተን ፡ ነገር ፡ ቢያስተምሩን ፡
አንቀበላቸው ፡ ብለን ፡ አሳልፈን ፡ ለአሕ
ዛብ ፡ እንሰጣቸው ፡ የነበረ ፡ የነዚያ ፡ አም
ላክ ፡ አንተ፡ ነህን ፡ ይሉታል ፡ እወ፡ ይላ
ቸዋል ፡ ይበክዩ ፡ ወአማን ፡ አሕዛብ ፡
ሐዋርያት፡ የአንተን፡ ነገር፡ ቢያስተምሯ
ቸው ፡ እስራኤል ፡ አንቀበላቸው ፡ ብለው፡
አሳልፈው ፡ ለኛ ፡ እየሰጡን ፡ ቍልቍ
ሊት ፡ እንሰቀላቸው ፡ አቀመዳቸውን ፡
እናወጣቸው ፡ የነበረ ፡ የነዚያ ፡ አምላክ ፡
ነህን ፡ ይሉታል ፤ አማን፡ ይላቸዋል፡ ይበ
ክዩ ። ዘካ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፯ ።

፰ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ አልፋ ፡ ወአ ፡

አልፋ ፡ አ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አ ፡ አብ ፡ ል ፡ ወ
ልድ ፡ ፋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አ ፡ አንድ
ነት ፡ አንድነት ፡ ሦስትነት ፡ ገንዘቤ ፡
የሚሆን ። አንድም ፡ ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡
የምሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሀሎ ፡ ወይሄሉ ፡ ዘመጽአ ፡
ወዘይመጽእ ፡ ዘውእቱ ፡ ይመልክ ፡ ኵሎ ።

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለሙን ፡ አሳ
ልፎ ፡ የሚኖር ፡ (ዘመጽአ) ፡ ለኩነተ ፡
ሥጋ ፡ የመጣ ፡ (ወዘይመጽእ) ፡ ዳግመኛ ፡
ዓለሙን ፡ ለማሳለፍ ፡ የሚመጣ ፡ (ዘው
እቱ ፡ ይመልክ) ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡
ይመልዕ ፡ ይላል ፡ በሁሉ ፡ በምልዐት ፡
አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ አልፋ ፡
አ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፲፫ ። ኢሳ ፡
፵፩ ፡ ፬ና ፡ ፵፬ ፡ ፮ና ፡ ፵፰ ፡ ፲፪ ።

፱ ፤ ወአነ ፡ ዮሐንስ ፡ እኁክሙ ፡ ወሱታፌክሙ ፡
በሕማምክሙ ፡ ወበትዕግሥትክሙ ፡ በእንተ ፡ ትዕ
ግሥቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡
ታግሦ ፡ ባመጣት ፡ ልጅነት ፡ ወንድማ
ችሁ ፡ የምሆን ፡ ወሱታፌክሙ ፡ ወበትዕ
ግሥትክሙ ፡ ታግሣችሁ ፡ በምትቀበሉት
ም ፡ መከራ ፡ ተባባሪያችሁ ፡ የምሆን ።
አንድም ፡ እኁክሙ ፡ በሕማምክሙ ፡ ወበ
ትዕግሥትክሙ ፡ በእንተ ፡ ትዕግሥቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ መከራ ፡ መስቀልን ፡ ታግሦ ፡ ስለ ፡ ተቀበለ ፡ ታግሣችሁ ፡ በምትቀበሉት ፡ መከራ፡ ወንድማችሁ ፡ የምሆን ፡ ወሱታፌክሙ ፡ በመንግሥትክሙ ፡ በልጅነትም ፡ ተባባሪያችሁ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ ዮሐንስ ፡ እኁክሙ ፡ በእንተ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ በመንግሥትክሙ ፡ ወሱታፌክሙ፡በሕማምክሙ ፡ በእንተ ፡ ትእግሥቱ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።

ወእንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ውስተ ፡ ደሴት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ፍጥሞ ፡

ፍጥሞ ፡ በምትባል ፡ ደሴት ፡ ሳለሁ ።

በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበእንተ ፡ ስምዑ ፡ ለኢየሱስ ።

ቅድምናውን ፡ ህልውናውን ፡ ምስክርነቱን ፡ ስለማስተማር ፡ ፍጥሞ ፡ ማለት ፡ መካነ ፡ ሣህል ፡ መካነ ፡ ራእይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ አይተውባታል ፡ ኋላም ፡ እለ፡ ዳንኤል ፡ እለ ፡ ኤርምያስ ፡ አይተውባታል ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ።

፲ ፤ መጽአ ፡ ላዕሌየ ፡ መንፈስ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡

እሑድ ፡ በሚባል ፡ ቀን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ አደረብኝ ። ሐተታ ፡ ተለይቶት ፡ ያውቃልን ፡ ሥራ ፡ አሠራኝ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ቀድሞ ፡ ራእዩን ፡ ያየው ፡ እሑድ ፡ ነው ፤ ኋላም ፡ የሚፈጸምበት ፡ እሑድ ፡ ነውና ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ አለ ። አንድም ፡ በዕለት ፡ አሐዱ ፡ ከዕለታት ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረብኝ ።

ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዐቢየ ፡ እምድኅሬየ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ቀርን ፡

ከወደ ፡ ኋላዬ ፡ እንደ ፡ ነጋሪት፡ ያለ፡ ቃል፡ ሰማሁ ፡ ቀርን ፡ አለ ። ሐተታ ፡ ነጋሪት ፡ ፈጥኖ ፡ ፈጥኖ ፡ ይመታል ፡ ራእዩም ፡ ፈጥኖ ፡ ፈጥኖ ፡ ይታየዋልና ። አንድም ፡ ነጋሪት ፡ የራቀውን ፡ ያቀርባል ፡ የቀረበውን ፡ ያርቃል ፤ ራእዩም ፡ የቀረበውን ፡ አርቆ ፡ የራቀውን ፡ አቅርቦ ፡ ያሳየዋልና። አንድም ፡ ነጋሪት ፡ ከዕሩቅ ፡ ይሰማል ፤ ራእዩም ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ደርሷል፤ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ሲያያዝ ፡ ሲነገር ፡ ይኖራልና ፡ ከወደ ፡ ኋላዬ ፡ አለ ፡ ከወደ ፡ ኋላ ፡ የመጣ ፡ ባላጋራ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ ጽኑ ፡ ራእይ ፡ አየሁ ፡ ሲል ፡ ነው። አንድም፡ ራእዩ ፡ የሚፈጸም፡ ወደኋላ፡ ነውና ፡ እምድኅሬየ ፡ አለ ፡ ቀ ፡ ፲፰ ።

፲፩ ፤ ወይቤለኒ ፡ ጸሐፍ ፡ እንከ ፡ ዘትሬኢ ፡ ወዘትሰምዕ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ።

የምታየውን ፡ የምትሰማውን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ። ሐተታ ፡ ምን ፡ አይቷል ፡ ምን ፡ ሰምቷል ፡ ቢሉ ፡ ከወደ ፡ ፊቱ፡ ብርሃን፡ አይቷል፡ ከወደኋላው፡ ቃል፡ ሰምቷል፡ ውስተ፡ መጽሐፍ ፡ አለ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተጽፎ ፡ አይደለም ፡ በኋላ ፡ ስሙ ፡ መጽሐፍ ፡ ብሎታል ። አንድም ፡ ውስተ፡ ምጽሐፍ ፡ ይላል ፡ በብራና ፡ ጻፍ ፡ አለኝ።

ወፈኑ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሰብዐቱ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ እስያ ፡

ጽፈህ ፡ በእስያ ፡ በሰባቱ ፡ አሕጉር ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ስደድ ፡ አለኝ ።

ዘኤፌሶን ፡

ሰባቱ ፡ ያላቸውን ፡ ይተረትራል ፡ በኤፌሶን ፡ ላሉ ፡

ወዘሴሜርኔስ ፡

በሴሜርኔስ ፡ ላሉ ፡

ወዘጴርጋሞን ፡

በጴርጋሞን ፡ ላሉ ፡



ወዘተያጥሮን ፡

በተያጥሮን ፡ ላሉ ፡

ወዘሰርዴስ ፡

በሰርዴስ ፡ ላሉ ።

ወዘፊልድልፍልያ ፡

በፊልድልፍልያ ፡ ላሉ ።

ወዘሎዶቅያ ፡

በሎዶቅያ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ጽፈህ ፡ ስደድ ፡ አለኝ ። አንድም ፡ (ኤፌሶን) ፡ ማለት ፡ አፈሳን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አፈሳን ፡ ማለት ፡ ቃለ ፡ አብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሱ ፡ ላመኑ ፡ (ሴሜርኔስ) ፡ ማለት ፡ ዘሠምረ ፡ ይኩን ፡ ሰብአ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሱ ፡ ላመኑ ፡ ጴርጋሞን ፡ ማለት ፡ ዘለብሰ ፡ ሥጋ፡ ማለት ፡ ነው፡ (ጥቅ) ፡ ብእሲ፡ ዘይለብስ ፡ ጠብደነ ፡ እንዲል ። በእሱ ፡ ላመኑ ፡ ፊልድልፍልያ ፡ ማለት ፡ መፍቀሬ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በእሱ ፡ ላመኑ ፡ ተያጥሮን ፡ ማለት ፡ ብእሲ ፡ ቅውም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሱ ፡ አምነው ፡ ላሉ ። (ሰርዴስ) ፡ ማለት ፡ ዘትሥልስት ፡ ወዘተዋሕዶ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሱ ፡ አምነው ፡ ላሉ ። ሎዶቅያ ፡ ማለት ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሱ ፡ አምነው ፡ ላሉ ፡ ጽፈሕ ፡ ስደድ ፡ አለኝ፡ ም፡ ፳፪ ፡ ፲፫ ።

፲፪ ፤ ወተመየጥኩ ፡ እርአይ ፡ ዝኩ ፡ ቃለ ፡ ዘይትናገር ፡ ምስሌየ ፡

የሚነግረኝን ፡ ቃል ፡ እሰማ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ተመለስሁ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚናገረውን ፡ ቢል ፡ ይሆናል ። አንድም ፡ ተመሠጥኩ ፡ ተራቀቅሁ ፡ ኀተሞሙ፡ ይላል፡ አብነት፡ አያስተረጉምም ።

ወሶበ ፡ ተመየጥኩ ፡

በተመለስሁ ፡ ጊዜ ፡ (በተራቀቅሁ ፡ ጊዜሙ ፡ ቢል) ፡ ይሆናል ፡

ናሁ ፡ እሬኢ ፡ ሰብዑ ፡ መኃትወ ፡ ዘወርቅ ።

ሰባት ፡ የወርቅ ፡ ፋና ፡ አየሁ ። ሐተታ ፡ ወርቁና ፡ ፋናው ፡ እንደ ፡ ሰምና ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ ተጣምቶ ፡ ሲነድ ፡ ያየዋል ፤ ፈትሉ ፡ የሰውነታቸው ፡ ወርቁ ፡ የንጽሕናቸው ፡ እሳቱ ፡ የመከራቸው ፡ ብርሃኑ ፡ የጸጋቸው፡ ምሳሌ፡ ነው፡ ተዋሕዷቸዋል ።

፲፫ ፤ ወማእከለ ፡ ሰብዑ፡ መኃትው ፡ ይነብር፡ ከመ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡

በሰባቱም ፡ የወርቅ ፡ ፋና ፡ መካከል ፡ ወልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው፡ ተቀምጧል ፡ አለ። ተዋሕዷቸዋል ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ አይደለምና ፡ ከመ ፡ ይላል ። አንድም ፡ (ናሁ ፡ እሬኢ) ፡ ሰባት ፡ የወርቅ ፡ ፋና ፡ አየሁ ። ምሳሌ፡ነው፡ ወርቁ፡ የንጽሕናቸው፡ እሳቱ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብርሃኑ ፡ የጸጋቸው ፤ (ወማእከለ ፡ ሰብዑ) ፡ በሰባቱም ፡ የወርቅ፡ ፋና ፡ መካከል ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ተቀምጧል ፡ አለ ፡ አድሮባቸዋል።

ወይለብስ ፡ ልብሰ ፡ ጶዴር ፡

እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥትነቱ ፡ አርድ ፡ አንቀጥቅጥ ፡ የሚባል ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሷል ።

ወቅኑት ፡ ውስተ ፡ ሐቌሁ ፡ በቅናት ፡ ዘወርቅ ።

የወርቅ ፡ አፋ ፡ ታጥቋል ፡ ትእምርተ ፡ ኃይል ፡ ነው ። አንድም ፡ (ወይለብስ) ፡ እንደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናትነቱ ፡ ሞሉጣ ፡ የምትባል ፡ እጀ ፡ ሰፊ ፡ ለብሷል ። (ወቅኑት) ፡ የወርቅ ፡ ዝናር ፡ ታጥቋል ፡ ትእምርተ ፡ ተልእኮ ፡ ነው ። አንድም ፡ (ወይለብስ) ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዷል። (ጥቅ) ፡ ብእሲ ፡ ዘይለብስ ፡ ጠብደነ ፡ እንዲል ። (ወቅኑት) ፡ ጽንዐ ፡ ተዋሕዶን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፩ ። ዳን ፡ ፺ ፡ ፲፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፬ ፤ ወጸዐዳ ፡ ርእሱ ።

ራስ ፡ ቅሉ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ ጽርየተ ፡ ባሕርዩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወሥዕርቱ ፡ ከመ ፡ ፀምር ፡ ጸዐዳ ፡

ጠጉሩም ፡ እንደ ፡ ነጭ ፡ ግምጃ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ግም ጃ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ ብሎየ ፡ መዋዕልነቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ ወጽሕሙ ፡ ጸዐዳ ፡ ከመ ፡ በረድ ፡ ወከመ ፡ አስሐትያ ፡ ይላል ። ኀተሞሙ ፡ አብነት ፡ አያስተረጉምም ፡

ወአዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡

ዐይኖቹም ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ ይመስላሉ ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፱። ም ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።

፲፭ ፤ ወእገሪሁ ፡ ከመ ፡ ብርተ ፡ ሊባኖስ ፡ ዘአርሰንዎ ፡ በእሳት ፡

እግሮቹም ፡ በእሳት ፡ እንደ፡ አፈሉት ፡ እንደ ፡ ደጋ ፡ ብረት ፡ ናቸው ፡ ትእምርተ ፡ በቀል ፡ ትእምርተ ፡ መዓት ፡ ነው ። አንድም ፡ አዕይንቲሁ ፡ ነቢያት ፡ ናቸው ፡ አዕይንት ፡ አላቸው ፡ ምስጢር ፡ ያያሉና ፡ እገሪሁ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ፡ እገሪሁ ፡ አላቸው ፡ ሑሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ብሏቸዋልና። አንድም ፡ አዕይንቲሁ ፡ ቀሳውስት ፡ ናቸው ፡ አዕይንት ፡ አላቸው ፡ ምስጢር ፡ ያያሉና ፡ እገሪሁ ፡ ዲያቆናት ፡ ናቸው ፡ እገሪሁ ፡ አላቸው ፡ በተልእኮ፡ ይኖራሉ፡

ወቃሉ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ማይ ፡ ብዙኅ ።

ቃሉም ፡ እንደ ፡ መጣያ ፡ ውኃ ፡ ነው፡ ያ ፡ ከሩቅ ፡ እንዲሰማ ፡ ለመቶ ፡ ሐያ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ሲያስተምር ፡ ይሰማል ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንደ፡ የጕርጓድ ፡ ውኃ ፡ ነው፡ ያ ፡ እንዲያስፈራ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ። ብዙኅ፡ ባለው፡ ክቡድ፡ ይላል ፡ ግሩም ፤ ሲል ፡ ነው ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።

፲፮ ፤ ወውስተ ፡ እዴሁ ፡ ዘየማን ፡ ሰብዐቱ ፡ ኮከብ ።

በቀኝ ፡ እጁ ፡ ሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ተይዘዋል ። አንድም ፡ በሥልጣኑ ፡ ሰባቱ ፡ መንፈሳውያን ፡ ከዋክብት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ጸንተዋል ።

ወይወፅእ ፡ እምነ ፡ አፉሁ ፡ ሰይፍ ፡ በሊሕ ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ ፡

ከአፉም ፡ ሁለት ፡ ልሳን ፡ ያለው ፡ ሰይፍ ፡ ይወጣል ፡ አለ ፡ በቃሉ ፡ ንዑና ፡ ሑሩ ፡ ይነገራል ፡ ዘሠለስቱ ፡ አፉሁ ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ በለው ፡ ሰይፍ ፡ ሦስት ፡ ልሳን ፡ ያለው፡ ሰይፍ፡ ከአፉ ፡ ይወጣል፡ አለ ፡ አንድነት ፡ ሦስትነት ፡ በቃሉ ፡ ይነገራል ፡

ወገጹ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ ብሩህ ፡ ዘያስተርኢ ፡ በኀይሉ ።

ፊቱም ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ በግድ ፡ እንደሚታይ ፡ ፀሓይ ፡ ነው ፡ በክበቡ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በሙቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉና ፡ አንድም ፡ ገጹ ፡ የአብ ፡ በገንዘቡ ፡ እንደሚገለጽ ፡ እንደ ፡ ወልድ ፡ ነው ። አንድም ፡ ገጹ ፡ የወልድ ፡ በልጁ ፡ እንደሚገለጽ ፡ እንደ ፡ አብ ፡ ነው ። አንድም ፡ ገጹ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በገንዘቡ ፡ እንደሚገለጽ ፡ እንደ ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ ቀ ፡ ፳ ። ም ፡ ፪ ፡ ፩ ። ም ፡ ፪ ፡ ፲፪ ። ፲፯ና ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ።

፲፯ ፤ ወሶበ ፡ ርኢክዎ ፡ ወደቁ ፡ ውስተ ፡ እገሪሁ ፡ ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ በድን ።

ባየሁትም ፡ ጊዜ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወደቅሁ ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ተለየኝ ፡ ሆንሁ ፤ ሐተታ፡ ጨርሶ ፡ አልተለየውምና፡ ከመ ፡ በድን ፡ አለ ።

ወአኀዘኒ ፡ በየማኑ ፡ ወአንሥአኒ ፡

በቀኝ ፡ እጁ ፡ ያዘኝ ፡ ይዞ ፡ አስነሣኝ ። አንድም ፡ በሥልጣኑ ፡ አጸናኝ ፡



ወይቤለኒ ፡ ኢትፍራህ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ወደኃራዊ፡ ዘሕያው ።

አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ አለኝ ፡ ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡ ሕያው ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ፡ ሐተታ ፡ ቀዳማዊነቱ ፡ ደኃራዊነቱ ፡ አያስፈራውም ፡ ቢሉ ፡ እኔ ፡ ሳላውቅ ፡ ሞት ፡ አይመጣብህም ፡ ሲለው ፡ ነው ፡ ዳን ፡ ፰ ፡ ፲፰ ።

፲፰ ፤ ወአንሰ ፡ ኮንኩ ፡ ከመ ፡ በድን ፡

እኔ ፡ ግን ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ተለየኝ ፡ ሆንሁ ፡

ወይቤለ ኒ፡ ናሁ ፡ ሕያው ፡ አነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡

እነሆ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ነኝ ።

ወኀቤየ ፡ ሀሎ ፡ መራኁተ ፡ ሞት ፡ ወሲኦል ።

ሞትን ፡ መቃብርን ፡ የማሳልፍበት ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ፡ አይዞህ ፡ ምን ፡ ያስፈራሃል ፡ አለኝ ፡ ምንም ፡ እንዲህ ፡ ቢለኝ፡ ኮንኩ ፡ ከመ ፡ በድን ። አንድም ፡ መቃብርን ፡ ሞትን ፡ የማሳልፍበት ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘቤ ፡ የሚሆን ፡ እኔስ ፡ እንኳ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሬ ፡ ተነሣሁ ፡ አይዞህ፡ ምን ፡ ያስፈራሃል ፡ አለኝ፡ ምንም ፡ እንዲህ ፡ ቢለኝ፡ ኮንኩ፡ ከመ፡ በድን፡ ሮሜ፡ ፮፡ ፱ ።

፲፱ ፤ ጸሐፍ ፡ እንከ ፡ ዘትሬኢ ፡

የምታየውን፡ የምትሰማውን፡ ጻፍ፡ አለኝ ።

ዘሀልው ።

የሆነውን ።

ወዘሀለዎ ፡ ይኩን ፡ እምድኅረዝ ።

ኋላ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ሐተታ ፡ ዘሀልው ፡ የጥጦስ ፡ ወዘሀለወ ፡ የሐሣዌ ፡ መሢሕ ። ዘሀልው ፡ የሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ወዘሀለወ ፡ የምጽአት ፡ ዘሀልው ፡ የምጽአት ፡ ወዘሀለወ ፡ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወምድረ ፡ ሐዳሰ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣው ። አንድም ፡ ዘሀልው ፡ በሱ፡ ጊዜ ፡ የሚሆነውን ፡ ይህስ ፡ ብቻ ፡ መጻእያትን ፡ አያሳየውም ፡ ኃላፍያትንም ፡ ያሳየዋል ፡ ብሎ ፡ (ዘሀልው) ፡ ከሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የሆነውን ፡ (ወዘሀለወ) ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ በኋላ ፡ የሚሆነውን ። ዘሀልው ፡ ወዘሀለወ ፡ ይኩን ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ፡ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ፡ ይህን ፡ እያፈራረቀ ፡ ይሄዳል ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፳ ፤ ወፍካሬሆሙሰ ፡ ለሰብዐቱ፡ ከዋክብት ፡ እለ ርኢከ ፡ ውስተ ፡ የማኑ ፡

በቀኝ ፡ እጁ ፡ ተይዘው ፡ ያየሃቸው ፡ የሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ ትርጓሜያቸው ፡

ወዘሰብዐቱ ፡ መኃትው ፡ እለ ፡ ወርቅ ፡ ዝንቱ ፡

የሰባቱም ፡ የወርቅ፡ መቅረዝ፡ (ፋናም ፡ ቢል) ፡ ትርጓሜያቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሰብዐቱ ፡ ከዋክብት ፡ መላእክት ፡ እሙንቱ ፡ እለ ሰብዐቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

ሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ በሰባቱ ፡ አህጉር ፡ ባሉ ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ ሰባቱ ፡ መንፈሳውያን ፡ ከዋክብት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ናቸው ።

ወእልክቱ ፡ ሰብዐቱ ፡ መኃትው ፡ ሰብዑ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እማንቱ ።

ሰባቱም ፡ የወርቅ ፡ መቅረዝ ፡ በሰባቱ ፡ አህጉር ፡ ያሉ ፡ ሰባቱ ፡ ምእመናን ፡ ናቸው ። ሐተታ ፡ ሁሉን ፡ ይተረጕምለታል ፡ ቢሉ ፡ ቢረቀው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያኀላለታል ፡ ለሄኖክ ፡ ለዳንኤል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንዳኀላላቸው ። አንድም፡ አዎን፡ ይተረጕምለታል ፡ ሚልክ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ዘኤፌሶን ፡

ወፊኑ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሰብዐቱ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ይተረትራል ፡ መልአከ ፡ ኤፌሶን ፡ ዮሐንስ ፡ ሁለተኛ ፡ ስሙ ፡ ደማትሬ ፡ ለሱ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ፡

ከመዝ ፡ ይቤለከ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡

ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ (ጥቅ) ፡ እግዚእ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ እንዲል ።

ዘያጸንዕ ፡ ሰብዐተ ፡ ከዋክብተ ፡ በየማኑ ፡

ሰባቱን ፡ ከዋክብት ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ያጸና ፡ እሱ።አንድም ፡ ሰባቱን ፡ መንፈሳውያን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ በሥልጣኑ ፡ ያጸና ።

ወዘየሐውር ፡ በማእከለ ፡ መኃትው ፡ ዘወርቅ ፡

በሰባቱ ፡ የወርቅ ፡ መቅረዝ ፡ መካከል ፡ የሚሄድ ፡ ፋናም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ ከዚያ ፡ ይነብር ፡ አለ ፡ ከዚህ ፡ የሐውር ፡ አለ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሠሩ ፡ ይለያቸዋልና ፡ ከዚህ ፡ የሐውር፡አለ፡ ጽድቅ፡ሲሠሩ፡ያድርባቸዋልና፡ከዚያ፡ይነብር፡አለ።አንድም፡የሐውርን፡ይነብር፡ሲል ፡ ነው። (ጥቅ)፡ ለምንት፡ የሐውር፡ወልደ፡ ብእሲት፡ምስለ፡ ብሉየ፡ መዋዕል፡ወእለ ፡አምሠጡ፡የሐውሩ፡ባቲ፡እንዲል፡ወእመ ፡ አኮሰ ፡ እመጽእ፡ ወአድለቀልቃ፡ለማኅቶትከ፡እምኑ፡ መካና፡ ብሎ ፡የሚያመጣ ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ አርእስት ፡ ዘየሐውር ፡ በማዕከለ ፡ መኃትው ፡ አለ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ።

፪ ፤ ርኢኩ ፡ ግብረከ ፡ ወጻማከ ፡ ወትዕግሥተከ ፡

ሥራህን ፡ ድካምህን ፡ መከራውን ፡ መታገሥህን ፡ አውቃለሁ ።

ወከመ ፡ ኢትክል ፡ ጸዊሮቶሙ ፡ ለእኩያን ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ርእሶሙ ፡ ሐዋርያተ ፡ ወኢኮኑ ፡ ወረከብካሆሙ ፡ ከመ ፡ ሐሰዉ ።

ሳይሆኑ ፡ ሐዋርያት ፡ ነን ፡ የሚሉትንም ፡ መታገሥ ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ እንዳይቻልህ ፡ አውቃለሁ ፡ በሐሰት ፡ ነን ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፪ ፡ ፫ ።

፫ ፤ ወተዐገሥከ ፡ ወጾርከ ፡ በእንተ ፡ ስምየ ፡

በስሜ ፡ ስላመንህ ፡ ስሜን ፡ ስላስተማርህ ፡ በስሜ ፡ ስለተጠራህ ፡ መከራውን፡ ታግሠህ ፡ ተቀብለሃል ፡ መከራውን ፡ አልሰለችህም ፡ ገላት ፡ ፮ ፡ ፱ ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።

፬ ፤ ወባሕቱ ፡ ቦ ፡ ዘአሐይሰከ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ የምነቅፍብህ ፡ አለኝ ፡ በዚህ፡ አልነቅፍህም ፡ በሌላው ፡ እነቅፍሃለሁ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡

እስመ ፡ ኀደገ ፡ አፍቅሮተከ ፡ ዘቀዲሙ ።

የቀደመ ፡ ሥራህን ፡ ትተሃልና ። ሐተታ ፡ ሥራው ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፡ አልታወቀም ። አንድም ፡ ታውቋል ፡ ምጽዋት ፡ ነበረ ፡ የተወበት ፡ ምክንያት ፡ አልታወቀም ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

፭ ፤ ወተዘከር ፡ በይነ ፡ ምንት ፡ ወደቀ ፡

አስተውል ፡ ምጽዋቱን ፡ ለምን ፡ ተውህ ፡ ምጽዋት ፡ አያጸድቅም ፡ አሉህን ፡ ገበሬ ፡ ከዕርበተ ፡ ፀሐይ ፡ በፊት ፡ ሥራውን ፡ ይፈታልን ፡ እንደዚህስ ፡ ከሞት ፡ አስቀድመህ ፡ ምጽዋቱን ፡ ለምን ፡ ተውህ ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ነስሕ ፡ እንከ ፡

ተው ፡ ተመለስ ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ እመጽእ ፡ ወአድለቀልቃ ፡ ለማኅቶትከ ፡ እምኑ ፡ መካና ፡ እመ ፡ ኢነሳሕከ ፡

ያለዚያ ፡ ግን ፡ ባትመለስ ።

ወከመ ፡ ቀዲሙ ፡ ግብረከ ፡ እመ ፡ ኢገበርከ ፡

እንደ፡ቀድሞው ፡ ሥራህን ፡ ባትሠራ ፡ በመዓት ፡መጥቼ፡ ሕዝቡን፡ከኤፌሶን፡ አጠፋቸዋለሁ፡ ሐተታ፡ ሕዝቡ፡ ቢጠፉ፡ እሱ፡ ምን ፡ ይጎዳል ፡ ቢሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ከጠፉ ፡ በማን፡ ላይ፡ ይሾማል ። አንድም ፡ (ጥቅ) ፡ ወበከመ ፡ ካህን ፡ ከማሁ ፡ ሕዝብኒ ፡ እንዲል፡ ግብረ፡ አበር ፡ ናቸውና ። አንድም ፡ ሹመትህን፡ ከማዕርግ፡ አዋርዳታለሁ። አንድም ፡ ነፍስህን ፡ ከሥጋህ ፡ እለያታለሁ ።

፮ ፤ ወዝንቱሰ ፡ ብከ ፡

ይህን ፡ ግን ፡ ይዞሃል ፡

እስመ ፡ ትጸልእ፡ ምግባሮሙ፡ ለኒቆላውያን ፡ በከመ ፡ አነ ፡ እጸልእ ።

እኔ ፡ እንድጠላ ፡ የኒቆላውያንን ፡ ግብር ፡ ትጠላለህና ። ሐተታ፡ እሊህ፡ ኒቆላውያን ፡ ግብረ ፡ ሰዶም ፡ የሚሠሩ ፡ ጥምቀት ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ፡ ግዝረት ፡ ባርባ ፡ ዘመን ፡ የሚሉ ፡ የኒቆላዎስ ፡ ፈላሲ ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ናቸው ፡ ይህስ ፡ ቢሆን ፡ ሐዋርያት ፡ በዘመኑ ፡ ነበሩና ፡ ብዙ ፡ ድርሰት ፡ በደረሱ ፡ ብዙ ፡ ተግሣጽ ፡ በጻፉ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ አበር፡ ቀኍ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፻፴፱፡፳፩ ።

፯ ፤ ዘቦ ፡ እዝነ ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

የኒቆላውያን፡ ግብር ፡ ድል፡ የነሣ፡ እንዳይጎዳ ፡ ድል ፡ ያልነሣ ፡ እንዲጎዳ ፡ እዝነ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ። አንድም ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይን ፡ በፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ እንዳይጎዳ ፡ ድል ፡ ያልነሣ ፡ እንዲጎዳ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ፡

ምንተ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡም ፡ ነው ። አንድም፡ ላለቃው፡ የተናገረ፡ ለሕዝቡም ፡

ወለዘሞዐስ ፡ እሁቦ ፡ ይብላዕ ፡ እምውስተ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ገነቱ ፡ ለአምላኪየ ።

የኒቆላውያንን ፡ ግብር፡ ድል፡ ለነሣ ። አንድም ፡ ፍቅረ ፡ ንዋን ፡ በፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ድል ፡ ለነሣ ፡ በፈጣሪዬ ፡ ገነት ፡ ካለ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እሰጠዋለሁ ፡ አለ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ የምትገኝ ፡ ልጅነትን ፡ እሰጠዋለሁ ። አንድም ፡ በፈጣሪዬ ፡ ሰውነት ፡ ያለ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ እሰጠዋለሁ ። አንድም ፡ በፍቅሩ ፡ ተሠውራ ፡ ያለች ፡ ፍቅሩን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ቀኍ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ፡ ፳፮ ። ም ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ፡፳፩። ም ፡ ፳፪ ፡ ፪ ። ዘፍጥ ፡ ፪ ፡ ፱ ።

፰ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሴሜርኔስ ፡

መልአከ፡ ሴሜርኔስ፡ ሄሬኔዎስ ፡ ሁለተኛ ፡ ስሙ ፡ ኢያሳ ፡ ለሱ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ።

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወውእቱ ፡ ደኃራዊ ፡ ዘሞተ ፡ ወሐይወ ።

ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡ የሚሆን ፡ ሙቶ ፡ የተነሣ ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ፡ ወኩን ፡ መሃይምነ ፡ እስከ ፡ ለሞት ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣ፡ ነውና ፡ እንደ፡ አርእስት፡ ተናገረ፡ ም፡ ፩፡ ፲፯ና፡ ፳፪፡ ፲፫ ።

፱ ፤ አአምር ፡ ሕማመከ ፡

ንዴትህን ፡ አውቃለሁ ፡

ወኃጣይእከ ፡

ከብዕለ ፡ ዓለም ፡ መቸገርህንም ፡ አውቃለሁ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወባሕቱ ፡ ብዑል ፡ አንተ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ባለጸጋ ፡ ነህ ፡

ወዕርፈቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይብሉ ፡ አይሁድ ፡ ንሕነ ፡ ወኢኮኑ ፡

ሳይሆኑ፡ ምእመናን ፡ ነን ፡ የሚሉትን ፡ በመንቀፍ ፡ ባለጸጋ ፡ ነህ ። አንድም ፡ ሕማመከ ፡ መከራህን ፡ አውቃለሁ ፡ ወኃጣይአከ ፡ ከብዕለ ፡ ኃጢአት ፡ መቸገርህን ፡ አውቃለሁ ፡ ባለጸጋም ፡ ነህ ፡ ሳይሆኑ ፡ ምእመናን ፡ ነን ፡ የሚሉትን ፡ በመንቀፍ። አንድም ፡ መንቀፍህን ፡ አውቃለሁ ።

አላ ፡ ማኅበሩ ፡ ለሰይጣን ፡ እሙንቱ ።

የሰይጣን ፡ አሽክርት ፡ ናቸው ፡ እንጅ ፡ ያዕ ፡ ፪ ፡ ፳ ። ም ፡ ፫ ፡ ፱ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

፲ ፤ ኢትፍራህ ፡ ምክተኒ ፡ በእንተ ፡ ዘሀለወከ ፡ ትሕምም ፡

ነገር ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ ስላለህ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አትፍራ ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ ሰይጣን ፡ ይወዲ ፡ እምኔክሙ ፡ ውስተ ፡ሞቅሕ ፡ ከመ ፡ ትትዓቀፉ ፡

እንሆ ፡ ሰይጣን ፡ ከናንት ፡ ወገን ፡ እንድትጋዙ ፡ ያደርጋልና ፡ መከራ ፡ የለብኝም ፡ እንዳይል፡ ኢትፍራ፡ በእንተ ፡ ዘሀለወከ ፡ ትሕምም ፡ አለ ፡ በኔ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንዳይል ፡ ይወዲ ፡ እምኔክሙ ፡ አለ ፡ የሽሕ ፡ ሞት ፡ ሠርግ ፡ ብሎ ፡ እንዳይዘለል ፡ ተሐሙ ፡ ይላል ።

ወተሐሙ ፡ ዐሡረ ፡ መዋዕለ ፡

ዐሥር ፡ ቀን ፡ መከራ ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ አለህና ፡ ሐተታ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ በሰማዕትነት ፡ ታስሮ ፡ ሰንብቶ ፡ ሙቷል ፡

ወኩን ፡ መሃይምነ ፡ እስከ ፡ ለሞት ፡

እስከ፡ መሞት፡ ደርሰህ፡ በሃይማኖት፡ጽና።

ወእሁበከ ፡ አክሊለ ፡ ሕይወት ።

መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አወርሳለሁ ፡ ሐተታ ፡ አክሊል ፡ አላት፡ የብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የብዕለ ፡ ነፍስም ፡ ፍጻሜ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ናትና ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፳፰ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬፡ ፰ ።

፲፩ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

ክህደትን ፡ በሃይማኖት ፡ ፍርሃትን ፡ በጥብዐት ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ እንዳይጎዳ ፡ ድል ፡ ያልነሣ ፡ እንዲጎዳ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ፡

ምንተ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ፡

ወዘሰ ፡ ሞዐ ፡ ኢይመውት ፡ ዳግመ ፡ ሞተ ።

ላለቃው ፡ የተናገረ ፡ ለሕዝቡም ፡ ክህደትን ፡ በሃይማኖት ፡ ፍርሃትን ፡ በጥብዓት ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ ዳግመኛ ፡ አይሞትም፤ ሐተታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢሞት ፡ ሁለተኛ ፡ በሥጋ ፡ ቢሞት ፡ በነፍስ ፡ አይሞትም ። አንድም ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ፈርሰህ ፡ በስብሰህ ፡ ቅር ፡ አይሉትም ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፲፬ ።

፲፪ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘጴርጋሞን ፡

መልአከ ፡ ጴርጋሞን ፡ ጋይዮስ ፡ ሁለተኛ፡ ስሙ ፡ ጠብዶን ፡ ለሱ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ፡

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ዘቦ ፡ ሰይፍ ፡ በሊሕ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ።

ሁለት ፡ ልሳን ፡ ሰይፍ ፡ ያለው ፡ እሱ ፡ እንዲህ፡ አለ፡ ብለህ፡ ጻፍለት፡ አለኝ፡ አለ ፡ ንዑና ፡ ሑሩ ፡ በቃሉ ፡ የሚናገር ፡ እሱ ። አንድም ፡ (ዘሠለስቱ ፡ አፉሁ) ፡ እንደ ፡ በለው ፡ ሰይፍ ፡ ሦስት ፡ ልሳን ፡ ያለው ፡ ሰይፍ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ እሱ ፡ አለ ፡ አንድነት ፡ ሦስትነት ፡ በቃሉ ፡ የሚናገር ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ። አንድም ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ እመጽእ ፡ ወእፀብእሙ ፡ በሰይፈ ፡ አፉየ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣ ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ አርእስት ፡ ተናገረ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።

፲፫ ፤ አአምር ፡ ኀበ ፡ ታነብር ፡ እዴከ ፡ መንበሩ ፡ ለሰይጣን ፡

እደ ፡ ሥጋህን ፡ ለጸሎት፡ እደ ፡ ቃልህን ፡ ለትምህርት ፡ ያኖርህባቸው ፡ ሰዎች ፡ የሰይጣን ፡ ማደሪያ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አውቃለሁ ። አንድም ፡ እደ ፡ ሥልጣንህን ፡ በግዝት ፡ ማኖርህ ፡ የሰይጣንን ፡ ማደሪያ ፡ ለማፍረስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቃለሁ ፡

ወታጸንዕ ፡ ስምዕየ ፡ ወኢክሕድከ ፡ ሃይማኖትየ ፡

አምልኮቴን ፡ አጽንተህ ፡ ይዘሃል ፡ ሃይማኖቴንም ፡ አለወጥህም ፡

በመዋዕል ፡ ዘቀተልዎ ፡ በኀቤክሙ ፡ ለጻድቅየ ፡ መሃይምን ፡ በኀበ ፡ ይነብር ፡ ሰይጣን ።

ሰይጣን ፡ ያደረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ወዳጄ ፡ ምእመንን ፡ በገደሉበት ፡ ወራት ፤ (ወበኀበ፡ ይነብር)፡ ሰይጣንም፡ ተበረታቶበት ፡ በነበረ ፡ ወራት ፡ ኢክሕድከ ፡ ላለው ፡ ሐተታ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ስምዖን ፡ ዮዳሄ ፡ ምናሴ ፡ መስም ፡ አንቱጳስ ፡ ይባላል ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፪ ። ም ፡ ፫ ፡ ፰ ።

፲፬ ፤ ወባሕቱ ፡ ቦ ፡ ዘአሐይሰከ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ የምነቅፍብህ ፡ አለኝ ፡

እስመ ፡ ሀለዉ ፡ ዝየ ፡ እለ ፡ ያጸንዑ ፡ ትምህርቶ ፡ ለበለዓም ፡ መምህሩ ፡ ለባላቅ ፡

የባላቅ ፡ መምህር ፡ የበለዓምን ፡ ግብር ፡ የያዙ፡ አሉና፡ ሐተታ፡ በለዓም ፡ የቀደመ ፡ በለዓም ፡ ነው ። አንድም ፡ ሌላ ፡ ስመ ፡ አበር ፡ ግብረ ፡ አበር ፡ ነው ። አንድም ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡ በለዓም ፡ ለጣዖት ፡ ስገዱ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡ ብሉ፡ ይል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ቤተ ፡ አይሁድም ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ያዙ ፡ መሥዋዕተ ፡ ኦሪትን ፡ ብሉ ፡ ይላሉና ፡

ወይወድዩ ፡ ዕቅፍተ ፡ ቅድሜሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ዝቡሐ ፡ ለአማልክት ።

ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ መሥዋዕት ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለጣዖቱ ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ክህደትን ፡ የሚያስተምሩ ፡ አሉና ፡ ዘኁል ፡ ፴፩፡ ፲፮። ይሁዳ ፡ ፲፩ ።

፲፭ ፤ ወእሉኒ ፡ ሀለዉ ፡ ኀቤከ ፡ እለ ፡ ያጸንዑ፡ ትምህርቶሙ ፡ ለኒቆላውያን ።

የኒቆላውያንንም ፡ ግብር ፡ አጽንተው ፡ የያዙ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ አሉና ፡ ቊ ፡ ፮ ፡

፲፮ ፤ ወይእዜኒ ፡ ነስሕ ፡

አሁንም ፡ ተመለስ ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ እመጽእ ፡ ወእጸብኦሙ ፡ ፍጡነ ፡ በሰይፈ ፡ አፉየ ።

ያለዚያ፡ግን፡ፈጥኜ፡ መጥቼ፡ በሥልጣኔ፡ አጠፋቸዋለሁ፤ ም ፡ ፩፡ ፲፮ና፡ ፲፱፡ ፲፭ ፡ ፳፩ ።

፲፯ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ።

የበለዓምን ፡ ግብር ፡ የያዘ ፡ እንዲጎዳ ፡ ያልያዘ ፡ እንዳይጎዳ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ፡

ምንተ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ፡

ወለዘሞዐ ፡ እሁቦ ፡ መና ፡ ዘኅቡእ ፡

ላለቃው ፡ የተናገረ ፡ ለሕዝቡም ፡ የበለዓምን ፡ ግብር ፡ ላልያዘ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ኅቡእ ፡ መናን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ አለ ፡ አእ
ምሮ ፡ ጠባይዕን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ሐተታ ፡
መና ፡ አለው ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ፡ ደም ፡
ይሆናል ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነፍስ ፡
ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳ ፡ ትኖራለችና ፡

ወእሁቦ ፡ መጽሐፈ ፡ ብርሃን ፡

አእምሮ ፡ መንፈሳዊንም ፡ እሰጠዋለሁ ፡

ወውስተ ፡ ውእቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽሑፍ ፡ ስም ፡ ሐዲስ፡
ዘአልቦ ፡ ዘየአምሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘነሥአ ።

በአእምሮ ፡ መንፈሳዊም ፡ በሃይማኖት ፡
ገንዘብ ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡
የሚያውቀው፡ የሌለ፡የሦስቱ፡ መመሳሰል፡
ተጽፏል ። አንድም ፡ (መና ፡ ዘኅቡእ) ፡
እስራኤል ፡ ሕገ ፡ ጣዖትን ፡ ትተው ፡ ሕገ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ቢይዙ ፡ መና ፡ እንደ ፡
ወረደላቸው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ እሰጠ
ዋለሁ ፡ (ወእሁቦ ፡ መጽሐፈ ፡ ብርሃን) ፡
እስራኤል፡ አምልኮተ ፡ ጣዖትን፡ ትተው ፡
አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢይዙ ፡
ሕገ ፡ ኦሪት ፡ እንደ ፡ ተሠራችላቸው ፡ ወን
ጌልን ፡ እሰጠዋለሁ፡ (ወውስተ ፡ ውእቱ)፡
በኦሪት ፡ አህያ ፡ ሸራህያ ፡ አልሻዳይ ፡
የሚል ፡ ተጽፎ ፡ እንዳለ ፡ በወንጌልም ፡
በተዋሕዶ ፡ ገንዘብ ፡ ካደረገው ፡ ከርሱ ፡
በቀር ፡ ሌላ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገው ፡ የሌለ ፡
ስመ ፡ ሥጋዌ ፡ ተጽፏል ፡ አማኑኤል ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መባል ፡ ነው ፡
ም ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፲፰ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ዘትያጥሮን ፡

መልአከ ፡ ትያጥሮን ፡ ሉክዮስ ፡ ሁለተኛ ፡
ስሙ ፡ ዴጀባል ፡ ለሱ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ፡

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡
አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ፡

ዘአዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ ወእገሪሁ ፡ ከመ፡
ርስነ ፡ ብርተ ፡ ሊባኖስ ።

ዐይኖቹ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ የሚመስሉ ፡ እግ
ሮቹም ፡ እንደ ፡ ደጋ፡ ብረት፡ ግለት፡ ያሉ፡
እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት ፡
አለኝ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፬ና ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ።

፲፱ ፤ አአምር ፡ ግብረከ ፡ ወተፋቅሮተከ ፡ ወሃይማ
ኖተከ ፡ ወመልእክተከ ፡ ወትዕግሥተከ ፡

ሥራህን ፡ ፍቅር ፡ መያዝህን ፡ ሃይማኖ
ትህን ፡ ተልእኮህን ፡ ትዕግሥትህን ፡ አው
ቃለሁ ።

ወግብርከኒ ፡ ደኃሪት ፡ ትበዝኅ ፡ እምነ ፡ ቀዳሚት ፡

ከቀደመ ፡ ሥራህ ፡ የኋላ ፡ ሥራህ ፡ የጸ
ናች ፡ ትሆናለች ። ሐተታ ፡ ሥራው ፡ ምጽ
ዋት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በሰማዕትነት ፡
ሙቷል ።

፳ ፤ ወባሕቱ ፡ ቦ ፡ ዘአሐይሰከ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ የምነቅፍብህ ፡ አለኝ ፡

እስመ ፡ አርመምከ ፡ ላቲ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ብእሲት ፡
እንተ ፡ ትብል ፡ ርእሳ ፡ ነቢይተ ፡ ወኢኮነት ፡

ሳትሆን ፡ አዋቂ ፡ ነኝ ፡ የምትል ፡ ኤልዛ
ቤልን ፡ ዝም ፡ ብለሃታልና ፡ ኤልዛቤል ፡
የቀደመች ፡ ኤልዛቤል ፡ ናት ። አንድም ፡
ሌላ ፡ ስመ ፡ አበር ፡ ግብረ ፡ አበር ። አን
ድም ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡ ኤልዛ
ቤል ፡ ለጣዖት ፡ ስገዱ ፡ መሥዋዕተ ፡
ጣዖቱን ፡ ብሉ ፡ ትል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ቤተ፡ አይሁድም ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ያዙ ፡
መሥዋዕተ ፡ ኦሪትን ፡ ብሉ ፡ ይላሉና ።

ወትሜህር ፡ በዘታስሕቶሙ ፡ ወታዜምዎሙ ፡ ለአግ
ብርትየ ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ዝቡሐ ፡ ለአማልክት ።

ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡
ወገኖቼን ፡ ጣዖት ፡ በምታስመልካቸው ፡
በምታስታቸው ፡ ገንዘብ ፡ የምታስተምር፡
ቍ ፡ ፬ ። ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፯ ፡ ፴፩ ።



፳፩ ፤ ወወሀብክዋ ፡ መዋዕለ ፡ በዘትኔስሕ ፡

ንስሐ ፡ በምትገባ ፡ ገንዘብ ፡ ዘመን ፡ አብ
ዝቼ ፡ ወራት ፡ አስፍቼ ፡ ሰጠኋት ፡

ወዐበየት ፡ ነስሐ ፡ እምነ ፡ ዝሙታ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ከኃጢአቷ ፡ ከዝሙቷ ፡ አል
መለስም ፡ አለች ።

፳፪ ፤ ወናሁ ፡ አገብአ ፡ ውስተ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ምስ
ካባ ፡

እንሆ ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ መሬትነቷ ፡ እመ
ልሳታለሁ ፡

ወለእለኒ ፡ ዘመዉ ፡ ምስሌሃ ፡ ውስተ ፡ ዐቢይ ፡ ሥ
ቃይ ፡

ከሷ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ እሷ ፡ የሴሰኑትንም ፡
ወደ ፡ መሬትነታቸው ፡ እመልሳቸዋለሁ ፡
አገብአሙ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ትኤምኃ
ክሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወማርቆስ ፡
ወልድየ ፡ ብሎ ፡ ይኤምኃክሙ ፡ እንዳለ
በት ። አንድም ፡ ለጽኑ ፡ ፍዳ ፡ አሳልፌ ፡
እሰጣቸዋለሁ ፡

እመ ፡ ኢነስሐት ፡ እምነ ፡ ምግባራ ።

ከክፉ ፡ ሥራዋ ፡ ካልተመለሰች ።

፳፫ ፤ ወእቀትል ፡ ደቂቃ ፡ በሞት ፡

ልጆቿን፡ በሞት፡ በጦር ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡

ወየአምሩ ፡ ኵሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከመ ፡
አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘእፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡

ኵላሊት ፡ ያመላለሰውን ፡ ልቡና ፡ ያሰበ
ውን ፡ መርምሬ ፡ የምፈርድ ፡ እኔ፡ እንደ፡
ሆንሁ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃሉ ፡

ወእፈድየክሙ ፡ ለለአሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡
በከመ ፡ ምግባሪክሙ ።

ከናንተ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ እንደ ፡ ሥ
ራችሁ ፡ ፍዳውን ፡ እከፍላችኋለሁ፡ መዝ ፡
፯ ፡ ፲ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲ ።

፳፬ ፤ ወለክሙኒ ፡ እብል ፡ ለእለ ፡ ተረፍክሙ ፡ ው
ስተ ፡ ትያጥሮን ፡

በትያጥሮን ፡ ላላችሁ ፡ ለናንተ ፡ እናገራ
ለሁ ።

ወለእለ ፡ አልብክሙ ፡ ዝንቱ ፡ ትምህርት ፡ ለእለ ፡
ኢተአምርዋ ፡ ለጕሕሉተ ፡ ሰይጣን ፡

ይህን ፡ ትምህርት ፡ ላልያዛችሁ ፡ የሰይ
ጣንንም ፡ ተንኰል ፡ ለማታውቁ ፡

ዘይብል ፡ እወዲ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ክልኤ ፡ ክበደ ።

ሕገ ፡ ሥጋንና ፡ ሕገ ፡ ነፍስን ፡ አንድ ፡
አድርጋችሁ ፡ ያዙ ፡ የሚል ፡ የሰይጣንን ፡
ተንኰል ፡ ለምታውቁ ። አንድም ፡ እብል፡
ኢይወዲ ፡ ሕገ ፡ ሥጋንና ፡ ሕገ ፡ ነፍስን ፡
አንድ ፡ አድርጋችሁ ፡ አትያዙ ፡ እላለሁ ።
አንድም ፡ ኢይብል ፡ እወዲ ፡ አንድ ፡ አድ
ርጋችሁ ፡ ያዙ ፡ አልልም ።

፳፭ ፤ ወባሕቱ ፡ ዘብክሙ ፡ አጽንዑ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ባላችሁበት ፡ ጽኑ ፡ ባላችሁ
በት ፡ ጽኑ ፡ እንጅ ።

እስከ ፡ አመ ፡ እሣህል ።

በሞት፡ ይቅር፡ እስክላችሁ፡ ድረስ፡ (ጥቅ)
እስመ ፡ ይሄይስ፡ እምሐይው ፡ ሣህልከ ፡
ወይጤይቁ ፡ ሣህሎ፡ እምዘወሀብክዎ፡ እን
ዲል ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፳፮ ፤ ወለዘሞዐ ፡ ወዐቀበ ፡ ሕግየ ፡ ለዝሉፉ ፡

የኤልዛቤልን ፡ ግብር ፡ ላልያዘ ፡ ለዘለ
ዓለሙ ፡ ሕጌን ፡ ለጠበቀ ፡

እሁቦ ፡ ሥልጣነ ፡ላዕለ ፡ አሕዛብ ።

በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ሥልጣንን ፡ እሰጠዋ
ለሁ ።

፳፯ ፤ ወይርእዮሙ ፡ በበትረ ፡ ኀጺን ፡

በኃ ፡ በኃያችን ፡ በጽኑ ፡ ሥልጣን ፡ ይጠ
ብቃቸዋል ፡ ብረት ፡ ያለበት ፡ ብትር ፡
ጽኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ፡ ንዋየ ፡ ለብሓ ፡ ይቀጠቅጦሙ ።

ክፉ ፡ ክፉዎችን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ይቀጠቅጣቸዋል ። አንድም ፡ በን ስሓ ፡ ያድሳቸዋል ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፭ ።

፳፰ ፤ በከመ ፡ አነ ፡ ነሣእኩ ፡ እምኀበ ፡ አቡየ ፡

እኔ፡ ካባቴ፡ ሥልጣንን፡ እንደ፡ ተቀበልኩ፡

ወእሁቦ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ።

እሁቦና ፡ እሁቦ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ እኔ ፡ እሰጠዋለሁ ። አን ድም ፡ በየራሱ ፡ ኮከብ ፡ ጽባሕ ፡ አእም ሮን፡እኔ፡አሳድርበታለሁ።አንድም፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ፡እኔ፡ አድርበታለሁ፡ መዝ፡ ፪፡ ፰ ።

፳፱ ፤ ዘቦ ፡ እዝነ ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

የኤልዛቤልን ፡ ግብር ፡ ድል ፡ ቢነሡ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለ ፡ ድል ፡ ባይነሡ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ።

ምንተ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስ ቲያናት ።

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ምንተ ፡ ይቤን ፡ እያስቀደመ ፡ ወለዘሞዐን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እያደረገ ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ። ከዚህ ፡ ወለ ዘሞዐን ፡ አስቀደመ ፡ የፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የኋላውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የማደርግ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲል ። አንድም ፡ ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፯ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ዘሰርዴሲሶን ፡

መልአከ ፡ ሰርዴሲሶን ፡ አርስጦን ፡ ሁለ ተኛ ፡ ስሙ ፡ ርሄል ፡ ለሱ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ።

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ዘቦ ፡ ሰብዐቱ ፡ መንፈስ ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

ፍጹም ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከእ ግዚአብሔርነቱ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ። አንድም ፡ ፍጹም ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከእግዚአብሔርነቱ ፡ የሚሰጥ ፡ እሱ፡እንዲህ፡አለ፡ ብለህ፡ ጻፍለት፡አለኝ ።

ወሰብዐቱ ፡ ኮከብ ፡

ሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ በእጁ፡ ተይዘው፡ ያሉ። አንድም ፡ ሰባቱ ፡ መንፈሳውያን ፡ ከዋክ ብት ፡ ኤጲስ፡ቆጶሳት፡ በሥልጣኑ ፡ የጸኑ ፡

አእምር ፡ ግብረከ ፡

ሐኬትህን ፡ አውቃለሁ ፡

ከመ ፡ ስምከ ፡ ሕያው ፡ ወምውት ፡ አንተ ።

ስምህ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ምውት ፡ እንደሆንህ ፡ አውቃለሁ ፡ ሐተታ ፡ ስሙ ፡ ሚካኤል ፡ ይባላል ፡ ተም ረህ ፡ እንዳታስተምር ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፯ ። ም ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

፪ ፤ ትጋህ ፡ እንከ ፡

ተግተህ ፡ አስተምር ፡

ወአጽንዖሙ ፡ ለእለ ፡ አልጸቁ ፡ ይሙቱ ፡

አብነት ፡ ትምህርት ፡ አጥተው ፡ ሊጎዱ ፡ የቀረቡትንም ፡ መክረህ ፡ አስተምረህ ፡ አድናቸው ፡ ሐተታ ፡ የሰው ፡ ባሕርዩ ፡ ባሕርይ ፡ እንስሳዊ ፡ ባሕርይ፡ መልአካዊ ፡ ነው ፡ ባሕርይ፡ እንስሳዊ ፡ ምግብ፡ ሲያጣ ፡



ይሞታል ፡ ባሕርይ ፡ መልአካዊ ፡ ትምህ ርት ፡ ሲያጣ ፡ ይጎዳል ፡ (ጥቅ) ፡ አእምር፡ ከመ ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲሳይ ፡ ዘበአ ማን ፡ ሲሲተ ፡ ልብ ፡ ቃላቲሁ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ አመጽእ ፡ ረኀበ ፡ እክል ፡ ወዕ ምዐ ፡ ማይ ፡ አኮ ፡ ረኀበ ፡ እክል ፡ ወዕ ምዐ ፡ ማይ ፡ ረኀብሰ ፡ ወዕምዕ ፡ ኢሰ ሚዐ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ኢረከብኩ ፡ ግብረከ ፡ ፍጹመ ፡ በቅድመ ፡ አምላኪየ ።

በፈጣሪዬ ፡ ዘንድ ፡ ሥራህን ፡ ፍጹም ፡ ሆኖ ፡ አላገኘሁትምና ፡ ቍ ፡ ፲፱ ። ሕዝ ፡ ፴፬ ፡ ፬ ።

፫ ፤ ወተዘከር ፡

አስተውል ፡

እፎ ፡ ነሣእከ ፡

መክሊቱን ፡ ለምን ፡ ተቀበልህ ፡ ሹመ ቱን ፡ ለምን ፡ ተሾምህ ፡ ማለት ፡ ነው ፡

ወሰማዕከ ፡

ምን ፡ ሲልስ ፡ ሰምተኸው ፡ ነበረ ፡ ገብር ፡ ሀካይ ፡ ለምንት ፡ ኢያገባእከ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ ማዕድየ ፡ ሲል ፡ ሰምተኸው ፡ አልነበረምን ። አንድም ፡ ትምህርቱን ፡ ለምን ፡ ነሣሃቸው ፡ ምን ፡ ሲልስ ፡ ሰም ተኸው ፡ ነበረ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በ ጸጋ ፡ ሀቡ ፡ ሲል ፡ ሰምተኸው ፡ አልነበ ረምን ። አንድም ፡ እፎ ፡ ሰማዕከ ፡ ወነሣ እከ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ፡ ሰምተህ ፡ ትምህርቱን ፡ ለምን ፡ ነሣሃቸው ።

ነስሕ ፡ እንከ ፡ ወእመሰ ፡ ኢተጋህከ ።

ተው ፡ ተመለስ ፡ ተግተህ ፡ አስተምር ፡ ተግተህ ፡ ባታስተምር ፡ ግን ፡

እበጽሐከ ፡ ግብተ ፡ ከመ ፡ ሠራቂ ፡

እንደ ፡ ሌባ ፡ አመጣጥ ፡ ድንገት ፡ እመጣ ብሃለሁ፡ ሐተታ ፡ሌባ ፡ ባላሰቡት ፡ ዕለት ፡ ባልጠረጠሩት ፡ ሰዓት ፡ እንዲመጣ ።

ወኢተአምር ፡ በአይ ፡ ሰዓት ፡ እመጽእ ፡ ላዕሌከ ።

በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ እንድመጣ ፡ አታ ውቅምና ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፭ ፡ ፪ ።

፬ ፤ ወባሕቱ ፡ ብከ ፡ ኅዳጣን ፡ ሰብእ ፡ ውስተ ፡ ሰር ዴስ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሰርዴስ ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ አሉህ ፡ በዚህ ፡ አልነቅፍህም ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

እለ ፡ ኢገመኑ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ምስለ ፡ አንስት ፡

ሰውነታቸውን ፡ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ ያላሳ ደፉ ። አንድም ፡ ሰውነታቸውን ፡ በኃጢ አት ፡ ያላሳደፉ ፡ (ጥቅ) ፡ ወትነብር ፡ ብእ ሲት ፡ ማእከለ ፡ መስፈርት ፡ እንዲል ።

ወየሐውሩ ፡ ምስሌከ ፡ በንጹሕ ።

ካንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳንተ ፡ በንጹሕ ፡ ነገር ፡ ጸንተው፡ የሚኖሩ ። አንድም ፡ በንጽሕና፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ይሁዳ ፡ ቍ ፡ ፳፫ ።

፭ ፤ ወለዘሞዐ ፡ ከመዝ ፡ ልብሰ ፡ ንጹሕ ፡ ይደ ልዎ ።

ሐኬትን ፡ በትጋት ፡ ኃጢአትን ፡ በንጽ ሕና ፡ ድል ፡ ለነሣ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ንጹሕ፡ ልብስ ፡ ይገባዋል ፡ አለ ፡ ክብር ፡ ይገባ ዋል ።

ወኢይደመሰስ ፡ ስሙ ፡ እምነ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡

ስሙ ፡ ከሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ አይፋ ቅም ፡ አለ ፡ በልበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታ ውቆ ፡ ይኖራል ፡

ወአአምኖ ፡ በስሙ ፡ በቅድመ ፡ አቡየ ፡ ወበቅድመ ፡ መላእክቲሁ ።

በስሙ ፡ አምነዋለሁ ፡ አለ፡ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እለዋለሁ ፡ ባባቴ ፡ ፊት ፡ በመላእክትም ፡ ፊት ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፬ና ፡ ፮ ፡ ፲፩ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ፊል ፡ ፬ ፡ ፫። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፪ ።

፰ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

ሐኬትን ፡ በትጋት ፡ ኃጢአትን ፡ በንጽሕ፡ ድል ፡ ቢነሡ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለ ፡ ድል ፡ ባይ ነሡ ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ፡

ምንተ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስ ቲያናት ።

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለ ቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ።

፱ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ዘፊልድልፍልያ ፡

መልአከ ፡ ፊልድልፍልያ ፡ ድሜጥርስ ፡ ሁለተኛ ፡ ስሙ ፡ ፌቤፌል ፡ ለሱ ፡ ጻፍ ለት ፡ አለኝ ።

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ።

ጽኑ ፡ ከሀሊ ።

ወጻድቅ ፡

ጻድቀ ፡ ባሕርይ ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ፡

ዘኅቤሁ ፡ ይነብር ፡ ኵሉ ፡ መራኁተ ፡ ቤተ ፡ ዳዊት፡

የዳዊት ፡ ቤት ፡ መክፈቻ ፡ በእጁ ፡ ያለ ። አንድም ፡ የዳዊትን ፡ ወገን ፡ የሚሾም በት ፡ የሚሽርበት ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡

ወአልቦ ፡ ዘያርኁ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየዐጹ ፡ ዘእንበሌሁ ።

ከሱ ፡ በቀር ፡ የሚከፍት ፡ የሚዘጋ ፡ የሌለ፡ አለ ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ የሚሽር ፡ የሚሾም ፡ የሌለ ፡ (እርሱ ፡ የሾመውን ፡ የሚሽር ፡ እርሱ ፡ የሻረውን ፡ የሚሾም ፡ የሌለ ፡ ቢ ል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ኢሳ ፡ ፳፪ ፡ ፳፪ ።

፰ ፤ አአምር ፡ ግብረከ ፡

ሥራህን ፡ አውቃለሁ ።

ወናሁ ፡ ወሀብኩከ ፡ ቅድሜከ ፡ ኆኅተ ፡ ርኁተ፡ ወአ ልቦ ፡ ዘይክል ፡ ዐጺዎታ ።

እነሆ ፡ እዝነ፡ ሰማዕያንን ፡ ትምህርትን ፡ ሰጠሁህ ፡ ትነገር ፡ ብል ፡ አትነገር ፡ ት ስማ ፡ ብል ፡ አትስማ ፡ ማለት ፡ የሚቻለ ው ፡ የሌለ ።

እስመ ፡ ውኁድ ፡ ኀይልከ ፡

ኀይልህ ፡ ደካማ ፡ ነውና ፡ ሐተታ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በዕርግና ፡ ተሹሟል ። አንድም ፡ አእምሮህ ፡ ጥቂት ፡ ነውና ። አንድም ፡ መምህር ፡ ያስተምራል ፡ እንጂ ፡ ሕሊና ፡ ማቅናት፡ ምስጢርን ፡ በልቡና ፡ መሳል ፡ አይቻለውምና ፡

ወዐቀብከ ፡ ቃልየ ፡

ሕጌን ፡ ጠብቀሃል ፡

ወኢክሕድከ ፡ ስምዕየ ።

አምልኮቴንም ፡ አለወጥህምና ፡፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ።

፱ ፤ ወናሁ ፡ አነ ፡ እሁበከ ፡ እምነ ፡ ማኅበሩ ፡ ለሰ ይጣን ።

የሰይጣን ፡ ማደሪያ ፡ ከሆኑት ፡ ወገን ፡ ማኅበርን ፡ አድርጌ ፡ አስነሣልሃለሁ ፡

ወእምነ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ርእሶሙ ፡ አይሁድ፡ ንሕነ ፡ ወኢኮኑ ፡ ወይሔስዉ ፡

በሐሰት ፡ ነን ፡ ይላሉ ፡ እንጅ ፡ ሳይሆኑ ፡ ምእመናን ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ማኅበርን ፡ አድርጌ ፡ አስነሣልሃለሁ ፡

ወይሰግዱ ፡ ቅድመ ፡ እገሪከ ፡ ወየአምሩ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ አፍቀርኩከ ።

እኔ ፡ እንደ ፡ ወደድሁህ ፡ አውቀው ፡ ይሰግ ዱልሃል ፡ ይገዙልሃል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፱ ። ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፳፫ና ፡ ፷ ፡ ፲፬ ።



፲ ፤ እስመ ፡ ዐቀብከ ፡ ቃልየ ፡

ሕጌን ፡ ጠብቀሃልና ።

ወትዕግሥትየ ፡

ትዕግሥቴንም ፡ ይዘሃልና ። አንድም ፡ ቃለ ፡ ትዕግሥትየ ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡ ታግሼ ፡ የሠራኋት ፡ ወንጌልን ፡ ጠብቀ ሃልና ። አንድም ፡ ወበትዕግሥትክሙ ፡ ታጠርይዋ ፡ ለነፍስክሙ ፡ ወዘአዝለፈ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ውእቱ ፡ ይድኅን ፡ እያለች ፡ ትዕግሥትን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ ጠብቀሃልና ፤

በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አነኒ ፡ ዐቀብኩከ ፡ እምነ ፡ ሰዓተ ፡ መንሱት ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ትምጻእ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ታመክሮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ፡ ምድር ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩን ፡ ሰ ዎች ፡ ትፈታተናቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያላት ፡ መከራ ፡ ከታዘዘባት ፡ ሰዓት ፡ ጠበቅሁህ ፡ ሐተታ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ ጨርሶ፡ መጽውቶ፡ በዘመነ ፡ ረኀብ ፡ ድስት ፡ ሙሉ ፡ ወርቅ ፡ አግኝቶ ፡ እሱም ፡ ተረድቶበታል ፡ ምእመ ናንንም ፡ ረድቶበታል ፡ ም፡ ፲፫ ፡ ፲። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፴፱ ።

፲፩ ፤ ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡ ወአጽንዕ ፡ ዘብከ፡

እነሆ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣለሁና ፡ ባለህበት ፡ ጽና ፡

ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይነሥእ ፡ አክሊለከ ፡

ክብርህን ፡ የሚወስድብህ ፡ እንዳይኖር ፡ ያንዱን ፡ ክብር ፡ አንዱ ፡ ይወስደዋልን ፡ ቢሉ ፡ ሥራውን ፡ ከሠራ ፡ አዎን ፡ ይወስ ደዋል ። (ታሪክ) ፡ እንደ ፡ አርባ ፡ ሐራ ፡ ሰማይ ፡ አርባ ፡ ሐራ ፡ ሰማይን ፡ አንድ ፡ አላዊ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ሰይፍ ፡ ከሚቆራ ርጥ ፡ ባሕር ፡ ጥሏቸው ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ሰን ብተዋል ። ባርባኛው ፡ ቀን ፡ መላእክት ፡ አርባ ፡ አክሊል ፡ ይዘው ፡ ወረዱ ፡ ከነ ዚያ ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ በናንተ ፡ ሃይማኖት ፡ አለሁ ፡ አውጡኝ ፡ ብሎ ፡ ሲወጣ ፡ አሕ ዛብ ፡ በአፍአ፡ እሳት፡ አንድደው ፡ ይጠብ ቋቸዋል ፡ ሠላሳ፡ ዘጠኙን ፡ ተቀብለውት ፡ አንዷቱ ፡ ስትቀር ፡ አይቶ፡ በአፍአ ፡ ካሉ፡ ከአሕዛብ ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖት፡ አለሁ፡ አግቡኝ፡ ብሎ፡ ገብቶ ፡ ተቀብሏታል ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፫ ። ፪ ፡ ፫ ፡ ፲ ።

፲፪ ፤ ወለዘሞዐስ ፡ እሬስዮ ፡ ዐምደ ፡ ውስተ ፡ መቅ ደሱ ፡ ለአምላኪየ ፡

ሐኬትን ፡ በትጋት ፡ ድል ፡ የነሣውን ፡ የጉባኤ ፡ ባለቤት ፡ አደርገዋለሁ ፡

ወኢይወፅእ ፡ እንከ ፡ አፍአ ፡

ከጉባኤ ፡ አልለየውም ። አንድም ፡ የመን ግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ባለቤት ፡ አደርገዋለሁ ፤ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አፍአ ፡ ወደ ፡ ገሃ ነም ፡ አልሰደውም ፡

ወእጽሕፍ ፡ ላዕሌሁ ፡ ስሞ ፡ ለአምላኪየ ፡

ስመ ፡ ወላዲን ።

ወስመ ፡ ሀገሩ ፡ ሐዳስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንተ ፡ ትወ ርድ ፡ እምሰማይ ፡ እምኀበ ፡ አምላኪየ ፡

ስመ ፡ ሠራፂን ፡

ወስምየኒ ፡ ሐዲሰ ።

ስመ ፡ ተወላዲን ፡ እጽፍበታለሁ ፡ በዚህ ፡ ስም፡ እሱ ፡ ቢጠራበት፡ እንጅ፡ አብ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይጠሩበትምና ፡ ስምየኒ ፡ ሐዲሰ ፡ አለ ። አንድም ፡ (ስሞ ፡ ለአምላ ኪየ)፡ ስመ ፡ ወላዲን ፡ ስመ ፡ ተወላዲን ፡ ስመ ፡ሠራፂን ፡ እጽፍበታለሁ ፡ (ወስመ ፡ ሀገሩ) ፡ የሦስቱን ፡ መመሳሰል ፡ (ወስም የኒ) ፡ ስመ ፡ ሥጋዌን ፤ እጽፍበታለሁ ፡ ገላት ፡ ፪ ፡ ፱ ። ም ፡ ፲፬ ፡ ፩ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ና ፡ ፳፩ ፡ ፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

ሐኬትን ፡ በትጋት ፡ ድል ፡ ቢነሡ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለ ፡ ድል ፡ ባይነሡ ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ፡

ምንተ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ።

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላለቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሎዶቅያ ፡

መልአከ ፡ ሎዶቅያ ፡ አርክቦስ ፡ ሁለተኛ ፡ ስሙ ፡ ገብጋብኤል ፡ ለሱ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ፡

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ዘውእቱ ፡ አሚን ፡

አሚን ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት ፡ አለኝ ።

ወውእቱ ፡ ስምዕ ፡ መሃይምን ፡

የታመነ ፡ ምስክር ፡ እሱ ፡

ወጻድቅ ፡

ጻድቀ ፡ ባሕርይ ፡

ወውእቱ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ። አንድም፡ እግዚአብሔርነቱ ፡ ከፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ፡ እሱ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ጻፍለት፡ አለኝ ፡ ም፡ ፩ ፡ ፭። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ቆላ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።

፲፭ ፤ አአምር ፡ ግብረከ ፡

ድንቁርናህን ፡ አውቃለሁ ፡

ከመ ፡ ኢኮንከ ፡ ቊሪረ ፡

አልተማርሁም ፡ ብለህ ፡ እንዳትማር ።

ወኢኮንከ ፡ ምውቀ ፡

ተምሪያለሁ ፡ ብለህ ፡ እንዳታስተምር ፡ አውቃለሁ ፡

ወርቱዕሰ ፡ ትኩን ፡ ቊሪረ ፡

አገባብስ ፡ አልተማርሁም ፡ ብለህ ፡ ልትማር ፡ ይገባል ፡

ወእመ ፡ አኮ ፡ ምውቀ ፡

ያውም ፡ ባይሆን ፡ ተምሪያለሁ ፡ ብለህ ፡ ልታስተምር ፡ ይገባል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ፱ ።

፲፮ ፤ እስመ ፡ ማእከላይ ፡ አንተ ፡

መካከለኛ ፡ ነህና ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ ማይ ፡ ይላል ፡ ማየ ፡ ገጽ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንደ፡ ፊት ፡ ውኃ ፡ የፊት ፡ ውኃ፡ እጅግ፡ የሞቀ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፊት ፡ ይጠብሳል ፡ እጅግም ፡ የበረደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፊት ፡ ይገበዝዛል ፡ ብለው ፡ መካከለኛ ፡ ያደርጉታልና ፡

፲፮ ፤ ወትብል ፡ ብዑል ፡ አነ ፡

ባለጸጋ ፡ ነኝ ፡

ወብዕልኩ ፡

ከብሪያለሁ ፡

ወአልቦ ፡ ዘእፈቅድ ፡ ምንተኒ ፡

ካንተ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የምሻው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ትላለህ ፡

ወለሊከ ፡ ተአምር ፡ ከመ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አንተ፡ ወዕሩቅ ፡ ወዕውር ፡ አንተ ።

ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ዕሩቅ ፡ ዕውር ፡ እንደ ሆንህ ፡ አንት ፡ ቅሉ ፡ ታውቃለህ፡ ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ዕሩቅ ፡ ዕውር ፡ ብሎ ፡ ሦስት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ፡ ለሦስቱም፡ ያመጣል ፡ ፩፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፰ና ፡ ፬ ፡ ፰ ።

፲፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ እብለከ ፡ ትንሣእ ፡ እምኀቤየ ፡ ወርቀ ፡ ዘኢአየ ፡ ዘንጡፍ ፡ ወጽሩይ ፡ በእሳት ፡

አሁንም ፡ በእሳት፡ የተፈተነውን፡ ከእኔ ፡



የተገኘውን ፡ ወርቅ ፡ ተቀበል ፡ እልሃለሁ ፡

ከመ ፡ ትብዐል ፡ ብየ ፡

በእኔ ፡ ወርቅ ፡ ትከብር ፡ ዘንድ ፡ ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ላለው ።

ወልብሰኒ ፡ ዘዚአየ ፡ ትልበስ ፡ ከመ ፡ ትትከደን ፡ ዕርቃነከ ።

የእኔን ፡ ልብስ ፡ ልበስ ፡ እልሃለሁ ፡ ዕርቃንህን ፡ ትሠውር ፡ ዘንድ ፡ ዕሩቅ፡ ላለው ።

ወበፈውሰ ፡ ዚአየ ፡ ትትኰሐል ፡ አዕይንቲከ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ።

በኔ ፡ ሥር ፡ ኵል ፡ ተኳል ፡ እልሃለሁ ። ብርሃን ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ዕውር ፡ ላለው ። አንድም ፡ (ወትብል ፡ ብዑል ፡ አነ) ፡ ተምሪያለሁ ፡ አዋቂ ፡ ነኝ ፡ ከአንት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የምሻው ፡ ትምህርት ፡ የለም ፡ ትላለህ፡ ከትምህርት፡ ነዳይ፡ ምስኪን፡ እንደሆንህ፡ አንተ፡ ቅሉ፡ ታውቃለህ፡ (ወዕሩቅ) ፡ ከክብር ፡ ባዶ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ (ወዕውር ፡ ምስጢር፡ እንዳታይ ፡ አንተ፡ ቅሉ ፡ ታውቃለህ ፡ (ወይእዜኒ፡ እብለከ)፡ አሁንም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተገለጠውን ፡ ትምህርት ፡ ከእኔ፡ ተማር፡ ከእኔ ፡ በተገኘው ፡ ትምህርት ፡ አዋቂ ፡ ትባል ፡ ዘንድ ፡ (ወበልብሰ ፡ ዚአየ) ፡ ከእኔ፡ የተገኘውን፡ ልጅነት ፡ ተቀበል ፡ ከእኔ ፡ ከተገኘው ፡ ክብር፡ ባዶ ፡ እንዳትሆን ፡ (ወበፈውሰ ፡ ዚአየ) ፡ ከእኔ፡ በተገኘ ፡ ዕውቀት ፡ ድንቁርናን ፡ አርቅ ፡ እልሃለሁ ፡ ምስጢርን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ኢሳ፡ ፶፩ ፡ ፩ ። ሚልክ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ራእ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ።

፲፱ ፤ አንሰ ፡ ለእለ ፡ አፈቅር፡ እጌሥጽ ፡ ወእሜህር፡

በዚህ ፡ ሰው ፡ ተግሣጽ ፡ ጸንቶበታል ፡ ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ዕሩቅ ፡ ዕውር ፡ ቢለው ፡ ደህውም ፡ ዕውሩም ፡ ዕሩቁም ፡ እኔ ፡ ብሎ ፡ እንዳያዝን ፡ እኔ ፡ የምወደውን፡ እንዲህ፡ እመክራለሁ፡ አስተምራለሁ ፡

ቅናእ ፡ እንከ ፡ ለንስሓ ፡

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ቀንተህ ፡ ተመለስ ፡ ምሳ፡፫፡፲፪። ፩፡ቆሮ፡፲፩፡ ፴፪። ዕብ፡፲፪፡ ፮ ።

ወናሁ ፡ ቆምኩ ፡ ኀበ ፡ ኆኅት ፡ ወእጐድጕድ ።

እነሆ ፡ ከበር ፡ ቁሜ ፡ ደጅ ፡ እጸፋለሁ ።

፳ ፤ ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘሰምዐኒ ፡ ወአርኀወኒ ፡

ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የከፈተልኝ ። አንድም ፡ ዋዌ ፡ ነው ፡ ዘሰምዐኒ ፡ ወአርኀወኒ ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የከፈተ ።

እበውእ ፡ ሶቤሃ ፡ ወአዐርፍ ፡ ምስሌሁ ፡ ወውእቱኒ ፡ ምስሌየ ፡

ፈጥኜ ፡ ገብቼ ፡ አብሬው ፡ አድራለሁ ፡ እሱም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ፡ ያድራል። አንድም ፡ (ወናሁ ፡ ቆምኩ) ፡ በጉባኤ ፡ ተገኝቼ ፡ ተማሩ፡ እላለሁ፡ (ወእመ፡ቦ)፡ትምህርቴን ፡ ሰምቶ ፡ በተቀበለ ፡ (እበውእ)፡ አድሬበት፡ እኖራለሁ፡ (ወውእቱኒ) ፡ እሱም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ፡ ይኖራል፡ እንደ ፡ እሳትና፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ኅፁዕ ፡ የጸጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ። ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ።

፳፩ ፤ ወለዘሞዐ ፡ እሁቦ ፡ ይንበር፡ ምስሌየ ፡ውስተ፡ መንበርየ ፡

ድንቁርናን ፡ በዕውቀት ፡ ድል ፡ ለነሣ ፡ እኔ ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት፡ ገብቼ፡ እንደ፡ ተቀመጥሁ ፡ መቀመጡን ፡ እሰጠዋለሁ ፡

በከመ ፡ አነ ፡ ሞዕኩ ፡

እኔ ፡ ድል ፡ እንደነሣሁ ፡ ድል ፡ ለነሣ ፡

ወነበርኩ ።

እኔ ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ ገብቼ ፡ እንደ ተቀመጥሁ ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ ገብቶ ፡ መኖሩን ፡ እሰጠዋለሁ ። አንድም፡ እኔ ፡ ድል ፡ ነሥቼ ፡ ውሳጤ፡ መንጦላዕት፡

www.ethiopianorthodox.org

ገብቼ ፡ እንደኖርሁ ፡ ገብቶ ፡ መኖሩን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፰ ።

፳፪ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

እዝነ ፡ ልቡና፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያስተውል ፡

ምንተ፡ይቤ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ለአብያተ፡ክርስቲያናት ።

ላለቃውስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ላለቃው ፡ የተናገረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ፡ ርኢኩ ፡ ኆኅተ ፡ ርኅዉተ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡

ዝ ፡ ሲናገረው ፡ የመጣው ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፡ የተከፈተ ፡ ደጅ ፡ አየሁ ፡ ሐተታ ፡ አሁን ፡ በሰማይ ፡ መከፈት ፡ መዘጋት ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ የተዘጋ ፡ ደጅ ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ያልታየ ፡ ዕቃ ፡ እንዲታይ ፡ ያልተገለጸ ፡ ምስጢር ፡ ተገለጸልኝ ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወቀዳማየ ፡ ቃለ ፡ ሰማዕኩ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ መጥቅዕ ፡ ይትናገር ፡ ምስሌየ ፡

እንደ ፡ ነጋሪት ፡ ለኔ ፡ የሚነግረኝን ፡ መዠመሪያውን፡ ቃል፡ ሰማሁ። አንድም ፡ ቀዳማይ ፡ ቃል ፡ ዘሰማዕኩ ፡ ይላል ፡ ወይቤለኒ ፡ ማንሻ ፡ እንደ ፡ ነጋሪት ፡ ለኔ ፡ ሲነግረኝ ፡ የሰማሁት ፡ መዠመሪያው ፡ ቃል ፡

ወይቤለኒ ፡ ዕርግ ፡ ዝየ ፡

ወደዚህ፡ ና ፡ አለኝ፡ አለ፡ ከአእምሮ፡ ወደ ፡ አእምሮ ፡ ከዕውቀት ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ አፋለሰኝ ።

ወአነ ፡ አርእየከ ፡ ዘሀለወ ፡ ይኩን ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ አሳይሃለሁ ፡ እገልጽልሃለሁና ፡ ወደዚህ ፡ ውጣ ፡ አለኝ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲ ። ወእምዝ ፡ ተመሰጥኩ ፡ በመንፈስ፡ ይላል፡ በልቡና ፡ ተራቀቅሁ ።

፪ ፤ ወናሁ ፡ ርኢኩ ፡ መንበር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ይነብር ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ በሰማይ ፡ መንበረ ፡ ብርሃን ፡ ተዘርግቶ፡ አየሁ ፡ ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ። ሕዝ ፡ ፲ ፡ ፩ ። ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩ ።

፫ ፤ ወዘዲቤሁ ፡ ይነብር ፡ ይመስል ፡ ኅብሩ ፡ ከመ ፡ ዕንቈ ፡ ኢያሰጲድ ፡ ወሰርዲኖ ፡

በመንበሩም ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ያለው ፡ ኅብሩ ፡ ኢያሰጲድ ፡ ሰርዲኖ ፡ የሚባል ፡ ዕንቍን ፡ ይመስላል፡ አለ ፡ ጽርየት፡ ባሕርዩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወካህናት ፡ እለ ፡ ዐውዱ ፡ ለውእቱ፡ መንበር ፡ ይመስል ፡ ኅብሮሙ ፡ ከመ ፡ መረግድ ።

በመንበሩም ፡ ዙሪያ ፡ ቆመው ፡ ያሉ ፡ ካህናት ፡ ኅብራቸው ፡ መረግድ ፡ የሚባል ፡ ዕንቍን ፡ ይመስላል ፡ አለ፡ እንበለ፡ ዘርዕ ፡ መገኘታቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወብርሃን ፡ የዐውዶ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ ይላል) ፡ በብርሃን ፡ ተከቦ ፡ ያየዋል ። ኅተሞሙ ፡ አብነት ፡ አያስተረጕምም ፡ ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ።

፬ ፤ ወበዐውዱ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ መናብርት ፡

በመንበሩ ፡ ዙሪያ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ መናብርት ፡ ተዘርግተዋል ፡

ወዲበ ፡ ውእቶን ፡ መናብርት ፡ ይነብሩ ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሊቃናት ።

በኻያ ፡ አራቱም ፡ መናብርት ፡ ላይ ፡ ኻያ፡ አራት ፡ መላእክት ፡ ተቀምጠዋል ። አንድም ፡ በመንበሩ ፡ ዙሪያ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ መላእክት ፡ ቆመዋል ፡ ሠራዊትም ፡ ቢል፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ በኻያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜያት ፡ ጸልየው ፡ ራሳቸውን ፡ ጠብቀው ፡ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለው ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ አላቸው ፡ በኻያ ፡ አራቱም ፡ መላእክት ፡ ላይ ፡ ኻያ፡ አራት ፡ ሊቃናት ፡ ተሹመዋል ፡ በኻያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜያት ፡ ጸልየው ፡ ሌላውንም ፡ ራሳቸውንም ፡ ጠብቀው ፡ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለው ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ አለ ፡

ወይለብሱ ፡ ጸዓድወ ፡ አልባሰ ፡

ብሩህ ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ፡ ጸጋቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወዲበ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ አክሊላት ፡ ዘወርቅ ።

በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ አክሊል ፡ ደፍተዋል፤ ክብራቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፳፫ ። ም ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ና ፡ ፰ ፡ ፲ ።

፭ ፤ ወእምነ ፡ ውእቱ ፡ መንበር ፡ ይወፅእ ፡ መብረቅ ፡ ወፀዓዕ ፡ ወነጐድጓድ ።

ከመንበሩም ፡ መብረቅ ፡ ፃዕ ፡ ነጐድጓድ ፡ ይወጣል ፡ ሐተታ ፡ ፃዕ ፡ ብልጭታው ፡ መብረቅ ፡ አሰይፎ ፡ የሚወርደው ፡ ነጐድጓድ ፡ ሲጥል ፡ የሚሰማው ፡ መቅሠፍተ ፡ ኃጥኣን ፡ ይታዘዛል ። አንድም ፡ (ወናሁ ፡ ርኢኩ) ፡ በጌትነት ፡ ያለ ፡ ትስብእትን ፡ በልዕልና ፡ አየሁት ። (ጥቅ) ፡ መንበረስ ፡ ሶበ ፡ ሰማዕከ ፡ ለብዎ ፡ ለመንበር ፡ ድልወተ ፡ መለኮት ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚእና፡ ወሥልጣን ፡ እንዲል ። (ወዘዲቤሁ) ፡ ትስብእትን ፡ የተወሐደ ፡ እሱ ፡ ሰርዲኖ ፡ ኢያሰጲድ ፡ የሚባል ፡ ዕንቍን ፡ ይመስላል ፡ እንበለ፡ ዘርዕ፡ መገኘቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወካህናት) ፡ በትስብእት ፡ ያመኑ ፡ ምድራውያን ፡ ካህናትም ፡ ኅብራቸው ፡ መረግድ ፡ የሚባል ፡ ዕንቍን፡ ይመስላል፡ አለ ፡ ንጽሕናቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወበዐውዱ፡ ለውእቱ)፡ በትስብእት ፡ ኻያ፡ አራት ፡ ምእመናን ፡ አምነዋል ፡ በኻያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜያት ፡ ጸልየው ፡ ራሳቸውን ፡ ጠብቀው ፡ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለው ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በኻያ ፡ አራቱም ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ መምህራን ፡ ተሹመዋል ፡ በኻያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜያት ፡ ጸልየው ፡ ራሳቸውን፡ ሌላውንም ፡ ጠብቀው ፡ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለው ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ (ወይለብሱ)፡ ጸጋቸውን ፡ (ወዲበ ፡ አርእስቲሆሙ) ፡ ክብራቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ። (ወእምነ ፡ ውእቱ) ፡ ከትስብእት ፡ ስመ ፡ ሥላሴ ፡ ይነገራል ፡ (በትስብእት ፡ አንድነት ፡ ሦስትነት ፡ ይታወቃል ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።

ወቅድሜሁ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ የኀትዉ፡ ሰብዑ ፡ መኃትው ፡

በመንበሩ ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ፋና ፡ ይበራሉ ፡ በተቅዋመ ፡ ወርቅ ፡ ባሉ ፡ በሰባቱ ፡ አዕፁቅ ፡ አምሳል ፡ ያሳየዋል ።

ዘውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘእግዚአብሔር ።

ይኸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ፍጹም ፡ ሀብቱ ፡ ሰባቱ ፡ ብሎታል ። አንድም ፡ በትስብእት ፡ ሰባቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ይነገራሉ ፡ በጉባኤ ፡ ጊዜ ፡ ቢሉ ፡ አንድ ፡ ወንጌል ፡ አራት ፡ ሐዲሳት ፡ ሁለት ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ክልኤቱ ፡ ገበዋቲሃ ፡ ለመጽሐፍ ፡ ይላልና ፡ መጽሐፈ፡ ኪዳንስ ፡ ከቀሌምንጦስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ (ዘውእቱ ፡ መንፈስ) ፡ መጻሕፍትን ፡ እስትፋሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላቸዋልና ። አንድም፡ ሰባቱ፡ መልእክታተ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያ ፡ ናቸው ፡ ዘውእቶሙ ፡ እልቀታሊቃን ፡ ይላቸዋል ፡ መጻሕፍትን ፡ እስትንፋሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላቸዋልና ። አንድም ፡ በትንቢት ፡ ያናገራቸው ፡ በምሳሌ ፡ ያሳያቸው ፡ ሰባቱ ፡ ጉባኤያት ፡ በትስብእት ፡ ቁመዋል ፡ ትንቢት ፡ ወርኢኩ፡ ሰብዐ፡ መድበረ፡ ማያት፡ ያለው፡ ነው፡ ምሳሌ ፡ ኖኅ ፡ ሤምን ፡ ሤም ፡ አርፋስክድን ፡ አርፋስክድ ፡ ቃይናንን ፡ ቃይናን ፡ ሳላን ፡ ሳላ ፡ ኤቦርን ፡ ኤቦር ፡ ፋሌቅን ፡ ይወልዳል ፡ ፋሌቅ ፡ ማለት ፡ ፍልጠት ፡ ክፍለት፡ ማለት፡ ነው። (ጥቅ)፡እስመ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ተከፍለት ፡ ምድር ፡ እንዲል ። በሱ ፡ ጊዜ ፡ ተለያይተዋል ። ሁለት ፡ ጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ ሁለት ፡ ጉባኤ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ሁለት ፡ ጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ አንድ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፣ ተለያይተዋል ። (ዘውእቱ) ፡ እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ እመንፈስ ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ ፡ ይላቸዋልና ። አንድም ፡ (ወቅድሜሁ ፡ ለውእቱ) ፡ ከትስብእት ፡ ሰባቱ፡ ልዑካን ፡ (ሰባቱ ፡ ሥዩማን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ። ተሹመዋል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ጳጳስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ኮሬ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቄስ ፡ ዲያቆን ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ናቸው ፡ (ዘውእቱ) ፡ እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ እመንፈስ ፡ መንፈስ ፡ውእቱ ፡ ይላቸዋልና ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ። ፲፮ ፡ ፲፰ ። ዘካ ፡ ፬ ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፮ ፤ ወቅድሜሁ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ ባሕር ፡ ከመ፡ እንተ ፡ በረድ ፡

በመንበሩም ፡ ፊት ፡ በረድ ፡ የምትመስል፡ ባሕር ፡ አየሁ ፡ ሐተታ ፡ ባሕር ፡ ባሕርየ ፡ አብ ፡ (ከመ ፡ እንተ ፡ በረድ) ፡ ጽርየቱን ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ (ባሕር)፡ ባሕርየ ፡ ወልድ ፡ (ከመ ፡ እንተ ፡ በረድ) ፡ ለበረድ ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ አለው ፡ ግዙፍም ፡ ረቂቅም ፡ ነው ፡ እሱም ፡ ግዙፍም ፡ ረቂቅም ፡ ነውና ። አንድም ፡ (ባሕር) ፡ ባሕርየ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ በረድ ፡ በረድ ፡ በክፍል ፡ በክፍል ፡ ይወርዳል ፡ (ጥቅ) ፡ ወያወርድ ፡ በረደ ፡ ከመ ፡ ፍተታት ፡ እንዲል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በክፍል ፡ በክፍል ፡ ይሰጣልና ። አንድም ፡ (ባሕር) ፡ ጥምቀት ፡ (ከመ ፡ እንተ ፡ በረድ) ፡ ጽርየቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወእምገበዋቲሁ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡

በመንበሩም ፡ አጠገብ ፡ አራቱን ፡ ኪሩቤል ፡ አየሁ ፡ እንደ ፡ አልጋ ፡ ሸንኮር ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ያያቸዋል ፡ ወእምገበዋቲሁ ፡ ባለው ፡ ወእምታሕቴሁ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ ይላል ፡ ከመንበሩ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ባሕረ ፡ ብርትና ፡ እንደ ፡ አልህምተ ፡ ብርት ፡ ሁነው ፡ ያያቸዋል ፡

ወምሉዓን ፡ እሙንቱ ፡ አዕይንተ ፡ እምቅድም ፡ ወእምድኅር ፡

በፊት ፡ በኋላ ፡ አዕይንትን ፡ የተመሉ ፡ ናቸው ፡ ይህስ ፡ እንደ ፡ ብርሌ ፡ እንደ ፡ ብርጭቆ ፡ እንደ ፡ መስተዋት ፡ እያወለወለ ፡ ለዐይን ፡ አይመችም ፡ ብሎ፡ አልፎ፡ አልፎ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ አልጋ ፡ መለበምያ ፡ እንደ ፡ ሶራ ፡ ግምጃ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ለምድ ፡ እንደ ፡ ዐይነ ፡ በጎ ፡ ይህም ፡ አይታወቅ ፡ ብሎ ፡ ዐይናቸው ፡ እንደኛ ፡ ሁለት፡ ነው ፡ ኀላፍያትን ፡ መጻእያትን ፡ ያውቃሉ ፡ ዘፀአ ፡ ፳፬ ፡ ፲ ። ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ ፳፪።

፯ ፤ ወቀዳማዊ ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡

መዠመሪያው ፡ አንበሳ ፡ ይመስላል ፡ ለአራዊት ፡ ጸልዮ ፡ አራዊትን ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡



ወካልኡ ፡ ይመስል ፡ከመ ፡ ላህም ፡

ሁለተኛውም፡ላም፡ይመስላል ፤ ለእንስሳ ፡ ጸልዮ ፡ እንስሳትን ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡

ወሣልሱ ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡

ሦስተኛውም፡ሰው፡ይመስላል ፡ ለሰው ፡ ጸልዮ ፡ ሰውን ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ስለ፡ ሆነ ፡ ሐተታ ፡ ሰውን ፡ በመካከል ፡ አመጣው ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ጌታ ፡ በፊትም ፡ በኋላም ፡ አይሄድም ፡ ሰውም ፡ የሊህ ፡ ሁሉ ፡ ገዣቸው ፡ ነውና ፡

ወራብዑ ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ዘይሠርር ፡

አራተኛውም ፡ ንስር ፡ ይመስላል ፡ ለአዕዋፍ ፡ ጸልዮ ፡ አዕዋፍን ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ፡ ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲ና ፡ ፲፬ ።

፰ ፤ ወለእሉ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ለለአሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በበስድስቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡

ለአራቱም ፡ ኪሩቤል ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ስድስት ፡ ክንፍ ፡ አላቸው ።

ወእንተ ፡ ዙሉንታሆሙ ፡ ምሉዐን ፡ እሙንቱ ፡ አዕይንተ ፡

የፊትና ፡ የኋላውን ፡ ተናግሮ ፡ የቀኙና ፡ የግራውን ፡ አልተናገረም ፡ ነበረና፡ እንተ፡ ዙሉንታሆሙ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ። አንድም ፡ መጻእያትን ፡ ኃላፍያትን ፡ ያውቃሉ ፡ (የወዲያና ፡ የወዲሁን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።

ወአልቦሙ ፡ ዕረፍት ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ እንዘ፡ ይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ አማልክት ፡ ዘሀሎ ፡ ወይሄሉ ።

ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ በመዓልትና ፡ በሌሊት ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ። (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ አኰቴቶሙ፡ ይእቲ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ እንዲል ፡ ምስጋናቸው ፡ ዕረፍታቸው ፡ ዕረፍታቸው ፡ ምስጋናቸው፡ናትና፡ (ጥቅ)፡ ወእምዝ፡በዓመተ፡ ሞተ ፡ ዖዝያን ፡ ንጉሥ ፡ ርኢክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ነዋኅ ፡ ወብሩህ ፡ ወሱራፌል ፡ ይቀውሙ ፡ ዐውዶ፡ ለለአሐዱ ፡ በበስድስቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ በክልኤቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ይከድኑ ፡ ገጾሙ ፡ ወበክልኤቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ይከድኑ ፡ እግሮሙ ፡ ወበክልኤቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ይሠሩ ፡ አንጻረ ፡ ወይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ፡ እንዲል ፡ ሕዝቅኤል ፡ ፲፮ ፡ ይላል ፤ ከዚህ ፡ ዮሐንስ፡ አራት ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ራእይ ፡ ተከፍሎ ፡ ቀርቶበታል ፡ ቢሉ ፡ ተከፍሎ ፡ ቀርቶበት ፡ አይደለም ፡ እንዳልተከፈለበትስ ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ከተገለጸው ፡ ምስጢር ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ የተገለጸው ፡ ምሥጢር ፡ እንዲበልጥ ፡ ለማጠየቅ ፡ የካህናተ ፡ ብሊት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡ ኻያ ፡ አራቱን ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ከመንበሩ ፡ አርቆ ፡ የካህናተ ፡ ሐዲስ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡ አራቱን ፡ ኪሩቤል ፡ ከመንበሩ ፡ አቅርቦ ፡ ያሳየዋል፡ ተከፍሎበትም ፡ አይደለ ፡ አራቱ ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ይታያሉ ፡ የቀሩት ፡ ከውስጥ ፡ ናቸው ፡ አይታዩም ፡ ዮሐንስ ፡ ለመንገር ፡ ከበቃ ፡ ብሎ ፡ የሚታዩትን ፡ ቆጥሮ ፡ አራት ፡ አለ ፡ እንጅ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ነው ፡ አስራ ፡ ስድስት ፡ ናቸው ፡ (ጥቅ) ፡ እምርእሶሙ ፡ እስከ ፡ ሐቌሆሙ ፡ አርባዕቱ ፡ ወእምሐቌሆሙ ፡ እስከ ፡ እግሮሙ ፡ አሐዱ ፡ ከመ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ርእየተ ፡ እለ ፡ ቄጥሩ ፡ ዘውእቱ ፡ ያፍ ፡ ዘይነብር ፡ በሀገረ ፡ ፋርስ ፡ እንዲል ። አን ድም ፡ ወእምገበዋቲሁ)፡ በትስብእት ፡ ባሉ ፡ ባራቱ ፡ ባሕርያት ፡ አራት ፡ ግብ ራት፡ አሉ፡ (ወምሉዐን) ፡ በዘመነ፡ ብሉይ፡ ነቢያትን ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ሐዋርያትን፡ ይሾማሉ ፡ (ወቀዳማዊ) ፡ አንበሳ ፡ ተን ሥአ ፡ እምገዳም ፡ ያለውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወካልኡ) ፡ ወዕአ ፡ ሦር ፡ ጸዓዳ ፡ ያለውን፡ መናገር፡ ነው ፡ (ወሣልሱ) ፡ ወብ እሲ፡ በውስተ፡ ሰብእ ፡ ያለውን፡ መናገር ፡ ነው ። (ወራብዑ) ፡ ያፍ ፡ ንኡስ ፡ ሠረረ ፡ ያለውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወለእሉ) ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ አን ድ ፡ አንድ ፡ ኀብረ ፡ መልክዕ ፡ ባላቸው ፡ ባራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ በኻያ ፡ አራቱ ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ቃል ፡ ይመሰ ገናሉ ። ወእንተ ፡ ዅለንታሆሙ ፡ ከሐዋ ርያት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚ ነሡ ፡ መምህራንን ፡ ይሾማሉ ፡ የምሳሌ ፡ ምሳሌ ፡ ያሳየዋል ፡ ባራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ሠረገላ ፡ መንበርን ፡ በሠረገላ ፡ መን በር ፡ ላይ ፡ መንበረ ፡ ብርሃን ፡ ተዘርግቶ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ የብርሃን ፡ ዘውድ ፡ ያያል ፤ ባራቱ ፡ ኀብር ፡ ላይ ፡ ብስጥ ፡ በብስጥ ፡ ላይ ፡ ማሕሰ ፡ መጸጺት ፡ በማሕሰ ፡ መጸ ጺት ፡ ላይ ፡ ብርሃን ፡ ሰፍሮ ፡ ይታይ ፡ እ ንደ ፡ ነበረ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ አራቱ ፡ ኅ ብር ፡ ያራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ብስጥ ፡ የደመ ፡ ነፍስ ፡ ማህሰ፡ መጸጺት፡ የነባቢት፡ ነፍስ፡ ብርሃን ፡ የመለኮት ፡ መለኮት ፡ አራቱን ፡ ባሕርያት ፡ ደመ ፡ ነፍስን ፡ ነባቢት ፡ ነፍ ስን፡ ለመዋሐዱ ። አንድም ፡ (ወእምገበዋ ቲሁ)፡ከትስብእት፡ አራቱ፡ ወንጌላውያን ፡ ተሹመዋል ፡ (ወእንተ፡ ዅለንታሆሙ)፡ ኃ ላፍያትን፡ መጻእያትን ፡ ያውቃሉ ፡ ያስተ ምራሉ ፡ (ወቀዳማዊ) ፡ ዘአንበሳ ፡ ማር ቆስ ፡ ያለውን ፡ መናገር ፡ ነው፡ (ወካልኡ፡ ዘላህም ፡ ሉቃስ ፡ ያለውን፡ መናገር፡ ነው፡ (ወሣልሱ) ፡ ዘብእሲ ፡ ማቴዎስ ፡ ያለውን፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወራብዑ) ፡ ዘንስር ፡ ዮሐንስ ፡ ያለውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወለ እሉ) ፡ አራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ ስድስቱን፡ ቃላት ፡ ያስተምራሉ ፤ (ወእንተ ፡ ዅለንታ ሆሙ) ፡ በየጊዜው ፡ የሚሆነውን ፡ ምስ ጢር ፡ ያውቃሉ ፡ ያስተምራሉ ። አንድም፡ (ወእምገበዋቲሁ) ፡ ከትስብእት ፡ አራቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ተሹመዋል ። (ወምሉ ዐን) ፡ ኃላፍያትን ፡ መጻእያትን ፡ ያው ቃሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ (ወቀዳማዊ) ፡ በማ ርቆስ ፡ ወንበር ፡ ተሹሞ ፡ ማስተማሩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወካልኡ) ፡ በሉቃስ ፡ ወንበር ፡ ተሹሞ ፡ ማስተማሩን ፡ መናገር፡ ነው ፡ (ወሣልሱ) ፡ በማቴዎስ ፡ ወንበር ፡ ተሹሞ ፡ ማስተማሩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወራብዑ) ፡ በዮሐንስ ፡ ወንበር ፡ ተሹሞ ፡ ማስተማሩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወለእሉ) ፡ አራቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በሰባተኛዩቱ ፡ መዓርግ ፡ ሁነው ፡ ስድስቱን ፡ መዓርጋት፡ ይሰጣሉ ፡ (ወእንተ ፡ ዅለንታሆሙ) ፡ በየጊዜው ፡ የሚሆነውን ፡ ምስጢር ፡ ያው ቃሉ ፡ ያስተምራሉ፡ አንድም፡ (ወእምገበ ዋቲሁ) ፡ በትስብእት ፡ አራቱ ፡ ጾታ ፡ ምእ መናን ፡ አምነዋል ፡ (ወምሉዐን) ፡ ኃላፍ ያትን ፡ መጻእያትን ፡ ይማራሉ፡ ያውቃሉ፤ (ወቀዳማዊ) ፡ ባሕታውያን፡ ናቸው ፡ በበ ረሃ ፡ ይኖራሉና ፡ (ወካልኡ) ፡ ሰማዕታት ፡ ናቸው ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ይሠዋሉና ፡ (ወሣ ልሱ) ፡ በዐለ ፡ አእምሮ ፡ ናቸው ፡ (ወራ ብዑ) ፡ ከሊህ ፡ ተመስጦ ፡ ያላቸው ፡ ና ቸው ፡ (ወለእሉ) ፡ አራቱ ፡ ጾታ ፡ ምእመ ናን ፡ ስድስቱን ፡ ቃላት ፡ ይማራሉ ፡ ያው



ቃሉ ፡ የምሳሌ ፡ ምሳሌ ፡ ላለው ፡ ጥቂሩ ፡ መከራቸው ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፡ ቀዩ ፡ ደማቸ ውን፡ ያፈሳሉና፡ ቢጫው፡ ባለተስፋ ፡ ናቸ ውና ፡ ነጩ፡ የንጹሐን ፡ ደናግል ፡ (ንጹ ሐን ፡ ናቸውና ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ (ወአልቦሙ) ፡ የፊተኛውን ፡ ይዞ ፡ ይሄ ዳል ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ፡ አምላከ ፡ አማል ክት ፡ ዘሀሎ ፡ ወይሄሉ ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰ ግኑ ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፫ ።

፱ ፤ ወሶበ ፡ ከመዝ ፡ ይብሉ ፡ እልክቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ወይሁቡ ፡ ስብሐተ ፡ ወክብረ ፡ ወአኰቴተ፡ ለዝክቱ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ ዘሕያው፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡

እንዲህ ፡ ስቡሕ፡ክቡር ፡ እኩት ፡ እያሉ ፡ ባመሰገኑ ፡ ጊዜ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ላለ ፡ ለእርሱ ። አንድም ፡ በጌትነት ፡ ላለ ፡ ለእ ርሱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ለሚሆን ።

፲ ፤ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ቅድሜሁ፡ ለዝክቱ፡ ዘይነብር፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ እልክቱ ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሊቃ ናት ፡ ለዝክቱ ፡ ዘሕያው ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ላለ፡ ለእሱ ። አንድም ፡ በጌትነት፡ ላለ ፡ ለእሱ፡ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናት ፡ ሰገዱለት ፡ ተሰጥዎ ፡ እንደ ፡ መቀበል ፡ ለዘለዓለም፡ ሕያው ፡ ለ ሚሆን ፡ ለዝክቱና ፡ ለዝክቱ ፡ ፩ ፡ወገን ፡

ወይወስዱ ፡ አክሊላቲሆሙ ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡

አክሊላቸውን ፡ ከራሳቸው ፡ አውርደው ፡ ከመንበሩ ፡ ፊት ፡ ያኖራሉ ፡ ሐተታ ፡ ቄሱ ፡ መጠምጠሚያውን ፡ ከራሱ ፡ አው ርዶ ፡ ከከርሠ ፡ ሐመሩ ፡ እንዲያኖር ፡ አክ ሊልን ፡ ካነሣ ፡ ዘንድ ፡ ቆብዕን ፡ ከዚህ ፡ ይናገራሉ ፡ ሕባኔው ፡ የእስክንድርያ ፡ ክቡ ፡ የሮምያ ፡ ስብስቡ ፡ የሶርያ ፡ ቅርጹ፡ የአንጾኪያ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፲፩ ።

፲፩ ፤ ወይብልዎ ፡ ለከ ፡ ይደሉ ፡ እግዚኦ ፡ አምላ ክነ ፡ ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ወኀይል ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ስቡሕ ፡ ክቡር ፡ ኀያል ፡ መባል ፡ ላንተ ፡ ይገባል ፡ እያሉ ፡ ሰገዱለት ፡

እስመ ፡ አንተ ፡ ፈጠርከ ፡ ዅሎ ፡ ወበፈቃደ ፡ ዚአከ ፡ ይሄሉ ፡ ዅሉ ፡ ዘተፈጥረ ።

ሁሉን ፡ አንተ ፡ ፈጥረሃልና ፡ የተፈጠ ረውም፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ፡ ባንተ፡ ፈቃድ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ፡ ወበፈቂደ ፡ ዚአከ ፡ ይላል ፡ አንተን ፡ በመውደድ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ውስተ ፡ የማኑ ፡ ለውእቱ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ መጽሐፈ ፡ ጽሑፍተ ፡ እንተ ፡ ውስጣ ፡ ወእንተ ፡ አፍአሃ ፡

ዝ ፡ ሲናገረው ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ባለ ው ፡ በእሱ፡ በቀኝ ፡ እጁ፡ በውስጥ ፡ በአ ፍኣ ፡ የተጻፈች ፡ መጽሐፍ ፡ አየሁ ፡ ገበ ታ ፡ ለገበታ ፡ ብራና ፡ ለብራና ፡ ጥራዝ ፡ ለጥራዝ ፡ የተያያዘች ፡

ወኅትምት ፡ በሰብዐቱ ፡ ማኅተም ።

በሰባት ፡ ቍልፍ ፡ የተቈለፈች ፡ እንደ ፡ ደብረ፡ ብርሃን፡ ወንጌል፡እንደ፡ አጣጣሚ ፡ ሐዊ ። አንድም፡ (ዘሀለወ፡ ይኩን፡ ላለው ፡ አመጣ) ፡ መጽሐፍ፡ ጽሕፍት፡ ምስጢረ ፡ ምጽአት ፡ (እንተ ፡ ውስጣ) ፡ ከምጽአት ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ የሚሆነው ፡ (እንተ ፡ አፍኣሃ) ፡ ከምጽአት፡ በኋላ፡ የሚሆነው ፡ (ወኅትምት) ፡ በሰባት ፡ መንፈቅ ፡ የምት

www.ethiopianorthodox.org

ፈጸም ፡ ከዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ ተንባላት ፡ ያለውን ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከዘመነ ፡ ተንባላት ፡ እስከ ፡ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አድርጎ ፡ ያነን ፡ በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ዘመን ፡ ልክ ፡ ከሦስት ፡ ከፍሎ ፡ አንድ ፡ አንዱን ፡ በሰባት ፡ መንፈቅ ፡ እየቀመረ ፡ ያሳየዋል ፡ እንዲህ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የኋላውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ያደርጋል ፡ ያቀዳድማል ። አንድም ፡ ሁሉም ፡ በሁሉ ፡ እየገባ ፡ ይተረጐማል ። አንድም ፡ መጽሐፍ ፡ ጽሕፍት ፡ ምስጢረ ፡ ዘመን ፡ (እንተ ፡ ውሥጣ) ፡ ያልተገለጸለት ፡ (እንተ ፡ አፍአሃ) ፡ የተገለጸለት ፡ ያልተገለጸለትስ፡ የለም፡ ብሎ፡ (እንተ ፡ ውስጣ) ፡ ከሱ ፡ አስቀድሞ፡ (ወእንተ ፡ አፍአሃ)፡ በእሱ፡ ጊዜ ፡ ከእሱ ፡ በኋላ ፡ የሚሆነው ፡ (ወኀትምት) ፡ በፍጹም ፡ ሥዋሬ ፡ ተሠውራ፡ ያለች ። አንድም ፡ (መጽሐፍ ፡ ጽሕፍት) ፡ ምሥጢረ፡ ዓለም ፡ (እንተ ፡ ውሥጣ) ፡ የሚታየው ፡ (ወአንተ ፡ አፍአሃ) ፡ የማይታየው ። አንድም ፡ (እንተ ፡ ውስጣ) ፡ ከሰማይ፡ በላይ፡ ከምድር፡በታች ፡ ያለው ፡ (ወእንተ ፡ አፍአሃ) ፡ ከሰማይ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ (ወኀትምት) ፡ በፍጹም ፡ መናሥግተ ፡ ጥበቡ ፡ ተሠውራ ፡ ያለች ። አንድም ፡ ወኀትምት ፡ በሰባት ፡ ክፍል ፡ የተወሰነች፡(ጥቅ)፡ ወኀተምኪ፡በሰብዐቱ፡ማኅተም፡ እንዲል፡ (ዘሕልው ፡ ላለው፡ አመጣ ። አንድም፡ ብቻ፡ መጻእያትን፡ አያሳየውም ፡ ኃላፍያትንም፡ ያሳየዋል፡ ብሎ፡ መጽሐፍ፡ ጽሕፍት ፡ አዳም ፡ እንተ ፡ ውሥጣ) ፡ ነፍሱ ፡ (ወእንተ ፡ አፍአሃ) ፡ ሥጋው ፡ ወኀትምት ፡ በሰባት ፡ ሀብታት ፡ የከበረ ፡ አሚን ፡ ሠናኔ ፡ ንጽሕና ፡ ኀይል ፡ መንግሥት ፡ ክህነት ፡ ትንቢት ። አንድም ፡ (መጽሐፍ ፡ ጽሕፍት) ፡ እመቤታችን ፡ (እንተ ፡ ውስጣ) ፡ ነፍሷ ፡ (ወእንተ ፡ አፍአሃ) ፡ ሥጋዋ ፡ (ወኀትምት ፡ )በፍጹም ፡ ክብር ፡ የከበረች ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ ጐልቍ ፡ ሰብዐቱ ፡ በኀበ ፡ ዕብራውያን ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ (መጽሐፍ ፡ ጽሕፍት) ፡ ጌታ ፡ እንተ ፡ ውስጣ ፡ ነፍሱ ፡ ወእንተ ፡ አፍአሃ ፡ ሥጋው ። አንድም ፡ (እንተ ፡ ውስጣ ፡ መለኮት ፡ (ወእንተ ፡ አፍአሃ) ፡ ትስብእት ፡ ወኀትምት፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገረለት፡ ሰባቱን፡ ሀብታት ፡ መስጠትን፡ በተዋህዶ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ መንፈሰ ፡ ለብዎ ፡ መንፈሰ ፡ አእምሮ ፡ መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ መንፈሰ ፡ ምክር ፡ መንፈሰ ፡ ኀይል ፡ መንፈሰ ፡ ረድኤት ፡ መንፈሰ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፪ ። ሕዝ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

፪ ፤ ወርኢኩ፡መልአከ፡ዐቢይ፡ይጸርሕ፡ወይብል፡በቃል፡ዐቢይ፡ለመኑ፡ይደልዎ፡ይክሥታ፡ለዛቲ፡መጽሐፍ ።

ግሩም ፡ መልአክ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ አሰምቶ ፡ ሲናገር ፡ ሰማሁ ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ሊያውቃት ፡ ሊመረምራት ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርጋት ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ፡

ወይፍታሕ ፡ ማኅተሚሃ ፡

ይህች ፡ መጽሐፍ ፡ ሊገልጻት ፡ ቍልፏን ፡ ሊፈታት ፡ ማለት ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ሊመረምራት ፡ ሊያውቃት ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ።

፫ ፤ ወአልቦ ፡ ዘክህለ ፡ ከሢቶታ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወኢርእዮታ ፡

ያችን ፡ መጽሐፍ ፡ ገልጦ ፡ ሊያያት ፡ የተቻለው ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ሊያውቃት ፡ ሊመረምራት ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርጋት ፡ የተቻለው ፡ የለም ፡

ኢበሰማይ ፡

መላእክትም ፡ ሆኖ ፡

ወኢበምድር ፡

ደቂቀ ፡ አዳምም ፡ ሆኖ ፡

ወብዙኃን ፡ እለ ፡ በከዩ ።

ያዘኑ ፡ ያለቀሱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ወአነኒ ፡ ምስሌሆሙ ፡

በከይኩ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ አዘንሁ ፡ አለቀስሁ ፡ ልጅነት ፡ በታጣበት ፡ ወራት ፡ ከሳቸው ፡ ጋራ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ያዝናል ፡ ያለቅሳል ፡

እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘተረክበ ፡ ዘይደልዎ ፡ ይክሥታ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወይርአያ ፡

ያችን ፡ መጽሐፍ ፡ ገልጾ ፡ ሊያያት ፡ የተቻለው ፡ የለምና ፡ አለ ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ሊያውቃት ፡ ሊመረምራት ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርጋት ፡ የተቻለው ፡ የለምና ።

፭ ፤ ወይቤለኒ ፡ አሐዱ ፡ እምውስተ ፡ እልክቱ ፡ ሊቃናት ፡ ኢትብኪ ፡

ከሊቃናትም፡ አንዱ፡ አይዞህ፡ አታልቅስ ፡ አለኝ ፡

ናሁ ፡ሞዐ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ዘእምውስተ ፡ ሥርዉ፡ ለዳዊት ፡ ከመ ፡ ይፍትሓ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወለማኅተሚሃ ።

ያችን ፡ መጽሐፍ ፡ ሊገልጻት ፡ ቍልፏን ፡ ሊፈታት ፡ አለ ፡ አንበሳ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ ከሚሆን ፡ ከዳዊት ፡ ባሕርይ፡ የሚሆን፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ሊያውቃት ፡ ሊመረምራት ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርጋት ፡ ተችሎታልና ። (ድል ፡ ነሥቷልና ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ሐተታ ፡ አንበሳ ፡ አለው ፡ አንበሳ ፡ ፍለጋው ፡ እን[illegible] ፡ [illegible]ፋው ፡ ይሄዳል ፡



የእርሱም ፡ አሰረ ፡ ባሕርዩ ፡ አይመረመርምና ፡ አንበሳ ፡ ሲተኛ ፡ ዐይኑ ፡ ይገለጣል፤ ሲነቃ ፡ ዐይኑ ፡ ይከደናል ፡ እሱም ፡ ንውም ፡ በሰውነቱ ፡ ንቁሕ ፡ በመለኮቱ ፡ ነውና ፡ አንበሳ ፡ ሲወለድ ፡ ደክሞ ፡ ይወለዳል ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ደክሞ ፡ ይሰነብታል ፡ አባቱ ፡ ከሩቅ ፡ ሁኖ ፡ ጣህሩን ፡ ባሰማው ፡ ጊዜ ፡ ኀይል ፡ አግኝቶ ፡ ይነሣል ፡ እሱም ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ አቡሁ ፡ አንሥአ ፡ ይለዋልና ፡ ዘፍጥ ፡ ፵፱ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ። ራእ ፡ ፳፪ ፡ ፮ ።

፮ ፤ ወርኢኩ ፡ ማእከለ ፡ ዝኩ ፡ መንበር ፡ ወእልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ወማእከለ ፡ እልክቱ ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሊቃናት ፡ ይቀውም ፡ በግዕ ፡ ከመ ፡ ዘርጉዝ ፡ ውእቱ ፡

በኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናት ፡ መካከል ፡ ባሉ፡ ባራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ጎኑን ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፡ ያለ ፡ በግ ፡ አየሁ ፡ አለ ፡ ጎኑን ፡ የተወጋ ፡ በግ ፡ አየሁ ፡ ሐተታ ፡ ድል ፡ ነሥቷልና ፡ አንበሳ ፡ መሥዋዕት ፡ ሆኗልና ፡ በግዕ ፡ አለው ፡ በግዕ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ አንበሳ ፡ እንደ፣ አምላክነቱ ፡

ወቦ ፡ ሰብዐቱ ፡ አቅርንት ፡ ወሰብዐቱ ፡ አዕይንት ፡

ሰባት ፡ አቅርንት ፡ ሰባት ፡ ዐይኖች ፡ አሉት ።

ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ መንፈሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘተፈነወ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ።

ይኸውም ፡ ሥራውን ፡ በምላት ፡ የሚሠራ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። አንድም ፡ አቅርንት ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ፡ ወይኬልሑ ፡ ከመ፡ ቃሉ፡ ቀርን ፡ ይላቸዋልና፡ አዕይንት፡ ነቢያት፡ ናቸው፡መጻእያትን፡ ያውቃሉና ።

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ፡ አዕይንት ፡ ቀሳውስት ፡ አቅር ንት ፡ ዲያቆናት ፡ ናቸው ፡ አቅርንት ፡ አላቸው ፡ በተልእኮ ፡ ይኖራሉና ፡ እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ እመንፈስ ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ፡ ይላቸዋልና ፡ ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፯ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ። ዘካ ፡ ፬ ፡ ፰ ፡ ፲ ።

፯ ፤ ወመጽአ ፡ ወተመጠዋ ፡ እምነ ፡ የማኑ ፡ ለዝ ክቱ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበር ።

በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ካለ ፡ ከእሱ ።
አንድም ፡ በጌትነት ፡ ካለ ፡ ከእሱ ፡ ከቀኝ፡ እጁ ፡ ተቀበላት ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ አወቃት ፡ መረመራት ፡ ገንዘብ ፡ አደረ ጋት ።

፰ ፤ ወሶበ ፡ ተመጠዋ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡

ያችን ፡ መጽሐፍ ፡ በተቀበላት ፡ ጊዜ ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ባወቃት ፡ በመረ መራት ፡ ገንዘብ ፡ ባደረጋት ፡ ጊዜ ።

ሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለውእቱ ፡ በግዕ ፡ እልክቱ ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሊቃናት ፡ ወእልክቱ ፡ አርባ ዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡

ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናት ፡ አራቱ ፡ ኪሩቤ ልም ፡ ሰገዱለት ፡

ወያጸንዑ ፡ ኵሎሙ ፡ ጽዋዓተ ፡ ወርቅ ፡ ዘምሉእ ፡ ዕጣነ ፡ ወመሰንቆ ፡ መዝሙር ፡

ጽዋዕ ፡ መሰንቆ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ዕጣን ፡ መዝሙር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ጽሩይ ፡ ምስ ጋና ፡ የሚያመሰግኑበትን ፡ አንደበት ፡ በተፈጥሮ ፡ ገንዘብ ፡ አድርገዋል ፡

ወዝ ፡ ውእቱ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ።

ይኸውም ፡ ቅዱሳን ፡ የሚያመሰግኑት ፡ ምስጋና ፡ ነው ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፪ና ፡ ፲፰ ፡ ፪ ። ም ፡ ፳ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፱ ፤ ወይዜምሩ ፡ በመዝሙር ፡ ሐዲስ ፡

በእንግዳ፡ ምስጋና፡ ያመሰግናሉ፡አምላክ፡ ሰው ፡ ሆነ፡ ሰው፡ አምላክ፡ ሆነ ፡ እያሉ ።

ወይብሉ ፡ ይደልወከ ፡ ትንሥአ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወትፍታሕ ፡ ማኅተሚሃ ፡

ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ ልትገልጻት ፡ ቍል ፏን ፡ ልትፈታት ፡ ይገባሃል ፡ እያሉ ፡ አለ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ልታውቃት ፡ ልት መረምራት ፡ ገንዘብ ፡ ልታደርጋት ፡ ይቻ ልሃል ፡ እያሉ ፡

እስመ ፡ ተቀተልከ ፡

መሥዋዕት ፡ ሆነሃልና ።

ወተሣየጥከ ፡ በደምከ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወአሕዛብ ፡

ከሕዝብም ፡ ከአሕዛብም ፡ ወገን ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመሆን ፡ ለማድረግ፡ በወርቀ ፡ ደምህ ፡ ዋጅተሃልና ።

ወነገድ ፡ ወበሐውርት ።

ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ውን ፡ በሐውርት ፡ ብሎ ፡ ደገመው ።

፲ ፤ ወረሰይከ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ካህናተ ፡ ወነገሥተ ፡

ኪያሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እሳቸውን ፡ ካህ ናት ፡ ነገሥታት ፡ እያደረግህ፡ ሹመሃልና። አንድም፡ከሳቸው፡ ወገን፡ ካህናትን፡ ነገሥ ታትን ፡ መርጠሃልና ፡ ለመንግሥተ ፡ እግ ዚአብሔር፡እግዚአብሔርን፡ ለማገልገል ።

ከመ ፡ ይምልኩ ፡ ኵሎ ፡ ምድረ ።

የጸጋ ፡ አማልክት ፡ ይባሉ ፡ ዘንድ ፤ ም፡ ፩፡ ፮ና ፡ ፳ ፡ ፮ና ፡ ፳፪ ፡ ፭ ።

፲፩ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ መላእክት ፡ ብዙኃን ፡ በዐ ውዱ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ ወዘእንስሳሁኒ ፡ ወዘእል ክቱኒ ፡ ሊቃናት ፡

በመንበሩም ፡ ዙሪያ ፡ የብዙ፡ መላእክትን፡ ቃል ፡ ያራቱን ፡ ኪሩቤልና ፡ የኻያ ፡ አ ራቱን ፡ ሊቃናት ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ።

ወኍልቆሙሰ ። እልፍ ፡ ወአእላፍ ፡ ወትእልፊተ ፡ አእላፋት ፡

ቍጥራቸውም፡ ብዙ፡ የብዙ፡ ብዙ፡ ነው ።



ዘእልፍ ፡ አግዐዚ ።

እልፍ ፡ አለቆች ፡ ያሏቸው ፡ ሠራዊት ። አንድም፡ ዘዘእልፍ፡ ይላል፡ እልፍ፡ እልፍ፡ ሠራዊት፡ ያሏቸው፡ አለቆች ፡ ዳን፡ ፯፡ ፲ ።

፲፪ ፤ ወይብሉ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡

በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮኸው ፡ ተናገሩ ፡

ይደልዎ ፡ ለውእቱ ፡ በግዕ ፡ ዘተቀትለ ፡

መሥዋዕት ፡ ለሆነው ፡ ለበጉ ፡ ይገባዋል ፡

ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ኃይለ ፡ ወብዕለ ፡ ወጥበበ ፡ ወጽንዐ ፡ ወመንግሥተ ፡ ወክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ወበረከተ ።

ጽኑዕ ፡ ባዕል ፡ ጠቢብ ፡ ኃያል ፡ ንጉሥ ፡ ክቡር ፡ ስቡሕ ፡ ቡሩክ ፡ መባል ፡ ይገባ ዋል ፡ ፩ ፡ ዜና ፡ ፴ ፡ ፲፩ ። ፊል ፡ ፪፡፱፡፲ ።

፲፫ ፤ ወኵሉ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ዘበሰማይ ፡ ወዘበምድር ፡ ወዘታሕተ ፡ ምድር ፡ ወዘውስተ ፡ ባሕር ፡ ወኵሉ ፡ ዘውስቴቶሙ ።

በሰማይ ፡ በምድር ፡ የተፈጠረው ፡ ፍጥ ረት ፡ ሁሉ ፡ በሰማይ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ በምድርም ፡ እንስሳት ፡ አራ ዊት ፡ ዕፀው ፡ አዕባን ፡ ወበታሕተ ፡ ም ድር ፡ ካልእ ፡ ፍጥረት ፡ በባሕርም ፡ ያሉ ፡ ዓሣ ፡ አንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬ ፡ እመ ቤታችንም ፡ በነገረ ፡ ማርያም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ያየቻቸው ፡

ይብሉ ፡ ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ወኀይል ፡ ወበረከት ፡ ለዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ።

ስቡሕ ፡ ክቡር ፡ ኀያል ፡ ቡሩክ ፡ መባል ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ላለ ። አን ድም ፡ በጌትነት ፡ ላለ ፡ ለእሱ፡ ይገባል ፡

ወለበግዑ ፡ ለዓለም ፡ ዓለም ።

ለበግዑም ፡ ይገባል ፡ ለዘለዓለሙ ።

፲፬ ፤ ወይብሉ ፡ እልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ አሜን ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ እልክቱ ፡ ሊቃናት ።

አራቱ ፡ ኪሩቤልም ፡ አሜን ፡ ይላሉ ፡ ተሰ ጥዎ ፡ እንደ ፡ መመለስ ፡ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናትም ፡ ሰገዱለት ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፬ ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ ፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ዝክቱ ፡ በግዕ ፡ አሐደ ፡ ማኅ ተመ ፡ እምነ ፡ ሰብዐቱ ፡ ማኅተሚሃ ።

ወኅትምት ፡ ይእቲ ፡ ብሎ ፡ መጽአ ፡ ወተ መጠዋ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ አለ ፡ በግዕ ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ ነው፡ በመዠመሪያው ፡ መንፈቅ ፡ ከሰባቱ ፡ ቍ ልፍ ፡ አንዱን ፡ ቍልፍ ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ከሰባቱ ፡ ሥራ ፡ አንዱን ፡ ሥራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

ይቤለኒ ፡ አሐዱ ፡ እምነ ፡ እልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስ ሳሁ ፡ ነዓ ፡ ርኢ ፡

ካራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ አንዱ ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ፡ (እይ ፡ ቢል ፡ ፩ ፡ ነው) ።

ወሰማዕኩ ፡ ቃሎ ፡ ከመ ፡ ነጐድጓድ ።

እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፯ና ፡ ፰ ፡ ፮ ፡ ፳ ።

፪ ፤ ወርኢኩ ፡ ናሁ ፡ ይወፅእ ፡ ፈረስ ፡ ጸዐዳ ፡

አምበላይ ፡ ፈረስ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡

ወዘይጼዐኖ ፡ ቀስተ ፡ ያጸንዕ ፡ ወወሀብዎ ፡ አክሊለ።

የተቀመጠበትም ፡ ቀስት ፡ ይዟል ፡ (ወወ ሀብዎ) ፡ ዘውድ ፡ ደፍቷል ፡

ወወፅአ ፡ ከመ ፡ ይማዕ ፡

ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡

ወሞዐ ።

ድል ፡ ነሣ። አንድም ፡ (ፈረስ ፡ ጸዓዳ) ፡ ዘ መነ፡ሐሳዌ፡ መሢሕ፡ ነው፡ ጸዓዳ፡ አለው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ነግሦላቸው ፡ ደስ ፡ ብሏ
ቸዋልና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ በዘመኑ ፡ ትእ
ምርተ ፡ ኀይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕ ፡አ
ለው ፡ (ወወሀብዎ) ፡ አይሁድ ፡ ያከብሩ
ታል ። (ወወፅአ) ፡ ምእመናንን ፡ ድል ፡
ሊነሣ ፡ ወጣ ፡ ወሞዐ ፡ ድል ፡ ነሣ ። አን
ድም ፡ (ፈረስ ፡ ጸዐዳ) ፡ ዘመነ ፡ ሐሳዌ ፡
መሢሕ፡ ነው፡ ጸዐዳ፡ አለው፡ ምእመናን ፡
በዘመኑ፡ መከራ፡ ተቀብለው፡ ዋጋቸውን ፡
አግኝተው ፡ ደስ ፡ ብሏቸዋልና ፡ (ወዘይ
ጼዐኖ፡)በዘመኑ ፡ ያሉ፡ ምእመናን፡ ትእም
ርተ ፡ ኀይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕ ፡ አላ
ቸው ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ክብራቸውን ፡ መና
ገር ፡ ነው ፡ (ወወፅአ) ፡ ድል ፡ ሊነሡ ፡
ወጡ ፡ (ወሞዐ) ፡ ድል ፡ ነሡ ፡ በሰማዕ
ትነት ፡ መሞታቸውን ፡ ድል ፡ መንሣት ፡
ብሎት ፡ በመዠመሪያው ፡ መንፈቅ ፡
ነው ። አንድም ፡ (ፈረስ ፡ ጸዐዳ) ፡ ሠረ
ገላ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፡ ጸዐዳ ፡ አለው ፡ ብሩህ፡
ነውና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ ብርሃኑ ፡ ተለ
ክቶ ፡ ተመጥኖ ፡ የሚወጣበት ፡ እንደ ፡
ጽንሐሕ ፡ እንደ ፡ ግርግራት ፡ ያለ ፡ አለ ፡
በዚያ ፡ ሲወጣ ፡ ቀስት ፡ መስሎ ፡ ይወ
ጣል ። አንድም ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ሲያዩት ፡ ዐይን ፡ ይወጋልና ።
አንድም ፡ ከዋክብት ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡
በፊት ፡ በኋላ ፡ ሁነው ፡ ሰልፍ ፡ ሠርተው፡
ይዘውት ፡ ይጓዛሉና ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ሥር
ቀተ ፡ ፀሐይ ፡ በአምሳለ ፡ ንጉሥ ፡ ይላ
ልና ፡ ወወፅአ ፡ ቍረትን ፡ ሌሊትን ፡
ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡ (ወሞዐ) ፡ ድል ፡
ነሣ ። አንድም፡ (ፈረስ ፡ ጸዐዳ)፡ ሠረገላ ፡
መንበር፡ ነው፡ ጸዐዳ፡አለው፡ብሩህ፡ ነውና፡
(ወዘይጼዐኖ) ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ትእምርተ ፡
መስቀል ፡ የብርሃን ፡ ዘውድ ፡ አለበት ፡
(ወወፅአ) ፡ ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡ (ወ
ሞዐ) ፡ ድል ፡ ነሣ ፡ አለመመርመሩን ፡
መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ዘህልው ፡ ላ
ለው፡ ፈረስ፡ ጸዐዳ፡ ሠረገላ፡ አዳም፡ ነው ፡
ጸዐዳ ፡ አለው ፡ ብሩህ ፡ ነውና ። (ወዘይጼ
ዐኖ) ፡ ተፈጥሮው ፡ ትእምርተ ፡ መስ
ቀል ፡ ነው ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ዘውድ ፡ ነው ፡
(ወወፅአ) ፡ ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡ (ወሞዐ)
ድል ፡ ነሣ ፡ በአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ
ፈጠሩን፡ መናገር፡ ነው። አንድም፡ (ፈረስ፡
ጸዐድ)፡ ሰብእና፡ አዳም፡ነው፡ጸዐዳ፡አለው፡
ብሩህ፡ ነውና። (ወዘይጼዐኖ፡ ወወሀብዎ) ፡
በተፈጠረ ፡ በአርባ ፡ ቀን ፡ መላእክት ፡
የብርሃን ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ አልብ
ሰው ፡ የብርሃን ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ የብ
ርሃን ፡ ጫማ ፡ አጫምተው ፡ በፊት ፡ በኋላ
በቀኝ ፡ በግራ ፡ ሁነው ፡ እያመሰገኑ ፡ ገ
ነት ፡ አግብተውታልና ። አንድም ፡ ፈረ
ስ ፡ ጸሀዳ ፡ ዘመነ ፡ አዳም ፡ ነው፡ ጸዐዳ ፡ አ
ለው ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በገነት ፡ ደስ፡ ብሎ
ት ፡ ኑሯልና ። (ወዘይጼዐኖ) ፡ በዘመኑ ፡
ትእምርተ ፡ ኀይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕ ፡
አለው ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ክብሩን ፡ መናገር ፡
ነው ፡ ወወፅአ ፡ ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡
(ወሞዐ)፡ ድል ፡ ነሣ ፡ አለ ፡ እኩያት ፡ ፍት
ወታት፡ ኃጣውእን፡ነው። አንድም፡ ፈረስ፡
ጸዐዳ፡ ዘመነ፡ አበው ፡ ነው፡ ጸዐዳ፡ አለው ፡
ሰባት ፡ ዓመት ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደስ ፡
ብሏቸው ፡ ኑረዋልና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ በሰ
ብዐቱ ፡ ዓመት ፡ ትእምርተ ፡ ኀይል ፡
ትእምርተ ፡ መዊዕ ፡ አላቸው ፡ (ወወሀ
ብዎ) ፡ ክብራቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡
(ወወፅአ) ፡ እኩያት ፡ ፍትወታት ፡ ኃጣ
ውእን ፡ ድል ፡ ሊነሡ ፡ ወጡ ፡ ድል ፡
ነሡ ። አንድም ፡ በማዕከለ ፡ ዘመን ፡ ቢ
መጡ ፡(ፈረስ ፡ ጸዐዳ) ፡ ዘመነ ፡ አውግስ
ጦስ ፡ ነው ፡ ጸዐዳ ፡ አለው ፡ አውግስጦስ ፡

www.ethiopianorthodox.org



ማለት ፡ ጸዐዳ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ (ወዘይጼ
ፀኖ) ፡ በዘመኑ ፡ ትእምርተ ፡ ኀይል ፡ ትእ
ምርተ ፡ መዊዕ ፡ አለውና ። አንድም ፡ ትእ
ምርተ ፡ መስቀል ፡ የሚሸከም ፡ ጌታ ፡ በዘ
መኑ ፡ ተወልዷልና ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ዘው
ድ ፡ ደፍቷል ። አንድም ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ፡
የሚሸከም ፡ ጌታ ፡ በዘመኑ ፡ ተወልዷ
ልና ፡ (ወወፅአ) ፡ ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡
(ወሞዐ) ፡ ድል ፡ ነሣ ። አንድም፡ (ፈረስ ፡
ጸዐዳ)፡ ዘመነ ፡ ጢባርዮስ ፡ ነው ፡ ጸዐዳ፡ አ
ለው ፡ ጌታ፡ በዘመኑ ፡ ተሰቅሏልና፡ (ወዘይ
ጼዐኖ) ፡ በዘመኑ፡ ትእምርተ ፡ ኀይል፡ ትእ
ምርተ፡ መዊዕ፡አለው። አንድም፡ ጌታ፡ በዘ
መኑ፡ ትእምርተ፡ መስቀል፡ ተሸክሟልና ፡
(ወወሀብዎ)፡ ዘውድ ፡ ደፍቷል ፡ ጌታ፡ አክ
ሊለ ፡ ሦክ ፡ ደፍቷልና ፡ (ወወፅአ) ፡ ድል ፡
ሊነሣ ፡ ወጣ ፡ (ወሞዐ) ፡ ድል ፡ ነሣ ። አን
ድም ፡ (ፈረስ ፡ ጸዐዳ)፡ ዘመነ፡ ቈስጠንጢ
ኖስ ፡ ነው ፡ ጸዐዳ ፡ አለው ። በዘመኑ ፡ ቀር
ነ ፡ ሃይማኖት ፡ ቈሟልና ፡ (ወዘይጼዐኖ ፡
ወሀብዎ) ፡ በጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፡ ኒቍስጣ ፡
ኒቍስጣጣኑ ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ ታይቶ
ታል ፡ የሚተረጐምለት ፡ አጥቶ ፡ ሳለ ፡
አውስግንዮስ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ አይሁ
ዳዊ ፡ በዝንቱ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡
ትመውዕ ፡ ፀረከ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ተርጕሞለታል ። አንድም ፡ ትርጓሜው ፡
ባንድ ፡ ወገን ፡ ተጽፎ ፡ ታይቶታል ፡ ይ
ህን ፡ አይቶ ፡ በፈረስህ ፡ አንገት ፡ በጦ
ርህ ፡ አንደበት ፡ በጋሻህ ፡ እንብርት ፡
ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ያላበጀህ ፡ ብሎ ፡
ዐዋጅ ፡ ነገረ ፡ መክስምያኖስ ፡ ቢጠይቅ ፡
ሊዋጋህ ፡ ጦር ፡ ይሰበስባል ፡ ብለው ፡
ነገሩት ፡ እሱ ፡ ከሚዘምትብኝ ፡ እኔ ፡ ልዝ
መትበት ፡ ብሎ ፡ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ክተት ፡
ሠራዊት ፡ ብሎ ፡ ዘመተበት ፡ ባለ ፡ ነጋ
ሪቱ ፡ ብቻ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺሕ ፡ ይሆናል ፡ ገጠ
መው፡ በቈስጠንጢኖስ፡ ሠራዊት፡ ያለው
ን፡ ትእምርተ፡ መስቀል፡ ባዩ ፡ ጊዜ፡ በመክ
ስምያኖስ፡ ሠራዊት፡ አድረው፡ ያሉ፡ አጋ
ንንት ፡ እየጣሉ ፡ ሸሹ ፡ ድል ፡ አድርጎ
ታል ፡ እሱም ፡ ሲሸሽ ፡ ድልድይ ፡ ተንዶ፡
ሙቷል ፡ መርከብ ፡ ተሰብሮም ፡ ቢል ፡
አንድ ፡ ነው ፡ እሱንም ፡ ምእመናን ፡ የመ
ስቀሉን ፡ የጽናውን ፡ ስባሪ ፡ ይዘው ፡ ተቀ
ብለውታል ፡ ሮም ፡ ገብቶ ፡ መንግሥቱን ፡
እጅ ፡ አድርጓል ፡ ዘመክስምያኖስ ፡ ዕል
ው ፡ ድኅረ ፡ ኀልቀ ፡ ዕድሜ ፡ ቈስጠንጢ
ኖስ ፡ ቦአ ፡ ወነግሠ ፡ በሮሜ ፡ እንዳለ ፡ (ስ
ንክሳር) ። አንድም ፡ ፈረስ ፡ ጸዐዳ ፡ ትስ
ብእተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡
ጸዐዳ ፡ አለው ፡ ጸዐዳ ፡ በመለኮቱ ፡ ይለ
ዋልና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ ትእምርተ ፡ መስ
ቀል ፡ ተሸክሟልና ፡ (ወወሀብዎ) ፡ አክ
ሊለ ፡ ሦክ ፡ ደፍቷል ፡ (ወወፅአ) ፡ አጋ
ንንትን ፡ ድል ፡ ሊነሣ ፡ ወጣ ፡ (ወሞዐ) ፡
ድል ፡ ነሣ ፡ ስብከተ ፡ ማቴዎስ ፡ ነው ፡
ይህን ፡ ያስተምራል ፡ ዘካ ፡ ፩ ፡ ፰—፲፯ ።
ዘካ ፡ ፮ ፡ ፩—፰ ።

፫ ፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ካልአ ፡ ማኅተመ ፡ ይቤለኒ ፡ እ
ምውስተ ፡ እንስሳሁ ፡ ነዓ ፡ ርኢ ።

በሁለተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሁለተኛውን ፡
ቍልፍ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ ካራቱ ፡ ኪሩቤል ፡
አንዱ ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ፡

፬ ፤ ወወጽአ ፡ ካልእ ፡ ፈረስ ፡ ቀይሕ ።

ሐመር ፡ ፈረስ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ።

ወአዘዝዎ ፡ ለዘይጼዐኖ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ሰላመ ፡
እምነ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ይትቃተሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡
ወመጠውዎ ፡ ዐቢየ ፡ መጥባሕተ ።

የተቀመጠበትን ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ ፍቅ
ርን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አጥፋ ፡ አሉት ፡ እር
ስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጋደሉ ፡ ዘንድ ። አን

ድም፡ በመንፈቅ፡ ቢመጡ፡ ፈረስ፡ ቀይሕ፡
ዘመነ ፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ ነው ፡ ቀይሕ ፡
አለው ፡ የምእመናንን ፡ ደም፡ ያፈሳልና ፡
(ወአዘዝዎ) ፡ ፍቅርን ፡ አጥፋ ፡ አሉት ፡
እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይዋጉ ፡ ዘንድ ፡ (ወመ
ጠውዎ) ፡ አይሁድ ፡ ያሰለጥኑታል ። አን
ድም፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ ፈረስ ፡ ቀይሕ ፡
ዘመነ፡ ረዓይት፡ ነው፡ቀይሕ፡አለ፡ የሰውን፡
ሁሉ፡ ደም ፡ ያፈሳሉና ፡ (ወአዘዝዎ) ፡ ከም
ድር፡ ፍቅርን፡ ያጠፉ፡ ዘንድ ፡ አጥፉ ፡ አሏ
ቸው፡ (ከሰው፡ ቢል ፡ አንድ፡ ነው) ፡ ከመ ፡
(ይትቃተሉ)፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይዋጉ ፡
ዘንድ ፡ የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ጨርሰ
ው ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጅተው ፡ ባለሦስ
ቱ ፡ ሽሕ ፡ ባለሁለቱን ፡ ሽሕ ፡ ባለሁለ
ቱ ፡ ሽሕ ፡ ባለአንዱን ፡ ሽሕ ፡ ባለአንዱ ፡
ሽሕ ፡ ባለአምስቱን ፡ መቶ ፡ ባለአምስ
ቱ ፡ መቶ ፡ ባለአራቱን ፡ መቶ ፡ እንዲህ ፡
እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተባልተው ፡
አልቀዋልና ፡ (ወመጠውዎ) ፡ ቅዱስ ፡
ገብርኤል ፡ ለስማዝያ ፡ ሰይፍ ፡ ሲሰጠው ፡
ታይቷል ። አንድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡
ቢመጡ ፡ ፈረስ ፡ ቀይሕ ፡ ዘመነ ፡ ጥጦስ ፡
ነው፡ ቀይሕ ፡ አለው፡ የአይሁድን፡ ደም ፡
ያፈሳልና ፡ (ወአዘዝዎ)፡ ከሰው፡ ፍቅርን ፡
ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ አጥፉ ፡ አሉት ፡ (ከመ ፡
ይትቃተሉ) ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይዋጉ ፡
ዘንድ ፡ ቀን ፡ ከጥጦስ ፡ ሠራዊት ፡ ሲዋጉ ፡
ይውላሉ ፡ ሌሊት ፡ ከእኔ፡ ወገን፡ አነግሥ ፡
ከእኔ ፡ ወገን ፡ አነግሥ ፡ በማለት ፡ እርስ ፡
በርሳቸው ፡ ሲዋጉ ፡ ያድራሉና ፡ (ወመጠ
ውዎ) ፡ ስንዝር ፡ ስንዝር ፡ ሾተል ፡ አበጅ
ተው ፡ አልፎ ፡ ሲሄድ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡
በጎኑ ፡ እየሸጐጠበት ፡ የሚገኝ ፡ ሁኗል ፤
ገዳዩ ፡ ስላልታወቀ ፡ ሞተ ፡ ዕውር ፡ ብለው
ታል።አንድም፡ (ፈረስ፡ቀይሕ)፡ትስብእተ፡
ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ቀይሕ ፡
አለው ፡ ወቀይሕ ፡ በትስብእቱ ፡ ይለዋ
ልና ፡ (ወአዘዝዎ) ፡ ከሰው ፡ ፍቅርን ፡ ያ
ጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አጥፋ ፡ አሉት ፡ አለ ፡ ኢያ
ምጻእኩ ፡ ሰላመ ፡ ለብሔር ፡ ያለውን ፡
መናገር ፡ ነው ፡ (ከመ ፡ ይትቃተሉ) ፡ እር
ስ ፡ በርሳቸው ፡ ይለያዩ ፡ ዘንድ ፡ መጻእ
ኩሰ ፡ እፍልጥ ፡ ብእሴ ፡ እምአቡሁ ፡ ወወ
ለተኒ ፡ እምእማ ፡ ወመርዓተኒ ፡ እምሐ
ማታ ፡ ያለውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወመጠ
ውዎ) ፡ አላ ፡ መጥባሕተ ፡ ያለውን ፡ መና
ገር ፡ ነው ፡ ስብከተ ፡ ማርቆስ ፡ ነው ፡ ይ
ህን ፡ ያስተምራል ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፺ ።

፭ ፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ሣልሰ ፡ ማኅተመ ፡ ይቤለኒ ፡
ሣልስ ፡ እምውስተ ፡ እንስሳሁ ፡ ነዓ ፡ ትርአይ ፡

በሦስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሦስተኛውን ፡
ቍልፍ ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ ካራቱ ፡ ኪሩ
ቤል፡ አንዱ ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ፡ (እይ) ፡

ወወፅአ ፡ ፈረስ ፡ ጸሊም ፡ ወዘይጼዐኖ ፡ መዳልወ ፡
ያጸንዕ ።

ዱሪ ፡ ፈረስ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡ የተቀመ
ጠበትም ፡ ሚዛን ፡ ይዟል ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፺ ።

፮ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ በማእከሎሙ ፡ ለእልክቱ ፡
አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ንስር ።

ባራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ንስ
ር ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡

ወይብል ፡ መስፈርተ ፡ ሥርናይ ፡ በዲናር ፡ ወሠለ
ስቱ ፡ መስፈርተ ፡ ሰገም ፡ በዲናር ።

ባንድ ፡ ድሪም ፡ ወርቅ ፡ ላዳን ፡ ስንዴ ፡
ይሸመታል ፡ ተርታው ፡ እህል ፡ ግን ፡ በአ
ንድ ፡ ድሪም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ላዳን ፡
ይሸመታል ።

ወወይንሰ ፡ ወቅብዕ ፡ ኢየዐብሩ ።

ወይንና፡ ቅቤ፡ግን፡ አይታጡም።አንድም ፡
በመንፈቅ ፡ ቢመጡ ፡ (ፈረስ ፡ ጸሊም) ፡



ዘመነ ፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ ነው ፡ ጸሊም ፡
አለው ፡ በዘመኑ ፡ ረኀብ ፡ ይሆናልና ።
አንድም ፡ በዘመነ ፡ ረኀብ ፡ ቀዩ ፡ ይጠቁ
ራል ፡ ወፍራሙ ፡ ይቀጥናልና ፡ (ወዘይጼ
ዐኖ) ፡ የሚቀመጥበትም ፡ ሚዛን ፡ ይዟል ፡
ሚዛን ፡ እንዲያስተካክል ፡ ረኀብም ፡ ያስ
ተካክላልና ፡ (ወሰማዕኩ) ፡ ባራቱ ፡ ኪሩ
ቤል ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ያለ፡ ቃል፡
ገንትቶ ፡ ሲጮህ ፡ ሰማሁ ፡ (ወይብል) ፡
በድሪም ፡ ወርቅ ፡ አንድ ፡ ላዳን ፡ ሥንዴ ፡
ይሸመታል ፡ ተርታው ፡ እህል ፡ ግን ፡ አባ
ሪሙ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ባንድ ፡ ድሪ
ም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ላዳን ፡ ይሸመታል ፡
ሲል ፡ ሰማሁ ፡ (ወይንሰ ፡ ወቅብዕ) ፡
ወይን ፡ ቅቤ ፡ ግን ፡ አይታጡም፡ በዘመነ ፡
ረኀብ ፡ ወይን ፡ ቅቤ ፡ አይታጣምና ። አን
ድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን፡ ቢመጡ፡ ፈረስ፡
ጸሊም ፡ ዘመነ ፡ ቀላውዴዎስ ፡ ነው ፡ ጸ
ሊም ፡ አለው፡ በዘመኑ ፡ ረኀብ ፡ ሆኗልና ።
አንድም ፡ በዘመነ ፡ ረኀብ ፡ ቀዩ ፡ ይጠቁ
ራል ፡ ወፍራሙ ፡ ይቀጥናልና ፡ (ወዘይጼ
ዐኖ ፡ መዳልወ) ፡ ከእህሉ ፡ መታጣት ፡
የተነሣ ፡ በሚዛን ፡ እስከ ፡ መመዘን ፡ ይደ
ርሳልና ፡ (ወሰማዕኩ) ፡ ባራቱ፡ ኪሩቤል ፡
መካከል ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ገን
ትቶ ፡ ሲጮህ ፡ ሰማሁ ፡ (ወይብል ፡ መስ
ፈርተ ፡ ሥርናይ) ፡ ባንድ፡ ከፈት፡ ወርቅ ፡
ከፈት ፡ ሥንዴ ፡ ይሸመታል ፡ እህል ፡ ማ
ለት ፡ ነው ፡ ተርታው ፡ እህል ፡ ግን ፡ ባን
ድ ፡ ከፈት ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ላዳን ፡ ይሸ
መታል ፡ (ወይንሰ ፡ ወቅብዕ) ፡ ወይን ፡
ቅቤ ፡ ግን ፡ አይታጡም ፡ በዘመነ፡ ረኀብ ፡
ወይን ፡ ቅቤ ፡ አይታጣምና ፡ በሽሕ፡ ቢመ
ጡ ፡ ፈረስ ፡ ጸሊም ፡ ዘመነ ፡ አብርሃም ፡
ነው ፡ ጸሊም ፡ አለው ፡ በዘመኑ ፡ ረኀብ ፡
ሆኗልና ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ሐሣዊ፡ መሢሕ፡
አውርድ ፡ (ትርፍ) ፡ ጸሊም ፡ አለው ፡ አም
ላክ ፡ ፀሐይ ፡ ተናበበኒ ፡ እስኪል ፡ ድረስ ፡
በከላውዴዎን ፡ በተልእኮ ፡ ጣዖት ፡ ኑሯ
ልና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡
በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ተመራምሮ ፡ ልቡና
ውን ፡ በሃይማኖት ፡ እንዳጸና ፡ መናገር ፡
ነው ፡ (ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ በማእከሎሙ) ፡
አራቱን ፡ ነገሥተ ፡ ኮሎዶጎሞር ፡ ድል ፡
ነሥቶ ፡ ሲመለስ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ በመዋ
እልየኑ ፡ ትፌኑ ፡ ቃለከ ፡ አው ፡ አልቦ ፡
ወሚመ ፡ ታርእየኒ፡ ኪያሃ ፡ ዕለተ፡ ባለው፡
ጊዜ ፡ ኢትሬኢ ፡ ኪያሁ ፡ ወባሕቱ ፡ ሑር፡
ዕድዎ ፡ ለዮርዳኖስ ፡ ወበህየ ፡ ትሬኢ ፡ አ
ምሳሊሁ ፡ እንዳለው ፡ መናገር ፡ ነው ፡
(ወይብል) ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ምእመናን ፡
በጥምቀት ፡ የሚያገኙዋቸው ፡ የሥጋው ፡
የደሙ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡ ኅብስተ ፡ አኰ
ቴትን ፡ ጽዋዐ ፡ በረከትን ፡ ሰጥቶ ፡ አብር
ሃም ፡ ቡሩኩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡
የሦስቱ ፡ ግብራት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡
ሦስቱን ፡ ንዋያት ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ መና
ገር ፡ ነው ፡ (ሦስቱ ፡ ንዋያት) ፡ ወርቅ ፡
ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ሦስቱ ፡ ግብራት ፡ መንግ
ሥት ፡ ክህነት ፡ ሞት ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ አብ
ርሃም፡ የምእመናን፡ ዮርዳኖስ፡ የጥምቀት ፡
መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የጌታ ፡ የቀሳውስትም ፡
ቢል ፡ ሕብስተ ፡ አኰቴት ፡ ጽዋዐ ፡ በረ
ከት ፡ የሥጋው ፡ የደሙ ፡ (ወይንሰ ፡
ወቅብዕ) ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለአብርሃም ፡
ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያቸው ፡ ኅብስተ ፡
አኰቴት ፡ ጽዋዐ ፡ በረከት ፡ እስከ ፡ ምጽ
አት ፡ ድረስ ፡ አማናዊ ፡ ሆነው ፡ በመሰ
ጠት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉና ። አንድም ፡
ፈረስ ፡ ጸሊም ፡ ትስብእተ ፡ ወልደ ፡ እግዚ
አብሔር፡ ነው ፡ ጸሊም፡ አለው፡ እንዘ፡ ሰብ
እሂ ፡ መኑ ፡ ይክል ፡ ያእምሮ ፡ እንዲል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሰው ፡ ሲሆን ፡ አለመመርመሩን ፡ መናገር ፡ ነው ። (ወዘይጼዐኖ) ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ባንድነት ፡ ባለመለዋወጥ ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወሰማዕኩ ፡ ቃለ) ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበረ ፡ (ወሠለስቱ) ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ግን ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ። አንድም ፡ ስማዕ ፡ እስራኤል ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ አምላክከ ፡ የምትል ፡ ሕገ ፡ ብሊት ፡ አሪትንና፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የምትል ፡ ወንጌልን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ለእመ ፡ ዐቀብከ ፡ ኦሪተከ ፡ ትበልዕ ፡ ከራሜ ፡ ከራሜከ ፡ ወይሰፍፍ ፡ ማኅበብተ ፡ ወይንከ ፡ ወትሬኢ ፡ ውሉደ ፡ ውሉድከ ፡ የምትል ፡ ኦሪትንና ፡ ዘበልዐ ፡ ሥጋየ ፡ ወሰትየ ፡ ደምየ ፡ የምትል ፡ ወንጌልን ፡ አንድ፡ አድርጎ ፡ ማስተማሩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወይንሰ ፡ ወቅብዕ ፡ ኢየዐብሩ) ፡ ወይን ፡ ሥጋው፡ ደሙ፤ ቅብዕ ፡ ልጅነት ፡ አይታጡም፡ ስብከተ ፡ ሉቃስ ፡ ነው፡ ይህን ፡ ያስተምራል ፡

፯፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ራብዐ ፡ ማኅተመ ፡ ይቤለኒ ፡ ራብዕ ፡ እምነ ፡ እንስሳሁ ፡ ነዓ ፡ ትርአይ ።

በአራተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አራተኛውን ፡ ቊልፍ ፡ በፈታ፡ጊዜ፡ ካራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ አንዱ ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ፡ (እይ) ።

፰፤ ወወፅአ ፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡

ሰራን ፡ ፈረስ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ። አንድም ፡ ቅጥልጣል ፡ ፈረስ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ። (ታሪክ) ፡ ሰሎሞን ፡ በባሕረ ፡ ድምያጥ ፡ ባዝራ ፡ አሥሮ ፡ ጅን ፡ ወጥቶ ፡ ረገጣት ፤ ቅጥልጣል ፡ ፈረስ ፡ ወለደች ፡ ይህን ፡ ለምን ፡ ይሻዋል ፡ ቢሉ ፡ ለፍጥነት ፡ ባሕረ ፡ ባዜቃን ፡ ለመውጋት ፡ ይህ ፡ ባሕረ ፡ ባዜቃ ፡ ፈጣን ፡ ውኃ ፡ ነው ፡ ወጋንህ ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እየተከተለ ፡ የሚያባርር፡ ነው፡ጕድጓድ፡ እየቆፈሩ፡ሂደው፡ ካጠገቡ ፡ ሲደርሱ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ወጋንህ ፡ ወጋንህ ፡ ብለውት ፡ ይሸሻሉ ፡ ይከተላቸዋል ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሸሽተው ፡ ያመልጡታል ፡ ሲመለስ ፡ እየተቈረሰ ፡ ከጕድጓዱ፡ ይቀራል፡ ማርከሻው፡ የውሻ ፡ ቈርበት ፡ ነው ፡ በዚያ ፡ እያነሡ ፡ እየወሰዱ ፡ ለንዋያት ፡ መርሕ ፡ ያደርጉታል ፡ ይህ ፡ ከፈረስ ፡ መልክ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ በመንፈቅ ፡ ቢመጡ ፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡ ዘመነ፡ሐሳዌ፡ መሢሕ፡ነው፡ሐመልሚል ፡ አለው ፡ አካሉ ፡ ቆቅሻም ፡ ነውና ። አንድም ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ነኝ ፡ ይላልና ፡

ወዘይጼዐኖ ፡ ሞት ፡ ስሙ ፡ ወሲኦል ፡ ትትልዎ ፡

የተቀመጠበት ፡ ሞት፡ ይባላል ፡ መቃብርም፡ ትከተለዋለች ፡ በየደረሰበት ፡ የሚያስገድል ፡ የሚያስቀብር ፡ ስለ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ ባመነበት ፡ ሞተ ፡ ነፍስን ፡ የሚያስፈርድ ፡ ርደተ ፡ ገሃነምን ፡ የሚያስከትል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡

ወወሀብዎ ፡ ሥልጣነ ፡ ላዕለ ፡ ራብዕተ ፡ እዴሃ ፡ ለምድር ።

አይሁድ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያሠለጥኑታል ፡

ከመ ፡ ያስተቃትሎሙ ፡ በኃይን ፡ ወበሞት ፡ ወበአራዊተ ፡ ምድር ።

ምእመናንን ፡ በጦር ፡ አስወግቶ ፡ (ወበረኀብ) ፡ ምግብ ፡ ነሥቶ ፡ (ወበሞት) ፡ መርዝ ፡ አጠጥቶ ፡ (ወበአራዊተ ፡ ምድር) ፡ ለአራዊት፡አስጥሎ፡ ያስገድላቸዋልና። አንድም፡በሽሕ፡ቢመጡ፡ፈረስ፡ ሐመልሚል ፡ ዘመነ፡ ሙሴ፡ ነው፡ ሐመልሚል፡ አለው ፡ እስራኤል ፡ በዘመኑ፡ አንድ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ጣዖት ፡ ብለዋልና ። አንድም ፡ የወጥ ፡ ቅመሙ ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዘመኑ ፡ የተሠራች ፡ የኦሪትም ፡ ሥራቷ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ በዘመኑ ፡ የተሠራች ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ከሞተ ፡ ነፍስ ፡ ከርደተ ፡ መቃብር ፡ የማታድን ፡ ስለ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ በግብፃውያን ፡ ዘጠኝ ፡ መቅሠፍት ፡ አሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵርን ፡ አሥራ ፡ አንደኛ ፡ ስጥመትን ፡ አድርጎ ፡ በዚያው ፡ ከነሥጋቸው ፡ ገሃነም ፡ አውርዷቸዋልና ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትን ፡ ከበው ፡ በሰፈሩ ፡ ባራቱ ፡ ቤት ፡ እስራኤል ፡ አሰለጠኑት ፡ (ከመ ፡ ያስተቃትሎሙ) ፡ እስራኤልን ፡ በጦር ፡ አስወግቶ ፡ ምግብ ፡ ነሥቶ ፡ (ወበሞት) ፡ ቸነፈር ፡ አምጥቶ ፡ ነዘር ፡ እባብ ፡ አስነሥቶ ፡ ያስገድላቸው ፡ ዘንድ። አንድም ፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡ በማዕከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ ዘመነ፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡ነው፡ ሐመልሚል፡ አለው፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ፡ ገዝቶ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይትዐጸዋ ፡ አብያተ ፡ ጣዖታት ፡ ይትረኀዋ ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነግሯልና ፡ (ወዘይጼዐኖ ፡ ወሲኦል) ፡ የተቀመጠበት ፡ ሞት፡ ይባላል ፡ መቃብርም ፡ ትከተለዋለች ፡ አለ ፡ በየደረሰበት ፡ የሚያስገድል ፡ በየደረሰበት ፡ የሚያስቀብር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ባሉ ፡ ምእመናን ፡ አሠለጠኑት ፡ (ከመ ፡ ያስተቃትሎሙ) ፡ ሰማዕታትን ፡ በጦር ፡ አስወግቶ ፡ ምግብ ፡ ነሥቶ ፡ (ወበሞት) ፡ ወርቅ ፡ አጠጥቶ ፡ (መርዝ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ለአራዊት ፡ ሰጥቶ ፡ ያስገድላቸው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡ ዘመነ ፡ መሐመድ ፡ ነው ፡ ሐመልሚል ፡ አለው ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አለች ፡ ምልክ፡ አላህ ፡ ነዘል ፡ ተዘል ፡ ተጌሠድ፡ ይህን ፡ ያልጻፈ ፡ ያነበበ ፡ የተረገመ ፡ ሰይፍ ፡ ይትአበዮ ፡ ይላልና ። አንድም፡ በእግዚአብሔር፡ አምናለሁ ፡ ይላል ፡ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ይላልና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ በየደረሰበት ፡ የሚያስገድል ፡ የሚያስቀብር ፡ ስለ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ እሱን ፡ በመሰለ ፡ ሞተ ፡ ነፍስን ፡ የሚያመጣ ፡ ርደተ ፡ ገሃነምን ፡ የሚያስከትል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ባራቱ ፡ ቤት ፡ እስላም ፡ አሠለጠኑት ፡ (ሐንበሊ ፡ መለኪ ፡ ሐነፊ ፡ ሳፍኢ ። ሼፊም ፡ ይላል) ፡ ምእመናንን ፡ በጦር ፡ አስወግቶ ፡ ምግብ ፡ ነሥቶ ፡ ዐይነ ፡ ወርቅ ፡ ነበረበት ፡ ሲያይ ፡ ይገላል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ለአራዊት ፡ አሰጥቶ ፡ ይገላቸው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡ ትስብእተ ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ ነው ፡ ሐመልሚል ፡ አለው ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ነውና ፡ (ወዘይጼዐኖ) ፡ ሰማዕታት ፡ በስሙ ፡ እያመኑ ፡ የሚሞቱ ፡ የሚቀበሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ይባላል ፤ ዲያብሎስን፡ ድል፡ ነሥቷልና፡ (ጥቅ)፡ በሞቱ፡ ለሞት፡ ደምሰሶ ፡ እንዲል ። ከመ ፡ ያስተቃትሎሙ ፡ ሰማዕታትን ፡ በጦር ፡ አስወግቶ ፡ ምግብ ፡ ነሥቶ ፡ መርዝ ፡ አጠጥቶ ፡ ለአራዊት ፡ ሰጥቶ ፡ ያስገድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ስብከተ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያስተምራል ፤ ኤር ፡ ፲፭፡ ፫ ። ሕዝ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩ ።

፱፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ኃምሰ ፡ ማኅተመ ፡

በአምስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አምስተኛው ፡ መልአክ ፡ አምስተኛውን ፡ ቊልፍ ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ርኢኩ ፡ ታሕተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበእንተ፡ ዘዐቀቡ ፡ ሕጎ ።

በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላመኑ ፡ ሕጉን ፡ ስለ ፡ ጠበቁ ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከምሥዋዑ ፡ በታች ፡ ተግዛ ፡ አየሁ ፡ ሐተታ ፡ በምሥዋዐ ፡ ብርቱ ፡ አምሳል ፡ አሳይቶታል ፡ ቁመቱ ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር፡ ወደ፡ላይ፡ ሁለት፡ ክንድ፡ ከስንዝር፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሲቀር ፡ በመካከል ፡ አራት ፡ ኵላብ ፡ አበጅተው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ የብረት ፡ ሰቅሰቅ ፡ ያኖራሉ ፡ በታች ፡ እሳት ፡ ያነዱበታል ፡ እንደ ፡ ወንፌት ፡ ያለ ፡ ነው፡ ነበልባሉ ፡ ሲመታው ፡ ስቡ ፡ እየቀለጠ ፡ እሳቱን ፡ ያጠፋዋል ፡ ስቡ ፡ የሰውነታቸው ፡ እሳቱ ፡ የመከራቸው ፡ ሰቅሰቅ ፡ የረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆነው ፡ መከራውን ፡ ለመቀበላቸው ፡ ምሳሌ ፡ የፈረስ ፡ መልክ ፡ ቢያልቅበት ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ ሄደ ። አንድም ፡ በአካላዊ ፡ ቃል ፡ ስላመኑ ፡ ሕጉን ፡ ስለ ፡ ጠበቁ ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸው ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በሲኦል ፡ በእደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተይዛ ፡ አየሁ ። (ጥቅ) ፡ ነፍሶሙስ ፡ለጻድቃን ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢለከፎሙ ፡ ላህበ ፡ ሥቃይ ፡ ወኢምንትኒ ፡ እንዲል ፤ ም ፡ ፫ ፡ ፩ ። ፲፬ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ።

፲ ፤ ወጸርኁ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡

በታላቅ ፡ ቃል ፡ አሰምተው ፡ ጮሁ ።

ወይቤሉ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ እግዚኦ ፡ ቅዱስ ፡ ወጻድቅ ፡ ኢትትቤቀሎሙኑ ፡ ወኢትኴንኖሙ ፡ በእንተ፡ ደምነ ፡ እምእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

(ቅዱስ) ፡ ጽኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ (ወጻድቅ) ፡ ጻድቅ ፡ ባሕርይ ፡ የምትሆን ፡ አቤቱ ፡ እስከመቸ ፡ አትፈርድባቸውም ፡ የማትፈርድባቸው ፡ እስከ ፡ መቸ ፡ ነው ። አንድም ፡ አትፈርድባቸውምን ፡ እስከ ፡ መቸ ፡ ነው፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ለይተው ፡ ደማችነን ፡ ስለ ፡ አፈሰሱ ። አንድም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ለይተህ ፡ አትፈርድባቸውምን ፡ ዘፍጥ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ም ፡ ፲፫ ፡ ፲ ።

፲፩ ፤ ወወሀብዎሙ ፡ አልባሰ ፡ ብሩሀ ፡ ለለአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ከመ ፡ ያዕርፉ ፡ ዓዲ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡

ለያንዳንዳቸው ፡ብሩህ ፡ብሩህ፡ ልብስ፡ ሰጥተው ፡ አለ ፡ ያረቦኑን፡ ክብር ፡ ሰጥተው፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ አርፉችሁ ፡ ቆዩ ፡ አሏቸው ፡

እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸሙ ፡ እለ ፡ ከማሆሙ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኀዊሆሙ፡ እለ ፡ ሀለዎሙ፡ ይትቀተሉ ፡ ከማሆሙ ።

እንደነሱ ፡ በሰማዕትነት ፡ ይሞቱ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው፡ አግብርተ፡ እግዚአብሔር፡ በሰማዕትነት፡እስኪፈጸሙ፡ድረስ፡ ሐተታ፡ መልአኩ ፡ለሄኖክ፡ማኅደረ፡ ነፍሳትን፡ እያዞረ ፡ ሲያሳየው፡ መንግሥተ፡ ሰማያትን፡አይቶ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ዝንቱ ፡ ዐቢይ ፡ ብሎታል ፡ አንተሰ ፡ ትጔጒእ ፡ በእንተ ፡ ርእስከ ፡ ልዑልሰ ፡ ይጔጒእ ፡ በእንተ ፡ ብዙኃን ፡ ወከመዝሰ ፡ ተስእላ ፡ ነፍሳት ፡ ወይቤላ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ንሄሉ ፡ በዝየ ፡ ወማእዜ ፡ ይከውን ፡ ማእረረ ፡ ዕሤትነ ፡ ወአውሥአን ፡ ኢዩርማኤል ፡ መልአክ ፡ ወይቤሎን ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸሙ ፡ እለ ፡ ከማክሙ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ መልሶለታል ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ በኤልያስ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ በክስረ ፡ በመርቅያን ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

፲፪ ፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ሳድስ ፡ ማኅተመ ፡ ኮነ፡ ካዕበ፡ ዐቢይ ፡ ድልቅልቅ ፡

በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ስድስተኛው ፡ መልአክ ፡ ስድስተኛውን ፡ ቍልፍ ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ስድስተኛ ፡ ሥራውን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ኅልፈተ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ፡

ፀሐይ ፡ ጸልመ ፡

ፀሐይ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ አለፈ ፡

ወወርኅኒ ፡ ከመ ፡ ደም ፡ ኮነ ፡ ኵለንታሁ ፡

ጨረቃም ፡ ደም ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ አለፈ ፡ ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲ ። ኢዮ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ።

፲፫ ፤ ወከዋክብትኒ ፡ ወድቁ ፡ እምሰማይ ፡ ከመ ፡ ቈጽለ ፡ በለስ ፡ ሶበ ፡ ይዘብጦ ፡ ዐቢይ ፡ ነፋስ፡

ከዋክብትም ፡ ቅጠል ፡ ነፋስ ፡ በመታው ፡ ጊዜ ፡ እንዲረግፍ ፡ ረገፉ ፡ አለ ፡ አለፉ ፡ ኢሳ ፡ ፴፬ ፡ ፬ ።

፲፬ ፤ ወሰማይኒ ፡ ተጠውመት ፡ ከመ ፡ ክርታስ ፡ ዘይጠወም ፡

ሰማይም ፡ እንደሚጠቀለል ፡ ብራና ፡ ተጠቀለለች ፡ አለ ፡ አለፈች ፡

አድባርኒ ፡ ወደስያት ፡ ሰሰሉ ፡ ኵሉ ፡

ተራራው ፡ ኮረብታው ፡ ሁሉ ፡ አለፈ ።

፲፭ ፤ ወነገሥተ ፡ ምድርኒ ፡ ወመሳፍንት ፡ ወመላእክት ፡ ወአብዕልት ፡ ወዐበይት ፡ ወኵሉ ፡ ገብር ፡ ወአግዐዚ ፡

ነገሥታቱ ፡ መሳፍንቱ ፡ ሹማምቱ ፡ ወይዛዝሩ ፡ ባለጸጎች ፡ ገዢም ፡ ተገዢም ፡ ሁሉ ፡

ተኀብኡ ፡ ውስተ ፡ በአታት ፡ ወውስተ ፡ አድባር ።

በዋሻ ፡ በፍርክታ ፡ ተሸሸጉ ፡ አለ ፡ አለፉ፤ ኢሳ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ።

፲፮ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ለአድባር ፡ ወለጸዋልዕት ፡ ደቁ ፡ ላዕሌነ ፡ ወክድኑነ ፡

ተራራው ፡ ኮረብታው ፡ ተንዶ ፡ ተጭኖን፡ ምድሩ ፡ ተከፍቶ ፡ አስጥሞን ፡ አሉ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡

እምገጸ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡

በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ካለ ፡ ከእሱ ፡ ከገጸ ፡ መዓቱ ፡ የተነሣ ፡

ወእምነ ፡ መዓት ፡ በግዑ ።

ከበግዑም፡ ፍርድ፡ የተነሣ፡ ሉቃ፡ ፳፫፡ ፴።

፲፯ ፤ እስመ ፡ በጽሐት ፡ ዕለተ ፡ መዓቱ ፡ ዐባይ ፡

ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ የሚፈርድባት ፡ ቀን ፡ ደርሳለችና ፡

ወመኑ ፡ ይክል ፡ ተቃውሞታ ።

መቃወም ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ፡ ሐተታ፡ መቃወም ፡ እንዳይገኙ ፡ መሆን ፡ ቢገኙም ፡ እንዳይጎዱ ፡ መሆን ፡ በሰባተኛው፡ መንፈቅ ፡ የሚሆነውን ፡ አስቀድሞ ፡ በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አሳይቶታል ፡ ራእይ ፡ ነውና ፡ የፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ፡ የኋላውን ወደ ፡ ፊት ፡ እያደረገ ፡ ያሳየዋል ፡ ያቀዳድማል ፡ ነቢያት ፡ የዃዋዌን ፡ ነገር ፡ ይዘው ፡ ሳለ ፡ የሚጠትን ፡ የሚጠትን ፡ ነገር ፡ ይዘው ፡ ሳለ ፡ የዃዋዌን ፡ እንዲናገሩ ። አንድም ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ኢትትቤቀሎሙ ፡ ወኢትኴንኖሙ ፡ ብለው ፡ ነበረና ፡ እንዲፈርድላቸው ፡ ለማጠየቅ ፡ በሰባተኛው ፡ መንፈቅ ፡ የሚሆነውን ፡ አስቀድሞ ፡ በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አሳይቶታል ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ (ኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ድልቅልቅ) ፡ የዕለተ ፡ ዐርቡን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ፀሐይ ፡ ጸልመ) ፡ ፀሐይ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ፡ ጨረቃም ፡ ደም ፡ ሆነ ፡ ከዋክብትም ፡ ቅጠል ፡ ነፋስ ፡ በመታው ፡ ጊዜ ፡ እንዲረግፍ ፡ ረገፉ ፡ (ወሰ

www.ethiopianorthodox.org

ማይኒ) ፡ ኀልፈተ ፡ ምኵራብ ፡ ሆነ ። አን
ድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ (ኮነ ፡
ዐቢይ)፡ ድልቅልቅ፡ በጥጦስ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ
ውን፡ መናገር፡ ነው፡ ፀሐይ፡ጨለማ፡ ሆነ ፡
ጨረቃም ፡ ደም ፡ ሆነ ፡ ከዋክብትም ፡ ረገ
ፉ ፡ ሐተታ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ፡ በሠሩት ፡ እ
ንደ፡ ተፈረደባቸው ፡ ለማጠየቅ ፡ በዕለተ ፡
ዐርብ ፡ የተደረገው ፡ ተአምራት ፡ ሁሉ ፡
ተደርጎባቸዋል ፡ (ወሰማይኒ) ፡ ምዝባሬ ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሆነ ፡ አድባር ፡ ያለውን፡
ነገሥት ፡ አውግር ፡ ያለውን ፡ መሳፍንት ፡
ብሎ ፡ ደገመው ፡ ነገሥታቱ ፡ መሳፍንቱ ፡
ባለጸጎች ፡ ሹማምት ፡ ወይዛዝር ፡ ገገፎም ፡
ተገገፎም ፡ በዋሻ ፡ በፍርክታ ፡ ተሸሸጉ ፡
አሁን ፡ የተመቸ ፡ ነው ፡ (ወይቤልዎሙ)፡
ተራራው ፡ ኮረብታው፡ ተንዱ፡ ተጭኖን ፡
መሬት ፡ ተከፍቶ፡ አስጥሞን ፡ አሉ ፡ (እም
ገጸ ፡ ዘይነብር) ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ ካለ ፡ ከእሱ ፡ በመዓት ፡ ከመገለጹ፡
የተነሣ ፡ (ወእምነ ፡ መዓተ ፡ በግዑ) ፡
ከበግዑ ፡ ፍርድ ፡ የተነሣ ፡ የሚፈርድ
ባት ፡ ቀን ፡ ደርሳለችና ፡ መቃወም ፡ ለ
ማን ፡ ይቻለዋል ፡ ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፭ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ርኢኩ ፡ አርባዕቱ ፡ መላ
እክት ፡ ይቀውሙ ፡ ውስተ ፡ አርባዕቱ ፡ መዓዝኒሃ ፡
ለምድር ፡

ዝ ፡ ሲናገረው ፡ የመጣ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ አራት ፡ መላእክት ፡ ባራቱ ፡ መዓ
ዝን ፡ ቁመው ፡ አየሁ ፡

ከመ ፡ የእኀዙ ፡ ከመ ፡ ኢይንፋሕ ፡ ነፋስ ፡

ነፋስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳይነፍስ ፡

ውስተ ፡ ምድር ፡ ወኢውስተ ፡ ባሕር ፡ ወኢውስተ ፡
ዕፀታት ።

በየብስ ፡ በባሕር ፡ በዕፀዋት ፡ እንዳይነ
ፍስ ፡ ወስነው ፡ ገተው ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡
ዳን ፡ ፯ ፡ ፪ ። ዘካ ፡ ፮ ፡ ፭ ። ማቴ ፡ ፳፬ ፡
፴፩ ።

፪፤ ወርኢኩ ፡ ወነጸርኩ ፡ ወመጽአ ፡ ካልእ ፡ መል
አክ ፡ እምነ ፡ ጽባሕ ፡ ወይጸውር ፡ ማኅተመ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ዘሕያው ፡ ለዓለም ።

ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሲመ
ጣ ፡ አየሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማኅተም ፡
ተሸክሟል ፡ አለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተል
ኬያለሁ ፡ ይላል ፡

ወይቤሎሙ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ለእልክቱ ፡ አርባዕቱ፡
መላእክት ፡ እለ ፡ ተውህበ፡ ሎሙ ፡ ይቅሥፍዋ ፡ ለም
ድር ፡ ወለባሕር ።

ይህን ፡ ዓለም ፡ ያሳልፉ ፡ ዘንድ ፡ ሥል
ጣን ፡ ለተሠጣቸው ፡ ላራቱ ፡ መላእክት ፡
በታላቅ ፡ ቃል ፡ ነገራቸው ፡ የብስን ፡ ባሕ
ርን ፡ ያሳልፉ ፡ ዘንድ ።

፫፤ ወባሕቱ ፡ ይቤሎሙ ፡ ኢታሕምሙ ፡ ምዕረሰ ፡
ኢምድረ ፡ ወኢባሕረ ፡ ወኢዕፀታተ ፡

አንድ ፡ ጊዜስ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አታሳ
ልፉ ፡ የብሱን ፡ ባሕሩን ፡ ዕፀዋትን ፡ አላ
ቸው ፡ ሐተታ ፡ ሰው ፡ እስትንፋሱን ፡
ባፈኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሞት ፡ ይህም ፡ ዓለ
ም ፡ የሚያልፍ ፡ ነፋሳት ፡ ሲያልፉ፡ነውና፤

እስከ ፡ ይትኀተሙ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ው
ስተ ፡ ፍጽሞሙ ።

አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምእመናን ፡
በግንባራቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስ
ኪጻፍባቸው ፡ ድረስ ፡ ሐተታ ፡ በተፈ
ጥሮ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርኣያነ ፡ ወበ
አምሳሊነ ፡ ብሎ ፡ በመሀል ፡ ራሱ ፡ ይጸ
ፍበታል ፡ ኃጢአት ፡ ሲሠራ ፡ መሬት ፡



አንተ ፡ ወትገብእ ፡ ውስተ፡ መሬት፡ ብሎ፡
በዙሪያው ፡ ይጻፍበታል ፡ ንስሓ ፡ ሲገባ ፡
ስመ ፡ ሥላሴ ፡ (ስመ ፡ በግዑም ፡ ፪ቢሉ) ፡
በግንባሩ ፡ ይጻፍበታል ፡ ሕዝ ፡ ፱፡፬፡ ፯ ።

፬፤ ወሰማዕኩ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለእለ ፡ ተኀትሙ ፡ ፻ወ
ርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ እልፍ ፡ ወአርብዓ ፡ ምእት ፡ እለ ፡
ተኀትሙ ፡ እምውስተ ፡ ኵሉ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ።

ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ በግንባራቸው፡ ስመ፡
እግዚአብሔር፡ የተጻፈባቸውን ፡ ቍጥራቸ
ውን፡ ሰማሁ ፡ አለ፡ አስራ ፡ አራት፡ እልፍ፡
ካራት ፡ ሽሕ፡ናቸው ። አንድም፡ (ወእምድ
ኅረ ፡ዝንቱ)፡ አራቱ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ባራ
ቱ፡ መዐዝን፡ ቁመው ፡ አየሁ ፡ በንፍሐት ፡
በጥምቀት ፡ ምክንያት ፡ ልጅነት ፡ እንዳይ
ሰጥ ፡ ይከለክሉ ፡ ዘንድ ፡ ሐተታ ፡ አሁን፡
ልጅነት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክሉ ፡ ሆ
ነው ፡ አይደለም ፡ ጌታ ፡ ካልሞተ ፡ ካሳ ፡
አይፈጸምም ፡ ካሳም ፡ ካልተፈጸመ ፡ አይ
ሾሙም ፡ ካልተሾሙም ፡ ልጅነት ፡ አያሰ
ጡምና ፡ ወኢውስተ ፡ ዕፀታት ፡ በዘጠኙ ፡
ዕፀወ ፡ ዕጣን ፡ ምክንያት ፡ ልጅነት ፡ እን
ዳይሰጥ ፡ ዘጠኙ ፡ ዕፀወ ፡ ዕጣን ፡ ሰሊክ ፡
መስተክ ፡ ስኂን ፡ ስንድሮስ ፡ አበሚ ፡ አ
በሞ ፡ ቀንሞ ፡ ቀናንሞ ፡ ዑድ ፡ ሚዓ ፡
ዱሪራ፡ ናቸው፡ (ወርኢኩ፡ወነጸርኩ)፡ ምክ
ንያተ ፡ ሕይወት፡ ጌታ ፡ ከመቤታችን ፡ ተ
ወልዶ ፡ አየሁ ፡ (ወይጸውር) ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕ
ርይ ፡ የሚተካከለው ፡ (ወይቤሎሙ) ፡ ሰ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ያጠምቁ ፡ ዘንድ ፡ ሥል
ጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ አራቱን ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ በጥምቀት ፡ በዘጠኙ ፡ ዕፀወ ፡
ዕጣን ፡ ምክንያት ፡ ልጅነት ፡ እንዳይሰጥ ፡
እንዲህ ፡ አላቸው (ወባሕቱ፡ ይቤሎሙ) ፡
አንድ ፡ ጊዜስ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አታጥ
ምቁ ፡ በጥምቀት ፡ በዘጠኙ፡ ዕፀወ፡ ዕጣን፡

ምክንያት ፡ ልጅነት ፡ እንዲሰጥ ፡ አታድ
ርጉ ፡ አላቸው ፡ ሐተታ ፡ ሕማም ፡ አላት፡
ጥምቀትን ፡ ተጠምቀው ፡ መከራ ፡ የሚ
ቀበሉባት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ይትኀ
ተሙ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምእ
መናን ፡ በገጸ ፡ ልቡናቸው ፡ ስመ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እስኪጻፍባቸው ፡ ድረስ ፡ ቆዩ ፡
አሏቸው ፡ እንጅ ፡ ወሰማዕኩ ፡ ከእስራ
ኤል ፡ ወገን ፡ በገጸ ፡ ልቡናቸው ፡ ስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ቍጥራ
ቸውን ፡ ሰማሁ ፡ (በሃይማኖት ፡ ፍጹ
ማን ፡ የሆኑ ፡ ማለት ፡ ነው) ፡ አስራ ፡ አ
ራት ፡ እልፍ ፡ ካራት ፡ ሽሕ ፡ ናቸው ፡
ም ፡ ፲፬ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፭፤ እለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ይሁዳ ፡ እልፍ ፡
ወዕሥራ ፡ ምእት ፡ ወእለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡
ሮቤል ፡ እልፍ ፡ ወዕሥራ ፡ ምእት ፡ ወእለ ፡ እምው
ስተ ፡ ሕዝበ ፡ ስምዖን፡ ፱ ፡ ወ፳፻፡ ወእለ፡ እምውስተ፡
ሕዝበ፡ ሌዊ፡ እልፍ ፡ ወዕሥራ፡ ምእት ፡ ወእለ ፡ እም
ውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ጋድ ፡ እልፍ ፡ ወዕሥራ ፡ ምእት ።

ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ በግንባራቸው ፡ ስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ እልፍ ፡
ከሁለት ፡ ሽሕ፡ ናቸው፡ ከሮቤልም፡ ወገን፡
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባው ፡ ይህን
ያህል ፡ ናቸው ፡ ከስምዖን ፡ ወገን ፡ ስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡
ያህል ፡ ናቸው ፡ ከሌዊ ፡ ወገን ፡ ስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡
ያህል ፡ ናቸው ፡ ከጋድ ፡ ወገን ፡ ስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡
ያህል ፡ ናቸው ።

፮፤ ወእለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ አሴር ፡ እልፍ ፡
ወዕሥራ ፡ ምእት ፡

ከአሴር ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡
የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡

ወእለ፡ እምውስተ፡ ሕዝበ፡ ንፍታሌም፡ እልፍ፡ ወ፳፻፡

ከንፍታሌም ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡
ናቸው ፡

፯ ፤ ወእለ፡ እምውስተ፡ ሕዝበ፡ምናሴ፡እልፍ፡ወ፳፻ ።

ከምናሴ ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ።

ወእለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ይሳኮር ፡ እልፍ ፡ ወ፳፻ ።

ከይሳኮር ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል፡ ናቸው ።

፰ ፤ ወእለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ዛብሎን ፡ እልፍ ፡ ወ፳፻ ፡

ከዛብሎን ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡

ወእለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ዮሴፍ ፡ እልፍ ፡ ወ፳፻ ፡

ከዮሴፍ ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡

ወእለ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ብንያም ፡ እልፍ ፡ ወ፳፻ ።

ከብንያም ፡ ወገን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡

ወእሉ ፡ እንከ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ተኀትሙ ፡

በግንባራቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ እለ፡ ፲፬ ፡ እልፍ ፡ ከራት ፡ ሽሕ ፡ ናቸው ።

፱ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰብአ ፡ ብዙኃነ፡ ዘአልቦ፡ ዘይክል ፡ ኈልቆቶሙ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወአሕዛብ ፡ ወነገድ ፡ ወበሐውርት ፡ ይቀውሙ ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ወቅድመ ፡ በግዑ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሕዝብም ፡ ከአሕዛብም ፡ ወገን ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ በበግዑም ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አየሁ ፡ እሊህ ፡ እንዲህ ፡ በተአምራት ፡ ተካክለው ፡ ተገኝተዋል ። አንድም ፡ ካንዱ ፡ ቢጎል ፡ ካንዱ፡ መልቶ ፡ ዳንን ፡ የሚጽፍም ፡ አለ ፡ የሚተውም ፡ አለ ፡ ቢጽፍ ፡ የተመቸ ፡ ብዙ ፡ ሰማዕታት ፡ ከእርሱ ፡ ይወለዳሉና ፡ ባይጽፍ ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ከእሱ ፡ ይወለዳልና ፡ መጻፍ ፡ አይገባውም ፡ ብሎ ፡ ትቶታል ፡ በዳን ፡ እግር ፡ ምናሴ ፡ ገብቷል ። አንድም፡ (እለ፡ እምውስተ ፡ ሕዝበ ፡ ይሁዳ) ፡ ይሁዳ ፡ ማለት ፡ ተአምኖ ፡ ተአማኒ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢያምኑት ፡ ሰው ፡ ሆኗልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ሮቤል ፡ ማለት ፡ ርእየኒ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሰውን ፡ በዐይነ ፡ ምሕረት ፡ አይቶ ፡ ሰው ፡ ሁኗልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት፡ ያመኑ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ስምዖን ፡ ማለት ፡ ሰምዐኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ገዐረ ፡ ምእመናንን ፡ ሰምቶ ፡ ሰው ፡ ሆኗልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ሌዊ ፡ ማለት ፡ ልጹቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዷልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ጋድ ፡ ማለት ፡ አክሊል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አክሊሎሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ይለዋልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ አሴር ፡ ማለት ፡ ብፁዕ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብፁዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአነ ፡ ተአመንኩ ፡ ቦቱ ፡ ይለዋልና፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ንፍታሌም ፡ ማለት ፡ በቀልት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በቀልት ፡ ምጡቅ ፡ ነው ፡ ልዑለ ፡ ባሕርይ ፡ ነውና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ምናሴ ፡ ማለት ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን፡ ማለት ፡ ነው ፡ ኀዘነ ፡ ምእመናንን ፡ አርቋልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ይሳኮር ፡ ማለት ፡ ዐስበ ፡ ኮል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ዐስበ ፡ ምእመናን ፡ ነውና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ዛብሎን ፡ ማለት ፡ መስተሳልም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ኅሩይ፡ ማእከለ ፡



እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ ይለዋልና ፡ በእሱ፡ ስብከት፡ ያመኑ፡ ይህን፡ ያህል፡ናቸው ፤ ዮሴፍ ፡ ማለት ፡ ገበገብ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አዲስ ፡ እህል ፡ በቀመሰ ፡ ጊዜ ፡ ጋፋት ፡ ገበገባኒ ፡ እንዲል ፡ በኵረ ፡ ምእመናን ፡ ነውና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ብንያም ፡ ማለት፡ ወልደ፡ ኀይል ፡ ወልደ ፡ የማን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ኀይሉ ፡ የማኑ ፡ ይለዋልና ፡ በእሱ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ በጌታ ፡ ስብከት፡ ያመኑ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ አለ ፡ አስራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ካራት ፡ ሽሕ ፡ ናቸው ። ያዕቆብ ፡ የጌታ ፡ ልያ ፡ የኦሪት ፡ ገረዱ ፡ የግዝረት ፡ ራሄል ፡ የወንጌል ፡ ገረዱ ፡ የጥምቀት ፡ ምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አለ ፡ ከጌታ ፡ በኋላ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ በሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ብዙ ፡ ምእመናን ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ አየሁ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ። አንድም ፡ (እለ ፡ እምውስተ ፡ ይሁዳ) ፡ ከቤተ፡ ይሁዳ ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ከሮቤል ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ከስምዖን ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ከሌዊ ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከጋድ ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከአሴር ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከንፍታሌም ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከምናሴ ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከይሳኮር ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከዛብሎን ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከዮሴፍ ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ከብንያም ፡ ወገን ፡ በተወለደ ፡ ሐዋርያ ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ በሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ ያመኑ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ አለ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ከአራት ፡ ሽሕ ፡ ናቸው ፡ ልያ ፡ የፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገረዱ ፡ የትሕትና ፡ ራሄል ፡ የፍቅር ፡ ገረዱ ፡ የጸሎት ፡ ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ ከአሕዛብ፡ ወገን ፡ በመምህራን ፡ ስብከት፡ ያመኑ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው፡ ብዙ ፡ ምእመናንን ፡ አየሁ ። አንድም ፡ (ወሰማዕኩ) ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱትን ፡ ቍጥራቸውን ፡ ሰማሁ ፡ (አወቅሁ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ካራት ፡ ሺሕ ፡ ናቸው ፡ (እለ ፡ እምውስተ ፡ ይሁዳ) ፡ ይሁዳ ፡ ማለት ፡ ተአምኖ ፡ ተአማኒ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ማመን ፡ እንጅ ፡ በልቡና ፡ ነው ፡ ልቡናቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ። ሮቤል ፡ ማለት ፡ ርእየኒ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ማየት ፡ እንጅ ፡ በዐይን ፡ ነው ፡ ዐይናቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ስምዖን ፡ ማለት፡ ሰምዐኒ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት ፡ ነው ፡ መስማት ፡ እንጅ ፡ በጆሮ ፡ ነው ፡ ጆሯቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ሌዊ ፡ ማለት ፡ ልፁቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተላዕቆ ፡ እንጅ ፡ በአባለ ፡ ዘርዕ ፡ ነው ፡ አባለ ፡ ዘራቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ጋድ ፡ አሴር ፡ ንፍታሌም ፡ ምናሴ ፡ እሊህ ፡ አራቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከቤተ ፡ ሰብእ ፡ ይወለዳሉ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ እንጅ ፡ በጅ ፡ በእግር ፡ ይመሰላል ፡ እጃቸውን ፡ እግራቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ይሳኮር ፡ ማለት ፡ ዐስበ ፡ ኮል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አለኝታ ፡ እንጅ ፡ በልብ ፡ ነው ፡ ልቡናቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ዛብሎን ፡ ማለት ፡ መስተሣልም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተሣልሞ ፡ እንጅ ፡ በአፍንጫ ፡ ነው ፡ አፍንጫቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ከልክለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ዮሴፍ ፡ ማለት ፡ ወልደ ፡ ፍቅርትየ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፍቅር ፡ እንጅ ፡ በልብ ፡ ነው ፡ በፍቅሩ ፡ ተሰውራ ፡ ያለች፡ ፍቅሩን ፡ ይዘው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው፡ ብንያም ፡ ማለት ፡ ወልደ ፡ ፃዕርየ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መከራን ፡ ተቀብለው ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ (መጥዎተ ፡ ርእስን ፡ ይዘው ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ከፍጹምነት ፡ የደረሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሕዝብ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ወጣንያን፡ አየሁ፡ በመንበሩ፡ ፊት ፡በበግዑም፡ ፊት ፡ ቁመዋል ፡ አለ ፡ ባለሟሎች ፡ ሆነዋል ፡ ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ አሕዛብ፡ ያለውን ፡ በሐውርት ፡ ብሎ ፡ ደገመው፡

ወይለብሱ ፡ አልባሰ ፡ ብሩሀ ፡

ብሩህ ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ፡ አለ ፡ ክብራቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወያጸንዑ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ጸበርተ ።

በእጃቸው ፡ ዘንባባ ፡ ይዘዋል ፡ አለ ። ትእምርተ ፡ ኀይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገዋል ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።

፲ ፤ ወይጸርኁ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ወይብሉ ፡ ፍርቃን ፡ ለአምላክነ ፡ ለዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ወሊበግዑ ።

በታላቅ ፡ ቃል ፡ አሰምተው ፡ ጮሁ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ፡ ላለ። አንድም፡ በጌትነት ፡ ላለ ፡ ለፈጣሪያችን ፡ መድኀኒት፡ መባል ፡ ይገባዋል ፡ ለበግዑም ፡ መባል ፡ ይገባዋል ፡ እያሉ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፲ ።

፲፩ ፤ ወይቀውሙ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ ወሊቃናት ፡ ዐውደ ፡ መንበሩ ፡

መላእክት ፡ ሊቃናት ፡ በመንበሩ ፡ ዙሪያ ፡ ቁመዋል ፡

ወእልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ሰገዱ ፡ በገጾሙ ፡ ወይብሉ ፡ አሜን ።

አራቱ ፡ ኪሩቤልም ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ በግንባራቸው ፡ አሜን ፡ ብለው ፡ ሰገዱ ፡ ሐተታ ፡ ተሰጥዎ ፡ እንደ ፡ መቀበል ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፲፩ ። ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ።

፲፪ ፤ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወባርኮት ፡ ወጥበብ ፡ ወኢኰቴት ፡ ወኀይል ፡ ወጽንዕ ፡ ለአምላክነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ለዘለዓለሙ ፡ ስቡሕ ፡ ቡሩክ ፡ ጠቢብ ፡ እኵት ፡ ኀያል ፡ ጽኑ ፡ መባል ፡ ይገባዋል ፡ እያሉ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፲፪ ።

፲፫ ፤ ወይቤለኒ ፡ አሐዱ ፡ እምነ ፡ ሊቃናት ፡ እሉ ፡ እለ ፡ ይለብሱ ፡ አልባሰ ፡ ብሩሀ፡ እምአይቴ፡ መጽኡ፡

ከሊቃናትም ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤ እሊህ ፡ ብሩህ ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ከወዴት ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፡ አለኝ ፡ ሊነግረው ፡ ቢሻ ፡ (ጥቅ) ፡ ምንተ ፡ ትሬኢ ፡ አሞፅ ፡ ምንት ፡ ዘውስተ ፡ እዴከ ፡ እንዲል ፡ወፅኡ ፡ ይላል ፡ ከወዴት ፡ የወጡ ፡ ናቸው ፡

፲፬ ፤ ወእቤሎ ፡ እግዚኦ ፡ አንተ ፡ ተአምር ፡

አቤቱ ፡ እኔ ፡ አላውቅም ፡ አንተ፡ ታውቃለህ ፡



ወይቤለኒ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ እምዐቢይ ፡ ሕማም ።

ዐቢይ ፡ ሕማምን ፡ ድል ፡ ነስተው ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፡ ከዐቢይ ፡ ሕማም ፡ የወጡ ፡ ናቸው ።

ወኀፀቡ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወአንጽሑ፡ በደመ ፡ በግዑ፡

ልብሳቸውን ፡ በበግዑ ፡ ደም ፡ አጥበው ፡ አንጽተዋል ፡ አለ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ ለይተዋል ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲ ። ማቴ ፳፬ ፡ ፳፩ ፡ ፶፩ ።

፲፭ ፤ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ በጽሑ ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ስለዚህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባለሟሎች ፡ ሆነዋል ፡

ወይሴብሕዎ፡መዐልተ፡ ወሌሊተ፡በውስተ፡መቅደሱ ፡

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በመመስገኛው ፡ ቦታ ፡ በጽርሐ ፡ አርያም ፡ ያመሰግኑታል ፡

ወየዐርፍ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ።

በመንበሩ ፡ ላይ ። አንድም ፡ በጌትነቱ ፡ ተቀምጦ ፡ ያለ ፡ እሱ ፡ አድሮባቸው ፡ ይኖራል ፡

ወይጼልል ፡ ላዕሌሆሙ ።

በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ያድርባቸዋል፡ስለ ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ ዘላለሙ ፡ ሲል ፡ ይደጋግማል ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ፡ ፲፭፡ ፭ ፡ ፰ ። ም ፡ ፲፯ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ።

፲፮ ፤ ኢይርኅቡኒ ፡ ወኢይጸምኡኒ ፡

ረኀበ ፡ ነፍስ ፡ ጽምአ ፡ ነፍስ ፡ አያገኛቸውም ፡

ወፀሐየ ፡ ሐሩርኒ ፡ ኢይረክቦሙ ።

መከራን ፡ የሚያመጣ ፡ ዲያብሎስ ፡ አያገኛቸውም ፡ ሐሩረ ፡ ፀሐይኒ ፡ ይላል ፡ ዲያብሎስን ፡ የሚያገኘው ፡ መከራ ፡ አያገኛቸውም ፡ ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፲ ።

፲፯ ፤ እስመ ፡ በግዑ ፡ ዘቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ይርዕዮሙ ፡

በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ያለ ፡ በግዑ ፡ ይጠብቃቸዋልና ፡

ወይመርሖሙ ፡ ውስተ ፡ ነቅዐ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡

በልጅነት ፡ ወደሚገኝ ፡ ክብር ፡ መርቶ ፡ ያደርሳቸዋልና።

ወያሴስል ፡ እግዚአብሔር ፡ አንብዐ ፡ እምአዕይንቲሆሙ ።

እግዚአብሔርም ፡ አንብዕን፡ ከዐይናቸው፡ ያርቅላቸዋል ፡ አለ ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ፡ አንድም ፡ ዕሤተ ፡ አንብዕን፡ ይሰጣቸዋል፡ ም ፡ ፭ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፳፫ ፡ ፪ ። ም ፡ ፳፩ ፡ ፩ ። ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፰ ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ ፤ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ሳብዐ ፡ ማኅተመ ፡ አርመመ ፡ ኵሉ ፡ ዘበሰማይ ፡ ወዘበምድር ፡ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ ሰዓት ።

ሰባተኛውን ፡ ሥራ ፡ በሠራ፡ ጊዜ ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የሰዓት ፡ እኩሌታ፡ያህል፡ ጸጥ፡ አለ፡ (ዕርቅ)፡ ዕዝራ፡ ዕለተ ፡ ደይንስ ፡ ለምዕር ፡ ይእቲ ፡ ይላል ፤ ከዚህ ፡ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ ሰዓት ፡ አለ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ዕዝራ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ የሚጽፍ ፡ ነውና ፡ እንዲረዳው ፡ የሰዓት ፡ እኩሌታ ፡ ያህል ፡ ጸጥ ፡ አድርጎ ፡ ያሳየዋል ፡ ዘካ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። እንባ ፡ ፪ ፡ ፳ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ሰብዐተ ፡ መላእክተ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

ርኢኩን ፡ ቢያይ ፡ ሰብዐተ ፡ ይቀውሙን ፡ ቢያይ ፡ ሰብዐቱ ፡ ይላል ፡ ከዚህ፡ በኋላ ፡ ሰባት ፡ መላእክት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቁመው፡አየሁ፡ አለ፡ ባለሟሎች፡ ሆነዋል።

ወወሀብዎሙ ፡ ለእልክቱ ፡ ፯ቱ ፡ መላእክት ፡ ሰብዐተ ፡ መጣቅዕተ ።

ለሊህ ፡ ለሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ሰባት ፡ ገንታ ፡ ሰባት ፡ ነጋሪት ፡ ሰባት ፡ መለከት ፡ ሰጥዋቸው ፡ አለ ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ አዘዟቸው ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፩ ።

፫ ፤ ወመጽአ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ወቆመ ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡

ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መጥቶ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ቆመ ፡

ወያጸንዕ ፡ ማዕጠንተ ፡ ወርቅ ፡

የወርቅ ፡ ጽና ፡ ይዟል ፡ በቁስ ፡ አምሳል ፡ ያየዋል ፡

ወወሀብዎ ፡ ብዙኀ ፡ ዕጣናተ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ለጸሎተ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ በዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘወርቅ ፡ ዘቅድመ ፡ መንበሩ ።

በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ለቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ዕጣን ፡ ያሳርግ ፡ ዘንድ ፡ አፍሰው ፡ ሰጡት ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፰ ።

፬ ፤ ወዐርገ ፡ ጢሱ ፡ ለውእቱ ፡ ዕጣን ፡ ምስለ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ እምውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለውእቱ ፡ መልአክ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

ጢሱ ፡ ለቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ከመሆን ፡ ጋራ ፡ በመልአኩ ፡ እጅ፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ዐረገ፡ መዝ፡ ፻፵፩፡ ፪ ።

፭ ፤ ወነሥአ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ማዕጠንተ ፡ እምኀበ ፡ እሳት ፡ ዘምሥዋዕ ።

ቢፈጀው ፡ ኀራረ ፡ ዕጣኑ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ አውርዶት ፡ ቆይቶ ፡ ሲያልቅ ፡ ሲያነሣው ፡ ያያል ፡

ወሶበ ፡ አውረደ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

ማዕጠንተ ፡ ወርቁን ፡ አንሥቶ ፡ የኃጥአን ፡ ጸሎት ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ የሚሆን ፡ ኀራረ ፡ ዕጣኑን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ደፋው ፡

ወሶበ ፡ አውረደ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

ወደ ፡ ምድር ፡ በደፋው ፡ ጊዜ ፡

ኮነ ፡ ነጐድጓድ ፡ ወፀዓዕ ፡ ወመብረቅ ፡ ወድልቅልቅ፡

ነጐድጓድ ፡ ፀዓዕ፡ መብረቅ፡ ድልቅልቅ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ መቅሠፍተ ፡ ኃጥአን ፡ ታዘዘ ። አንድም ፡ አሐዱ ፡ መልአክ ፡ መጋቤ ፡ ብሉይ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡ ጸሎት ፡ የሚያሳርግበትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ (ወወሀብዎ ፡ ብዙኀ) ፡ ጌትነቱ ፡ በሚታወቅበት ፡ ጽኑይ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረድበት ፡ በዓለመ ፡ መላእክት ፡ የቅዱሳን ፡ ቀደምት ፡ ጸሎት ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ የሚሆን ፡ የሱን ፡ ጸሎት ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ዕጣን ፡ አድርጎ ፡ ያሳርግ ፡ ዘንድ ፡ አሳርግ ፡ አሉት፡ (ወዐርገ፡ ጢሱ)፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ጸሎቱ ፡ ከጸሎተ ፡ ቅዱሳን ፡ ቀደምት ፡ ጋራ ፡ በሱ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐረገ ፡ (ወነሥአ) ፡ የቅዱሳን ፡ ቀደምት ፡ ጸሎትን ፡ የሚያሳርግበትን ፡ ሥልጣን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳደረገ ፡ ኃጥአንን ፡ የሚያጠፋበትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ (ወአውረደ) ፡ ለጻድቃን ፡ እንደ ፡ ጸለየ ፡ በኃጥአን ፡ ጸለየባቸው ፡ (ወሶበ ፡ አውረደ) ፡ በጸለየባቸውም ፡ ጊዜ፡ መቅሠፍተ ፡ ኃጥአን ፡ ታዘዘ ። አንድም ፡ (ወመጽአ ፡ ካልእ) ፡ መጋቤ ፡ ሐዲስ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡ ጸሎት ፡ በሚያሳርግበት ፡ ቦታ ፡ ቆመ ፤ ጸሎት ፡ የሚያሳርግበትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ጌትነቱ ፡ በሚታወቅበት ፡ ጽኑይ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈርድበት ፡ በዓለመ ፡ መላእክት ፡ በሱ ፡ ጸሎት ፡ ጸሎተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደኀርትን ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ዕጣን ፡ አድርጎ ፡ ያሳርግ ፡ ዘንድ ፡ አሳርግ ፡ አሉት ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው ፡ (ምእመናንም ፡ ቢሉ) ፡ (ወዐርገ፡ ጢሱ)፡ የእርሱ ፡ ጸሎት ፡ ከጸሎተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደኀርት ፡ ጋራ ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ዕጣን ፡ ሆኖ ፡ በርሱ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐረገ ፡ (ወነሥአ) ፡ ጸሎተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደኀርት ፡ የሚያሳርግበትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ አደረገ ፡ ኃጥአንን ፡ የሚያጠፋበትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ (ወአውረደ) ፡ ለጻድቃን ፡ እንደ ፡ ጸለየ ፡ በኃጥአን ፡ ጸለየባቸው ፡ (ወሶበ ፡ አውረደ) ፡ በኃጥአን ፡ በጸለየባቸው ፡ ጊዜ፡ መቅሠፍት ፡ ሆነ ። አንድም ፡ (ወመጽአ) ፡ ምክንያተ ፡ ሕይወት ፡ ጌታ ፡ ራሱ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ በመስቀል ፡ ተሰቀለ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መባልን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ (ወወሀብዎ) ፡ ጌትነቱ ፡ በሚታወቅበት ፡ ጽኑይ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረድበት ፡ በሱ ፡ ፈቃድ ፡ በተተከለ ፡ በመስቀል ፡ ጸሎተ ፡ ቀደምትን ፡ ከጸሎተ ፡ ደኀርት ፡ ጸሎተ ፡ ደኀርትን ፡ ከጸሎተ ፡ ቀደምት ፡ ጋራ ፡ አሳርጎ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ አሳርግ ፡ አሉት (ወዐርገ) ፡ ጸሎቱ ፡ ከጸሎተ ፡ ቀደምት ፡ ከጸሎተ ፡ ደኀርት ፡ ጋራ ፡ በእሱ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፡ ዐረገ ፡ (ወነሥአ) ፡ መሥዋዕትነቱን ፡ ከሠመረለት ፡ ከመንፈስ ፡ቅዱስ ፡ካባቱም ፡ራሱን ፡መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ የሚያቀርብበትን ፡ ሊቀ፡ ካህናትነትን ፡ በፈቃዱ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ። አንድም ፡ ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ የሚያቀርብባትን ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ለየ ፡ (ወአውረደ) ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ሲኦል ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሄደ ፡ (ወሶበ ፡ አውረደ) ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ በዐቀብተ ፡ መቃብር፡ በዐቀብተ፡ገሃነም፡ ዘንድ፡ፍርሀት፡ሽብር፡ሆነ። አንድም፡ (ወወረደ) ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ አድሮ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ (ኮነ) ፡ ነጐድጓድ ፡ ስብከት ፡ ሐዋርያት ፡ ተደረገ ፡ ሕዝ ፡፤፲ ፡ ፲፪ ።

፮ ፤ ወእልክቱኒ ፡ ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ያጸንዑ ፡ ሰብዐተ ፡ መጣቅዕተ ፡ ተደለዉ ፡ ከመ ፡ ይጥቅዑ ፡ ቦሙ ፡

ሰባት ፡ ገንታ ፡ ሰባት ፡ ነጋሪት ፡ ሰባት ፡ መለከት ፡ የያዙ ፡ ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ኪያሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሰባቱን ፡ ገንታ ፡ ሰባቱን ፡ ነጋሪት፡ ሰባቱን፡ መለከት፡ ይመቱ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጁ ፡ ቦሙ ፡ ይላል ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ይመቱ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጁ ፡ ሐተታ ፡ እንደ ፡ ሀገረ ፡ ሰብእ ፡ ጥምቀት ፡ ነጋሪቱን ፡ አሳዝለው፡ ሲመቱበት፡ እንዲውሉ። አንድም ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ የታዘዙ ፡ ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ሰባቱን ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጁ ፡ ቦሙ ፡ በሰዎች ፡ ይሠሩባቸው ፡ ዘንድ፡ተዘጋጁ ።

፯ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ቀዳማዊ ፡ መልአክ ፡

በመዠመሪያው ፡ መንፈቅ ፡ መዠመሪያው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ፤

ኮነ ፡ በረድ ፡ ወእሳት ፡ ምስለ ፡ ደም ፡ ድሙር ፤ ወወረደ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

በረድና ፡ እሳት ፡ ከደም ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅሎ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወረደ ።



www.ethiopianorthodox.org

ወውዕየ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሃ ፡ ለምድር ፡

የምድር ፡ ሲሦም ፡ ተቃጠለ ፡

ወውዕዩ ፡ ኵሉ ፡ ዕፅ ፡ ወሐመልማል ፡

ሣሩ ፡ ዕንጨቱ ፡ ቅጠሉ ፡ ተቃጠለ ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ (ኮነ ፡ በረድ) ፡ ደመ ፡ በለስን ፡ ከማፍሰስ ፡ ጋራ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ለኃጢአት ፡ መናደድ ፡ ከምግባር ፡ ከትሩፋት ፡ መባረድ ፡ ሆነ ፡ (ወውዕየ) ፡ ከሰው ፡ ሲሦው ፡ ጠፋ ፡ በነፍስ ፡ ተጎዳ ፡ (ወውዕዩ) ፡ የክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸው ፡ የበጎዎች ፡ ሰዎች ፡ ሥጋቸው ፡ የሚጎዳ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ (ኮነ ፡ በረድ) ፡ ደመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማፍሰስ ፡ ጋራ ፡ በአይሁድ ፡ ለኃጢአት ፡ መናደድ ፡ ከምግባር ፡ ከትሩፋት ፡ መባረድ ፡ ሆነ ። (ወውዕየ) ፡ ከአይሁድ ፡ ነው ፡ ሲሦዎቹ ፡ ጠፉ ፡ (ወውዕዩ ፡ ሣዕር) ፡ ሣዕር ፡ አሪት ፡ አስተጋብእ ፡ ሣዕረ ፡ ደብር ፡ እንዲል ፡ ሐመልማል ፡ ወንጌል ፡ ወእምክልኤሆሙ ፡ ሐመልማለ ፡ ዘርዕ ፡ እንዲል ፤ ጠፉ ፡ አለ ፡ ሕጋቸው ፡ አለመጠበቁን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ዘፀአ ፡ ፱ ፡ ፳፫ ።

፰ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡

በሁለተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሁለተኛው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

ወረደ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ እሳት ፡ ዐቢይ ፡ ዘመጠነ ፡ ደብር ፡ እንዘ ፡ ይነድድ ፡

ተራራ ፡ የሚያክል ፡ እሳት ፡ እየበራ ፡ እየነደደ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ወረደ ፡

ወኮነ ፡ ደመ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሃ ፡ ለባሕር ።

የባሕር ፡ ሲሦው ፡ ደም ፡ ሆነ ፡ ከሦስቱ ፡ ባሕር ፡ አንዱ ። አንድም ፡ ከዚያው ፡ ካንዱ ፡ ባሕር ፡ ሲሦው ፤ ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፳፭ ። ዘፀአ ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።

፱ ፤ ወሞተ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሁ ፡ ለዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ዘተፈጥረ ፡ ዘቦ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ፡

በባሕር ፡ ተፈጥሮ ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕይወት ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ከሚኖር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሲሦው ፡ አለቀ ፡ አለ ፡ በጽምዕ ፡ ምግብ ፡ ቢለወጥበት ፡

ወሣልስተ ፡ እዴሆን ፡ ለአሕማር ፡ ማሰና ።

ከመርከቦችም ፡ ሲሷቸው ፡ ጠፋ ፡ ከሦስቱ ፡ መርከቦች ፡ አንዱ ። አንድም ፡ ከአንዱ ፡ መርከብ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ መቀደድ ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ (ወረደ ፡ እሳት) ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ የኖሩትን ፡ ያህል ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ በነበሩ ፡ አበው ፡ ለኃጢአት ፡ መናደድ ፡ ከምግባር ፡ ከትሩፋት ፡ መባረድ ፡ ሆነ ፡ (ወኮነ ፡ ደመ) ፡ ከከተማው ፡ ሲሦው ፡ ጠፋ ፡ ከሦስቱ ፡ ከተማ ፡ አንዱ ። አንድም ፡ ካንዱ ፡ ሲሦው ፡ (ወሞተ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሁ) ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተፈጥሮ ፡ በነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ሕይወት ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ከሚኖር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲሦው ፡ ጠፋ ፡ አለ ፡ በነፍስ ፡ ተጎዳ ፡ (ወሣልስተ) ፡ ከአበውም ፡ ሲሦዎቹ ፡ ጠፉ ፡ አለ ፡ በነፍስ ፡ ተጎዱ ። አንድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ቢመጡ፡(ወረደ) ዲያብሎስ ፡ እየተናደደ ፡ ወደ ፡ ጥሙቃኑ ፡ ወረደ ፡ ደብር ፡ አለው ፡ ስለ ፡ ትዕቢቱ፡ (ጥቅ)፡ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ደብር፡ ቅድመ፡ ዘሩባቤል ፡ ወሰመዮ ፡ ደብረ ፡ በእንተ ፡ ትዕቢቱ ፡ እንዲል ፡ (ወኮነ ፡ ደመ) ፡ ከጥሙቃኑ ፡ ሲሦዎቹ ፡ ጠፉ ፡ አለ ፡ በነፍስ ፡ ተጎዱ ፡ (ወሞተ) ፡ በሐዲስ ፡ ተፈጥሮ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሕይወት ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ከሚኖር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲሦው ፡ ሞተ ፡ አለ ፡ በነፍስ ፡ ተጎዳ ፡ (ወሣልስተ ፡ እዴሆን) ፡ ከመምህራኑም ፡ ሲሦዎቹ ፡ ጠፉ ፡ አለ ፡ በነፍስ ፡ ተጎዱ ።



፲ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ሣልስ ፡ መልአክ ፡

በሦስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሦስተኛው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

ወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ኮከብ ፡ ዐቢይ ፡ እንዘ ፡ ይነድድ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡

ከሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ኮከብ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እየነደደ ፡ እየበራ ፡ ወረደ ፡

ወወረደ ፡ ውስተ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለአፍላግ ፡ ወለአንቅዕተ ፡ ማያት ።

በአፍላግ፡ በአንቅዕት፡ በሲሷቸው፡ ወረደ ፡ አፍላግ ፡ የሚላቸው ፡ እንደ ፡ መገጭ፡ እንደ ፡ ጉማራ ፡ አንቅዕት ፡ እንደ ፡ ቅሀ፡ እንደ፡ አንገረብ፡ ያሉ፡ ናቸው ። አንድም፡ አፍላግ ፡ የሚላቸው ፡ እንደ ፡ ዐባይ ፡ እንደ ፡ በሽሎ ፡ እንደ ፡ ርብ ፡ አንቅዕት ፡ እንደ ፡ መገጭ ፡ እንደ ፡ ጉማራ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ኢሳ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪ ። ዳን ፡ ፰ ፡ ፲ ።

፲፩ ፤ ወስሙ ፡ ለውእቱ ፡ ኮከብ ፡ ዕጉስታር ፡

ስሙም ፡ ሬቶ ፡ ይባላል ፡

ወኮነ ፡ ዕጉስታረ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለማያት ፡

ከውኃው፡ሲሦው፡ ሬት፡ ሆነ፡ አለ፡ መረረ ፡

ምስለ ፡ ዐውሎ ፡

ወረደ ፡ ምስለ ፡ ዓውሎ ፡ ከጠሮ ፡ ጋራ ፡ ወረደ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡

ወብዙኅ ፡ ሰብእ ፡ ዘሞተ ፡ እምነ ፡ ምረሮሙ ፡ ለማያት ።

ከውኃውም ፡ ምሬት ፡ የተነሣ ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ በጽምዕ ፡ ምግብ፡ ቢለወጥበት ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ (ኮከብ ፡ ዐቢይ) ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ እፎ ፡ ወድቀ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ እንዲል ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እየተናደደ ፡ ከእስራኤል ፡ በልዑላኑ ፡ በትሑታኑ ፡ ወረደባቸው ፡ ስሙ ፡ እብስትዮን ፡ ይባላል ፡ ሕግ ፡ የሚለዋውጥ ፡ ማለት ፡ ነው፡ (ወኮነ) ፡ የኩሌቶች፡ የእስራኤል ፡ ሕጋቸው ፡ ተለወጠ ፡ ወረደ ፡ ምስለ ፡ ዓውሎ ፡ ከማሳት ፡ ጋራ ፡ ወረደ ፡ (ወብዙኅ ፡ ሰብእ) ፡ ከሕጉም ፡ መለወጥ ፡ የተነሣ ፡ በነፍስ ፡ የተጎዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። አንድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ (ኮከብ ፡ ዐቢይ) ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ እየተናደደ ፡ ወረደ ፡ ከጥሙቃኑ ፡ በልዑላኑ ፡ በትሑታኑ ፡ ወረደ ፡ ስሙም ፡ እብስትዮን ፡ ይባላል ፡ አእምሮ ፡ የሚለዋውጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከጥሙቃኑ፡ የኩሌቶች ፡ አእምሯቸው ፡ ተለወጠ ፡ (ወረደ ፡ ምስለ ፡ ዓውሎ) ፡ ከማሳት ፡ ጋራ፡ ወረደ ፡ ከአእምሯቸውም ፡ መለወጥ ፡ የተነሣ ፡ በነፍስ ፡ የተጎዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

፲፪ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ራብዕ ፡ መልአክ ፡

ባራተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አራተኛው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

ተቀሥፈት ፡ ፀሐይ ፡

ፀሐይ ፡ ተለወጠች ፡ ተከፈለች ፡

ወጸልመት ፡ ሣልስተ ፡ እዴሃ ፡

ሲሦዋ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ፡ ከሰሌዳው ፡ ሲሦው ። አንድም ፡ እየቆየ ፡ ድብ ፡ ማለት ፡

ወሣልስተ ፡ እዴሃ ፡ ለወርኅ ፡

የጨረቃም ፡ ሲሦዋ ፡ ደም ፡ ሆነ ፡

ወሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለከዋክብት ፡ ከመ ፡ ኢያብርሁ ፡

የከዋክብትም ፡ ሲሷቸው ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ፡ እንዳያበሩ ።

ወሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለዕለት ፡ ወለሌሊት ።

የመዓልት ፡ የሌሊትም ፡ ሲሷቸው ፡ ጠፋ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከመዓልቱ ፡ አራት ፡ ከሌሊቱ፡ አራት ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ይነሣለታልና ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ በዧዋዌ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ፀሐይ ፡ የእስራኤል ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ወር
ኅ ፡ ንጉሡ ፡ በሚጠት ፡ ፀሐይ ፡ የአሕዛብ፡
ንጉሡ ፡ ወርኅ ፡ ቢትወደዱ ፡ ጠፉ ፡ በዬ
ዋዌ ፡ ኤልያቄም ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡
በሴዴቅያስ፡ ጊዜ፡ ፍጹም፡ ዬዋዌ፡ ተደርጓ
ልና ፡ በሚጠት ፡ ናቡከደነጾር ፡ የሮማሎ
ዴቅ፡ብልጣሶር፡በብልጣሶር፡ ጊዜ፡ ፍጹም፡
ሚጠት፡ተደርጓልና፡ ሣልስተ፡ እዴሃ፡ለፀሐ
ይ፡አለ ፡ወሣልስተ፡ እዴሃ፡ ለወርኅ፡ ወሣል
ተ፡ እ.ዴሆሙ፡ ለከዋክብት፡ ፡ ከመኳንንቱ
ም፡ሲሦዎቹ፡ ጠፉ፤እንዳይፈርዱ፡ አለ ፡ የዕ
ውቀት፡ሥራ፡እንዳይሠሩ፡ እንዳይገዙ፡ ፀሐ
ይ፡ያለውን፡ ዕለት፡ወርኅ፡ ያለውን፡ ሌሊት፡
ብሎ፡ደገመው።አንድም፡በማእከለ፡ዘመን፡
ቢመጡ፡ፀሐይ፡ ሊቀ፡ጳጳስ፡ወርኅ ፡ ጳጳስ ።
አንድም፡ ፀሐይን፡ጳጳስ፡ያሉ፡ እንደ፡ሆነ፡ወ
ርኅ፡ ኤጲ.ስ፡ቆጶስ፡ ነው፡ ጠፉ፡በነፍስ፡ ተጎ
ዱ፡ሣልስተ፡እዴሃ፡ላለው፡ ሊቀ፡ጳጳሱ፡ ለኤ
ጲ.ስ፡ቆጶስ፡ ሦስተኛ፡ነውና፡ (ወሣልስተ፡እ
ዴሆሙ)ከመምህራኑም፡ ሲሦዎቹ፡ጠፉ፡እ
ንዳያስተምሩ፡(ወሣልስተ፡እዴሆሙ)፡መዓ
ልቱን ፡ ከሦስት፡ ከፍለው፡በአንዱ ፡ እጅ ፡
ተግባረ ፡ እድ ፡ ይይዙበታል ፡ በአንዱ ፡
እጅ ፡ ጊዜያት ፡ ያደርሱበታል ፡ በአንዱ ፡
እጅ ፡ ያስተምሩበታል ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡
በሚይዙበት ፡ ጊዜያት ፡ በሚያደርሱበት፡
ቀርቶ ፡ በሚያስተምሩበት ፡ ይመጣባቸዋ
ልና ፡ ሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለዕለት ፡ ወለ
ሌሊት ፡ አለ ፤ ም፡ ፯ ፡ ፲፪። ዘፀአ፡ ፲፡ ፳፩ ።

፲፫ ፤ ወሰማዕኩ ፡ አሐዱ ፡ ንስር ፡ ይሠርር ፡ ማእ
ከለ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ወይብል ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡

ንስር ፡ መልአክ ፡ ነው ፡ በኅዋ ፡ እየበረረ ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ሰማሁ ፡

አሌ ፡ ሎሙ ፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ፡
ምድር ፡ እምነ ፡ ዘተርፈ ፡ ቃለ ፡ መጥቅዖሙ ፡ ለሡ
ለስቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይጥቅዑ ።

ሥራቸውን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡
ሦስቱ ፡ መላእክት ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ ከመቅረቱ ፡ የተነሣ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ፡
ወዮ፡ ሊሉላቸው፡ይገባል፡ ሲል፡ሰማሁ፡ም፡
፲፬፡ ፯ ። ም፡ ፱፡ ፲፪ና፡ ፲፩ ፡ ፲፬ና ፡፲፪፡ ፲፪።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ኃምስ ፡ መልአክ ፡

ባምስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አምስተኛው ፡
መልአክ ፡ ሥራውን፡ ሁሉ ፡ በሠራ፡ ጊዜ ፡

ወረደ ፡ ኮከብ ፡ እምሰማይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

ኮከብ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ፡ አለ ፡ መልአክ ፡
ነው ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡

ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ መራኁተ ፡ አንቅዕተ ፡ ቀላያት ።

የሰበድአትን ፡ ከተማ ፡ በር ፡ የሚከፍት
በት ፡ ቊልፍ ፡ አለ ፡ የሚከፍትበት ፡ ሥል
ጣን ፡ ተሰጠው ፡ (ታሪክ) ፡ እስክንድር ፡
እየዞረ ፡ ሲወጋ ፡ ከሰበድአት ፡ ከተማ ፡
ደረሰ ፡ እሊህ ፡ ሰበድአት ፡ ብዙ ፡ ኅብረ ፡
መልክ ፡ ያላቸው ፡ ደንጊያውን ፡ ብረቱን ፡
እንደ ፡ እንጀራ ፡ የሚያላምጡ ፡ እሳቱን ፡
እንደ ፡ ውኃ ፡ የሚጠጡ፡ ናቸው ፡ አይቶ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ግሩም ፡ ፍጥረት ፡ ይህ ፡
በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይተርፈዋል ፡ አቤቱ፡
ለፍጥረትህ ፡ እዘንለት ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ፡ ኅቡዕ ፡ ፍ
ኖት ፡ ተገለጸለት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ገስግሶ ፡
ከደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ፡ ይህ ፡
የደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ከተማ ፡ ዙሪያው ፡ ሰባ ፡
ቀን ፡ የሚያስሄድ ፡ ነው ፡ (ሰማንያ ፡ ቀ



ንም ፡ ይላሉ) ። ቅፅሩ ፡ የብረት፡ ሣንቃው፡
የብርት ፡ ነው ፡ ብረትስ ፡ በሀገራቸው ፡
ውድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቅፅሩ ፡ የብርት ፡ ሣን
ቃው ፡ የብረት ፡ ነው ፡ የቅፅሩ ፡ ቁመት ፡
አሥር ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ብላቴኖችን ፡ የተ
ምር ፡ መሰላል ፡ አበጅቶ ፡ ወጥታችሁ ፡
ክፈቱ ፡ አላቸው ፡ እንከፍታለን ፡ ብለው ፡
ሲወጡ፡ ሐለይተ ፡ ብርትን ፡ ሰምተው ፡
እሰይ ፡ እሰይ ፡ እያሉ ፡ ወድቀው ፡ ወድ
ቀው ፡ አልቀዋል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እሱ ፡
ወጥቶ ፡ ድጉን ፡ በመሰላል ፡ አሥሮ ፡ እየ
ተረተረ ፡ ወርዶ ፡ በዙሪያው ፡ የብረት ፡
ምስል ፡ ጦሩን ፡ ጕራዴውን ፡ ሰይፉን ፡
እየያዘ ፡ ቁሟል ፡ ያን ፡ እንዳይነካ ፡ ተጠ
ንቅቆ ፡ ጥግ ፡ ለጥግ ፡ ሲሄድ ፡ ወረቀት ፡
ወድቆ ፡ አገኘ ፡ አንሥቶ ፡ ቢመለከት ፡
የሀገራችን፡ ብዕሉ፡ ብዙ፡ነው፡ ከብዕሉም፡
ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የቤታችን ፡ ዐምዱ ፡
ሠረገላው፡ የዕንቊ ፡ መረባው፡ ወልወሉ ፡
የወርቅ ፡ ነው ፡ ይህስ ፡ ከወዴት ፡ የተ
ገኘ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ነጋድያን ፡ አልፈው ፡
ሲሄዱ ፡ ምድሩን ፡ አጕድጕደን፡ ቆፍረን ፡
ጦሩን ፡ አንካሴውን ፡ ሰይፉን ፡ ጕራዴ
ውን ፡ ተክለን ፡ ላዩን ፡ የተለፋ ፡ መስክ ፡
(ሜዳ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ አስመስለን ፡
እናሳያቸዋለን ፡ መጥተው ፡ ይሰፍራሉ ፤
ያልቃሉ ፡ዕቃቸውን ፡ አንሥተን ፡ እናገ
ባዋለን ፡ የሀገራችን ፡ ተድላ ፡ ደስታው ፡
ብዙ ፡ ነው ፡ ከተድላ ፡ ደስታው ፡ ብዛት ፡
የተነሣ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ስና
ጨበጭብ ፡ እጃችን ፡ ቢደክም ፡ በገዛ ፡
እጃቸው ፡ የሚያጨበጭቡ ፡ ሐለይተ ፡
ብርት ፡ አበጅተን ፡ ስንዘፍን ፡ ስናጨበ
ጭብ ፡ በአባር ፡ በቸነፈር ፡ ቢለን ፡ የማን
መለስ ፡ ብንሆን ፡ ሰባ ፡ ፡ቀን የሚያስሄ
ደውን ፡ ከተማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንድ፡
ቀን ፡ አጥፍቶት ፡ አደረ ፡ የዛሬ ፡ አምሳ ፡
ዘመን ፡ ንጉሥ ፡ ይመጣል ፡ እሱን ፡ የተከ
ተለ ፡ ይድን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንጃ ፡ እኔም ፡
ይህን ፡ ጽፌ ፡ ከአባቶቼ ፡ እደረባለሁ ፡ የ
ሚል ፡ ነው ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ እሊህ ፡ ሰዎ
ች ፡ አልቀዋል ፡ ካለቁም ፡ አምሳ ፡ ዘመን ፡
ሆኗቸዋል ፡ ንጉሥ ፡ ይመጣል ፡ የተባለ ፡
እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ሂዶ ፡ የሣንቃው ፡ መወ
ርወሪያ ፡ ቁመቱ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡
ነው ፡ ያን ፡ በጥበብ ፡ ከፍቶ ፡ ወጥቶ ፡
ዐዋጅ ፡ ይነግራል ፡ ከመንገድ ፡ የወጣህ ፡
እኔን ፡ ያልተከተልህ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡
ማለቱ፡ የብረቱ፡ ምስል፡ እንዳይነካቸው ፡
ነው ፡ እሱን፡ ተከትሎ፡ ለገባ፡ ለሠራዊቱ ፡
ወርቁ ፡ ዕንቊ ፡ ብቻ ፡ በቅቶታል ፡ የቀ
ረውን ፡ ያነሣው ፡ የለም ፡ እሊያንም ፡
ሐለይተ፡ ብርት ፡ ከመዋድ ፡ከመዋዳቸው፡
ለይቶ ፡ ወስዶ ፡ በሰበደአት ፡ ከተማ ፡ ቅር
ፍትኤል ፡ ምድቅኤል ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡
ተራሮች ፡ አሉ ፡ እሊያን ፡ በጸሎት ፡ በተ
አምራት ፡ አቃርቦ ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ አድር
ጓቸዋል ፡ እሊያን ፡ እየሰሙ ፡ ሲሸሹ ፡
ይኖራሉ ፡ ነፋስ ፡ ወዲህ ፡ ሲመልሳቸው ፡
እስክንድር ፡ ሄደልን ፡ እያሉ፤ እንወጣለን፤
ይላሉ ፡ ነፋስ ፡ ወዲያ ፡ ሲመልሳቸው ፡
እስክንድር ፡ መጣብን ፡ እያሉ ፡ ሲሸሹ ፡
ይኖራሉ፡ በአምስተኛው፡ መንፈቅ ፡ መል
አክ፡ ሰብሮ፡ አስወጥቶ፡ ይሰዳቸዋል፡ መጥ
ተው፡ ያጠፋሉ ፡ ም፡ ፳ ፡ ፲ ። ም፡ ፳፡ ፩ ።

፪ ፤ ወዐርገ ፡ ጢስ ፡ እምነ ፡ ቀላይ ፡ ከመ ፡ ጢሰ ፡
እቶን ፡ ዐቢይ ፡

ከከተማው ፡ ሠራዊት ፡ በዝቶ ፡ ወጣ ፤
ጢስ ፡ ከጕድጓዱ ፡ በዝቶ ፡ እንዲወጣ ፡

ወከደኖ ፡ ለፀሐይ ፡

ምድሩን ፡ አለበሰው ፡ (ጥቅ) ፡ መራኁተ ፡
አወፍዮ ፡ ለፀሐይ ፡ እንዲል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኮነ ፡ ከመ ፡ ደመና ፡ ውእቱ ፡ ጢስ ፡ ቀላይ ።

ብዛቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ኢዮ፡ ፪፡ ፪፡ ፲ ።

፫ ፤ ወእምነ ፡ ውእቱ ፡ ጢስ ፡ ወፅአ ፡ አንበጣ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

ለሠራዊቱ ፡ መልክዓ ፡ አንበጣ ፡ አላ ቸው ፡

ወወሀብዎሙ ፡ ሥልጣነ ፡ ይኩኑ ፡ ከመ ፡ አቃርብት ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

መልክዓ ፡ አንበጣ ፡ ላላቸው ፡ ለሠራዊቱ ፡ መልክዓ ፡ አቃርብት ፡ እንዳላቸው ፡ ይሆ ኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጧቸው ።

፬ ፤ ወአዘዝዎሙ ፡ ከመ ፡ ኢያማስኑ ፡ ሣዕረ ፡ ወኢ ሐመልማለ ፡ ወኢኵሎ ፡ ዕፀ ፡

ሣሩን ፡ ቅጠሉን ፡ እህሉን ፡ ተክሉን ፡ እን ዳያጠፉ ፡ አታጥፉ ፡ አሏቸው ፡

ዘእንበለ ፡ ለሰብእ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ማኅተመ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ፍጽሞሙ ።

በግንባራቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካልተጻፈባቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ያልተ ጻፈባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፫ ።

፭ ፤ ወአዘዝዎሙ ፡ ከመ ፡ ኢይቅትልዎሙ ፡

እሊያን ፡ ቅሉ ፡ እንዳይገሏቸው ፡ አትግ ደሉ ፡ አሏቸው ፡

ዳእሙ ፡ ከመ ፡ ያሕምምዎሙ ፡ ኅምስተ ፡ አውራኀ ፡

አምስት ፡ ወር ፡ መከራ ፡ ያጸኑባቸው ፡ ዘንድ ፡ እንጅ ፡ መንፈቁ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ አይደለም ፡ ቢሉ ፡ አንዱን ፡ ወር ፡ መጡ ፡ ሲባሉ ፡ ይቆያሉ ። አንድም ፡ መጥተው ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ይታገሣሉ ፡

ወሕማሞሙሰ ፡ ከመ ፡ ሕማመ ፡ ዐቅራብ ፡ ሶበ ፡ ይነ ድፍ ፡ ሰብአ ።

በሰው ፡ የሚያመጡትም ፡ መከራ ፡ ጊንጥ፡ በነደፈ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያቅበዘብዝ ፡ እንደ ዚያ ፡ የሚያቅበዘብዝ ፡ ነው ።

፮ ፤ ወበውእቶን ፡ መዋዕል ፡ የኀሥሥ ፡ ሰብእ ፡ መዊተ ፡

በዚያ ፡ ወራት ፡ ሰው ፡ ሊሞት ፡ ይወዳል ፡

ወኢይረክብ ፡

አያገኝም ።

ወይፈቱ ፡ ይሙት ፡ ወይትኀጣእ ፡ እምኔሁ ፡ መዊት ።

ሊሞት ፡ ይወዳል ፡ ሞት ፡ ከእሱ ፡ ይር ቃል ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴ ፡ ፴፱ ።

፯ ፤ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ራእዮሙ ፡ ለእልክቱ ፡ አና ብጥ ፡ ከመ ፡ አፍራስ ፡ ዘድልዋን ፡ ለፀብዕ ፡ ይመስሉ ፡

መልክዓ ፡ አናብጥ ፡ ያላቸው ፡ ሠራዊቱ ፡ መልክዓ ፡ አፍራስ ፡ እንዳላቸው ፡ ናቸው ፡ ይመስላሉ ፡ ለሰልፍ ፡ ተጸርረው ፡ ያሉ ፡

ወውስተ ፡ ርእሶሙ ፡ ቦሙ ፡ ቀጸላ ፡ በአምሳለ፡ ወርቅ፡

በራሳቸው ፡ የወርቅ ፡ ቀጸላ ፡ አድርገዋል ፡ አለ ፡ ትርፍ ፡ አላቸው ፡

ወገጾሙ ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ።

መልክዓ ፡ ሰብእ ፡ እንዳላቸው ፡ ናቸው ፡ ኢዮ ፡ ፱ ፡ ፩ ።

፰ ፤ ወሥዕርቶሙ ፡ ከመ ፡ ሥዕርተ ፡ አንስት ፡

መልክዓ ፡ አንስት ፡ አላቸው ፡

ወስነኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ስነነ ፡ አናብስት ፡

መልክዓ ፡ አናብስት ፡ አላቸው ፡

፱ ፤ ወቦሙ ፡ ጌራ ፡ ከመ ፡ ጌራ ፡ ኀጺን ፡

የትርፍ ፡ ትርፍ ፡ አላቸው ፡

ወድምፀ ፡ እገሪሆሙ ፡ ከመ ፡ ድምፀ ፡ ሠረገላ ፡ ብዙኅ ዘያረውጹ ፡ አፍራስ ፡ ውስተ ፡ ቀትል ።

ከግዘፋቸው ፡ የተነሣ ፡ የእግራቸው ፡ ኮቴ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚገቡ ፡ አፍራስ ፡ እንደ ሚስቡት፡ ሠረገላ ፡ መንኰራኵር፡ነው ፡ ከ ሩቅ፡ ነጐዶ ፡ እንዲሰማ፡ ከሩቅ፡ ይሰማል።

፲ ፤ ወቦሙ ፡ ዘነብ ፡ ከመ ፡ ዘነበ ፡ አቅራብ ፡

እንደ ፡ ጊንጥ ፡ ያለ ፡ ጅራት ፡ አላቸው ፡



ወውስተ ፡ ዘነቦሙ ፡ ቦሙ ፡ ቅንዋት ፡ በዘቦቱ ፡ ይነ ድፍዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ኅምስተ ፡ አውራኀ ።

በጅራታቸውም ፡ አምስት ፡ ወር ፡ ሰውን ፡ የሚወጉበት ፡ መውጊያ ፡ አላቸው ።


፲፩ ፤ ወቦሙ ፡ ንጉሥ ፡ መልአከ ፡ ቀላይ ፡ ወስሙ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አብዶን ፡ ወበፅርዕ ፡ አጵልዮን፡ ወበቅ ብጥ ፡ አርማቅጦን ፡ ወዐረብ ፡ ስናሴር ፡ ወበግዕዝ ፡ ማሕጐሊ ፡

በከተማ ፡ ነግሦ ፡ የሚወጣ ፡ ንጉሥ ፡ አላ ቸው ፡ በዕብራይስጥ ፡ አብዶን ፡ ይባላል ፡ በፅርዕ ፡ አጵልዮን ፡ በቅብጥ ፡ አርማቅ ጦን ፡ በዐረብ ፡ ስናሴር ፡ በግዕዝ ፡ ማ ሕጐሊ፡ ይባላል ። አንድም ፡ (ወሶበ ፡ ጠቅ ዐ)፡በአምስተኛው፡መንፈቅ፡አምስተኛው፡ መልአክ፡ ሥራውን፡ በሠራ ፡ ጊዜ፡ (ወረደ፡ ኮከብ) ፡ መልአክ ፡ ነው፡ ሥራውን ፡ ሠራ፤ (ወተውህበ ፡ ሎቱ) ፡ የደቂቀ ፡ ያፌትን ፡ ከተማ ፡ በር ፡ የሚከፍትበት ፡ ቍልፍ ፡ ተሰጠው ፡ አለ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፡ (ወዐርገ) ፡ ከደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ከተማ ፡ ሠራ ዊት ፡ በዝቶ ፡ ወጣ ፡ ጢስ ፡ ከጕድጓዱ ፡ በዝቶ ፡ እንዲወጣ ፡ ( ታሪክ ) ፡ እስክን ድር ፡ ንጉሡ፡ ሲንገና ፡ ንጉሠ ፡ ህንድን ፡ ወግቶ ፡ ሲመለስ ፡ ከደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ከተ ማ ፡ ደረሰ ፡ ይህ ፡ የደቂቀ ፡ ያፌት፡ ከተማ፡ ዙሪያው ፡ ገደል ፡ ነው ፡ በሩ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እየዞረ ፡ ሲያይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘ ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ አነዋወር ፡ እንደ ፡ ምን፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ የፀነሰች ፡ ሴት ፡ አምጥተው ፡ በመካከል ፡ አስተኝ ተው ፡ ቅቤ ፡ ቀብተው ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ እሳት ፡ ያነዳሉ ፡ ፅንሱ ፡ እየቀለጠ ፡ ይወ ርዳል ፡ ያን ፡ እየተቀበሉ ፡ ለግንባራቸው ፡ ለጋሻቸው ፡ ለጦራቸው ፡ ለመሣሪያቸው ፡ ይቀቡታል ፡ ይህን ፡ ያስደረገ ፡ ሰይጣን ፡ በሄዱበት ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ እንዲያደርጉ ፡ እንጅ ፡ ድል ፡ እንዲነሡ ፡ አያደርጋቸ ውም፡ አለው ፡ አሁንስ ፡ አሉን ፡ አለው ፡ ሰባት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ዘምተው ፡ ሰባት ፡ አህጉር ፡ ያህል ፡ ወግተው ፡ ተመልሰው ፡ ገብተዋል ፡ አለው ፡ በሩን ፡ ቢሰፍረው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ ሆነ ፡ ለመዋ ጋት ፡ ቢጠበው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ብዙ ፡ እንጥረኛ ፡ ይከተለው ፡ ነበረና ፡ የአራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ ምስል ፡ አስቀርጾ ፡ በበሩ ፡ ዘግቶባቸው ፡ ሂዷል ፡ መልአክ ፡ በዚያ ፡ አድሮ ፡ ሲጠብቃቸው ፡ ይኖራል ፡ በአምስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ መልአክ ፡ ያን ፡ ሰብሮ ፡ ያስወጣቸዋል ፡ መጥተው ፡ ያጠፉሉ ፡ (ወከደኖ) ፡ ምድሩን ፡ አለበ ሰው ፡ (ወኮነ ፡ ከመ ፡ ደመና) ፡ ብዛቱን ፡ መናገር፡ ነው ፡ (ወእምነ፡ ውእቱ)፡ እግረኛ፡ ከፈረሰኛ ፡ ተለየ ፡ እንደ ፡ ጠዳ ፡ ሲደርስ ፡ እግረኛ ፡ ከፈረሰኛ ፡ ተለይ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ፡ ይነግራል ፡ (ወወሀብዎሙ) ፡ ለሠራዊቱ ፡ እንደ ፡ አለቆች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣ ንን ፡ ሰጥዋቸው ፡ (ወአዘዝዎሙ)፡ ሣሩን ፡ ቅጠሉን፡ እህሉን ፡ ተክሉን፡ እንዳያጠፉ፡ አታጥፉ ፡ አሏቸው ፡ (ዘእንበለ ፡ ለሰብእ) ፡ በግንባራቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልተጻፈባቸውን ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ካልተ ጻፈባቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ (ወአዘዝ ዎሙ) ፡ እሊያን ፡ ቅሉ ፡ እንዳይገሏቸው ፡ አትግደሏቸው ፡ አሏቸው ፡ (ዳዕሙ፡ ከመ ፡ ያሕምምዎሙ) ፡ አምስት ፡ ወር ፡ መከራ ፡ ያጸኑባቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ (ወሕ ማሞሙሰ) ፡ የሚያመጡትም ፡ መከራ ፡ ጊንጥ ፡ በነደፈ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያቅበዘብዝ ፡ እንደዚያ ፡ የሚያቅበዘብዝ ፡ ነው ፡ (ወበ ውእቶን) ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ሰው ፡ ሊሞት፡ ይሻል ፡ (ወኢይረክብ) ፡ አያገኝም ፡ (ወ ይፈቱ) ፡ ሊሞት ፡ ይወዳል ፡ ሞት ፡ አይገ

www.ethiopianorthodox.org

ኝም፡(ወይትኀጣእ)፡ ሞት፡ ይታጣል፡(ወከ
መዝ ፡ ውእቱ) ፡ የሠራዊቱ ፡ ግርማ ፡ እን

ዲህ ፡ ነው ፡ (ከመ ፡ አፍራስ ፡ ዘድልዋ
ን) ፡ ተቀልቦ ፡ ተገርቶ ፡ ለሰልፍ ፡ ተፀ



የፀነሰችውን ፡ ሴት ፡ አሥረው ፡ እሳት ፡ እንዳነደዱባት ።

ራእየ ፡ ዮሐንስ ። 

ርሮ ፡ እንዳለ ፡ መዝሐት ፡ ፈረስ ፡ ናቸው፤
መዝሐት ፡ ፈረስ ፡ ይመስላሉ ፡ (ወው
ስተ ፡ ርእሶሙ) ፡ በራሳቸው ፡ የወርቅ ፡
ቀጸላ ፡ አሥረዋል ፡ አለ ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፡
ደፍተዋል ፡ (ወገጾሙ) ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡
(ወሥዕርቶሙ) ፡ ፀጕራቸውን ፡ ወረዳ ፡
ተሠርተዋል ፡ (ወስነኒሆሙ) ፡ ያለቆቹ ፡
ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ነገሥታቱ ፡ ነው ፡
(ወቦሙ ፡ ጌራ ፡ ከመ ፡ ጌራ ፡ ኀጺን) ፡ የብ
ረት ፡ ራስ፡ ቍር ፡ ደፍተዋል፡ (ወድምፀ ፡
እገሪሆሙ) ፡ ከብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ የእ
ግራቸው ፡ ኮቲ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚገቡ ፡
አፍራስ ፡ እንደ ፡ ሚስቡት ፡ ሠረገላ ፡
መንኰራኵር ፡ ድምፅ ፡ ነው ፡ (ወቦሙ ፡
ዘነብ) ፡ ለሠራዊቱ ፡ እንደ ፡ አለቆች ፡ ያለ፡
ጓዝ ፡ አላቸው ፡ (ወውስተ ፡ ዘነቦሙ) ፡ የ
ጓዝ ፡ ጓዝ ፡ አላቸው ፡ (ወቦሙ) ፡ አም
ስት ፡ ወር ፡ ሰውን ፡ እየወጉ ፡ የሚጥሉ
በት ፡ (ወቦሙ ፡ ንጉሥ)፡ በከተማ ፡ ነግሦ ፡
የወጣ ፡ ንጉሥ ፡ አላቸው ፡ ንጉሥ ፡ ገለው፡
ንጉሥ ፡ አንግሠው ፡ ይወጣሉና ። አንድ
ም ፡ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡
ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ከሲኦል ፡ ሲወጡ ፡
ያያቸው ፡ ረቂቃን ፡ አጋንንት ፡ እመቤታ
ችን ፡ ከባሕር ፡ ሲወጡ ፡ ያየቻቸው ፡ ግዙ
ፋን፡አጋንንት፡ናቸው፡ እንደፊተኛው፡ እን
ደ ፡ሰበድአት፡ ያወርዳል፡ ነገሥተ ፡ ፋርስ ፡
ቢሉ ፡ እንደ ፡ ሁለተኛው ፡ እንደ ፡ ደቂቀ ፡
ያፌት ፡ ያወርዳል ። አንድም ፡ (ወሶበ ፡ ጠ
ቅዐ) ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ አም
ስተኛው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ በሠራ ፡
ጊዜ ፡ (ወረደ) ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡ መጣ ፡ (ጥቅ) ፡
ወበሳድስ፡ ወርኀ ፡ ተፈነወ፡ ገብርኤል ፡ መ
ልአክ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡
(ወተውህበ ፡ ሎቱ) ፡ ቀላይ፡ እመቤታችን፡
አንቅዕት፡ ጀሮዎቿ፡መራኁት፡ ብሥራት ፡
ለእመቤታችን ፡ ብሥራት ፡ የሚያበሥር
በት ፡ ሥልጣን ፡ ተሠጠው ፡ (ወዐርገ ፡
ጢስ ፡ ከመ ፡ ጢሰ ፡ እቶን) ፡ በንፍሓተ ፡
እስትንፋስ ፡ እሳት ፡ ከዕንጨት ፡ ጋራ ፡
በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ልምላሜ ፡ ጢስ፡
እንዲወጣ ፡ ያለ፡ ዘርዕ፡ ያለ፡ ሩካቤ፡ በግብ
ረ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡ሥጋ ፡ ሰማያዊ፡ ቃልን፡
ተዋሐደ ፡ (በተዋሕዶተ ፡ ቃል ፡ ተከፈለ ፡
ቢል ፡ አንድ ፡ነው ፡ (ወከደኖ ፡ ሥጋ) ፡
ትስብእት ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ። ፀሓይ ፡
ቃልን፡ሠወረው፡ (ጥቅ)ወበከመ፡ኮነ፡እንከ፡
ሰይጣን ፡ በጕኅሉት ፡ ተኀብአ ፡ ውስተ ፡
ሥጋ ፡ ከይሲ ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ድኅነትነ ፡
በተሠውሮተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘ
መድነ ፡ ወሠወሮ ፡ እምኔነ ፡ እንዲል ።
(ወኮነ ፡ ከመ ፡ ደመና) ፡ ከባሕር ፡ ርጡብ ፡
ጢስ ፡ ከየብስ ፡ ይቡስ ፡ ጢስ ፡ በንፍሓተ ፡
ነፋስ፡ እየተቋጠረ ፡ ወጥቶ፡ አንድ ፡ ደመ
ና ፡ እንዲሆን፡ (ጥቅ)፡ ወኮኑ፡ አሐደ ፡ ደመ
ና፡ እንዲል ፡ ርጥበት ፡ ልምላሜ ፡ ያለው፡
ሥጋ ፡ (ትስብእት ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።
ርጥበት ፡ ልምላሜ ፡ ከሌላው ፡ ቃል ፡
ጋራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡
ሆነ ። አንድም ፡ (ወሶበ ፡ ጠቅዐ) ፡ አምስ
ተኛው፡መልአክ፡ሥራውን፡ ሠራ፡ በሠራ ፡
ጊዜ፡(ወረደ፡ኮከብ)፡ዮሐንስ፡መጥምቅ፡ ከእ
ግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ታዝዞ ፡ መጣ፡ (ጥቅ)፡
ወሀሎ፡አሐዱ፡ብእሲ፡ ዘ ተፈነወ፡እምኀበ ፡
እግዚአብሔር፡ዘስሙ፡ዮሐንስ፡እንዲል፡(ወ
ተውህበ፡ ሎቱ)፡ ጌታን፡ የሚያጠምቅበት ፡
ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፡ (ወዐርገ ፡ ጢስ) ፡
ዐርገ ፡ ለሁለቱም ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ ተጠ
ምቆ ፡ ከውኃው ፡ ሲወጣ ፡ መንፈስ ፡ ቅ
ዱስ ፡ ግዘፍ ፡ ባለው ፡ መልክዐ ፡ ርግብ ፡
አምሳል ፡ ከረቂቅ ፡ ባሕርዩ ፡ ተገለጸ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እሳት ፡ ከዕንጨት ፡ ጋራ፡ በተዋሐደ ፡
ጊዜ ፡ በግዙፍ ፡ ዕንጨት ፡ ምክንያት ፡
ከረቂቅ ፡ እሳት ፡ ጢስ ፡ እንዲወጣ ፡
(ወከደኖ) ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀበሓይ ፡
ቃል ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡
(ወኮነ) ፡ የሀብቱን ፡ ብዛት ፡ መናገር ፡
ነው ። አንድም ፡ አብ ፡ በደመና ፡ ዝንቱ ፡
ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ አሰምቶ ፡ የባሕ
ርይ ፡ ልጅነቱን ፡ እንደ ፡ መሰከረ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስም፡ በርግብ፡ አምሳል፡ ወርዶ ፡
በራሱ ፡ ላይ ፡ በመቀመጡ ፡ የባሕርይ ፡
ልጅነቱን ፡ መሰከረ ። አንድም ፡ (ወሶበ ፡
ጠቅዐ) ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡
መጣ ፡ (ጥቅ) ፡ ወፃእኩ ፡ እምአብ ፡ ወመ
ጻእኩ ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወአነ ፡ ተፈኖኩ፡
እንዲል ፡ (ወረደ) ፡ በመስቀል ፡ ነፍሱን ፡
ከሥጋው ፡ ለይቶ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡
ሲኦል ፡ ሄደ፡ (ወተውህበ ፡ ሎቱ) ፡ ለሐራ
ዊ ፡ የጌታን ፡ ጎን፡ የሚወጋበት፡ ጦር ፡ ሥ
ልጣን ፡ ተሰጠው ፡ (ወዐርገ ፡ ጢስ) ፡ ከጌ
ታ ፡ ጎን ፡ ትኩስ ፡ ደም ፡ ጥሩ ፡ ውኃ ፡
ፈሰሰ ፡ ጢስ ፡ ከጕድጓዱ፡ በዝቶ ፡ እንዲወ
ጣ ፡ (ወከደኖ) ፡ ፀሓይ ፡ ቃልን ፡ አለ
በሰው ። አንድም ፡ ወርዶ ፡ ምድሩን ፡
አለበሰው ፡ (ወኮነ ፡ ከመ ፡ ደመና) ፡ ቀ
ስተ ፡ ደመና ፡ ነው ፡ አራት ፡ ኅብር ፡ አለ
ው ፡ ነጭ ፡ ቀይ ፡ ብጫ ፡ ጥቁር ፡ አራቱ ፡
ባሕርያት፡ እንዳልተያዩበት ፡ ለማጠየቅ ፡
ትኩስ፡ ደም፡ ጥሩ፡ ውኃ፡ ሙቀት፡ ትንታ፡
ያላቸው ፡ ሁነው ፡ ፈሰዋልና ፡ ከዚያው
ም፡ ነጩና፡ ቀዩ፡ ጎልቶ፡ ይታያል ፡ እንደ ፡
ለ ፡ ፊደል ፡ ሁኖ ፡ ፈሷልና ፡ (ወእምነ ፡
ውእቱ ፡ ጢስ) ፡ ከጎኑ ፡ በፈሰሰ ፡ ውኃ ፡
ተጠምቀው ፡ ምእመናን ፡ ከመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ተወልደው ፡ ከብረው ፡ ታዩ ።
ሐተታ ፡ አንበጣ ፡ አላቸው ፡ ለአንበጣ ፡

ክንፍ ፡ አለው ፡ ክንፈ ፡ ጺጋ ፡ አላቸውና ፡
በፋጨት ፡ ይጣራል ፡ በስብከት ፡ ይጣራ
ሉና ፡ አንዱ ፡ የወደቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክ
ንፍ ፡ ለክንፍ ፡ ተደጋግፎ ፡ ይዞት ፡ ይሄ
ዳል ፡ አንዱ ፡ ቢደክም ፡ አንዱ ፡ ያጸና
ዋል ፡ ካንዱ ፡ የቀረውን ፡ አንዱ ፡ ይፈ
ጽመዋል ፡ (ጥቅ)፡ ለእመ፡ ወድቀ ፡ አሐዱ፡
አሐዱ ፡ ያነሥእ ፡ እኁኒ ፡ ዘይትራዳእ ፡
እኁሁ ፡ ከመ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ባ ፡ ጥቅም ፡
ወፈነዎሙ ፡ በክልኤቱ ፡ እንዲል ፡ አን
በጣ ፡ ከጕድጓዱ ፡ በዝቶ ፡ ይወጣል፡ በዝ
ተው ፡ ይወጣሉና ፡ በየደረሰበት ፡ ወድቆ፡
ወድቆ ፡ ይቀራል ፡ በየደረሱበት ፡ ወድ
ቀው ፡ ወድቀው ፡ ይቀራሉና ፡ ዘአልቦ ፡
ንጉሥ ፡ ይለዋል ፡ አልብነ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእ
ንበለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይላሉና ፡ አን
በጣ ፡ መጥቆ ፡ ይበራል ፡ ተመስጦ ፡ አላ
ቸውና ፡ (ልዕልና ፡ ነፍስም ፡ ቢል ፡ አንድ፡
ነው) ፡ (ወወሀብዎሙ ፡ ይኩኑ) ፡ እንደ ፡
ሐዋርያት ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥዋቸው ፡
ሐተታ ፡ አቃርብት ፡ አላቸው ፡ ጊንጥ ፡
በአፍዋም ፡ በጅራቷም፣ ትናደፋለች፤ ሐዋ
ርያትም ፡ በወዲሁ ፡ የፈረዱት ፡ በወዲ
ያው፡ አይገሠሥባቸውምና፡ ዘዐሰርክሙ ፡
በምድር ፡ ይኩን ፡ዕሱረ ፡ በሰማያት ፡ ወ
ዘፈታሕክሙ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ፍቱሐ ፡
በሰማያት ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ላዕለ ፡
አቃርብት፡ ይላል፡ በአጋንንት ፡ ላይ፡ ሥል
ጣንን፡ ሰጥዋቸው ፡ (ጥቅ) ፡ ወሀብኩክሙ፡
ሥልጣነ ፡ ትኪዱ ፡ ላዕለ ፡ አቃርብት ፡
ወዲበ፡ ኵሉ፡ ኃይለ፡ ጸላኢ፡ እንዲል ፡ (ወአ
ዘዝዎሙ)፡ ሣዕረ፡ አሪትን፡ ወሐመልማለ ፡
ወንጌልን፡ አታጥፉ፡ አሏቸው፡ (ጥቅ) ፡ አስ
ተጋብእ፡ሣዕረ፡ደብር፡ ወእምክልኤሆሙ ፡
ሐመልማለ ፡ ዘርዕ ፡ እንዲል ፡ ማስጠበቃ
ቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ። (ወኢኵሎ፡ ዕፀ)፡



ሰባቱን ፡ ዕፀዋት ፡ አታጥፉ ፡ አሏቸው ።
ዕፀ ፡ ታቦት ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡
ዕፀ ፡ ሜሮን ፡ ዕፀ ፡ ሥርናይ ፡ ዕፀ ፡ ወይን ፡
ዘጠኙ ፡ ዕፀወ ፡ ዕጣን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
(ዘእንበለ ፡ እለ ፡ አልቦሙ) ፡ በገጸ ፡ ልቡ
ናቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካልተጻፈ
ባቸው ፡ ሰዎች፡ በቀር፡ ያልተጻፈባቸውን፡
ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ (ወአዘዝዎሙ) ፡
እሊያን፡ ቅሉ ፡ አውግዘው ፡ እንዳይለይዋ
ቸው፡ አትለይዋቸው፡ አሏቸው፡ (ዳዕሙ ፡
ከመ፡ ያሕምምዎሙ)፡ ዘመነ፡ ሥጋዌ ፡ እስ
ኪፈጸም፡ ቀኖና፡ እየሰጡ ፡ መከራ ፡ ያጸኑባ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ እንጅ ፡ (ጥቅ) ፡ ተሠርዐ ፡
ዓለም ፡ ለ኎በ ፡ ዐሠርቱ ፡ ክፍል ፡ ወበጽ
ሐ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ወተርፈ ፡ መንፈቀ ፡
ዐሥር ፡ እንዲል፡ አጽኑባቸው፡ አሏቸው ፡
(ወሕማሞሙሰ) ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ በቀኖና ፡
የሚያመጡትም ፡ መከራ ፡ ሐዋርያት ፡
እንደሚያመጡት ፡ መከራ ፡ ነው ። (ወበ
ውእቶን ፡ መዋዕል) ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡
ሰው ፡ በሰማዕትነት ፡ ሊሞት ፡ ይሻል ፡
አያገኝም ፡ በሰማዕትነት ፡ ሊሞት ፡ ይወ
ዳል ፡ በሰማዕትነት ፡ መሞት፡ ከእሱ፡ ይታ
ጣል ፡ ሁሉ ፡ አማኒ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ (ወከ
መዝ ፡ ውእቱ) ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
ምሥጢር ፡ አስተያየት ፡ እንዲህ ፡ ነው ።
(ከመ ፡ አፍራስ) ፡ መናፍቃንን ፡ ለመር
ታት ፡ ተፀርረው ፡ እንዳሉ፡ እንደ ፡ መም
ህራኑ ፡ ምስጢር ፡ አስተያየት ፡ ነው ።
አንድም ፡ የመምህራኑ ፡ ምስጢር ፡ አስተ
ያየት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ለፀቢዐ ፡ አጋንን
ት ፡ ተፀርረው ፡ ያሉ ፡ ባሕታውያን ፡ እን
ደሚያዩት ፡ ምስጢር ፡ ነው ፡ (ወውስተ ፡
ርእሶሙ ፡ ቦሙ) ፡ በአእምሯቸው ፡ በን
ጽሐ ፡ ልቡና ፡ የሚገለጽ ፡ ብዙ ፡ ምስ
ጢር ፡ አለ ፡ ሥላሴን ፡ መላእክትን ፡ በ

ሚያዩበት ፡ በንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ቢል ፡ አን
ድ ፡ ነው ፡ (ወገጾሙ ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ) ፡
በሥላሴ ፡ ፊት ፡ በባለሟልነት ፡ መገለጻ
ቸው፡ ሃይማኖታቸውን፡ በሰው ፡ ፊት፡ ገል
ጸው፡ እንደ፡ መመስከራቸው፡ ነው፡ (ጥቅ)፡
ዘሰ ፡ አምነኒ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ አነኒ ፡
አእምኖ ፡ በቅድመ ፡ አቡየ ፡ ዘበሰማያት ፡
ወዘሰ ፡ ክሕደኒ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ አነኒ ፡
እክሕዶ ፡ በቅድመ ፡ አቡየ ፡ ዘበሰማያት ፡
እንዲል ፡ (ወሥዕርቶሙ) ፡ ለመምህራኑ ፡
እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ያለ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር፡
አላቸው ፡ ሐተታ ፡ ሥዕርት ፡ አላቸው ፡
ጠጉር ፡ ለራስ ፡ ጌጥ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደቀ ፡
መዝሙርም ፡ ለመምህሩ ፡ ጌጥ ፡ ነውና ።
ጠጉር ፡ ያደገው ፡ እየተላጨ ፡ ያላደገው ፡
እያደገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደቀ ፡ መዝሙርም ፡
ያላጠናው ፡ እየገባ ፡ ያጠናው ፡ እየወጣ ፡
ነውና ፡ አንስት ፡ አላቸው ፡ ሐዋርያትን ፡
የሴት ፡ ፀብዋ ፡ በአፍዋ ፡ ነው ፡ ሐዋርያ
ትም ፡ ሲያስተምሩ ፡ በአፋቸው ፡ ይሞታ
ሉና ፡ ሴት ፡ ፀንሳ ፡ ወልዳ ፡ በወተት ፡ በፍ
ትፍት፡እንድታሳድግ፡ ምእመናንን፡በትም
ህርት ፡ ፀንሰው ፡ በሃይማኖት ፡ ወልደው ፡
በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ ያሳድጋሉና ፡ (ወስ
ነኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ስነነ ፡ አናብስት)፡ የደቀ፡
መዛሙርቱ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ መምህ
ራኑ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። አንድም ፡ የመም
ህራኑ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ሥ
ልጣን ፡ ነው ፡ (ወቦሙ ፡ ጌራ ፡ ከመ ፡
ጌራ ፡ ኀጺን ፡ )ለመምህራኑ ፡ ጽኑ ፡ ሥል
ጣን ፡ አላቸው ፡ (ወድምፀ ፡ እገሪሆሙ) ፡
የደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስብከት ፡ ትምህርት፡
ለፀቢአ ፡ አጋንንት ፡ እንደሚፋጠኑ ፡
እንደ ፡ መምህራኑ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፡
ሐተታ ፡ አፍራስ ፡ አላቸው ፡ መምህራ
ንን ፡ ፈረስ ፡ ያሸከሙትን ፡ እንዲሸከም ፡

www.ethiopianorthodox.org

መምህራንም ፡ በሕዝቡ ፡ የተፈረደውን ፡ ፍዳ ፡ ኃጢአት ፡ ይቀበላሉና ፡ (ጥቅ) ፡ አንትሙ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ካህናት ፡ ትጸውሩ ፡ አበሳሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲል፤ (መናፍቃንን ፡ ለመርታት ፡ ቢል ፡ ይሆናል ) ፡ (ወቦሙ ፡ ዘነብ) ፡ ለመምህራኑ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ያለ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አላቸው ፡ (ወውስተ ፡ ዘነቦሙ) ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ እስኪፈጸም ፡ እየዞሩ ፡ ሰውን ፡ የሚያሳምኑበት ፡ የሚያስተምሩበት ፡ የደቀ ፡ መዝሙር ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አላቸው ፡ (ወቦሙ ፡ ንጉሥ ፡ መልአከ ፡ ቀላይ) ፡ በዮርዳኖስ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅነቱን ፡ አስመስክሮ ፡ የወጣ ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ አላቸው ፡ (ወስሙ) ፡ አይሁድ ፡ አብድ ፡ ይሉታል ፡ (ወበዕርዕ) ፡ በዕርዕ ፡ አጽልዮን ፡ ይሉታል ፡ (ጥቅ) ፡ መልአኮሙ ፡ ለአጋይዶን ፡ እንዲል ፡ (ወበቅብጥ) ፡ በቅብጥ ፡ አርማቅጦን ፡ ይሉታል ፡ መልአከ ፡ ርቀት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መምህረ ፡ ርቀትም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ (ወበዐረብ) ፡ በዐረብ ፡ ስናሴር ፡ ይባላል ፡ ስም፡ ሠናይ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ወበግዕዝ) ፡ በግዕዝ ፡ የሞት ፡ሞት ፡ ይባላል ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፲፪ ፤ ወበዝ ፡ ኀለፈት ፡ አሐቲ ፡ ሕማም ፡ ወተርፈ ፡ ክልኤ ፡ ሕማም ፡

አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምነ ፡ ዘተርፈ ፡ ቃለ ፡ መጥቅዖሙ፡ ለሠለስቱ ፡ መላእክት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከሦስቱ፡ መከራ ፡ አንዲቱ ፡ መከራ ፡ በዚህ ፡አለፈች ፡ ሁለት ፡ መከራ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ፲፫ና ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ።

፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ሳድስ ፡ መልአክ ፡

በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ስድስተኛው ፡ መልአክ፡ ሥራውን ፡ ሠራ፡ በሠራ፡ ጊዜ ።

ሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ አሐደ ፡ እምነ ፡ አቅርንተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘወርቅ ፡ ዘቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ለእግዚአብሔር።

እምን ፡ በ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጌትነቱ ፡ በሚታወቅበት ፡ ዘወርቅ ፡ ጽሩይ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረድበት ፡ በዓለመ ፡ መላእክት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ አቅርንት ፡ አለው፡ ዓለመ ፡ መላእክትን ፡ ምዕዙን ፡ ነውና ፡ ከአቅርንተ ፡ ምሥዋዑ ፡ ቃል ፡ ይሰማ ፡ እንደ ፡ ነበረ ። አንድም ፡ ቃለ ፡ አሐዱ ፡ እምአቅርንተ ፡ ምሥዋዕ ፡ በዓለመ፡ መላእክት ፡ ካሉ ፡ መላእክት ፡ ያንድ ፡ መልአክ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ፡ ም ፡ ፰ ፡ ፫ ። ዘፀአ ፡ ፴ ፡ ፩ ።

፲፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ለዝክቱ ፡ ሳድስ ፡ መልአክ ፡ ዘያጸንዕ ፡ መጥቅዐ ፡

ሥራውን ፡ የሚሠራ ፡ ስድስተኛውን ፡ መልአክ ፡ ሰማዕኩ ፡ ወይቤሎ ፡ ሰማዕኩ ፡ እንዘ ፡ ይብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ እንዲህ ፡ ሲለው ፡ ሰማሁ ፡

ፍትሐሙ ፡ ለእልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ እሡራን ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ዐቢይ ።

በኤፍራጥስ ፡ ተግዘው ፡ ያሉ ፡ አራቱን ፡ መላእክት ፡ ፈተህ ፡ ስደዳቸው ፡ አለው ፤ ሲለው ፡ ሰማሁ ፡ (ታሪክ) ፡ ኖኅ ፡ ከመርከብ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ። አጋንንት ፡ በዝተው ፡ ሲወጡ ፡ አይቶ ፡ የእኔ ፡ ልጆች ፡ ኀዳጣን ፡ እሊህ ፡ ብዙኃን ፡ የኔ ፡ ልጆች ፡ ድኩማን ፡ እሊህ ፡ ኀያላን ፡ እንደምን ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አዘነ ፤ አይዞህ ፡ ይጋዙልህ ፡ ብሎ ፡ አራቱን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አራቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ዘጠነኛውን ፡ በመካከል ፡ እንደ ፡ ቍራኛ ፡ አድርጎ ፡ አግዟቸዋል ፡ አሥረኛውን፡ እደ ግመዋለሁ ፡ ሲል፡ ሁላችንማ ፡ ከተጋዝን ፡ ከፈቃድህ ፡ የወጣውስ ፡ ያልወጣውስ ፡ በምን ፡ ይታወቃል ፡ ብሎት ፡ ትቶታል ፡



በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ የማይሠራ ፡ ሥራ ፡ የለም ፡ ፈቶ ፡ ይሰዳቸዋል ፡ መጥተው ፡ ያጠፋሉ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፲፪ ።

፲፭ ፤ ወሶበ ፡ ፈትሐሙ ፡ ለእልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ መላእክት ፡

ባንድ ፡ ወገን ፡ ያሉትን ፡ ብቻ ፡ ቆጥሮ ፡ አርባዕቱ ፡ አለ ፡ (ደርቦ ፡ ቆጥሮ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ አራቱን፡ መላእክት ፡ፈቶ ፡ ሰደዳቸው ፡ በሰደዳቸው ፡ ጊዜ ፡

እለ ፡ ድልዋን ፡ ለሰዓት ፡ ወለዕለት ፡ ወለወርኅ ፡ ወለዓመት ፡ ከመ ፡ ይቅትሉ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ።

አንድ ፡ ሰዓት ፡ አንድ ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ ወር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከሰው ፡ ሢሦ ፡ ሢሦውን ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ያሉ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ፯ ።

፲፮ ፤ ወኍልቈ ፡ አፍራሲሆሙ ፡ ምክዕቢተ ፡ እልፍ፡ እምአእላፍ ።

የሠራዊታቸው ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

፲፯ ፤ ወከመዝ ፡ ርእየተ ፡ አፍራሲሆሙ ፡

ሠራዊቶቻቸው ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ፡

ወዘእለ ፡ ይጼዐንዎሙ ፡ ቦሙ ፡ ጌራ ፡ ዘእሳት ፡ ዘኀብረ ፡ ደርከኖ ፡

ለአለቆች ፡ ደርከኖ ፡ የሚመስል ፡ የእሳት፡ ራስ ፡ ቍር ፡ አላቸው ፡ (ትርፍ ፡ አካል ፡ አላቸው ፡ ማለት ፡ ነው ፡

ወአርእስተ፡ አፍራሲሆሙ፡ከመ፡አርእስተ፡አናብስት፡

መልክዓ ፡ አፍራስ ፡ ላላቸው ፡ ለሠራዊቱ፡ መልክዓ ፡ አናብስት ፡ አላቸው ። አንድም፡ ለሠራዊቱ ፡ መልክዓ ፡ አፍራስ ፡ እንዳላቸው ፡ ለአለቆቹ ፡ መልክዓ ፡ አናብስት ፡ አላቸው ፡ ፈቶ ፡ በሰደዳቸው ፡ ጊዜ ፡

ወይወፅእ፡ እምነ፡ አፉሆሙ፡እሳት፡ ወጢስ፡ ወተይ ።

ይዘው ፡ ቢመጡ ፡ ይወፅእ ፡ እየሠሩ ፡ ቢመጡ ፡ ወይወፅእ ፡ ከአፋቸው ፡ እሳት ፡ ጢስ ፡ ተይ ፡ ይወጣል ።

፲፰ ፤ ወእምነ ፡ ዝንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ሕማም ፡ ሞተ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ እምነ ፡ እሳት ፡ ወጢስ ፡ ወተይ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምነ ፡ አፉሆሙ ።

ከአፋቸው ፡ ከሚወጣ ፡ እሳት ፡ ጢስ ፡ ተይ ፡ በሚመጣ ፡ መቅሠፍ፡ ትከሰው ፡ ሲሦው ፡ ጠፋ ፡ ጢስ ፡ ቋዱ ፡ ሲቃጠል ፡ ተይ ፡ ከደሐራው ፡ ሲገናኝ ፡ እሳት፡ አረሩ፡ ሲመታ ፡ በግሥ ፡ ተናግሮታል ፡ እስክንድር ፡ ንጉሥ ፡ ሲንን ፡ ወግቶ ፡ ከራብዕ ፡ ዳራ ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ፡ ፋጥ፡ ንጉሠ፡ ህንድ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ያራዊት ፡ ለማዳ ፡ ነበረው ፡ አውጥቶ ፡ አፈሰሰበት ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመልሶ ፡ ብዙ ፡ አንጥረኛ ፡ ይከተለው ፡ ነበረና ፡ በዚያ ፡ ባየው ፡ አራዊት ፡ ልክ ፡ በአንበሳው ፡ የአንበሳ ፡ በነብሩ ፡ የነብር ፡ ምስል ፡ አሠርቶ ፡ ባሩዱን ፡ እየመላ ፡ አረሩን ፡ እያገባ ፡ በመንኰራኵር ፡ የሚሄድ ፡ በመዘወር ፡ የሚተኰስ ፡ አድርጎ ፡ አሠርቶ ፡ በፊት ፡ አሰልፎ ፡ ሂዶ ፡ ገጠመው ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ አውጥቶ ፡ አፈሰሰበት ፡ ወገን ፡ ወገኑን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳው ፡ ከአንበሳው ፡ ነብሩ ፡ ከነብሩ ፡ ገጠመ ፡ ፈረሰኛ ፡ በኋላ ፡ እየተከተለ ፡ መዘወሩን፡ ሲነካው ፡ እየተተኰሰ ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ፈጅቶ ፡ ድል ፡ አድርጎታልና ፡ በዚያ ፡ ግሥ ፡ ይወፅእ ፡ እሳት ፡ ወጢስ ፡ ወተይ ፡ አለ ።

፲፱ ፤ እስመ ፡ ሥልጣኒ ፡ አፍራሲሆሙ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡

በቃላቸው ፡ መቅሠፍት ፡ ይታዘዛልና ፡

ወአዝናቢሆሙ ፡ ከመ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡

ለሠራዊቱ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ያለ ፡ ጅራት ፡ አላቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወቦሙ ፡ ህየ ፡ አርእስት ፡ በዘቦቱ ፡ ይነስኩ ፡ ሰብአ ፡ ኀምስተ ፡ አውራኀ ።

አምስት ፡ ወር ፡ ሰውን ፡ እየወጉ ፡ የሚጥሉበት ፡ መውጊያ ፡ አላቸው ።

፳ ፤ ወዘተርፈ ፡ ሰብእ ፡ ድኅነ ፡ እምነ ፡ ውእቱ ፡ መቅሠፍት ፡

ከእንቢታ ፡ የቀረው ፡ ከመቅሠፍት ፡ ዳነ ።

ወቦ ፡ እለ ፡ ተኰነኑ ፡ በአምልኮ ፡ ግብረ ፡ እደዊሆሙ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ጣዖት ፡ በማምለካቸው ፡ የተጎዱ ፡ አሉ ። አንድም ፡ (ወይቤሎ ፡ ለዝክቱ) ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራ ፡ ስድስተኛውን ፡ መልአክ ፡ (ፍትሖሙ) ፡ በፈለገ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ተግዘው ፡ ያሉ ፡ አራቱን ፡ መላእክት ፡ ፈተሕ፡ ስደዳቸው ፡ ሲለው ፡ ሰማሁ ፡ የሊህ ፡ መጋዝ ፡ አይደለም ፡ መወሰን ፡ ነው ፡ እስክንድር ፡ በደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ከተማ ፡ በር ፡ የአራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ ምስል ፡ አስቀርጾ ፡ ዘግቶባቸው ፡ ሂዷል ፡ እንዳይወጡ ፡ መልአክ ፡ አድሮ ፡ ይጠብቃቸዋል ፡ በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ የማይሠራ ፡ ሥራ ፡ የለም ፡ ሰብሮ ፡ ያስወጣቸዋል ፡ መጥተው ፡ ያጠፋሉ ፡ (ወሶበ ፡ ፈትሖሙ) ፡ ለመጠበቅ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ያሉ፡አራቱን፡መላእክት፡ አሰናበታቸው፡ባሰናበታቸው፡ ጊዜ፡ ደቂቀ ፡ ያፌት፡ ከመ ፡ ይቅትሉ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ አንድ ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ ወር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከሰው ፡ሲሦውን ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ያሉ፡ ወኍልቈ ፡ አፍራሲሆሙ ፡ የፈረሰኛው ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ (ወከመዝ ፡ ርእየተ ፡ አፍራሲሆሙ፡ የሠራዊቱ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ (ያለቆች ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡(ወዘእለ ፡ ይጼዐንዎሙ) ፡ ላለቆች ፡ የብረት ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ አላቸው ፡ (ወአርእስተ ፡ አፍራሲሆሙ) ፡ የሠራዊቱ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ አለቆች ፡ ነው ፡ ያለቆች ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ነገሥታቱ ፡ ነው ፡ (ወይወፅእ ፡ እምነ ፡ አፉሆሙ) ፡ በቃላቸው ፡ ጦር ፡ ይታዘዛል ፡ (ወእምነ ፡ ዝንቱ) ፡ በቃላቸውም ፡ ከሚታዘዝ ፡ ጦር ፡ የተነሣ ፡ በሚመጣ ፡ መከራ ፡ ከሰው ፡ ሲሦው ፡ ጠፋ ፡ (እስመ ፡ ሥልጣነ ፡ አፍራሲሆሙ) ፡ የሠራዊቱ ፡ ሥልጣን ፡ በአለቆች ፡ ሥልጣን ፡ ይታዘዛልና ፡ (በቃላቸው ፡ ጦር ፡ ይታዘዛልና ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ (ወአዝናቢሆሙ) ፡ ለሠራዊቱ ፡ እንደ ፡ አለቆች ፡ ያለ ፡ ጓዝ ፡ አላቸው ፡ (ለአለቆች ፡ እንደ ፡ ነገሥታቱ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ (ወቦሙ) ፡ አምስት ፡ ወር ፡ ሰውን ፡ እየወጉ ፡ የሚጥሉበት ፡ የጓዝ ፡ ጓዝ ፡ አላቸው ፡ (ወዘተርፈ ፡ ሰብእ) ፡ ከእንቢታ ፡ የዳነ ፡ ከመቅሠፍት ፡ ዳነ ፡ እነሱን ፡ የመሰለ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ ተኰነኑ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጣዖት ፡ በማምለክ ፡ የተጐዱ ፡ አሉ ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ ሰበድአት ፡ ቢሉ ፡ እንደ ፡ መዠመሪያው ፡ እንደ ፡ አጋንንት ፡ ነገሥተ ፡ ፋርስ ፡ ቢሉ ፡ እንደ ፡ ሁለተኛው ፡ እንደ ፡ ደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ያወርዳል። አንድም ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ (ወይቤሎ ፡ ለዝክቱ) ፡ በጥምቀት ፡ ልጅነት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክሉ ፡ አራቱን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አሰናብት ፡ አለው ፡ ሐተታ ፡ አሁን ፡ ልጅነት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክሉ ፡ ሁነው ፡ አይደለም ፡ ጌታ ፡ ካልሞተ ፡ ልጅነት ፡ አይሰጥም ፡ ልጅነት፡ ካልተሰጠ፡ አይሾሙም፡ ካልተሾሙም፡ ልጅነት፡ አያሰጡምና፡እንዲህ፡ አለ፡ እንጅ ፡ (ወሶበ፡ፈትሖሙ)፡አንድ፡ ሰዓት፡ አንድ፡ዕለት፡ አንድ፡ ወር፡ አንድ፡ ዓመት፡ (ከመ ፡ ይቅትሉ) ፡ ከሰው ፡ ሲሦውን ፡ በቀኖና ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ያሉ ፡ አራቱን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ባሰናበታቸው ፡ ጊዜ ፡ (ወኍልቈ ፡ አፍራሲሆሙ) ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱ፡ቍጥር፡ብዙ፡የብዙ፡ብዙ፡ነው፤ (ወከመዝ ፡ ርእየተ ፡ አፍራሲሆሙ) ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ምስጢር ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ መምህራኑ ፡ ነው ፡ (ወዘእለ ፡ ይጼዐንዎሙ) ፡ ለመምህራኑ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰማያዊ ፡ ሥልጣን፡ አላቸው ፡ (ወአፍራሲሆሙ) ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ መምህራኑ ፡ ነው ፡ የመምህራኑ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ነው ፡ (ወይወፅእ) ፡ ይዞ ፡ ቢመጡ ፡ ይወፅእ ፡ እያሠሩ ፡ ቢመጡ ፡ ወይወፅእ ፡ በቃላቸው ፡ ስመ ፡ ሥላሴ ፡ ይነገራል ፡ (ወእምነ ፡ ዝንቱ) ፡ በቃላቸው፡ ከሚነገረው ፡ ስመ ፡ ሥላሴም፡ የተነሣ፡ ከሰው፡ ሲሦው ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ፡ (እስመ ፡ ሥልጣነ ፡ አፍራሲሆሙ) ፡ በቃላቸው ፡ ስመ ፡ ሥላሴ ፡ ይነገራልና ፡ (ወአዝናቢሆሙ ፡ ከመ ፡ አራዊተ ፡ ምድር) ፡ ለመምህራኑ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ያለ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አላቸው ፡ (ወቦሙ ፡ ህየ) ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ እስኪፈጸም ፡ ሰውን ፡ የሚያሳምኑበት ፡ የደቀ ፡ መዝሙር ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አላቸው ፡ (ወዘተርፈ ፡ ሰብእ) ፡ ከማመን ፡ የቀረ ፡ ከመቅሠፍት ፡ ዳነ ፡ በሰማዕትነት ፡ አይሞትም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ወቦ ፡ እለ ፡ ተኰነኑ) ፡ ጣዖት፡ በማምለክም፡ የተጎዱ፡ አሉ ፡



እስመ ፡ ኢነስሑ ፡

አላመኑምና ፡

አላ ፡ አቅነዩ ፡ ርእሶሙ ፡ እንዘ ፡ ይሰግዱ ፡ ለአጋንንት ፡ ወለአማልክት ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ፡ ወዘብርት ፡ ወዘዕፅ ፡ ወዘእብን ፡

(ግጥ) ፡ እንዘ ፡ ይሰግዱ ፡ ለአማልክት ፡ አቅነዩ ፡ ርእሶሙ ፡ ለአጋንንት፡ ለጣዖት፡ እየሰገዱ ፡ ራሳቸውን፡ ለአጋንንት ፡ አስገዝተዋል፡ እንጅ፡ ከወርቅ ፡ ከብር፡ ተመተው ፡ ከዕንጨት፡ ከደንጊያ ፡ ተቀርጸው ፡ ለተሠሩ ፡ ጣዖታት ፡ እየሰገዱ ፡

እለ ፡ ኢይሬእዩ ፡ ወኢይሰምዑ ፡ ወኢየሐውሩ ።

ዐይን ፡ ሳላቸው ፡ ለማያዩ ፡ ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡ ለማይሰሙ ፡ እግር ፡ ሳላቸው ፡ ለማይሄዱ ፡ ለጣዖታት ፡ እየሰገዱ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ፡ ፳፩ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳ ።

፳፩ ፤ ወኢነስሑ ፡ ዓዲ ፡ እምነ ፡ ቀትሎሙ ፡ ወእምነ ፡ ሥራያቲሆሙ ፡ ወእምነ ፡ ዝሙቶሙ ፡ ወእምነ ፡ ስርቆሙ ።

ዳግመኛም ፡ ነፍስ ፡ ከመግደላቸው ፡ ሥራይ ፡ ከማድረጋቸው ፡ ዝሙት ፡ ከመሥራታቸው ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ ከመሥረቃቸው ፡ አልተመለሱምና ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ተኰነኑ ፡ ላለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ወረደ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ዐቢይ ፡ እምሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ግሩም ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየሁ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ። አንድም ፡ ጌታ ፡

ወይትዐጸፍ ፡ ደመና ፡ ውስተ ፡ ርእሱ ፡

በራሱ ፡ ደመናውን ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ተጠምጥሟል፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ነው፡ ቢሉ ፡ ክብሩን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ቢሉ፡ የባሕርይ፡ ክብሩን ፡ መናገር፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወብሩህ ፡ ገጹ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡

ፊቱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፡ ለ ጌታ፡ ምሳሌ ፡ ቢያጣለት ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካ ኤል ፡ የተመቸ ፡ ነው ፡

ወእገሪሁ ፡ ከመ ፡ አዕማደ ፡ እሳት ።

አፍሐመ ፡ እሳት ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እግሮ ቹም ፡ እንደ ፡ አፍሐመ ፡ እሳት ፡ ናቸው፡ ትእምርተ ፡ መዓት ፡ ነው ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፪ ። ም ፡ ፬ ፡ ፫ ።

፪ ፤ ወውስተ ፡ እዴሁ ፡ ያጸንዕ ፡ መጽሐፈ ፡ ክሡተ ፡

በእጁ ፡ የተገለጸች ፡ መጽሐፍ ፡ ይዟል ፡ አለ፡ ምስጢረ ፡ ምጽአት ፡ ግፍዐ ፡ ሰማ ዕታት ፡ በቃሉ ፡ ትነገራለች ፡

ወኬደ ፡ በእግሩ ፡ እንተ ፡ የማን ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወእንተ ፡ ፀጋም ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡

በቀኝ ፡ እግሩ ፡ ባሕርን ፡ በግራ ፡ እግሩ ፡ የብስን ፡ ተረግጥዋል ፡ ጌታ ፡ አምላከ ፡ ባሕር ፡ ወየብስ፡ ነኝ፡ ይላል ፡ ቅዱስ ፡ ሚ ካኤል ፡ እስራኤልን ፡ በየብስ ፡ ያሻገርሁ ፡ ግብፃውያንን ፡ በባሕር ፡ ያሰጠምሁ ፡ እኔ፡ ነኝ ፡ ይላል ። አንድም ፡ በፈጣን ፡ ሥል ጣኑ ፡ የሐሳዊ ፡ መሢሕን ፡ ከተማ ፡ ያጠ ፋል ፡ በኅዱዕ፡ ረድኤቱ ፡ የምእመናንን ፡ ከተማ ፡ ይጠብቃል ፡ ሐተታ ፡ ባሕር ፡ አለው ፡ የሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ ከተማ ፡ ከባ ሕር ፡ ሁከት፡ እንዳይታጣ፡ ከከተማውም ፡ ሁከት ፡ አይታጣምና ። አንድም ፡ ኬደ ፡ በእግሩ ፡ እንተ ፡ የማን ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወእንተ ፡ ፀጋም ፡ ላዕለ ፡ ባሕር ፡ ብሎ ፡ ሐሳዌ፡መሢሕን፡ አለመርዳቱን፡ ምእመና ንን፡መርዳቱን፡ መናገር፡ ነው፡ ም፡ ፫፡ ፩ ።

፫ ፤ ወጸርሐ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ዘይ ጥሕር ፡

በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮሆ ፡ ተናገረ ፡ እንደሚ ያነፋ ፡ አንበሳ ፡

ወሶበ ፡ ጸርሐ፡ ተናገሩ ፡ ሰብዐቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ በበቃ ላቲሆሙ ፡ በበይነ ፡ ዘሀለዎ ፡ ይጸሐፍ ።

ጮሆ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሰባቱ ፡ መላእ ክት ፡ በየቃላቸው ፡ ተናገሩ ፡ ይጻፍ ፡ ዘን ድ ፡ ስላለው ፡ ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፴ ። ሆሴ ፡ ፲፩ ፡ ፲ ። አሞ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፬ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዘይቤሉ ፡ ሰብዐቱ ፡ ነጐድ ጓድ ፡

ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ።

ወፈቀድኩ ፡ እጽሐፎ ፡

ልጽፈው ፡ ወደድሁ ፡

ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከሰማይ ፡ ተነገረ ፡

ኅትም፡ ዘነበቡ፡ ሰብዐቱ ፡ ነጐድጓድ፡ ወኢትጽሐፍ ።

ሠውር ፡ አትናገር ፡ አትጻፍ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማሁ፡ ኅትም ፡ በልቡና ፡ ኢትጽ ሐፍ፡ በብራና ። አንድም ፡ ኅትም ፡ ለአ ዋቂዎች ፡ ኢትጽሐፍ ፡ ላላዋቂዎች ። አን ድም ፡ ኅትም ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ ኢትጽሐፍ ፡ ጊዜው ፡ ባይደርስ ፡ ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ (መላእክት ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ያልታወቁ ፡ ናቸው ። አንድም ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ፡ ሃይማኖት ፡ ፍቅር ፡ ወኀብአ ፡ ዕለተ ፡ ፍጻሜ ፡ ያላት ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ናሁ ፡ ኀቡአ ፡ ነገረ ፡ እነግረክሙ ፡ ያለው ፡ ምስጢረ ፡ አዝዋግ ፡ እንዘ ፡ ም ራቅ ፡ ከዊነ ፡ ሰብእ ። ምሥጢረ ፡ አዝዋ ግና ፡ እንዘ ፡ ምራቅ ፡ ከዊነ ፡ ሰብእስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተረክቦተ ፡ ሐሊብ፡ ወደም ፡ እምአሐዱ ፡ ጥብ ፡ ምሥ ጢረ ፡ ምጽአት ። አንድም፡ ምሥጢረ ፡ ጥምቀት፡ ምሥጢረ ፡ ዘይት፡ ምሥጢረ ፡ ሜሮን ፡ ምሥጢረ፡ ታቦት ፡ ምሥጢረ ፡

www.ethiopianorthodox.org



ሥርናይ ፡ ወወይን ፡ ምሥጢረ ፡ ንስሐ ፡ ምሥጢረ፡ ምሕረቱ፡ በምሥጢረ፡ ዘይት፡ ቦታ ፡ ምሥጢረ ፡ ክህነት ፡ ቢል፡ ይቀ ናል ፡ በማእከለ ፡ ዘመን ፡ ቢመጡ ፡ ነው ፡ ዳን ፡ ፰ ፡ ፳፮ ። ም ፡ ፲፪ ፡ ፬ ፡ ፱ ።

፭ ፤ ወውእቱስ ፡ መልአክ ፡ ዘርኢኩ ፡ ዘኬደ ፡ ውስ ተ ፡ ባሕር ፡ ወውስተ ፡ ምድር፡ አልዐለ፡ እዴሁ፡ እን ተ ፡ የማን ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

በቀኝ ፡ እግሩ ፡ ባሕርን ፡ በግራ ፡ እግሩ ፡ የብስን ፡ ተረግጦ ፡ ያየሁት ፡ መልአክ ፡ ግን ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ።

፮ ፤ ወመሐለ ፡ በዘሕያው ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡

የዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ በሚሆን ፡ በጌታ ፡ ማለ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ በሚሆን ፡ በራሱ ፡ ማለ ፡ አማንየ ፡ በርእ ስየ ፡ ሕያው ፡ አነ ፡ ብሎ ።

ዘፈጠረ ፡ ሰማየ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቱ ፡

ሰማይን ፡ በፈጠረ ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላ እክትን ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትን ፡

ወምድረ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቱ ፡

ምድርን ፡ በምድርም ፡ ያሉ ፡ዕፀው ፡ አ ዕባንን ፡ እንስሳት ፡ አራዊትን ፡ ደቂቀ ፡ አዳምን ፡ በፈጠረ ፡ በጌታ ፡ ማለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ አማንየ ፡ በርእስየ ፡ ሕያው፡ አነ ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ማለ ፡

ወባሕረ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቱ ፡

ባሕርን ፡ በፈጠረ ፡ በባሕር ፡ ያሉ ፡ ዓሣ ፡ አንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬን ፡ በራሱ ፡ ማለ ፡ ዳን ፡ ፲፪ ፡ ፯ ። ም ፡ ፮ ፡ ፲፩ ፡

፯ ፤ ወአልቦ ፡ እንከ ፡ መዋዕል ፡ ዘእንበለ ፡ መዋ ዕለ ፡ ቃሉ ፡ ለሳብዕ ፡ መልአክ ፡ ዘሀለዎ ፡ ይጥቃዕ ፡

ሥራውን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ሰባ ተኛው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ ከሚሠራ በት ፡ ዘመን ፡ በቀር ፡ የሚሠራበት ፡ ዘ መን ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ አማንየ ፡ በርእስየ ፡ ሕያው ፡ አነ ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ማለ ፡ ለመማል ፡ እጁን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ። አንድም ፡ ባይኖር ፡ ባይኖርስ ፡ ብሎ ፡ ማለ ፡

ወቦቱ ፡ የኀልቅ ፡ ምሥጢሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘአ ሰፈዎሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ ወለነቢያቲሁ ።

ለወዳጆቹ ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ ተስ ፋ ፡ ያናገረላቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጢሩ ፡ የሚፈጸምበት ፡ አለ ፡ መንግ ሥተ ፡ ሰማያት ፡ የምትወረስበት ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፭ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፩ ።

፰ ፤ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘሰማዕኩ ፡ እምሰማይ ፡

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ የሰማሁት ፡ ቃል ፡

ተናገረ ፡ ካዕበ ፡ ምስሌየ ፡

ዳግመኛ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ተናገረ ፡ አለ ፡ ለኔ ፡ ነገረኝ ፡

ወይቤለኒ ፡ ሑር ፡ ንሥአ ፡ ለእንታክቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ክሡት ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለዝክቱ ፡ መል አክ ፡ ዘኬደ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወውስተ ፡ ምድር ።

ባሕርን ፡ የብስን ፡ ተረግጦ ፡ ካለ ፡ ከሱ ፡ ከቀኝ ፡ እጁ ፡ ይችን ፡ የተገለጠች ፡ መጽ ሐፍ ፡ ሂደህ ፡ ተቀበላት ፡ አለኝ ።

፱ ፤ ወሖርኩ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ወእቤሎ ፡ ከመ ፡ የሀበንያ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡

ከመልአኩ ፡ ዘንድ ፡ ሂጄ ፡ ያችን ፡ መጽ ሐፍ ፡ ስጠኝ ፡ አልሁት ፡

ወይቤለኒ ፡ ንሥአ ፡ ወብልዓ ፡ ወለትምረራ ፡ ለከር ሥከ ፡

ንሣ ፡ ብላት ፡ ለልቡናህ ፡ ትምረርህ ፡ አት ስማማህ ፡

ወበውስተ ፡ አፉከሰ ፡ ጥዕምተ ፡ ለትኩንከ ፡ ከመ ፡ መዓር ።

ለአፍህ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ትጣፍጥህ ፡ አለኝ ፡ ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፩ ።

፲ ፤ ወነሣእክዋ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ እምነ ፡ እ
ዴሁ ፡ ለውእቱ ፡ መልአክ ፡ ወበላዕክዋ ፡

ያችን ፡ መጽሐፍ ፡ ከመልአኩ ፡ እጅ ፡ ተ
ቀብዬ ፡ በላኋት ፡

ወኮነተኒ ፡ ጥዕምተ ፡ በውስተ ፡ አፉየ ፡

ላፌ ፡ ጣፈጠችኝ ፡

ወሶበ ፡ ውኅጥክዋ ፡ አምረረታ ፡ ለከርሥየ ፡

ከበላኋት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለልቡናዬ ፡ አልተ
ስማማችኝም ። አንድም ፡ (ወውእቱ ፡
ቃል) ፡ ከወደ ፡ ሰማይ ፡ የሰማሁት ፡ ቃል ፡
ለኔ ፡ ነገረኝ ፡ ዳግመኛ ፡ ምሥጢረ፡ ምጽ
አትን ፡ ግፍዐ ፡ ሰማዕታትን ፡ ግብር ፡ ገብ
ተህ ፡ ከመላኩ ፡ ዘንድ ፡ ዕወቃት ፡ መር
ምራት ፡ አለኝ ፡ (ወሖርኩ) ፡ ከመላኩ ፡
ዘንድ ፡ ሂጄ ፡ ምሥጢረ፡ ምጽአትን ፡ ግ
ፍዐ ፡ ሰማዕታትን ፡ ግለጥልኝ ፡ አልሁት ፡
(ወይቤለኒ ፡ ንሥአ ፡ ወብልዓ) ፡ ትገለጥ
ልህ ፡ አለኝ ፡ (ወለትምረራ) ፡ ለልቡናህ ፡
ታሳዝንህ ፡ ለጊዜው ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ታሰ
ኝህ ፡ አለኝ ፡ (ወነሣእክዋ ፡ ለይእቲ ፡ መጽ
ሐፍ)፡ ምሥጢረ ፡ ምጽአትን ፡ ግፍዐ ፡ ሰ
ማዕታትን ፡ ግብር ፡ ገብቼ ፡ አወቅኋት ፡
መረመርኋት ፡ (ወኮነተኒ) ፡ ለጊዜው ፡
ደስ ፡ አሰኘችኝ ፡ (ወሶበ ፡ ውኅጥክዋ) ፡
ካወቅኋት ፡ ከመረመርኋት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡
አሳዘነችኝ፡ ምሥጢር፡ ለጊዜው፡ ሲገለጥ፡
ደስ ፡ ያሰኛል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ያሳዝናልና።

፲፩ ፤ ወይቤለኒ፡ሀለወከ፡ካዕበ፡ትትነበይ፡ለአሕዛብ ፡
ወለሕዝብ ፡ ወለበሐውርት ፡ ወለነገሥት ፡ ብዙኃን ፡

ዳግመኛም ፡ ሕዝብን ፡ አሕዛብን ፡ ታስተ
ምር ፡ ዘንድ ፡ አለህ ፡ አለኝ ፡ አሕዛብ ፡
ያለውን ፡ በሐውርት ፡ ሕዝብ ፡ ያለውን ፡
ነገሥት ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ሐተታ ፡ ካዕ
በ ፡ ለጥንተ ፡ ስብከት ፡ ነው ። አንድም ፡
የእሱን፡ ለሐዋርያት ፡ ካዕበ ፡ አለ ። አን
ድም ፡ በደሴተ ፡ ፍጥሞ ፡ ሳለ ፡ ወንድሞ
ቼ ፡ ሁሉ ፡ በየሀገረ ፡ ስብከታቸው ፡ ጸን
ተው ፡ ያስተምራሉ ፡ የእኔ፡ ማስተማር ፡
ፈቃድህ ፡ ባይሆን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢያመ
ለክት ፡ አይዞህ ፡ ሕዝብን ፡ አሕዛብን ፡
ታስተምር ፡ ዘንድ ፡ አለህ ፡ ብሎት ፡ ነበ
ረና ፡ ሀለወከ ፡ ካዕበ ፡ ትትነበይ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ ፤ ወመጠወኒ ፡ ሕለተ ፡ ወርቅ ፡ ዘመጠነ ፡ በትር ፡

ብትር ፡ የሚያህል ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ሰጠ
ኝ ፡ ሐተታ ፡ ብትር ፡ የሚቈረጥ ፡ በሰው ፡
ቁመት ፡ ልክ ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡
ነውና ፡ ዘመጠነ ፡ በትር ፡ አለ ፡

ወይቤለኒ ፡ ንሣእ ፡ ወመጥን ፡ ቤተ ፡ መቅደሰ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡

እንካ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ስፈር ፡

ወምሥዋዖ ፡

ቅድስቱን ፤
ወኀበሂ ፡ ይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡

ቅኔ ፡ መዐልቱን ፡ ስፈር ፡ አለኝ ፡ ሕዝ ፡
፵ ፡ ፫ ፡ ዘካ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡

፪ ፤ ወዐጸደሰ ፡ ጸናፌ ፡ ኅድግ ፡ ወኢትመጥን ፡

ከቅጽር ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ እሰፍ
ራለሁ ፡ አትበል ፡

እስመ፡ ተውህበት፡ ለአሕዛብ፡ በዛ፡ ሀገር፡ ቅድስት ፡

ምእመናን ፡ በዙሪያው ፡ ተሳፍረው ፡ ሊሰ
ፍሩባት ፡ ታዝዟልና ፡

ወይትካየድዋ ፡ አርብዓ ፡ ወክልኤተ ፡ አውራኀ ።

በፍጹም ፡ ቍጥር ፡ አርብዓ ፡ ወክልኤተ ፡
አውራኀ ፡ አለ ፡ የከተማ ፡ ቦታ ፡ ውድ ፡
ነውና ። አንድም ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ፡ ቤተ ፡
መቅደስ ፡ እንዳይገባ ፡ ዕወቅ ፡ (ወዐጸደሰ)፡
ከከተማው ፡ ግን ፡ አይገባም ፡ አትበል ፤
(እስመ ፡ ተውህበት) ፡ ከቢታንያ ፡ እስከ ፡
ደብረ ፡ ዘይት ፡ ተሳፍረው ፡ ሊሰፍሩባት ፡
ታዝዟልና ፡ (ዕርቅ) ፡ ከዚያ ፡ ቅዱስ ፡
ጳውሎስ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይላል ፡ ከዚህ ፡ ዮሐንስ ፡ አይገባም ፡ አለ ፡
እንደምነው ፡ ቢሉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ዮሐ
ንስ ፡ ነው ፡ አይገባም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡
ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ ከከ
ተማው ፡ ይገባል ፡ የካህናቱን ፡ ቤት ፡
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተጠራበት ፡ ብሎ
ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለው ፡ እንጅ ፡
ነገር ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡ አይገባም ፡
(ወይትካየድዋ) ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመ
ንፈቅ ፡ ተሳፍረው ፡ ይሰፍሩባታል ። አን
ድም ፡ (ንሣእ ፡ ወመጥን) ፡ ብዕለ ፡ እስራ
ኤል ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕወቅ ፡ (ወዐ
ጸደሰ)፡ ብዕለ፡አሕዛብ፡ግን፡ ጥቂት፡ ነው፡አ
ትበል ፡ (እስመ ፡ ተውህበት)፡ ብዕል ፡ ለአ
ሕዛብ ፡ ተሰጥቷልና ። አንድም ፡ እስራ
ኤል ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ዕወቅ ፡ አሕ
ዛብ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፡ ፡አትበል፡
ብዛት ፡ ለአሕዛብ ፡ ተሰጥቷልና ። አን
ድም ፡ እመቤታችን ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡
እንበለ ፡ ሩካቤ ፡ እንድትወልድ ፡ ዕወቅ ፡
ሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ግን ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡
እንበለ ፡ ሩካቤ ፡ ይወልዳሉ ፡ አትበል ፡
በዘርዕ ፡ በሩካቤ ፡ ሊወልዱ ፡ ታዝዟልና ።
አንድም ፡ በጌታ ፡ በመለኮቱ ፡ ሕማም ፡
ሞት ፡ እንደሌለበት ፡ ዕወቅ ፡ በሰውነቱ ፡
ግን ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የለበትም ፡ አትበል፡
በሰውነቱ ፡ ሊታመም ፡ ሊሞት ፡ ለአይ
ሁድ ፡ ተሰጥቷልና ። አንድም ፡ በሰማዕ
ታት ፡ በነፍስ ፡ መከራ ፡ እንደሌለባቸው ፡
ዕወቅ ፡ በሥጋ ፡ ግን ፡ መከራ ፡ የለባቸ
ውም ፡ አትበል ፡ በሥጋ ፡ መከራ ፡ ሊቀ
በሉ ፡ ለአሕዛብ ፡ ተሰጥተዋልና ።
አንድም ፡ ኃጥአን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
እንዳይገቡ ፡ ዕወቅ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ግን፡
አይገቡም ፡ አትበል ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡
ሊገቡ፡ ታዝዟልና ። አንድም፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስ ፡ ተባርኮ ፡ እንዲሠራ ፡ ዕወቅ ፡ ሌሎ
ቹ ፡ ምኵራባት ፡ ግን ፡ ተባርከው ፡ ይሠ
ራሉ ፡ አትበል ፡ ሳይባረኩ ፡ እንዲሠሩ ፡
ታዝዟልና፡ ምሥጢሩ፡ ደሙ፡ በነጠበበት፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዲሠራ ፡ ማለት ፡
ነው፡ (ወይትካየድዋ) ፡ የፈተኛውን፡ ይዞ ፡
ይሄዳል ፡ ይከይድዋም ፡ ይላል ፡ ሉቃ ፡
፳፩ ፡ ፳፬ ። ም ፡ ፲፩ ፡ ፫ና ፡ ፲፪ ፡ ፮፡ ፲፬ና፡
፲፫ ፡ ፭ ።

፫ ፤ ወእኤዝዞሙ ፡ ለክልኤቱ ፡ ጻድቃንየ ፡ ከመ ፡
ይትነበዩ ፡ መዋዕለ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ምእተ ፡
ወስሳ ፡

ሁለቱን ፡ ወዳጆቼን ፡ አዝዛቸዋለሁ፡ ሽሕ፡
ከሁለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዕለት ፡ ያስተ
ምሩ ፡ ዘንድ ፡ ሐተታ ፡ የሦስቱ ፡ ዓመት ፡
መቶ ፡ መቶው ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡
ስድሳው ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ የመንፈቁ ፡
መቶ ፡ ሰማንያ ፡ መቶ ፡ ሰማንያና ፡ መቶ ፡
ሰማንያ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ይሆናል ፡
ሽሕ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዕለት ፡
ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወሰመንቱ ፡ ይላል ፡
ያንዱን ፡ ዓመት ፡ ጳጉሜን ፡ ትቶ ፡ የሁ
ለቱን ፡ ዓመት ፡ ቆጥሮ ።

እንዘ ፡ ሠቀ ፡ ይለብሱ ።

በሰማዕታት ፡ ሞት ፡ ኀዘንተኞች ፡ ናቸ
ውና ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሰው ። አንድም ፡
መከራ ፡ እየተቀበሉ ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡
እኤዝዞሙ ፡ ላለው ፡ ቍ ፡ ፪ ።



www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ክልኤ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡

ሁለቱ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ እሊህ ፡ ኤልያስና ፡ ሄኖክ ፡ ናቸው ፡ ሄኖክ ፡ ማለት ፡ ተሐድሶ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተሐድሶ ፡ በዘይት ፡ ነውና፡ ኤልያስም ፡ ማለት ፡ ዘይት ፡ ማለት ፡ ነው፡ (ጥቅ) ፡ ወገደፈቶ ፡ ታሕተ ፡ አሐቲ ፡ ዕፀ ፡ ኤልያስ ፡ ወአሐቲ፡ መሥፈርተ፡ ኤልያስ ፡ ትገብር ፡ ዐሥርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ምክያዳተ ፡ እንዲል ።

ወክልኤ ፡ መኃትው ፡ እለ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሎች ፡ የሚሆኑ ፡ ሁለት ፡ መምህራን ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ መኃትው ፡ አላቸው ፡ በትምህርታቸው ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ብሩህ ፡ ያደርጋሉና ፡

እለ ፡ ሥዩማን ፡ ላዕለ ፡ ምድር ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ ዘካ ፡ ፬ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ።

፭ ፤ ወለዘፈቀደ፡ይስሐጦሙ፡እምውስተ፡ጸላእቶሙ፡

ከጠላቶቻቸውም ፡ ወገን ፡ ሊጣሏቸው ፡ የወደደውን ፡

ትወፅእ ፡ እሳት ፡ እምነ ፡ አፉሆሙ ፡ ወታጠፍአሙ ፡ ለጸላእቶሙ ፡

እሳት ፡ ከአፋቸው ፡ ወጥታ ፡ ታቃጥላቸዋለች ፡ አለ ፡ መቅሠፍት ፡ በሥልጣናቸው ፡ ታዝዛ ፡ታጠፋቸዋለች ።

ወከመዝ ፡ ይመውቱ ፡ እለ ፡ ይስሕጥዎሙ ።

የሚጣሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ይጠፋሉ ፡ ፪ ፡ ነገሥ ፡ ፩ ፡ ፲ ።

፮ ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ሥሉጣን ፡ ላዕለ ፡ ሰማይ ፡

ሰማዩን ፡ ያዝዙታልና ፡

ከመ ፡ ይዕጽውዋ ፡ ከመ ፡ ኢይዝንም ፡ ዝናም ፡ ላዕለ፡ ምድር ፡ በመዋዕለ ፡ ትንቢቶሙ ፡

በሚያስተምሩበት ፡ ወራት ፡ ሰማይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ እንዳይሰጥ፡ ይከለክሉ ፡ ዘንድ ፡ ሥሉጣን ፡ ሳለው ፡ ተመልሶ ፡ በኤልያስ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡

ወዓዲ ፡ ሥሉጣን ፡ እሙንቱ ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡

ዳግመኛም ፡ ውኃውን ፡ ያዝዙታልና ፡

ከመ ፡ ይረስይዎ ፡ ደመ ፡

ደም ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ በሄኖክ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡(ትርጓሜ ፡ ቀለምሲስ ፡ ግን ፡ ሙሴ ፡ ይላል ፡ የተመቸ ፡ ነው) ፡

ወያሐምምዋ ፡ ለምድር ፡ በኵሉ ፡ መቅሠፍት ፡ መጠነ ፡ ፈቀዱ ።

የወደዱትን ፡ ያህል ፡ መቅሠፍት ፡ እያመጡ ፡ በሰው ፡ መከራ ፡ ያጸናሉ ፡ ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ዘፀአ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፯ ፤ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ስምዖሙ ፡

ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ መስክረው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡

ወትንቢቶሙ ፡

ሰማዩን ፡ ምድሩን ፡ የብሱን ፡ ባሕሩን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ አስተምረው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡

አርዌ ፡ ዘዐርገ ፡ እምቀላይ ፡ ተበዐሰ ፡ ምስሌሆሙ ፡

ከከተማ ፡ ነግሦ ፡ የወጣ ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ፡ (ይትበዐስ)፡ ከሳቸው፡ ጋራ፡ ይጣላል፡

ወሞዖሙ ፡ ወቀተሎሙ ፡

(ይመውአሙ) ፡ ድል ፡ ይነሣቸዋል ፡ ያስገድላቸዋል ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፺ና ፡ ፲፺ ፡ ፰ ።

፰ ፤ ወአንበረ ፡ በድኖሙ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ፍጥሞ ፡ ዘበኀቡእ ፡ ሰዶም ፡ ወግብፅ ፡

ሬሳቸውን ፡ (አስከሬናቸውን ፡ ቢል) ፡ በምሥጢር ፡ ሰዶም ፡ ግብፅ ፡ በምትባል ፡ አገር፡ያስጥለዋል፡(ጥቅ)ስምዑ፡መላእክተ፡ ሰዶም ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአፅምዑ፡ ሕዝበ ፡ ገሞራ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡

ኀበ ፡ ተጸልበ ፡ እግዚእሙ ።

ጌታቸው ፡ በተሰቀለበት ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬ ።

፱ ፤ ወይሬእይዎ ፡ አሕዛብ ፡ ወሕዝብ ፡ ወነገድ ፡ ወበሐውርት ፡ ለበድኖሙ ፡ ሠሉሰ ፡ መዋዕለ ፡ ወመንፈቀ ፡

ሕዝብ ፡ አሕዛብም ፡ ሦስት ፡ ቀን፡ ተኩል፡ ሬሳቸውን ፡ ወድቆ ፡ ያዩታል ፡ ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ አሕዛብ ፡ ያለውን ፡ በሐውርት ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡

ወኢያበውሕ ፡ ይቅብርዎ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ለበድኖሙ ፡

ቀባሪ ፡ ይከለክልባቸዋልና ።

፲ ፤ ወይትፌሥሑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በእሳቸው ፡ ጥፋት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡

ወይጸገዉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አምኃ ፡ ወይብሉ ፡

እርስ፡ በእርሳቸው፡ አጋናእ፡ይማታሉ፡አጥፋኝ ፡ አጥፋኝ ፡ ይባባላሉ ፡

እስመ ፡ እሉ ፡ ክልኤቱ ፡ ነቢያት ፡ አሕመምዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ መምህራን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ መከራ ፡ አጽንተውባቸዋልና ።

፲፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕል ፡ ወመንፈቅ ፡ ትመጽእ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር፡ ወትበውእ ፡ ውስቴቶሙ፡ ወይትነሥኡ ፡

ከሦስት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ በኋላ ፡ ነፍሳቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዛ ፡ መጥታ ፡ ታድርባቸዋለች ፡ ይነሣሉ ፡

ወይቀውሙ ፡ በእገሪሆሙ ፡

ጥግ ፡ መቋሚያ ፡ ሳይሹ ፡ ይቆማሉ ፡ ሐተታ ፡ ሁሉም ፡ ተካክሎ ፡ እንዲያያቸው ፡ (ሐተታ)፡ የከተማው፡ ሌሊት፡ አይተኛም፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ያድራል ፡ ሲነጋ ፡ ፀሐይ ፡ እስትትሞቅ ፡ ተኝቶ ፡ ያረፍዳል ፡ የገጠሩ፡ ማልዶ፡ ተነሥቶ፡ ሲገሠግሥ ፡ ይረፍድበታል ፡ ሁሉም ፡ ተካክሎ ፡ እንዲያያቸው ፡ ከቀን ፡ እኩል ፡ በኋላ ፡ አለ ፡

ወኮነ ፡ ፍርሀት ፡ ዐቢይ ፡ ላዕለ፡ እለ፡ ይሬእይዎሙ ።

በሚያይዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ፍርሀት ፡ ሽብር ፡ ሆነ ፡ ከምጽአት ፡ አስቀድሞ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የተመቸ ፡ በምጽአት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኀልፈተ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ።

፲፪ ፤ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ዕርጉ ፡ ዝየ ፡

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ ቃል ፡ ይሰማል ፡ ኑ ፡ ወደ ዚህ ፡ ውጡ ፡ የሚል ፡

ወእምዝ ፡ ዐርጉ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ በደመና ፡ ወርእይዎሙ ፡ ጸላእቶሙ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በክብር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያርጋሉ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ እያዩአቸው ፡ ፪ ፡ ነገሥ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፲፫ ፤ ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ድልቅልቅ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ መነዋወጽ ፡ ሆነ ፡ ከምጽአት ፡ አስቀድሞ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ መቅሠፍተ ፡ ኃጥአን ፡ ታዘዘ ፡ በምጽአት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኀልፈተ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ፡

ወወድቀ ፡ ዐሥርተ ፡ እዴሃ ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡

የዚያች ፡ ሀገር ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅዋ ፡ ጠፋ ፡ ከምጽአት ፡ አስቀድሞ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የተመቸ ፡ በምጽአት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ በፍጹም ፡ ቍጥር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወሞቱ ፡ በውእቱ ፡ ድልቅልቅ፡ ሰብዓ ፡ ምእት ፡ ነፍስ፡

በዚያም ፡ ድልቅልቅ ፡ ሰባት ፡ ሽሕ ፡ ሰዎች ፡ አለቁ ፡ ከምጽአት ፡ በኋላ ፡ በል ፡ እንዳለፈው ።

ወደንገፁ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ወአእኰትዎ ፡ ለአምላከ ፡ ሰማይ ።

የቀሩት ፡ ግን፤ የአንክሮ ፡ ድንጋፄ ፡ እየደነገጡ፡በልዕልና ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናሉ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያምናሉ።

፲፬ ፤ ወበዝ ፡ ኀለፈት ፡ ካልእት ፡ ሕማም ፡ ወተርፈት ፡ ሣልሲት ፡ ሕማም ፡

ወተርፈ ፡ ክልኤ ፡ ሕማም ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ከሁለቱ ፡ መከራ ፡ አንዲቱ ፡ በዚህ ፡ አለፈች ፡ ገና ፡ አንዲቱ ፡ መከራ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለች ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ።

፲፭ ፤ ወሶበ ፡ ጠቅዐ ፡ ሳብዕ ፡ መልአክ ፡

በሰባተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሰባተኛው ፡ መልአክ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

መጽአ ፡ ቃል ፡ ዐቢይ ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡ ኮነት፡ መንግሥተ ፡ ዓለም ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ መንግሥት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተሰጠች ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ይሰማል ፡

ወለመሢሑ ፡

ለመሢሑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ተሠጠች ፡

ወይነግሥ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡

ለዘለዓለሙ ፡ ነግሦ ፡ ይኖራል ፡ ዳን ፡ ፪ ፡ ፵፬ና ፡ ፯ ፡ ፳፯ ። ዘካ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ።

፲፮ ፤ ወእልክቱኒ ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሊቃናት ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በበመናብርቲሆሙ ፡

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በባለሟልነት ፡ ያሉ ፡ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናትም ፡

ሰገዱ ፡ በገጾሙ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በግንባራቸው ፡ ሰገዱ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ም ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።

፲፯ ፤ ወይቤሉ ፡ ነአኵተከ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ትመልክ ፡

አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እናመሰግንሃለን ፡ ሁሉን ፡ የምትገዛ ፡ (ትመልዕ) ፡ በሁሉ ፡ ምሉዕ ፡ የምትሆን ፡

ዘሀሎከ ፡ ወትሄሉ ፡

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበርህ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፈህ ፡ የምትኖር ፡

እስመ ፡ አንሣእከ ፡ ኀይለከ ፡ ዐቢየ ፡ ወነሣእከ ፡ መንግሥተ ።

ሥራህን ፡ ሠርተሃልና ፡ መንግትንም ፡ እጅ ፡ አድርገሃልና ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፰ ።

፲፰ ፤ ወአሕዛብሰ ፡ ተምዑ ፡

አሕዛብ ፡ ግን ፡ ተበሳጩ ፡ ተቆጡ ፡

እስመ ፡ በጽሐሙ ፡ መዓትከ ፡

ፍርድህ ፡ ደርሶባቸዋልና ፡ እንደ ፡ ሰኔ ፡ ሹም ፡

ወዘመኖሙ ፡ ለሙታን ፡ በዘይትኳነኑ ፡

ሙታኑ ፡ ሥጋ ፡ ሙታኑ ፡ ሕሊና ፡ በሚፈረድባቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈረድባቸው ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡

ወከመ ፡ ተሀበሙ ፡ ዕሤቶሙ ፡ ለአግብርቲከ ፡ ለነቢያት ፡ ወለቅዱሳን ፡

ለወዳጆችህ ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ ለምእመናን ፡ ዋጋቸውን ፡ የምትሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡

ወለእለ ፡ ይፈርሁ ፡ ስመከ ፡ ለንኡሶሙ ፡ ወለዐቢዮሙ ፡

ስምህን ፡ ለሚፈሩ ፡ በስምህ ፡ ለሚያምኑ ፡ ዋጋቸውን ፡ ለታላቁም ፡ ለታናሹም ፡ ትሰጣቸው፡ዘንድ፡ (የዕድሜ፡ የመዓርግ፡ነው)።



ወከመ ፡ ትኰንኖሙ ፡ ለእለ ፡ ያማስንዋ ፡ ለምድር ።

ምድር፡ ሰውነታቸውን፡ በኃጢአት፡ የሚያሳድፉትን፡ በሚያሳድፉ፡ ትፈርድባቸው ፡ ዘንድ፡ የምትፈርድባቸው፡ ጊዜ፡ደርሷልና፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፪፡ ፩ና ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፲፱ ፤ ወእምዝ ፡ ተርኅወ ፡ መቅደሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘውስተ ፡ ሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰማይ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ተከፈተ ፡ አለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ተሰጠች ፡

ወአስተርአየት ፡ ታቦተ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ መቅደሱ ፡

ሕጉን ፡ ጠብቃ ፡ የምትኖር ፡ ምእመን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ወርሳ ፡ ክብራ ፡ ታየች ፡

ወመጽአ ፡ መብረቅ ፡ ወቃለ ፡ ነጐድጓድ ፡ ወድልቅልቅ ፡ ወበረድ ፡ ዐቢይ ።

መብረቅ ፡ ነጐድጓድ፡ ድልቅልቅ፡ በረድ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ መቅሠፍተ ፡ ኃጥአን ፡ ታዘዘ ፡ ኀልፈተ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ። አንድም፡ (ወእምዝ) ፡ ቃል ፡ ሥግው ፡ ጎኑን ፡ ተወጋ፡ (ወአስተርአየት) ፡ ሕጉን ፡ የምትጠብቅ ፡ ምእመን ፡ ከጎኑ ፡ በፈሰሰ ፡ ውኃ ፡ ተጠምቃ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተወልዳ ፡ ክብራ ፡ ታየች ፡ (ወመጽአ) ፡ ስብከተ ፡ ሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ተደረገ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ፤ ወአስተርአየ፡ ተአምር፡ ዐቢይ፡በውስተ፡ሰማይ፡

በሰማይ ፡ ደገኛ ፡ ምልክት ፡ ታየ ፡

ብእሲት ፡ እንተ ፡ ትለብስ ፡ ፀሓየ ፡

ፀሓይን ፡ ተጐናጽፋ ፡

ወወርኅ ፡ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሃ ፡

ጨረቃን ፡ ተጫምታ ፡

ወዲበ ፡ ርእሳኒ ፡ አክሊል ፡ ዘዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ከዋክብት ።

አሥራ ፡ ሁለት ፡ ከዋክብት ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርፅ ፡ ያለበት ፡ ዘውድ ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ ደፍታ ፡ ታየች ።

፪ ፤ ወፅንስት ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡

ፀንሳለች ።

ወትገዕር ፡ ወተሐምም ፡ ለወሊድ ።

ምጥ ፡ ተይዛ ፡ ለመውለድ ፡ ትጮሃለች ፡ ሚካ ፡ ፬ ፡ ፲ ።

፫ ፤ ወአስተርአየ፡ ካልእ፡ተአምር፡ በውስተ፡ ሰማይ፡

ዳግመኛም፡ በሰማይ፡ ሌላ፡ ምልክት፡ታየ ፡

አርዌ ፡ ዐቢይ ፡ ወቀይሕ ፡

እሳት ፡ የሚመስል ፡ ታላቅ ፡ ዘንዶ ፡ ታየ ፡

ዘሰብዐቱ ፡ አርእስቲሁ ፡ ወዐሠርቱ ፡ አቅርንቲሁ ፡

ሰባት ፡ አርእስት፡ዐሥር፡ ቀንዶች፡ያሉት ፡ በስድስቱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ በሰባተኛው ፡ አራት ፡ በቅሎ ፡ ያያል ። አንድም ፡ ስድስቱ ፡ ሁሉ ፡ ጎዳ ፡ ሆነው ፡ በሰባተኛው ፡ ዐሥር ፡ በቅሎ ፡ ያየዋል ፡

ወውስተ ፡ አርእስቲሁ ፡ ሰብዐቱ ፡ ቀጸላ ።

በሰባቱ ፡ አርእስት፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ትርፍ ፡ ያለበት ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፬ ፤ ወበዘነቡ ፡ ይስሕብ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለከዋክብተ ፡ ሰማይ ፡ ወያወርዶሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

በጅራቱ፡ እየጠረገ ፡ ከከዋክብት ፡ ሲሦዋቸውን ፡ ወደ ፡ ምድር፡ ያወርዳቸዋል ፡

ወቆመ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ አንፃረ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ።

ያ ፡ አውሬ ፡ በዚያች ፡ ሴት ፡ ፊት ፡ ለፊት፡ ቆመ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ሶበ ፡ ወለደት ፡ ይብላዕ ፡ ሕፃና ።

በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ብላቴናውን ፡ ይበላ ፡
ዘንድ ፡ ዳን ፡ ፰ ፡ ፲ ።

፭ ፤ ወወለደት ፡ ወልደ ፡ ተባዕተ ፡

ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ።

ዘውእቱ፡ ይርዕዮሙ፡ለኵሉ፡ አሕዛብ፡ በበትረ፡ኀፂን፡

በተወደደ ፡ በጽኑዕ ፡ ሥልጣን ፡ የሚጠብ
ቃቸው ፡

ወመሰጥዎ ፡ ለውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ወወሰድዎ ፡ ኀበ ፡
እግዚአብሔር ፡ ወኀበ ፡ መንበሩ ።

ያን ፡ ብላቴና ፡ ነጥቀው ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አወጡት ፡ ወደ ፡ መንበሩ ፡ አደ
ረሱት ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ራእ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ።

፮ ፤ ወጐየት ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡
ወውስተ ፡ መካን ፡ ዘአስተዳለወ፡ላቲ፡ እግዚአብሔር፡

ያችም ፡ ሴት ፡ ሸሽታ ፡ ወደ ፡ በረሃ ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ወዳዘጋጀላትም፡ ቦታ፡ሄደች ።

ከመ ፡ ትትዐቀብ ፡ በህየ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ፡ ዐሠ
ርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ምእተ ፡ ወተስዓ ፡ ዕለተ ።

ሽሕ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ከዘጠና ፡ ዕለት ፡
ትጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፡
የሦስቱ፡ ዓመት፡ ጳጕሜን፡ ፲፭፡የ፩፡ዓመት፡
፫ ፡ ቀን ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ፡ ሽሕ ፡
ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ይሆ
ናል ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ጎደለሳ ፡ ቢሉ ፡ ስድስቱ፡
የሄደችበት ፡ ስድስቱ ፡ የተመለሰችበት ።
አንድም ፡ (ብእሲት ፡ እንተ ፡ ትለብስ) ፡
መምህራን ፡ ብሉይና፡ ሐዲስን ፡ ሲያስተ
ምሩ ፡ ታዩ ፡ ፀሐይ ፡ አምስቱ፡ መጻሕፍተ፡
ሙሴ ፡ ስድስተኛ ፡ መጽሐፈ ፡ ነቢያት ፡
ወርኅ ፡ ወንጌል ፡ ወርኅ ፡ አላት ፡ ወንጌ
ልን ፡ የጨረቃ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ከፀሐይ፡
ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ሰባተኛ ፡ እጅ ፡ ነው ፡
(ጥቅ) ፡ ወትነሥእ ፡ ሳብዐየ፡ እደ ፡ እምብር
ሃነ፡ ፀሐይ፡ እንዲል ፡ ወንጌልንም፡ እስመ ፡
ሳብዐይ ፡ ንባቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይላታ
ልና ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ በከ
በሩበት ፡ ክብር ፡ ከብረዋል ። አንድም ፡
ብእሲት ፡ ምእመናን ፡ ናቸው ፡ የብሉ
ይንና ፡ የሐዲስን ፡ ግብር ፡ በምሳሌ ፡ ገን
ዘብ ፡ አድርገዋል ፡ ምእመናን ፡ አሥራ ፡
ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ በከበሩበት ፡ ክብር ፡
ከብረዋል ፡ (ወፅንስት) ፡ መምህራን ፡
ምእመናንን ፡ በትምህርት ፡ ፀንሰዋል ፡
(ወወለደት) ፡ ምእመናን ፡ ምግባር ፡ ሃይ
ማኖትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገዋል ፡ (ወትግ
ዕር) ፡ መምህራን ፡ ምእመናንን ፡ በትም
ህርት ፡ ለመውለድ ፡ መከራ ፡ ይቀበላሉ ፡
ምእመናን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትን ፡ ገን
ዘብ ፡ ለማድረግ ፡ መከራ ፡ ይቀበላሉ ፡
(ወአስተርአየ) ፡ ካልእ ፡ በሰማይ ፡ ሌላ ፡
ምልክት ፡ ታየ ፡ አርዌ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው፡
ቀይሕ ፡ አለው ፡ ተፈጥሮው ፡ ከእሳት ፡
ነውና ፡ ዐቢይ ፡ አለው ፡ በቦታ ፡ ከሁሉ ፡
በላይ ፡ ነበረና ፡ (ወሰብዐቱ) ፡ ሰባት ፡ ተወ
ራጆች ፡ ያሉት ፡ የእኔ ፡ ናቸው ፡ ይላል ።
አንድም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይሾማል ፡ (ወዐሠ
ርቱ) ፡ ዐሥር ፡ አለቆች ፡ ያሉት ፡ ዐሥሩ ፡
አለቆች ፡ የእኔ ፡ ናቸው፡ ይላል።አንድም ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ይሾማል ፡ (ወውስተ ፡ አርእስ
ቲሁ) ፡ የአለቃ ፡ አለቃ ፡ ያለው ፡ የእኔ ፡
ናቸው ፡ ይላል ። አንድም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
ይሾማል ፡ (ወበዘነቡ) ፡ አርዌ ፡ ብሎታል
ና ፡ ወበዘነቡ ፡ አለ ፡ ሰማያውያን ፡ ከሆኑ ፡
በኋላ ፡ በማሳቱ ፡ ምእመናንን ፡ ምድራዊ ፡
ሥራን ፡ ያሠራቸዋል ፡ (ወቆመ ፡ውእቱ) ፡
በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ አድሮ ፡ መምህራን ፡
ምእመናንን ፡ በትምህርት ፡ በወለዱ ፡
ጊዜ ፡ ምእመናን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትን ፡
ገንዘብ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ይጣላቸው ፡ ዘን
ድ ፡ ሔዋንን ፡ ባሳተበት ፡ በጥንተ፡ ክፋቱ፡



ጸና ፡ (ወወለደት) ፡ መምህራን ፡ ምእመና
ንን ፡ በትምህርት ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉ ፡
(ዘውእቱ) ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ በአሕ
ዛብ ፡ ዘንድ ፡ የጠፋ ፡ መስሎ ፡ ሳለ ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለኋላ ፡ ትውልድ ፡
መጠበቁን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ምእመናን ፡
በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ቢጎዱ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ዘንድ ፡ አለመጎዳታቸውን ፡ መና
ገር ፡ ነው ፡ (ወመሰጥዎ) ፡ ብላቴናውን ፡
ነጥቀው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡
መንበሩ ፡ አደረሱት ፡ (ዘውእቱ ፡ ይርዕ
ዮሙ) ፡ በተወደደ ፡ በጽኑ ፡ ሥልጣን ፡
የሚጠብቃቸው ፡ (ወጐየት ፡ ይእቲ) ፡
መምህራን ፡ ምእመናን ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡
ሸሽተው ፡ ሄዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡
አዘጋጀላቸው ፡ ቦታ ፡ ሄዱ ፡ ሦስት ፡ ዓመ
ት ፡ ከመንፈቅ ፡ ሊጠበቁ ፡ ተጠብቀው ፡
ይኖሩ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ብእሲት ፡ እመ
ቤታችን ፡ ጌታን ፡ ወልዳ ፡ ወርኅ ፡ ዮሐ
ንስ ፡ መጥምቅ ፡ ሲሰግድላት ፡ ታየ ፡ ወር
ኅ ፡ አለው ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅን ፡ ጨረ
ቃ ፡ ሠርቅ ፡ ካደረገች ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡
አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ምልዓት ፡ እያደ
ረገች ፡ ትሄዳለች ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን፡
ሕጸፅ ፡ እያደረገች ፡ ትሄዳለች ፡ እሱም ፡
አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ አስተምሮ፡
በብሔረ፡ ዐረቢያ ፡ አርፍዋልና ፡በዐሥራ ፡
ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ፡ አድሮባታል ። (ወፅንስት) ፡
ጌታን ፡ ፀንሳለች ። ወትግዕር ፡ በሌሎቹ ፡
ሴቶች ፡ ልማድ ፡ ትግዕር ፡ አለ ፡ እንጅ ፡
በሷስ ፡ የለባትም ። አንድም ፡ አይሁድ ፡
ማየ ፡ ዘለፋን ፡ ያጠጧታል፡ ወአስተርአየ፡
(እንዳለፈው ፡ በል) ፡ (ወቆመ ፡ ውእቱ) ፡
በመቤታችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆመ ። አን
ድም ፡ ሔዋንን ፡ ባሳተበት ፡ በጥንተ ፡
ክፋቱ ፡ ጸና ፡ ጌታን ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡
በሄሮድስ ፡ አድሮ ፡ ያስገድለው ፡ ዘንድ ፡
(ወወለደት) ፡ ኀያል ፡ ወልድን ፡ ወለደች ፤
(ጥቅ) ፡ ወልዳ ፡ ለአርዌ ፡ ዘስሙ ፡ ተባ
ዕት ፡ ላዕላይ ፡ ማይ ፡ ተባዕታይ ፡ ውእቱ ፡
እንዲል ፡ (ዘውእቱ) ፡ አሕዛብን ፡ በጽኑ ፡
በተወደደ ፡ ሥልጣን ፡ የሚጠብቃቸው ፡
(ወወሰድዎ)፡ ጌታ ፡ እንደ፡ ሰውነቱ ፡ ሲሰ
ደድ ፡ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ በአብ ፡ ዕሪና ፡
እንዳለ ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እመቤታችን ፡
ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሄደች ፡ እግዚአብሔር ፡
ወደ ፡ አዘጋጀላትም ፡ ወደ ፡ደብረ ፡ ቍስቋ
ም ፡ሄደች፡(ከመ ፡ ትትዐቀብ) ፡ በግብፅ፡
ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ትጠበቅ ፡
ዘንድ ፡ ማቴ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። ራእ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ።

፯ ፤ ወፀብእዎ ፡ በሰማይ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡ ሚካ
ኤል ፡ ወመላእክቲሁ ።

ሚካኤል ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ከሠራዊቱ ፡
ጋራ ፡ አርዌ ፡ ዲያብሎስን ፡ ተዋጉት ፡

ወተፃብአሙ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ ምስለ ፡ መላእክቲሁ ።

እሱም ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ተዋጋቸው ፡
ዳን ፡ ፲ ፡ ፲፫ ፡ ፳፩ና ፡ ፲፪ ፡ ፩ ።

፰ ፤ ወስእኖሙ ፡

ድል ፡ ነሡት ።

ወኢረከበ ፡ እንከ ፡ መካነ ፡ በውስተ ፡ ሰማይ

በሰማይ ፡ ቦታ ፡ አላገኘም ፡ እንከ ፡ ከዚያ፡
በኋላ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፱ ፤ ወወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡
ዐቢይ ፡

ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ወረደ ፡

ወአርዌሰ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ ቀዲሙ ፡ ዘአስሐቶ፡
ለኵሉ ፡ ዓለም ፡ ዘውእቱ ፡ ሰይጣን ።

አርዌም ፡ የተባለ ፡ ቀድሞ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ፡
ያሳተ ፡ ሰይጣን ፡ የሚባል ፡ ዲያብሎስ ፡
ነው ፡ ሰይጣን ፡ ማለት ፡ መስተፃርር ፡ መ

www.ethiopianorthodox.org

ስተ፡ቃርን፡ ባላጋራ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ ወዐቀመ ፡ አዴርሃ ፡ ሰይጣነ ፡ ላዕለ ፡ ሰሎሞን ፡ እንዲል ።

ወወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወመላእክቲሁኒ ፡ ወድቁ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ወረደ ፡ ሠራዊቱም ፡ ከእሱ ፡ ጋራ፡ እንደሱ ፡ወረዱ ። አንድም ፡ (ወፀብእዎ) ፡ ሚካኤል ፡ ማለት ፡ መኑ ፡ ከማከ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መኑ ፡ ከማከ ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ ምእመናንን ፡ ይዞ ፡ ሰማይ ፡ መስቀል ፡ ነው ፡ በመስቀል ፡ ተዋጋው ፡ እሱም ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ተዋጋው ፡ ወስዕኖሙ ፡ ድል ፡ ነሡት ፡ (ወኢረከበ) ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኀይል ፡ አላገኘም ፡ (ወወድቀ) ፡ ድል ፡ ተነሣ ፡ አርዌም ፡ የተባለ ፡ ቀድሞ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ያሳተ ፡ ሰይጣን ፡ የተባለ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ (ወወድቀ) ፡ ድል ፡ ተነሣ ፡ (ወመላእክቲሁኒ) ፡ ሠራዊቱም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ድል ፡ ተነሡ ፡ ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩። ዘፍጥ፡ ፫፡፩፡፲፬።

፲ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዐቢየ ፡ በውስተ ፡ ሰማይ ፡ ዘይብል ፡ ኮነት ፡ መድኃኒት ፡ ወኀይል ፡ ወመንግሥት ፡ ለአምላክነ ፡ ወሥልጣን ፡ ለመሢሑ ፡

በሰማይ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ (ኮነት) ፡ መድኀኒት ፡ ኀይል ፡ መንግሥት ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አብ፡ ሥልጣንም፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ሰጠች ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡

እስመ ፡ ወድቀ ፡ መስተዋድይ ፡ ዘአስተዋደዮሙ ፡ ለአበዊነ፡ቅድመ፡ እግዚአብሔር፡መዓልተ፡ ወሌሊተ።

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ አባቶቻችንን ፡ የሚከሳቸው ፡ የሚያጣላቸው ፡ ዲያብሎስ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ወርዷልና ፡ ምሳ ፡ ፲፩ ፡ ፲፰ ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ዘካ ፡ ፫፡፩ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፴፩ ።

፲፩ ፤ ወሞዕዎ ፡ እሙንቱ ፡ በእንተ ፡ ደመ ፡ በግዑ ፡

በጉ ፡ ደሙን ፡ ስላፈሰሰ ፡ የመስቀል ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ የብርሃን ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ ድል ፡ ስለነሡት ፡ በእንተ ፡ ደመ ፡ በግዑ ፡ አለ ፡

ወበንእተ ፡ ቃለ ፡ ጽድቆሙ ፡

ስለ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነገራቸው ፡

እስመ፡ ኢያብደሩ ፡ ነፍሶሙ ፡ እስከ ፡ ለሞት ።

ከእሱ ፡ እስከ ፡ መለየት፡ ድረስ፡ ደርሰው ፡ እኛም ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ነን ፡ አላሉምና ። አንድም፡ (ዘይብል፡ ኮነት)፡ መንግሥት፡ ኃይል፡ መድኀኒት፡ ለአምላክነ፡ለመሢሑ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ተሰጠች ፡ የሚል፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ (እስመ፡ ወድቀ) ፡ ድል ፡ ተነሥቷልና ፡ (ወሞዕዎ ፡ እሙንቱ)፡ ምእመናን፡ ናቸው፡ ድል፡ ነሡት፡ (በእንተ፡ ደመ፡ በግዑ)፡ በጉ፡ ደሙን ፡ ስላፈሰሰላቸው ፡ (ወበእንተ ፡ ቃለ ፡ ጽድቆሙ) ፡ በአካላዊ ፡ ቃል ፡ ስለማመናቸው፡ (እስመ ፡ ኢያብደሩ) ፡ በሰማዕትነት ፡ እስከ ፡ መሞት ፡ ድረስ ፡ ደርሰው ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ እንኑር ፡ አላሉምና ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፯ ። ም ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። ቀ ፡ ፲፯ ።

፲፪ ፤ ወበእንቲአሆሙ ፡ ተፈሥሑ ፡ ሰማያት ፡ ወእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴቶን ፡

ስለሳቸውም ፡ ሰማያት ፡ መላእክት ፡ (ወእለ ፡ ይነብሩ) ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። አንድም ፡ ልዑላኑ ፡ ትሑታኑ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

አሌ ፡ ላ ፡ ለምድር ፡ ወለባሕር ፡

ለየብስ ፡ ለባሕር ፡ ወዮላት ። አንድም ፡ ለጥሙቃኑ ፡ ለኢጥሙቃኑ ፡ ወዮላቸው ፡

እስመ ፡ ወረደ ፡ ሰይጣን ፡ ውስቴቶሙ ፡ ምስለ ፡ ዐቢይ ፡ ኀምዙ ፡

ሰይጣን ፡ ከጽኑ ፡ ማሳቱ ፡ ጋራ ፡ ወደሳቸው ፡ ወርዷልና ፡



እስመ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ ውኁድ ፡ መዋዕል ፡ ተርፎ ።

ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ቀረው ፡ ስላወቀ ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ ነው ፡ (በሐሣዌ ፡ መሢሕ) ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ከመ ፡ ወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

ወደዚህ፡ ዓለም፡እንደ፡ ወረደ፡ ባየ፡ ጊዜ። አንድም፡ ድል ፡ እንደ፡ ተነሣ፡ ባየ፡ጊዜ ፡

ዴገና ፡ ለእንታክቲ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ወለደት ፡ ሕፃነ ፡ ተባዕተ ።

ወንድ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ ያችን ፡ ሴት ፡ ተከተላት ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ አድሮ ፡ ምእመናንን ፡ በትምህርት ፡ የወለዱ ፡ መምህራንን ። አንድም ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረጉ ፡ ምእመናንን ፡ ተከተላቸው ። አንድም ፡ በሄሮድስ ፡ አድሮ፡ ኀያል ፡ ወልድን ፡ የወለደች ፡ እመቤታችንን ፡ ተከተላት ።

፲፬ ፤ ወተውህባ ፡ ለይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ክልኤ ፡ ክንፍ ፡ ከመ ፡ ዘዐቢይ ፡ ንስር ፡

ለዚያች ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ንስር ፡ ያለ ፡ ሁለት ፡ ክንፍ ፡ ተሰጣት ፡ ለመምህራን ፡ ለምእመናን ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ ተሰጣቸው። አንድም ፡ ለመቤታችን ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡ ነፍስ፡ ተሰጣት ፡ (ከመ፡ ዘዐቢይ)፡ የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ማደሪያ፡ እንደ፡ መሆኗ፡

ከመ ፡ ትሥርር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡

ወደ ፡ ገዳም ፡ ሸሽታ ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ መምህራን ፡ ምእመናን ፡ ሸሽተው ፡ ወደ፡ በረሃ ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ እመቤታችን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡

ወውስተ ፡ መካን ፡ ከመ ፡ ትትዐቀብ ፡ በዝሉ ፡ መዋዕል ፡ ዘመነ ፡ ወአዝማነ ፡ ወመንፈቀ ፡ ዘመን ።

በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ወደምትጠበቅበት፡ ቦታ፡ ትሄድ፡ ዘንድ ፡ እመቤታችን፡ መምህራን ፡ ምእመናን ፡ ናቸው ፡ (ዘመነ) ፡ አንዱን ፡ ዘመን ፡ (ወአዝማነ) ፡ ሁለቱን ፡ ዘመን ፡ (ወመንፈቀ ፡ ዘመን) ፡ መንፈቁን ። አንድም ፡ ዘመነ ፡ ወዘመነ ፡ ዘመን ፡ወመንፈቀ ፡ ዘመን ፡ ይላል ፡ አብነት ፡ (ዘመነ) ፡ አንዱን ፡ ዓመት ፡ (ወዘመነ ፡ ዘመን) ፡ ሁለቱን ፡ ዓመት ፡ (ወመንፈቀ ፡ ዘመን) ፡ መንፈቁን ። አንድም ፡ ዘመነ ፡ ወዘመነ ፡ ወዘመነ ፡ ወመንፈቀ ፡ ዘመን ፡ ይላል ፡ አብነት ፡ ትርጓሜው ፡ አንድ ፡ ነው ፡

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ።

ከሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ፊት ፡ ትጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፳፭ና ፡ ፲፪ ፡ ፯ ።

፲፭ ፤ ወሠረረ ፡ ወዴገና ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡

ያችን ፡ ሴት ፡ ተከተላት ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ አድሮ ፡ መምህራንን ፡ ምእመናንን ፡ በሄሮድስ ፡ አድሮ ፡ እመቤታችነን ፡ ተከተላት ፡

ወአውፅአ ፡ እምነ ፡ አፉሁ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ ማየ ፡ ብዙኀ ፡ እንተ ፡ ድኅሬሃ ፡ ለይእቲ ፡ ብእሲት ፡

ከአፉ ፡ ብዙ፡ ውኃ ፡ አውጥቶ ፡ በዚያች ፡ ሴት ፡ በኋላዋ ፡ አፈሰሰ ፡

ከመ ፡ ፈለግ ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ ይንሥእ ፡ ውሒዙ ።

እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ያለ ፡ ፈሳሹ ፡ ይዞ ፡ ያስቀራት ፡ ዘንድ ።

፲፮ ፤ ወረድአታ ፡ ምድር ፡ ለይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ወአርኀወት ፡ አፉሃ ፡ ምድር ፡ ወሰረበቶ ፡ ለውእቱ ፡ ውሒዝ ፡ ዘአውሐዘ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ እምነ ፡ አፉሁ ፡

ምድር፡ አገዘቻት፡ አፍዋን፡ ከፍታ፡ካፉም፡ አውጥቶ ፡ ያፈሰሰውን፡ ውኃ ፡ ጠጣችው ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ አድሮ፡ በቃሉ ፡ ጦር፡ አዝዞ ፡ ሰደደ ። አንድም ፡ በሄሮድስ ፡ አድሮ ፡ ጦሩ ፡ ምእመናንን ፡ መምህራንን ፡ እመቤታችነን ፡ ያስቀራቸው ፡ ዘንድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

(ወረድአታ) ፡ ርኀቀተ ፡ ሀገር ፡ ርኀቀተ ፡
ፍኖት ፡ ሞተ ፡ ሰማዕታት ፡ አስቀረላቸው፡
ርኀቀተ ፡ ፍኖት ፡ ሂዶ ፡ ሂዶ ፡ መመለስ ፡
ርኀቀተ ፡ ሀገር ፡ ጥንቱን ፡ ሳያስቡ ፡ መቅ
ረት ፡ ነው ፡ ሞተ ፡ ሰማዕታት ፡ ላለው ፡
(ጥቅ) ፡ እምአመ ፡ አእተቶ ፡ ኤፍሬም ፡
እምይሁዳ ፡ ለንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ይእተ ፡
አሚረ ፡ ይመጽእ ፡ መዋዕለ ፡ ሣህል ፡ እን
ዲል ። አንድም ፡ ለእመቤታችን ፡ መላእ
ክት ፡ ጽዋዕ ፡ ሲያፈሱ ፡ ማሰሬ ፡ ሲመቱ ፡
ታይተዋል ።

ወኢያእመረ ፡ ከመ ፡ ተውህበ ፡ ላቲ ፡ ክንፍ ።

ለመምህራን ፡ ለምእመናን ፡ ምግባር ፡
ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ተሰጣቸው ። አንድም፡
ለእመቤታችን ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡
ነፍስ ፡ እንደ ፡ ተሰጣት ፡ አላወቀም ።

፲፯ ፤ ወተምዐ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ ላዕለ ፡ ይእቲ ፡
ብእሲት ፡

በዚያች፡ ሴት፡ተቆጣ።አንድም፡በመምህራ
ን፡ በምእመናን ፡ በእመቤታችን ፡ ተቆጣ ፡

ወሖረ ፡ ይዕብኦሙ ፡ ለእለ ፡ ተርፉ ፡ ውሉዳ ፡

ከሞት ፡ የቀሩ ፡ ልጆችዋን ፡ ይጣላቸው ፡
ዘንድ ። አንድም ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡
አድሮ ፡ ሕፃናትን ፡ ይጣላቸው ፡ ዘንድ ፡
ሄደ ፡

ወለእለ ፡ የዐቅቡ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጠብ
ቁትን ።

ወይሄልዉ ፡ በጽድቁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ቸርነት፡ ጸንተው፡የሚ
ኖሩትን፡ ይጣላቸው፡ዘንድ፡(ታሪክ)፡ ጌታ፡
መላእክትን፡በነገድ፡መቶ፡በከተማ፡ዐሥር፡
አድርጎ፡ፈጥሮ፡ ተሠወራቸው፡ ካልሹኝ ፡
አልገኝም፡ባሕርዬ፡ ይመረአመርም፡ ሲል፡
ዐይን ፡ በገለጡት ፡ ጊዜ ፡ ከማያት ፡ ላይ ፡
እንዲያርፍ ፡ እነሱም ፡ ዕለቱን ፡ ተፈጥ
ረው ፡ አዋቆች ፡ ናቸው ፡ እንጅ ፡ አላዋ
ቆች ፡ አይደሉምና ፡ ምንት፡ ንሕነ ፡ እም
አይቴ ፡ መጻእነ ፡ መኑ ፡ ፈጠረነ ፡ በበርእ
ስነኑ ፡ ተፈጠርነ ፡ ወሚመ ፡ እምካልእ ፡
ብለዋል ፡ ዲያብሎስን ፡ በቦታ ፡ ከሁሉ ፡
በላይ ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮት ፡ ነበርና ፡ ከወ
ደታች ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ሰማ ፡ ከወደ ፡ ላ
ይ ፡ እኔ ፡ ፈጠርሁ ፡ የሚል ፡ አጣ ፡ እኔ ፡
ፈጠርሁ ፡ ልበል ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡ አስቦም፡
አልቀረ ፡ እኔ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ አለ ፡ ነው ፡
ሰጊድ ፡ ይገባዋል ፡ ያሉ ፡ አሉ ፡ ነው ፡
ሰጊድ፡ አይገባም፡ ያሉ፡ አሉ፡ ነውስ፡ብሎ፡
ሰጊድ ፡ አይገባውም ፡ ማለት ፡ አይሆንም፡
ብሎ ፡ እኛም ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ነን ፡ ያሉ ፡
አሉ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ያለስ ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ይሆን ፡ አይሆን ፡ ብ
ለው ፡ የተጠራጠሩ ፡ አሉ ፡ እንዲያውም፡
ሀልዎተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሳይመረምሩ፡
የቀሩ ፡ አሉ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ግን ፡ በምን ፡
ነገር ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ ይለናል ፡ በቦታ ፡
በላይ ፡ በመሆን ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ እንዳይ
ለን ፡ እኛ ፡ ከበታች ፡ ያሉትን ፡ አልፈጠ
ርናቸውም ፡ በዚያውስ ፡ ላይ ፡ እኛ ፡ ምቀ
ኞቹ ፡ ነን ፡ ፈጣሪ ፡ እንጅ ፡ በሥራው ፡
ይታወቃል ፡ ፈጥረህ ፡ አሳየን ፡ እንበለው፡
ብለው ፡ ፈጥረህ ፡ አሳየን ፡ አሉት ፡ እፈጥ
ራለሁ ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ ከእሳት ፡ ጨመረ ፡
ፈጀው ፡ ዋይ ፡ አለ ፡ አፍአዊ ፡ አምላክ ፡
ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ውሳጣዊማ ፡ አም
ላክ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ስትል ፡ ነው ፡ ባላለኝ፡
ነበር ፡ የነቢቡን ፡ የገቢሩን ፡ እንጅ ፡ የሐ
ልዮውን ፡ አያውቀውም ፡ አለ ፡ ልቡን ፡
ተሰማው ፡ ዋይ ፡ አለ ፡ ፈወሰው ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ በመላእክት ፡ ሽብር ፡ ጸንቶባቸ
ዋል ፡ ወአኀድዖሙ ፡ መልአከ ፡ ሰላም ፡



ይላል ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ንቁም ፡ በበ
ህላዌነ ፡ እስከ ፡ ንረክቦ ፡ ለአምላክነ ፡
ብሎ ፡ አጽንቷቸዋል ፡ በጎ ፡ አርበኛ ፡
ጦር ፡ በተፈታ ፡ ጊዜ ፡ አይዞህ ፡ ባለህ ፡
ጽና ፡ ብሎ ፡ እንዲያጸና ፡ ወበእንተ ፡ ዝ ፡
ደለዎ፡ ይፁር፡ ዜናሁ፡ ለማርያም፡ እንዲል ፡
ስለዚህ፡ ብሥራት ፡ ተሰጥቶታል ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ጨርሶ ፡ ሳያስታቸው ፡ ብሎ ፡ እኔ ፡
ፈጠርሁ ፡ እንዳይል ፡ እሱ ፡ በሌለበት ፡
በኩል ፡ በስተምሥራቅ ፡ እቤ ፡ አነ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ለይኩን ፡ ብርሃን ፡ ብሎ ፡
ባሕረ ፡ ብርሃን ፡ አፍሶላቸዋል ፡ ወዲያው፡
ስሙ ፡ የተጻፈበት ፡ መጽሔተ ፡ ብርሃን ፡
ሰዶላቸው ፡ ያን ፡ ይዘው ፡ አንድነት ፡ ሦስ
ትነት ፡ ተገልጾላቸው ፡ አሐዱ ፡ አብ ፡
ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡
ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ አመ
ስግነዋል ፡ እሱንም ፡ በአደረው ፡ ጨለማ፡
ጠቅሎ ፡ በኢዮር ፡ ካሉ ፡ መላእክት ፡ ደር
ቦታል ፡ ንጉሥ ፡ የተጣላውን ፡ በርጥብ ፡
ቆርበት ፡ አስጠቅልሎ ፡ በገደል ፡ እንዲያ
ስጥል ፡ በኢዮር ፡ ሁኖ ፡ በዕለተ ፡ ሠሉስ ፡
የተፈጠሩ ፡ ዕፀዋት ፡ አዝርዕት ፡ አትክ
ልት ፡ ጽጌያትን ፡ አይቶ ፡ እንዲህ ፡ አድ
ርጎ ፡ አከናውኖ ፡ መፍጠርን ፡ ወይም ፡ እ
ንጅ ፡ የያዘለት ፡ ይኖራል ፡ አለ ፡ ወደድ
ሃት ፡ ላኑርህ ፡ አለው ፡ እንዲያው ፡ አልሁ፡
እንጅ፡ እኔማ፡ ደገኞዩቱን፡ ማን፡ ነሥቶኝ፡
ብሎ ፡ ከሚካኤል ፡ ከገብርኤል ፡ ዘንድ ፡
ይልካል ፡ እናንተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊ
ት ፡ ይሏችኋል ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ እንኳ ፡
አያህሏትም ፡ እኛ ፡ ከጨኸት ፡ በቀር ፡
የተጠቀምነው ፡ የለም ፡ ገገር ፡ ነኝ ፡ የሚ
ለውን ፡ ወግተን ፡ እጅ ፡ እናድርግ ፡ ብሎ ፡
ሂደው ፡ ነገሯቸው ፡ ከትዕይንተ ፡ ንጉሥ ፡
እንደ ፡ ገባ ፡ ዕብድ ፡ ውሻ ፡ አድርገው ፡
ሰደዷቸው ፡ ሂደው ፡ አልተቀበሉንም ፡
አሉት ፡ ሚካኤል ፡ ገብርኤል ፡ ቢሏቸው ፡
በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ናቸው ፡
እንደ ፡ ቀለምፂጸ ፡ እሳት ፡ እንጅ ፡ ያይ
ደሉ ፡ ተሸከሙኝና ፡ እንሂድ ፡ አላቸው ፡
ባራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ አምሳል ፡ አራት ፡
ሆነው ፡ ተሸክመውት ፡ ሽቅብ ፡ እወጣ
ለሁ ፡ ቢል ፡ ኀይል ፡ ተነሥቶታልና ፡ ወደ
ታች ፡ እንጅ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡
የማይቻለው ፡ ሆነ ፡ ጐየ ፡ እግዚእ፡ ምስለ፡
አርያሙ ፡ ብሎ፡ ሰማዩን፡ ጠቅልሎ፡ ሸሸ ፡
ብሎ ፡ አዝምሮ ፡ ተመለሰ ፡ መላእክት ፡
ፍጥረት፡ እየተፈጠረ፡እያዩ፡ ያመሰግናሉ ፡
(ጥቅ) ፡ ወአመ ፡ ተፈጥሩ ፡ ከዋክብትየ ፡
ሰብሑኒ ፡ መላእክትየ ፡ እንዲል ፡ በዕለተ ፡
ረቡዕ ፡ የተፈጠሩ ፡ ፀሐይ ፡ ከዋክብት ፡
ጨረቃን ፡ አይተው ፡ አመስግነው ፡ አመ
ስግን ፡ አሉት ፡ አንሰ፡ ዕድው ፡ እምዝንቱ፡
ሕሊና ፡ ውፁእም ፡ ይላል ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡
ውፁእ ፡ ነኝ ፡ ቢሆንስ ፡ እኔን ፡ አራተኛ ፡
አድርጋችሁ ፡ ብታመሰግኑኝ ፡ እወዳለሁ፡
አላችው፡ ይህ፡ ስሑት፡ ፍጥረት ፡ እንዲህ ፡
እያለ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ሲታበይ ፡ ይ
ኖራል፡ብለው፡ ሂደው ፡ ገጠሙት ፡ ድል ፡
አደረጋቸው ፡ ሁለተኛ ፡ ገጠሙ ፡ ድል ፡
አደረጋቸው ፡ እኛ ፡ ለአምላክነትህ ፡ ቀን
ተን ፡ ነበረ ፡ ፈቃድህ ፡ ባይሆን ፡ ነው ፡
ብለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያመለ
ክቱ ፡ ፈቃዴስ ፡ ፈቃዴ ፡ ነው ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ድል ፡ የሚነሣበትን ፡ ታውቁ ፡
ብዬ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስሙ ፡ የተጻፈበት ፡
ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ሰጣቸው ፡ ያን ፡
ይዘው ፡ ገጠሙት ፡ ድል ፡ አድርገው
ታል ፡ እሑድ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሰማያ
ዊት፡ ወደ ፡ ኢዮር ፡ አውርዶታል ፡ ረቡዕ ፡
ከኢዮር ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ አውርዶታል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኅሙስ ፡ ወደ ፡ አንጦርጦስ ፡ አውርዶ ታል ፡ በዚህ፡ የእሱ ፡ ወገን፡ ከሦስት ፡ተከ ፍለዋል ፡ ሀለዎተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሳይ መረምሩ ፡ የቀሩ ፡ በዐየር ፡ ቀርተዋል ፡ ይሆን ፡ አይሆን ፡ ብለው ፡ የተጠራጠሩ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቀርተዋል ፡ ነው ፡ ሰጊድ ፡ ይገባዋል ፡ ያሉ ፡ አብረው ፡ አንጦርጦስ ፡ ወርደዋልና ፡ ወመላእክቲሁኒ ፡ ወድቁ ፡ ምስሌሁ፡አለ፡ (ጥቅ)፡ ቦ፡ ዘወድቀ፡ ውስተ፡ ዐየር፡ ወቦ፡ ዘወድቀ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ወቦ፡ ዘወድቀ፡ ውስተ ፡ አንጦርጦስ፡ እንዲል ፡ ም፡ ፲፬ ፡ ፲፪ና፡ ፲፱ ፡ ፲ ። ፩ ፡ ዮሐ፡ ፳፡ ፲ ።

፲፰ ፤ ወቆመ ፡ ውእቱ፡ አርዌ ፡ ላዕለ ፡ ኖጻ ፡ ባሕር፡

ውእቱ፡ አርዌ፡ ዲያብሎስ፡ ነው፡ በባሕር ፡ አሸዋ ፡ ላይ፡ ቁሞ ፡ አየሁ ፡ ውኃ ፡ ሲመላ፡ ከዳር ፡ ጥቂት ፡ አሸዋ ፡ ዘልቆ ፡ ይታያል ፡ በፍጻሜ፡ ዘመን፡ በጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ነግሦ ፡ ሰልጥኖ ፡ አየሁ ። አንድም ፡ ውኃ ፡ ሲጎል፡ ከዳር ፡ ብዙ ፡ አሸዋ ፡ ይታያል ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነግሦ ፡ ሰልጥኖ ፡ አየሁ ። አንድም ፡ ውኃ ፡ ሲጎል ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ ተከፍሎ ፡ ይወርዳል ፡ በመካከል ፡ ብዙ ፡ አሸዋ ፡ ይታያል ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነግሦ ፡ ሰልጥኖ ፡ አየሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡

፩ ፤ ወወዕአ ፡ ካልእ ፡ አርዌ ፡ እምነ ፡ ባሕር ፡

ሌላ፡ አውሬ፡ ከባሕር፡ ሲወጣ፡ አየሁ፡ አለ፡ ሐሣዌ፡ መሢሕ፡ ነው ፡ መንግሥቱ ፡ ገና ፡ አልተደላደለምና፡ እምባሕር፡አለ፡ ታሪክ፡ የሐሣዌ ፡ መሢሕን ፡ ትውልድ ፡ ከዚህ ፡ ይናገሩታል ፡ እናቱ ፡ ከነገደ ፡ ዳን፡ አባቱ፡ ከነገደ ፡ ኤሳው፡ ናቸው፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት፡ በድንግልና ፡ ትፀንሻለሽ ፡ በድንግልና ፡ ትወልጃለሽ ፡ ብለዋት ፡ እናቱ ፡ ከመቃ ብረ ፡ አረሚ ፡ ቁማ ፡ ስትጸልይ ፡ ከነገደ ፡ ኤሳው ፡ የተወለደ ፡ አንድ ፡ ዐይና ፡ ጉል መሳ ፡ ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መጥቶ ፡ ከክ ብር ፡ ያሳንሳታል ፡ ሰይጣን ፡ ትዕቢት ፡ አሳድሮባት ፡ በድንግልና ፡ ፀነስሁ ፡ በድ ንግልና ፡ ወለድሁ ፡ ትላለች ፡ እሱም ፡ ተወልዶ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ መል ኩንም ፡ ከዚህ ፡ ይናገሩታል ፡ ወይመስል፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ ነምረ ፡ ብሎ ፡ አሁን ፡ እንዲያመጣው ፡ አካሉ ፡ ቆቅሻም ፡ ነው ፡ አሐቲ ፡ ዐይኑ ፡ ዘፍስሕት ፡ ይላል ፡ አንድ ዐይኑ ፡ የሞተች ፡ ናት ፡ ወአሐዱ ፡ ዐይኑ ፡ ዘስሩር፡ በደም፡ ይላል፡አንድ፡ ዐይኑ፡ደም ፡ የሰረበው ፡ ፈጣጣ ፡ ነው ። ታሕታይ ፡ ከን ፈሩ ፡ የዐቢ ፡ ይላል ፡ ለበናም ፡ ነው ፡ ወአ ፉሁ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ብሎ ፡ እንዲያመ ጣው፡ ጽንጽዋት፡ እደዊሁ፡ ይላል፡አውራ ጣቱ ፡ ጠማማ ፡ ነው፡ ወእገሪሁ ፡ ከመ ፡ ድብ ፡ ብሎ ፡ እንዲያመጣው ፡ ዘጼያፍ ፡ እገሪሁ ፡ ይላል ፡ እግሩ ፡ ወለፎ ፡ ነው ፡

ዘዐሥርቱ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ወሰብዐቱ ፡ አርእስቲሁ ፡

ዐሥር፡ ቀንዶች፡ ያሉት፡ ሰባት፡ አርእስት፡ ያለው ፡

ወውስተ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቀጸላ ፡

በዐሥር ፡ ቀንዶቹ ፡ ላይ ፡ ዐሥር ፡ ትርፍ ፡ ያለው ። አንድም ፡ ዐሥር ፡ ተወራጆች ፡ ያሉት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይሾማሉ ። አንድም ፡ የእኔ፡ ናቸው ፡ ይላል ፡ ያለቃ፡ አለቃ፡ ያሉ ት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሾማል ። አንድም ፡ የእኔ ፡ ናቸው ፡ ይላል ።

ወውስተ ፡ አርእስቲሁ ፡ ስመ ፡ ፅርፈት ።

በሰባቱ ፡ አርእስት ፡ ላይ፡ የስድብ፡ ስም ፡ ተጽፎበታል ፡ አለ፡ አምላክ፡ ነኝ ፡ ይላል። አንድም፡ሰባቱ፡አርእስተ፡ ኃጣውኡ፡በሱ ፡ ጊዜ ፡ ይሠራሉ ፡ ኃጢአተ ፡ አዳም ፡ ቅት ለተ ፡ አቤል ፡ ጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ ኃጢ አተ ፡ ሰዶም ፡ ኃጢአተ ፡ እስራኤል ፡ ቅት ለተ ፡ ዘካርያስ ፡ ሞተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአ ብሔር ። አንድም ፡ ሰባቱ ፡ አህጉር ፡ ያመ ልኩታል ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ ፅርዕ ፡ ሜ ዶን ፡ ግብፅ ፡ ሮም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፯ና ፡ ፲፯ ፡ ፫ ። ዳን ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

፪ ፤ ወይመስል ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡ ነምረ ፡

ነብር ፡ ይመስላል ፡ አለ ፡ አካሉ ፡ ቆቅ ሻም ፡ ነው ። አንድም ፡ ነብር ፡ ዕለቱን ፡ አርዶ ፡ አይበላውም ፡ አሰንብቶ ፡ አሽ ትቶ ፡ አትልቶ ፡ ይበላዋል ፡ እሱም ፡ ኑሮ፡ ኑሮ ፡ መንግሥተ ፡ ፋርስን ፡ እጅ ፡ ያደር ጋል ። አንድም ፡ ያነገሥሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይላል ። አንድም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላ ልሶ ፡ የወጋ ፡ መንግሥተ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የእኔ ፡ ነው፡ ይላል። አንድም ፡ ያነገሥሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡

ወእገሪሁ ፡ ከመ ፡ ድብ ፡

እግሩም ፡ እንደ ፡ ድብ ፡ አንበሳ ፡ ይመስ ላል ፡ አለ ፡ ወለፎ ፡ ነው ፡ ድብ ፡ አንበሳ ፡ ግስላ ፡ ጅብ ፡ ተዥላ ፡ ነው ፡ ድብ ፡ ትው ልዱ ፡ ከአንበሳና ፡ ከጅብ ፡ ነው ፡ ከፅር ዕና ፡ ከሜዶን ፡ የሚወለድ ፡ መንግሥተ ፡ ዳርዮስ ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ ይላል ። አንድም ፡ ያነጋገሥሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡

ወአፉሁ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡

አፉም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ይመ ስላል ፡ ለበናም ፡ ነው ። አንድም ፡ አንበሳ፡ ዕለቱን ፡ አርዶ ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ደ ሙን ፡ ጠጥቶ ፡ ይሄዳል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የወጋ ፡ መንግሥተ፡ ስልምናሶር፡ የእኔ ፡ ነው ፡ ይላል ። አንድም ፡ ያነጋገሥሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይላል ። አንድም ፡ መንግሥተ ፡ ባቢሎንን ፡ እጅ ፡ ያደርጋል ፡

ወወሀቦ ፡ ዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይሎ ፡

ዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ዲያብሎስ፡ ነው፡ ኀይሉን፡ ሰጠው ፡

ወመንበሮ ፡

ኀይል ፡ ኑሮት ፡ ጌትነት ፡ የሌለው ፡ አለና፡ ጌትነቱን ፡ ሰጠው ፡

ወዕበየ ፡ ሥልጣኑ ።

ጌትነት ፡ ኑሮት ፡ ገናንነት ፡ የሌለው ፡ አለና ፡ ገናንነቱን ፡ ሰጠው ።

፫ ፤ ወአሐቲ ፡ እምነ ፡ አርእስቲሁ ፡ እንተ ፡ ተረግዘት ፡ በሞት ፡ ወቍስለ ፡ ሞቱስ ፡ ሐይወ ፡

ከሰባቱ ፡ አርእስት፡ አንዲቱ ፡ በሞት፡ አወ ጋግ ፡ የተወጋች ፡ ናት ፡ ቍስሉም ፡ ዳነ ። አንድም ፡ ከሰባቱ ፡ አርእስተ ፡ ኃጣውኡ ፡ አንዲቱ ፡ ኃጢአተ ፡ አዳም ፡ በሞተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠፍታ ፡ ትኖራ ለች ፡ በእሱ ፡ ጊዜ፡ ትሠራለች፡ (አምላክ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው) ። አንድም ፡ ከሰባቱ ፡ አህጉር ፡ አንዲቱ ፡ ኢየሩሳሌም፡ ጠፍታ ፡ ትኖራለች ፡ በእሱ ፡ ጊዜ ፡ ትቀ ናለች ፡

ወአንከረቶ ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡ ወተለውዎ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያምንበታል ፡ ሐሣዌ ፡ መሢ ሕን ፡ ይከተሉታል ፡ ያምኑበታል ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፰ ።

፬ ፤ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ቀዳማዊ ፡

ለዲያብሎስ ፡ ሰገዱለት ፡

እስመ ፡ ወሀቦ ፡ ለዝንቱ ፡ አርዌ ፡ ሥልጣኖ ፡

ለሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ሥልጣኑን ፡ ሰጥቶታልና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡

ለሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ሰገዱለት ፡

እንዘ ፡ ይብሉ ፡ መኑ ፡ ይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ አርዌ ፡

ይህን ፡ አውሬ ፡ ማን ፡ ይመስለዋል ፡ እያ ሉ ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ አርዌ ፡ ይል ባቸዋል ፡ እንጅ ፡ እነሱስ ፡ አምላክነ ፡ ንጉሥነ ፡ ይሉታል ፡

ወመኑ ፡ ይክል ፡ ፀቢኦቶ ፡

ድል ፡ ሊነሣው ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ።

፭ ፤ ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ አፍ ፡ ከመ ፡ ይንብብ ፡ ዐቢያተ ፡ ወዕርፈታተ ።

ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ ስድብ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ አለ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ውሸት ፡ ተሰጠው ፡

ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ሥልጣን ፡ ይግበር ፡ ተአምረ ፡ ዘፈቀደ ፡ አርብዓ ፡ ወክልኤተ ፡ አውራኀ ።

ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ የወደደ ውን ፡ የምትሐት ፡ ታምራት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፲፭ ። ፪ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ራእ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ።

፮ ፤ ወእምዝ ፡ ፈትሐ ፡ አፉሁ ፡ ከመ ፡ ይፅርፍ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወላዕለ ፡ ስሙ ፡ ወላዕለ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደሱ ፡ ዘበሰማይ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገር ፡ ጀመረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ (ወላዕለ ፡ ስሙ) አምላክ ፡ ነኝ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ውሸቱን ፡ ለቀቀ፡ (ወላዕለ ፡ መቅደሱ) ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ የእኔ ፡ ናት ፡ ይል ፡ ዘንድ ።

፯ ፤ ወተውህቦ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ፀብአ ፡ ምስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ወይማዖሙ ፡

ከቅዱሳን ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ይጣላ ፡ ዘንድ ፡ ድል ፡ ይነሣቸው ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፡

ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወሕዝብ ፡ ወበሐውርት ፡ ወነገድ ።

በሕዝብ ፡ በአሕዛብ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፡ ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ አሕዛብ ፡ ያለውን ፡ በሐውርት ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ፯ ። ዳን ፡ ፯ ፡ ፳፭።

፰ ፤ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ፡ ሁሉ፡ ሰገዱለት፤

እለ፡ኢኮኑ፡ጽሑፋነ፡ አስማቲሆሙ፡ ውስተ፡መጽሐፈ፡ ሕይወት፡ ዘበግዑ፡ ዘተቀትለ ፡ ዘእምፍጥረተ፡ ዓለም ።

ስማቸው ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፈ ፡ አለ ፡ መሥዋዕት ፡ በሆነው ፡ በበግዑ ፡ ልቡና ፡ ያልታወቀ ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ጽሑፈ ፡ ዘእምፍጥረተ ፡ ዓለም ። ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ መሥዋዕት ፡ በሆነው ፡ በበግዑ ፡ ልቡና ፡ ያልታወቀ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ። ም ፡ ፫ ፡ ፭ ። ም ፡ ፲፯ ፡ ፰ ።

፱ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ፡

እዝነ፡ ልቡና፡ያለው፡ሰው፡ ያስተውል፡አለ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ያመነ ፡ እንዲጎዳ ፡ ያላመነ ፡ እንዳይጎዳ ፡ አርዌ ፡ የተባለ ፡ በቁሙ ፡ አርዌ ፡ እንዳይደለ ፡ ሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እዝነ፡ ልቡና፡ ያለው፡ ሰው ፡ ያስተውል ።

፲ ፤ ወተጼወወኒ ፡ ሕሊናየ ፡

ልቡናዬ ፡ አዘነብኝ ፡ የቀለምሲስ ፡ እኅሌታ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፲፬ ፡

ወዘሰ ፡ ቀተለ ፡ በመጥባሕት ፡ ሀለዎ ፡ ይሙት ፡ በመጥባሕት ፡

በሰይፍ፡ የገደለ፡እንጅ፡ በሰይፍ፡ ይሞታል፡ ምን፡ያሳዝንሃል፡ አይዞህ፡አትዘን፡ አለኝ፡አንድም፡ያሳዝነም፡እንጅ፡ሳያዝን፡አይቀርም፡ አይዞህ፡ አትዘን፡ አለኝ። አንድም፡ ወዘሰ ፡ ጼወወ ፡ ሀለዎ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ተጼውዎ ፡ ይላል ፡ የማረከ ፡ እንጅ ፡ ሳይማረክ ፡ አይቀርም፡ እደዚህም፡ያሳዝነም፡ እንጅ፡ ሳያዝን ፡አይቀርም ፡ አይዞህ ፡ አትዘን ፡ አለኝ ፡

ወዝየ ፡ ውእቱ ፡ ትዕግሥቶሙ ፡ ወሃይማኖቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ብፅዕት ።

ንዕድ ፡ ክብርት ፡ የምትሆን ፡ የቅዱሳን ፡ የምእመናን ፡ ትዕግሥታቸው ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ይህን ፡ ያስደርግላቸዋል ። አንድም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡

ወኢአንክሮቱ ፡ ለሰይጣን ።

በሰይጣን ፡ አለማመናቸው ፡ ለሰይጣን ፡ አለመገዛታቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አንድም ፡ ይህን ፡ ያስደርግላቸዋል ፡ ዘፍጥ ፡ ፱ ፡ ፮ ። ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፩ ። ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፶፪ ። ራእ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪ ።

፲፩ ፤ ወእምዝ፡ ወፅአ፡ ካልእ፡ አርዌ፡እምነ፡ ምድር ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ አውሬ ፡ ከየብስ ፡ ወጣ ፡ አለ ፡ ሐሣዌ ፡ ኤልያስ ፡ ነው ፡ ከየብስ ፡ ተነሣ ፡ የሚነሣ ፡ የሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ መንግሥት ፡ ከተደላደለ ፡ በኋላ ፡ ነውና ፡ እምነ ፡ ምድር ፡ አለ ፡

ዘክልኤቱ ፡ አቅርንቲሁ ፡

ሁለት ፡ አቅርንት ፡ ያለው ፡ ሐሣዌ ፡ ኤልሳዕና ፡ ሐሣዌ ፡ አብድዩ ፡ ናቸው ፡

ወይመስል ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡

በግ፡ ይመስላል፡ አለ፡ኤልያስ፡ ነኝ፡ ይላል፡

ወይነብብ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ።

ሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይናገራል፡ ም፡ ፲፮፡ ፲፫። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ና ፡ ፳፬ ፡ ፭ ።

፲፪ ፤ ወበሥልጣኑ ፡ ለቀዳማዊ ፡ አርዌ ፡ ይገብር ፡ ኵሎ ፡ በቅድሜሁ ፡

በዲያብሎስ ፡ ሥልጣን ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ፊት ፡ የምትሐት ፡ ታምራት ፡ ያደርጋል ፡

ወይሬስያ ፡ ለምድር ፡

ሰውን ፡ ሁሉ ፡

ወለእለሂ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ ይስግዱ ፡ ሎቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ አርዌ ፡

ልዑላኑን ፡ ትሑታኑን ፡ እንዲሰግዱለት ፡ ያደርጋል ።

ዘሐይወ ፡ እምቍስለ ፡ ሞቱ ።

በሞት ፡ አወጋግ ፡ ተወግቶ ፡ ለዳነ ፡ ለሐሣዊ ፡ መሢሕ ። አንድም ፡ ከሰባቱ ፡ አርእስተ ፡ ኃጣውእ ፡ አንዲቱ ፡ ኃጢአተ ፡አዳም ፡ በእሱ ፡ ጊዜ፡ ለምትሠራ። አንድም ፡ ከሰባቱ ፡ አህጉር ፡ አንዲቱ ፡ ኢየሩሳሌም፡ በእሱ ፡ ጊዜ፡ ለምትቀና ፡ ለሐሣዊ፡ መሢሕ ፡ እንዲሰግዱለት ፡ ያደርጋል ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፲፫ ፤ ወገብረ ፡ ተአምራተ ፡ ዐበይተ ፡

የምትሐት ፡ ታምራት ፡ ያደርጋል ፡

ከመ ፡ ያውርድ ፡ እምሰማይ ፡ እሳተ ፡ ውስተ ፡ ምድር፤

ኤልያስ ፡ ነኝ ፡ ብሏልና ፡ እሳት ፡ ከሰማይ፡ ያወርድ፡ ዘንድ ።

በቅድመ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ።

በሰው ፡ ፊት ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፬ ። ፪ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፰ ፡ ፳፬ ።

፲፬ ፤ ወያስሕቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩትን፡ ያስታቸዋል ። አንድም ፡ ያስሕቶሙ ፡ ያስታቸው፡ ዘንድ፡

በእንተ ፡ ተአምር ፡ ዘተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ይግበር ፡ በቅድመ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ፡

በዲያብሎስ ፡ ሥልጣን ፡ በሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ፊት ፡ ስለሚያደረገው፡ የምትሐት ፡ ታምራት ፡ ያስታቸዋል ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ቢል፡ ይሆናል ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩትን ፡ ያዝዛቸዋል ፡

ከመ ፡ ይግበሩ ፡ አምሳሎ ፡ ለዝንቱ ፡ አርዌ ፡ ዘቈሰለ ፡ በመጥባሕት ፡ ወሐይወ ።

በሾተል ፡ ተወግቶ ፡ የዳነ ፡ አለ ፡ ከሰባቱ ፡ አርእስተ ፡ ኃጣውእ፡ አንዱቱ፡ ኃጢአተ ፡ አዳም ፡ በሞተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠፍታ ፡ ትኖራለች ፡ በእሱ ፡ ጊዜ ፡ የም ትሠራ ። አንድም ፡ ከሰባቱ ፡ አህጉር ፡ አን ዱቱ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ጠፍታ ፡ ትኖራለች ፡ በእሱ ፡ ጊዜ፡ የምትቀና፡ የሐሳዌ፡ መሢሕ ን ፡ ሥዕሉን ፡ ሥለው ፡ ምስሉን ፡ መስ ለው ፡ እንዲይዙ ፡ ያደርጋል ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ ያዝዛቸዋል ፡ ዘዳግ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።

፲፭ ፤ ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ይደይ ፡ ውስቴቱ ፡ መንፈሰ ፡ ለአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ አርዌ ፡

በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ በተመሰለው ፡ ምስል፡ በተሣለው ፡ ሥዕል ፡ ቃል ፡ ያሳድርበት ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፡ ይሰጠዋል ፡

ከመ ፡ ይንብብ ፡ ምስሉ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡

የተመሰለው ፡ ምስል ፡ የተሣለው ፡ ሥዕ ል ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡

ወገብሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኢሰገዱ ፡ ለአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ አርዌ ፡ ከመ ፡ ይሙቱ ።

በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ለተመሰለው ፡ ምስል፡ ለተሣለው ፡ ሥዕል ፡ ያልሰገዱትን ፡ እን ዲሞቱ ፡ ያደርጋል ፡ (በዐዋጅ ፡ ነው) ።

፲፮ ፤ ወይገብር ፡ ኵሉ ፡ ንኡሱ ፡ ወዐቢዩ ፡

ታላቁ ፡ ታናሹም ፡

አብዕልት ፡ ወነዳያን ፡ አግብርት ፡ ወአግዐዝያን ፡

ድሆችም፡ባለጸጎችም፡ ጌቶችም፡ ባሮችም፡

ከመ ፡ ይጽሐፉ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ እንተ ፡የማን፡

በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው፡ ይጽፉ ፡ ዘንድ ፡

ወእመ ፡ አኮ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሞሙ ።

ያውም ፡ ባይሆን ፡ በግንባራቸው ፡ ይጽፉ፡ ዘንድ ፡ ያዝዛቸዋል ፡ እንዲጽፉ ፡ ያደርጋ ቸዋል ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፲፯ ፤ ወከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ሠይጦ፡ ወተሣይጦ ፡ እንበለ ፡ ጽሑፋን ፡ እሙንቱ ፡ ትእምርተ ፡ ስሙ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡

ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው፡ ከተከተቡ ፡ በግንባራቸው ፡ ከጻፉ፡ ሰዎች፡ በቀር ፡ የጻፉ ፡ ሰዎች ፡ እንጅ ፡ ዋጋ ፡ እንዳ ይገባላቸው ፡ ይከለክላል ፡

አው ፡ ዘኍልቈ ፡ ስሙ ።

ዘመርምያዋዖስ ፡ ብለው፡ ከጻፉ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ የጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ እንጅ ፡ ከእነሱ ፡ በቀር ።

፲፰ ፤ ወዘሰ ፡ ጠቢብ ፡ ውእቱ ፡

ብልህ ፡ አዋቂ ፡ የሆነ ፡

ወዘቦ ፡ ልብ ፡

ዕውቀት ፡ ያለው ፡

የአምር ፡ ኍላቈሁ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡

የሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ መጠኑን ፡ ያውቃል ፡

እስመ ፡ አምጣነ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ውእቱ ።

በሰው ፡ ልክ ፡ መጠን ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ከ ስንዝር ፡ ቁመት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ወኍላቈሁኒ ፡ ስድስቱ ፡ ምእት ፡ ወስሳ ፡ ወስድስቱ ።

ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ አሥ ራው ፡ ያሉት ፡ የዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ፍጥረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃል ። አንድም ፡ (ወዘ ሰ) ፡ ብልህ ፡አዋቂ ፡ የሆነ ፡ (ወዘቦ) ፡ ዕው ቀት ፡ ያለው ፡ የሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ የስ ሙን ፡ ቍጥር ፡ ያውቃል ፡ በእጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርምያዋዖ ስ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ሰባት ፡ ነው ፡



ስድስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ ስድስት ፡ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ሚም ፡ አርባ ፡ ምሜ ፡ አርባ ፡ ሰማንያ ፡ ዔ፡ ሰባ፡ ሰማንያና ፡ ሰባ ፡ መቶ፡ አምሳ ፡ ሬስ ፡ ሁለት ፡ መቶ፡ ሳን ፡ ሦስት፡ መቶ ፡ አምሳን ፡ ቢጨምሩ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዋው ፡ ስድስት ፡ ዮድ ፡ ዐ ሥር ፡ ስድስት ፡ መቶ፡ ስሳ ፡ ስድስት ፡ ይ ሆናል ። ም ፡ ፲፯ ፡ ፱ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፪ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩ ፤ ወእምዝ፡ቆመ፡ዝክቱ፡በግዕ፡ላዕለ፡ደብረ፡ ጽዮን፡

ይቀውም ፡ በግዕ ፡ ከመ ፡ ዘርጉዝ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ወእምዝ ፡ ቆመ ፡ አለ ፡ ዝክቱ ፡ በግዕ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቁሞ ፡ አየሁ ፡ ምጽአት ፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ ነውና። አንድም ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ በዐፈር ፡ በጠጠር ፡ ብሎ ፡ ጠላቱን ፡ ድል ፡ እንዲ ነሣ ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አየሁ ። አንድም ፡ በመስቀል ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አየሁ ፡

ወምስሌሁ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ እልፍ ፡ ወአርብዓ ፡ ምእት ፡

ከእሱም፡ ጋራ፡ እንደ፡ እሱ፡ ዐሥራ፡አራት፡ እልፍ ፡ ካራት፡ ሺሕ፡ ሰማዕታት፡ ሕፃናት ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ አየሁ ፡

ሕለ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሞሙ ፡ ስሙ ፡ ወስመ ፡ አቡሁ ፡ ወስመ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈሱ ።

በግንባራቸው ። አንድም ፡ በገጸ ፡ ልቡና ቸው ፡ ስመ ፡ ተወላዲ ፡ ስመ ፡ ወላዲ ፡ ስመ ፡ ሠራፂ ፡ የተጻፈባቸው ፡ ም ፡ ፯፡ ፬፡ ፱ ። ም ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፪ ፤ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ማይ ፡ ብዙኅ ፡

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ (ተሰማ) ፡ እንደ ፡ መጣያ ፡ ውኃ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ያ ፡ ከሩቅ ፡ እንዲሰማ ፡ ከሩቅ፡ የሚሰማ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብዙኅ ፡ ባለው ፡ ክቡድ ፡ ይላል፡ እንደ፡ ጕድጓድ ፡ ውኃ ፡ ፡ እንደ ፡ የሚያስፈራ ፡

ወከመ ፡ ቃለ ፡ ነጐድጓድ ፡ ዐቢይ ፡

እንደ ፡ ታላቅ ፡ ነጐድጓድ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡

ወቀመ ፡ ቃለ ፡ መሰናቁት ፡

እንደ ፡ መሰንቆ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡

ሶበ ፡ ይሰነቀዉ፡ በበመሰንቆታቲሆሙ ።

በየስልቱ ፡ በተመታ ፡ ጊዜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።


፫ ፤ ወየኀልዩ ፡ ማኅሌተ ፡ ሐዲሰ ፡

በእንግዳ ፡ ምስጋና ፡ ያመሰግናሉ ፡ አም ላክ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ እያሉ ፡

ቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ወቅድመ ፡ እልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ወእልክቱኒ ፡ ሊቃናት ።

በመንበሩ ፡ ፊት ፡ ባራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ በ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናት ፡ ፊት ፡ (ታሪክ) ፡ የአሥሩ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮራም ፡ የሁ ለቱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ይባ ላሉ ፡ ንጉሠ ፡ ሞአብ ፡ ላሥሩ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ይገዛል ፡ ንጉሠ ፡ ኤዶምያስ ፡ ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ይገዛል ፡ ንጉሠ፡ ሞአብ ፡ ባሥሩ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ አመፀ በት ፡ እርዳኝ ፡ ብሎ ፡ በሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ላከበት ፡ ንጉሠ ፡ ኤዶምያስን ፡ አስረድቶ ፡ ገሥገሥ ፡ በበረሃ ፡ ሲጓዝ ፡ በውኃ ፡ ፅምዕ ፡ የሚያልቁ ፡ ሆኑ ፡ የሁ ለቱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ከሆነ ፡ ፈጽሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አይለቅምና ፡ ኢሀሎኑ ፡ በገዝ ፡ ብሔር ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡

www.ethiopianorthodox.org



በግዕ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ።

ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ መኖሩንስ ፡ ሀሎ ፡ አሐ
ዱ ፡ ዘሐጸበ ፡ እዴሁ ፡ ለኤልያስ ፡ የኤልያ
ስን ፡ እጅ ፡ ያስታጥብ ፡ የነበረ ፡ ኤልሳዕ ፡
የሚባል ፡ አለ ፡ ለኔ ፡ በጎ ፡ አይመልስል
ኝም ፡ እንጅ ፡ አለው ፡ ከመዝሰ ፡ ኢት
በል ፡ ንጉሥ ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህስ ፡ አት
በል ፡ እንሂድ ፡ አለው ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ፡
ባየው ፡ ጊዜ ፡ ምንት ፡ አምጽአከ ፡ ኀቤየ ፡
አላ ፡ ሑር ፡ ተሰአሎሙ ፡ ለነቢያተ ፡ አበ
ዊከ ፡ ከአምላከ ፡ አቃሮን ፡ ከበዐለ ፡ ጽን
ጽንያ፡ ሂድ፡ እንጅ ፡ ከእኔ፡ ዘንድ ፡ለምን ፡
መጣህ ፡ ብሎ ፡ ተቆጣበት ፡ እኔማ ፡ አላ
ልሁህም ፡ አለው ። ከመዝሰ ፡ ኢትበል ፡
ነቢየ ፡ እግዚ

www.ethiopianorthodox.org



ብሔር፡ እንዲህስ ፡ አትበል ፡ አምጽአነኑ ፡
ዝየ፡ እግዚአብሔር፡ ለሠለስቱ ፡ ነገሥት ፡
ከመ፡ይቅትለነ፡በፅምዕ፡ አለው። ሶበሰ፡ ኢ
ኀፈርኩ፡ ገጾ፡ ኢዮሳፍጥ፡እምኢርኢኩከ፡ገ
ጸከ፡ወእምኢርኢከኒ፡ገጽየ፡አሁን፡ ኢዮሳፍ
ጥን ፡ ባላፍር ፡ ፊትህን ፡ ባላየሁትም፡ ነበ
ር። አሁንም፡አምጽኡ፡ብእሴ፡ ሠናየ፡ዘይዜ
ምር ፡ በገና ፡ አስማምቶ ፡ የሚመታ ፡ አም
ጡልኝ ፡ አለ ፡ አመጡለት ፡ ያ ፡ አሥሩን ፡
ጣቶቹን ፡ ካሥሩ ፡ አውታረ ፡ በገና ፡ አስ
ማምቶ ፡ ሲመታ ፡ ተገልጾለት ፡ እንዘ ፡ ኢ
ትሬእዩ ፡ ደመና ፡ (ነፋስም ፡ ይላል) ፡ ነ
ፋስ ፡ ሳይነፍስ ፡ ደመና ፡ ሳይዞር ፡ ዘንሞ
ላችሁ ፡ ጠጥታችሁ ፡ ታድራላችሁ ፡ በየ
ድንኳናችሁ ፡ ደጅ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፍሩ ፡
አላቸው ፡ ነፋስ ፡ ሳይነፍስ ፡ ደመና ፡ ሳይ
ዞር ፡ ዝናም ፡ ዘንሞላቸው ፡ ጕርፉ ፡ በየጕ
ድጓዳቸው፡ መልቶላቸው፡ አድሯል፡ በነጋ
ው ፡ የጥዋት፡ ጮራ፡ ወድቆበት፡ ለሞአብ፡
ሰዎች ፡ ደም ፡ መስሎ ፡ ታይቷቸዋል ፡
እሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ነገሥታት ፡ ተቃተሉ ፡
በበይናቲሆሙ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተዋ
ግተው ፡ አልቀዋል ፡ ምርኮውን ፡ እንካ
ፈል ፡ ብለው ፡ ሄዱ ፡ ተሰልፈው ፡ ቈይ
ተው ፡ ገጠሚቸው ፡ እስራኤል ፡ ድል ፡
አድርገዋቸዋል ፡ ንጉሡ ፡ ኤዶምያስ ፡ ባለ
በት ፡ በኩል ፡ ንጉሡ ፡ ሞአብ ፡ ጥቂት ፡
ራሱን ፡ ሁኖ ፡ ሲሸሽ ፡ የንጉሡ ፡ ኤዶም
ያስን ፡ ልጅ ፡ ነጥቆ ፡ ወስዶ ፡ ግምስስ ፡
ለሚባል ፡ ጣዖት፡ሠውቶበት፡በዚህ፡ ብቻ፡
አዝነዋል ፡ እንጅ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ድል ፡
አድርገው ፡ ተመልሰዋል ። ያ ፡ ዐሥሩን ፡
ጣቶቹን ፡ ካሥሩ፡ አውታረ፡ በገና፡ አስማ
ምቶ፡ሲመታ፡ተገልጾለት፡ትንቢት፡ እንደ፡
ተናገረ ። የመቤታችንም ፡ ዐሥሩ ፡ ሕዋ
ሳቶችዋ ፡ በዐሥሩ ፡ ቃላት፡ ጸንተው ፡ ቢ
ገኙ ፡ ጌታ ፡ ከእመቤታችን ፡ ተወልዶ ፡
አምላክ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡
ሆነ ፡ እያሉ ፡ ለማመስገናቸው ፡ ምሳሌ ፡

ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ አእምሮታ ፡ ለይእቲ ፡ ማኅሌት ፤

ያችን ፡ ምስጋና ፡ ሊያውቃት ፡ የሚቻ
ለው ፡ የለም ፡ ሐተታ ፡ ሥራቸውን ፡ ካል
ሠራ ፡ ከመዐርጋቸው ፡ አይደርስም ፡ ከመ
ዐርጋቸውም ፡ ካልደረሰ ፡ ምስጋናቸውን ፡
ማመስገን ፡ የሚቻለው ፡ የለምና ፡

ዘእንበለ ፡ እልክቱ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ እልፍ ፡
ወአርብዓ ፡ ምእት ፡ እለ ፡ ተቤዘዉ ፡ እምነ፡ ምድረ ፡
ግብፅ ።

ካሥራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡
ሰማዕታት ፡ ሕፃናት ፡ በቀር ፡ (እለ ፡ ተቤ
ዘዉ) ፡ ከፍዳ ፡ የዳኑ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፱ ።

፬ ፤ እለ ፡ ንጹሓን ፡ እሙንቱ ፡ እምአንስት ፡

ከኃጢአት፡ ንጹሐን፡ የሆኑ፡ (ጥቅ)፤ ብእሲ
ት፡ትንብር፡ ማእከለ፡ መስፈርት፡ እንዲል።

በከመ ፡ ተወልዱ ፡ እሙንቱ ፡

እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ጊዜ ፡ ንጹሓን ፡ የሆኑ ፡
ሰማዕታት ፡ በንስሓ ፡ ሕፃናት ፡ በንጽሓ ፡
ጠባይዕ ። አንድም ፡ እምአንስት ፡ በከመ ፡
ተወልዱ ፡ ከናቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ተወለዱ፡
ንጹሐን ፡ የሚሆኑ ፡ ሕፃናት ፡ በንጽሓ ፡
ጠባይዕ ። እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ጊዜ ፡ ንጹ
ሐን ፡ የሚሆኑ ፡ ሰማዕታት ፡ በንስሓ ፡

እለ ፡ ተለውዎ ፡ ለበግዑ ፡ ኀበ ፡ ሖረ ።

በጉን ፡ ወደሄደበት ፡ የተከተሉት ፡ አለ ፡
አብነት ፡ ያደረጉት ፡

እለ ፡ ቀደሙ ፡ ተቤዝዎ ፡ እምነ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ወለበግዑ ።

ከኃጢአት ፡ የነጹ ፡ ከፍዳ ፡ የተለዩ ፡ ከሰ
ው ፡ ተለይተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለበ
ግዑ ፡ ማደሪያ ፡ ለመሆን ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡
፪ ። ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፳፯ ። ም ፡ ፫ ፡ ፱ ።

፭ ፤ ወኢተረክበ ፡ ሐሰት ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡

ባንደበታቸው ፡ ሐሰት ፡ ያልተገኘበት ፡ ሰማዕታት ፡ በንስሓ ፡ ሕፃናት ፡ በንጽሓ ፡ ጠባይዕ ።

እስመ ፡ ንጹሐን ፡ እሙንቱ ፡ እምኃጢአት ።

ከኃጢአት ፡ ንጹሐን ፡ ናቸውና ፡ ሰማዕ ታት፡ በንስሓ፡ሕፃናት፡ በንጽሓ፡ ጠባይዕ።

፮ ፤ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ እንዘ ፡ ይሠርር ፡ ማእከለ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ በሕዋ ፡ እየበረረ ፡ መጣ ፡ ሲመጣ ፡ አየሁ ፡

ወይጸውር ፡ ወንጌለ ፡ ዘለዓለም ፡

የዘለዓለም ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ ተሸክሟ ል ፡ አለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝ ዣለሁ ፡ ይላል ።

ከመ ፡ ይስብክ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ፡ ምድር፡

በምድር ፡ ለሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዣለሁ ፡ ይላል ፡

ወለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ወሕዝብ ፡ ወነገድ ፡ ወበሐ ውርት ።

ለሕዝቡ ፡ ለአሕዛቡ ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ውን ፡ በሐውርት ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፯ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ፍርህዎ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ወሰብሕዎ ፡ እስመ ፡ በጽሐት ፡ ሰዓተ ፡ ደይኑ ፡ ዐቢይ ።

የሚፈርድባት ፡ ጊዜ ፡ ደርሳለችና ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ፍሩት ፡ ወሰብሕዎ ፡ አመ ስግኑት ፡ እያለ ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ታዝ ዣለሁ ፡ ይላል ፡

ወስገዱ ፡ ሎቱ፡ ለዘገብረ፡ ሰማየ፡ ወምድረ፡ ወባሕረ፡ ወአፍላገ ፡ ወአንቅዕተ ፡ ማያት ።

ሰማዩን ፡ ምድሩን ፡ ባሕሩን ፡ ፈሳሹን ፡ ምንጩን ፡ ለፈጠረ ፡ ለእሱ ፡ ስገዱ ፡ እያ ለ ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዣለሁ ፡ ይላል ፡ ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፫ ። የሐዋ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

፰ ፤ ወካልዕ ፡ መልአክ ፡ ተለዎ ፡

ሁለተኛው ፡ መልአክ ፡ ተከተለው ፡ ያል ታወቀ ፡ መልአክ ፡ ነው ፡

እንዘ ፡ ይብል ፡ ወድቀት ፡ ባቢሎን ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡ እምነ ፡ ወይነ ፡ መንሱታ ፡ ወዝሙታ ፡ ዘአስተየት ፡ ለኵሉ ፡ አሕዛብ ።

አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አበርትታ ፡ ጥላ ፡ ካጠ ጣቻቸው ፡ ጠጅ ፡ የተነሣ ፡ ደጊቱ ፡ አገ ር ፡ ባቢሎን ፡ ተፈታች ፡ እያለ ፡ ተከት ለው ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ናት ፡ ም ፡ ፲፰፡፪። ኢሳ ፡ ፳፩ ፡ ፱ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፰ ።

፱ ፤ ወሣልስ ፡ መልአክ ፡ ተለዎ ፡

ሦስተኛው ፡ መልአክ ፡ ተከተለው ፡

እንዘ ፡ ይብል ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡

በታላቅ፡ ቃል፡እንዲህ፡ እያለ፡ ተከተለው ፡

ዘሰገደ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ወለምስሉ ፡

ለሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ የሰገደ ፡ በሐሳዊ ፡ መ ሢሕ ፡ ለተሳለው ፡ ሥዕል ፡ ለተመሰለው፡ ምስል ፡ የሰገደ ፡

ወዘጽሑፍ ፡ ትእምርተ ፡ ስሙ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ፡ አው ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።

ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብሎ ፡ በግንባሩ ፡ የጻ ፈ ፡ በእጁ ፡ የተከተበ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ።

፲ ፤ ይስተይ ፡ ውእቱኒ ፡ ወይነ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ዘቅዱሕ ፡ ውስተ ፡ ጽዋዐ ፡ መዓቱ ፡

መዓቱ ፡ በሚገለጥበት ፡ ሥራ፡ የሚፈጸም፡ ጠጅ ፡ መዓትን ፡ ይሰቲ ፡ ይቀምሳል ፡ ይስ ተይ ፡ ይቅመስ ፡

ዘኢኮነ ፡ ቱሱሐ ፡

ጠጅ ፡ ምሕረቱ ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ፍ ሡሐ ፡ ይላል ፡ ወይን ፡ ያስተፌሥሕ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ እንዳለው፡ ያይደለ፡ ሐተታ፡ ቀዳማዊ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሣ ልስ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ። አን ድም ፡ ቀዳማዊ ፡ መልአክ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ጌታ ፡ ሣል ስ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ። አንድም፡ ቀዳማዊ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ሣ ልስ ፡ መልአክ ፡ ያልታወቀ ። አንድም ፡ ቀዳማዊ ፡ መልአክ ፡ ጌታ ፡ ካልእ ፡ መል አክ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሣልስ ፡ መል አክ ፡ ያልታወቀ ፡ ሐዋርያ ፡ ነው ፡

ወይትኴነን ፡ በእሳት ፡ በቅድመ ፡ መላእክቲሁ ፡ ወበ ቅድመ ፡ በግዑ ።

በመላእክት፡ በበግዑ፡ፊት፡ይፈረድበታል፡ ይትኴነን ፡ ይፈረድበት ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ። ኤር ፡ ፳፭ ፡ ፲፭ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፲፩ ፤ ወዐርገ ፡ ጢሰ ፡ ደይኖሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡

የዘለዓለም ፡ የፍርጃቸው ፡ ጢስ ፡ ወጣ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ተመዞ ፡ ሲወጣ፡ ያየዋል ፡ በሐልዮ ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ እንደ ፡ ተፈረደባቸው ፡ ለማጠየቅ ፡

ወአልቦሙ ፡ ዕረፍት ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ፍዳቸውን ፡ ሲቀበሉ ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ፡

ወዘንተ ፡ ኵነኔ ፡ ይረክቡ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ፡ ወለምስሉ፡ ወእለ፡ይጽሕፉ፡ ትእምርተ፡ስሙ ።

ለሐሳዊ፡መሢሕ፡የሰገዱ፡ አለ፡ ለተለሣው፡ ሥዕል ፡ ለተመሰለው ፡ ምስል ፡ የሰገዱ ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ የጻፉ ፡ ይህን ፡ ፍዳ ፡ ይቀበላሉ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፫ ።

፲፪ ፤ ወዝ፡ ውእቱ፡ ትዕግሥቶሙ፡ ለቅዱሳን ፡ እለ ፡ የዐቅቡ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጠብቁ ፡ የቅዱሳን ፡ ትዕግሥታቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አንድም፡ ይህን፡ ያስደርግላቸዋል ።

ወሃይማኖቶ ፡ ለኢየሱስ ።

በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማመናቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አንድም ፡ ይህን ፡ ያስደርግ ላቸዋል ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፲ ። ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ።

፲፫ ፤ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተሰማ ።

ጸሐፍ ፡ ይእዜ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ በእንተ ፡ እግ ዚአብሔር ፡

በእግዚአብሔር ፡ አምነው ፡ በሰማዕት ነት ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተሰማ ፡

እወ ፡ ከማሁ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዕውነት ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ብሏልና ፡

ከመ ፡ ያዕርፉ ፡ እምነ ፡ ጻማሆሙ ፡

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚደክሙት ፡ ድካም ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ፡

ወይተልዎሙ ፡ ግብሮሙ ፡

ግብራቸው ፡ ይከተላቸዋል ፡ አለ ፡ ዋጋ ቸውን ፡ ያሰጣቸዋል ፡

ወይወስዶሙ ፡ ኀበ ፡ ነቅዐ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡

በልጅነት ፡ ወደሚገኘው ፡ ክብር ፡ መርቶ፡ ያደርሳቸዋል፡ ኢሳ፡ ፶፯፡ ፩፡ ፪ ። ዕብ፡ ፬፡፲፡

፲፬ ፤ ወመጽአት ፡ ደመና ፡ ብርህት ፡

ብህርት ፡ ደመና ፡ መጣች ፡ አለ ፡ የባሕ ርይ፡ክብሩ ፡ ተገለጠች ፡

ወውስተ ፡ ይእቲ ፡ ደመና ፡ ይነብር ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡

በደመናይቱ ፡ ውስጥ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡



www.ethiopianorthodox.org

እመሕያው ፡ ተቀምጧል ፡ አለ ፡ በባሕ
ርይ ፡ ክብሩ ፡ ተገለጠ ።

ወአክሊለ ፡ ወርቅ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡

ለምእመናን ፡ የሚሰጣቸው ፡ ክብር ፡ የባ
ሕርዩ ፡ ነው ፡

ወማዕፀድ ፡ በሊሕ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡

ዓለሙን ፡ (ሰውን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡
የሚያሳልፍበትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡
አድርጓል ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፲፫ ። ማቴ ፡ ፲፫ ፡
፴፱ ፡ ፵፩ ።

፲፭ ፤ ወወጽአ ፡ካልእ ፡ መልአክ ፡ እምነ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

አንድ ፡ መልአክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መቅ
ደስ፡ ወጣ፡ አለ፡ ከዓለመ፡ መላእክት፡ነው፡

ወይጸርኅ ፡ ሎቱ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ለዘይነብር ፡
ውስተ ፡ ደመና ፡ ወይብል ፡

በባሕርይ ፡ ክብሩን፡ ለገለጠ ፡ ለእሱ፡ እን
ዲህ ፡ አለው ፡

ፈኑ ፡ ማዕፀደከ ፡ በሊሐ ፡

ዓለሙን ፡ የምታሳልፍበትን ፡ ሰውን ፡
የምታጠፋበትን ፡ ሥልጣን ፡ ግለጥ ፡

ወዕዐድ ፡

ዓለሙን ፡ አሳልፍ ፡ ሰውን ፡ አጥፋ ፡
አለው ፡

እስመ ፡ በጽሐት ፡ ሰዓት ፡ ለዐፂድ ፡

ዓለሙን ፡ ሰውን ፡ የሚያሳልፍበት ፡ ጊዜ፡
ደርሷልና ፡

እስመ ፡ የብሰ ፡ ማእረረ ፡ ምድር ።

የሚያልፍ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኢዮ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፮ ፤ ወእምዝ ፡ አልዐለ ፡ ማዕፀደ ፡ ውእቱ ፡ ዘይነ
ብር ፡ ውስተ ፡ ደመና ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ የተገ
ለጠ ፡ እሱ ፡ ሥልጣኑን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ገለጠ ፡

ወተዐፅደት ፡ ምድር ።

ዓለም ፡ አለፈ ፡ (ሰዉ ፡ ጠፋ ፡ ቢል ፡ አን
ድ ፡ ነው) ።

፲፯ ፤ ወወፅአ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ እምነ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከዓለመ ፡
መላእክት ፡ መጣ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡
ነው ፡

ወይጸውር ፡ ውእቱኒ ፡ ማዕፀደ ፡ በሊሐ ።

ዓለሙን ፡ የሚያሳልፍበትን ፡ ሥልጣን ፡
ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ (ሰውን ፡ የሚያጠፋ
በትን ፡ ሥልጣን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።

፲፰ ፤ ወካልእ ፡ መልአክ ፡ ተለዎ ፡ እምነ ፡ ምሥ
ዋዕ ፡ ዘውእቱ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ እሳት ፡

ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከዓለመ ፡ መላእክት ፡
ተከተለው ፡ ይኸውም ፡ መጋቤ ፡ እሳት ፡
መልአክ ፡ ነው ፡

ወጸውዖ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ለዝኩቱ ፡ ዘይጸውር ፡ ማዕ
ፀደ ፡ በሊሐ ።

ዓለሙን ፡ የሚያሳልፍበትን ፡ ሥልጣን ፡
ገንዘብ ፡ ያደረገውን ፡ መልአክ ፡ በታ
ላቅ ፡ ቃል ፡ ጠርቶ ፡ (ሰውን ፡ የሚያጠፋ
በትን ፡ ሥልጣን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።

ወይቤሎ ፡ ፈኑ ፡ ማዕፀደከ ፡ በሊሐ ፡

ዓለሙን ፡ የምታሳልፍበትን ፡ ሥልጣን ፡
ግለጥ ፤ (ሰውን ፡ የምታጠፋበት ፡ ቢል ፡
አንድ ፡ ነው) ።

ወቅስም ፡ አስካሎ ፡ ለዐፀደ ፡ ወይና ፡ ለምድር ፡

ዓለሙን ፡ አሳልፍ ፡ ሰውን ፡ አጥፋ ፡
አለው ።

እስመ ፡ ዐቢይ ፡ አስካሉ ።

በሰለ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ የሚያልፍበት ፡
ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡ ሰው ፡ የሚጠፋበት ፡
ጊዜ ፡ ደርሷልና ።



፲፱ ፤ ወነሥአ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ማዕፀዶ ፡ ወአ
ውረደ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

መልአክ፡ እንደ ፡ ማጭድ ፡ መክድን ፡ ያለ፡
ሰይፍ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሲጥል ፡
ያየዋል ፡ አለ ፡ ዓለሙን ፡ የሚያሳልፍበ
ትን፡ ሰውን ፡ የሚያጠፋበትን ፡ ሥልጣን ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ገለጠ ፡

ወቀሠመ ፡ ቦቱ ፡ ዐጸደ ፡ ወይና ፡ ለምድር ፡

ዓለሙን ፡ አሳለፈ ፡ (ሰውን ፡ አጠፋ ፡ ቢል
አንድ ፡ ነው) ።

ወወደዮ ፡ ውስተ ፡ ምክያደ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ዐቢይ ፡

የእግዚአብሔር ፡ መዓቱ ፡ በሚፈጸምበት፡
አውድማ ፡ ጨመረው ፡ አለ ፡ መዓቱ ፡
በሚፈጸምበት ፡ ሥራ ፡ አጠፋው ፡ ም ፡
፲፱ ፡ ፲፭ ።

፳ ፤ ወአኬድዎ ፡ በምክያድ ፡ በአፍአ ፡ እምነ ፡
ሀገር ፡

ከከተማ ፡ በአፍአ ፡ በአውድማ፡ ጠመቁት፡

ወወፅአ ፡ ደም ፡ እምነ ፡ ውእቱ ፡ ምክያድ ፡

ደሙ፡ በአውድማው፡ ፈሰሰ ፡ ሐተታ፡ በወ
ይን፡ግሥ፡ተናግሮታል፡አውድማ፡ አበጅተ
ው፡በኖራ፡ ለቅልቀው፡ መካከሉን፡ እንደ፡
ጭልባ ፡ ጕድጓድ ፡ አበጅተው ፡ ከመካ
ከሉ ፡ የብረት ፡ ጋን ፡ ያኖራሉ ፡ አፉን ፡
እንደ ፡ ወንፊት ፡ ያለ ፡ ሰቅሰቅ ፡ ገጥ
መው ፡ ይተውታል ፡ እግራቸውን ፡ ታጥ
በው ፡ ወይኑን ፡ ካውድማው ፡ ላይ ፡ ያሹ
ታል ፡ ደሙ ፡ እየወረደ ፡ ከጋኑ ፡ ይመላ
ልና ፡ በዚያ ፡ ግሥ ፡ ተናግሮታል ፡

ወበጽሐ ፡ እስከ ፡ ልጓመ ፡ ፈረስ፡

እስከ ፡ ፈረስ ፡ ዕምቢያ ፡ ድረስ ፡ ደረሰ ፡
(ጥቅ)፡ወፈረስ ፡ የሐውር ፡ እስከ ፡ እንግድ
ዓሁ ፡ በደም ፡ ወሠረገላ ፡ ትሰጠም ፡ እስ
ከ ፡ መልዕልታ ፡ እንዲል ፡

ወውሒዘ ፡ እስከ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወስድስቱ ፡ ምዕራፍ ።

እስከ ፡ አስራ ፡ ስድስት ፡ ምዕራፍ ፡ ድረስ፡
ደረሰ ። አጼ ፡ መለከ ፡ ሰገድ ፡ ፈላሻን ፡
በካይላ ፡ሜዳ ፡ ባስፈጁ ፡ ጊዜ ፡ ደሙ ፡
ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ድንኳን ፡ እንዳስነቀለ ።
አንድም ፡ (ወመጽአ ፡ ደመና) ፡ ባሕርየ ፡
ቃል ፡ በሥጋ ፡ ተገለጠ ። (ወውስተ ፡ ይ
እቲ) ፡ እመቤታችን ፡ ጌታን ፡ ለመውለድ፡
በቅታ ፡ ተገኘች ። አንድም ፡ ሥጋ ፡ ባሕር
የ፡ ቃልን ፡ በተዋህዶ ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል፡
ቃል ፡ የመቤታችነን ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡
አድርጎ፡ ከእመቤታችን፡ ተወልዷል።(ወአ
ክሊለ ፡ ወርቅ) ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡
ክብርን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ። ወማዕፀድ፡
ወንጌል ፡ በቃሉ ፡ ይነገራል ፡ (ወወፅአ) ፡
ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከዓለመ ፡ መላእክ
ት ፡ ወጣ ፡ ከእመቤታችን ፡ ለተወለደ ፡
ለእርሱ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ነገረው፡ ባሕ
ርየ ፡ ቃልን ፡ በተዋሕዶ ፡ ገንዘብ፡ ላደረገ፡
ለወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዲህ ፡
አለው ። (ፈኑ ፡ ማዕፀደከ) ፡ ወንጌል ፡ እን
ድትነገር ፡ አድርግ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አሳ
ምን ፡ አለው ፡ (እስመ ፡ በጽሐ)፡ ወንጌል ፡
የምትነገርበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያምን
በት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡ (እስመ ፡ የብሰ)፡
የሚያምን ፡ ስለ ፡ ሆነ ። (ወእምዝ ፡ አል
ዐለ)፡ ከዚህ፡በኋላ፡ ከእመቤታችን፡ የተወለ
ደ ፡ ባሕርየ፡ ቃልን ፡ በተዋሕዶ ፡ ገንዘብ ፡
ያደረገ ፡ እሱ ፡ ወንጌል ፡ እንድትነገር ፡
አደረገ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ነው ። (ወተዐፅ
ደት) ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አመነ ፡ (ወወፅአ ፡
ካልእ) ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከዓለመ ፡ መላ
እክት ፡ ወጣ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡
ከልዑል ፡ ባሕርዩ ፡ ተገለጠ ፡ በልዕልና ፡
ካለ ፡ ከምስጉን ፡ ባሕርዩ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡
ነው ፡ ተገለጠ ፡ (ወይጸውር) ፡ ወንጌል ።

www.ethiopianorthodox.org

በቃሉ ፡ ትነገራለች ፡ (ወካልዕ ፡ መልአክ) ሌላ ፡ መልአክ ፡ ተከተለው ፡ (ዘውእቱ) ፡ ይኸውም ፡ መጋቤ ፡ እሳት ፡ መልአክ ፡ ነው ፡ አለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በማሰጠት ፡ ሥሉጥ ፡ የሆነ ፡ ሐዋርያ ፡ ተከተለው ፡ (ወጸውዖ ፡ በቃል) ፡ ወንጌል ፡ በቃሉ ፡ የምትነገር ፡ እሱን ፡ ጠርቶ ፡ ወንጌል ፡ እንድትነገር ፡ አድርግ ፡ (ወቅሥም) ፡ ሰውን ፡ አጥፋ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሰማዕትነት ፡ እንዲሞት ፡ አድርግ ፡ አለው ፡ የሚጠፋበት ፡ የሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡ ወንጌል ፡ በቃሉ ፡ እንድትነገር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሰማዕትነት ፡ እንዲሞት ፡ አደረገ ፡ ሰውን ፡ አሳመነ ፡ (ወወደዮ) ፡ ኃጥአን ፡ በሚጠፉበት ፡ መቅሠፍት ፡ ጻድቃን ፡ እንዲጠፉ ፡ አደረገ ፡ (ወአኬድዎ)፡ ጻድቃንን ፡ ሰማዕታትን ፡ ከከተማ ፡ በአፍኣ፡ ደበደብዋቸው፡ ደማቸው፡ ባደባባይ፡ ፈሰሰ፡ (ወበጽሐ)፡ ነገረ ፡ መስቀልን፡ በሚናገሩበት ፡ በሚያስተምሩበት፡ በአፋቸው፡ ደም ፡ አስጎነጭዋቸው፡ (ወውሕዘ)፡እስከ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሥዩማን፡ እስከ፡ አራቱ፡ ጾታ፡ምእመናን፡ደረሰ፤አራቱ፡ጾታ፡ ምእመናን ፡ ዕድ ፡ ወአንስት ፡ አዕሩግ ፡ ወሕፃናት ፡ ዐቢይ ፡ ወንኡስ ፡ ገብር፡ ወአግዐዚናቸው ፡ ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፫ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፭።

፩ ፤ ወአስተርአየ ፡ ተአምር ፡ ዐቢይ ፡ በሰማይ ፡

በሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ምልክት ፡ ታየ ፡

ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ፡ ይጸውሩ ፡ ሰብዐተ ፡ መቅሠፍተ ፡ በዘቦቱ ፡ የኀልቅ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር፡ መዓቱ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ የታዘዙ ፡ ሰባት ፡ መላእክት ፡ ታዩ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ም፡ ፲፩፡ ፲፰።

፪ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ባሕረ ፡ እንተ ፡ ትመስል ፡ ከመ ፡ ማህው ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሞ ፡ የምትመስል ፡ ባሕር ፡ አየሁ ፡

ወድምርት ፡ ይእቲ ፡ በእሳት ፡

እሳት ፡ የተቀላቀለባት ፡

ወእልክቱ ፡ እለ ፡ ሞዕዎ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ወለምስሉ ፡ ወለኍልቈ ፡ ስሙ ፡

ሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ ለምስሉ ፡ ያልሰገዱ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ በእጃቸው ፡ ያልተከተቡ ፡ በግንባራቸው ፡ ያልጻፉ ፡

ይቀውሙ ፡ ላዕለ ፡ ይእቲ ፡ ባሕር ፡

በዚያች ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ቁመዋል ። አንድም ፡ ባሕር ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡ ናት ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ አየሁ ፡ ሞ ፡ የምትመስል ፡ አለ ፡ ሞ ፡ እንድትወደድ ፡ የምትወደድ ፡ ፍቅሯ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ያቃጥላል ፡ ሐሳዌ፡ መሢሕን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ ለምስሉ ፡ ያልሰገዱ ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ ያልጻፉ ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ ንቀዋታል ፡ አጥቅተዋታል ። አንድም ፡ ተዋልጦተ ፡ ገድልን ፡ አየሁ ፡ (እንተ ፡ ትመስል ፡ ከመ ፡ ማህው) የሞ ፡ ኅብሯ ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተዋልጦተ ፡ ገድልም ፡ ኅብሯ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ (ወድምርት) ፡ ሰማዕታትን ፡ አናዳ ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ጻድቃንን ፡ አናዳ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ትወስዳለች ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ ለምስሉ ፡ ያልሰገዱ ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ ያልጻፉ ፡ በተዋልጦተ ፡ ገድል ፡ ጸንተዋል ። አንድም ፡ እመቤታችንን ፡ አየሁ ፡ (እንተ ፡ ትመስል) ፡ ገጸ

www.ethiopianorthodox.org



ሕናዋን ፡ መናገር ፡ ነው ። (ወድምርት) ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮባታል ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ ለምስሉ ፡ ያልሰገዱ ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ ያልጻፉ ፡ በእመቤታችን ፡ አምነው ፡ ጸንተዋል ። አንድም ፡ ጥምቀትን ፡ አየሁ ፡ (እንተ ፡ ትመስል) ፡ ጽርየቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወድምርት) ፡ ልጅነትን ፡ ታሰጣለች ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ ለምስሉ ፡ ያልሰገዱ ፡ ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ ያልጻፉ ፡ በጥምቀት ፡ ጸንተዋል ፡

ወይጸውሩ ፡ መሰንቆ ፡ መዝሙር ፡ ዘእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ የሚያመሰግኑበትን ፡ አንደበት ፡ ገንዘብ ፡ በማድረግ ፡ ጸንተዋል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፮ ። ም ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ። ም ፡ ፳ ፡ ፰ ።

፫ ፤ ወይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአ ፡ ኵሉ ፡

ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፡

በከመ ፡ ሰብሐ ፡ ሙሴ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡

ሙሴ ፡ ንሴብሖ ፡ ብሎ ፡ እንዳመሰገነ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ያመሰግኑታል ፡

በስብሐተ ፡ በግዑ ፡

በግዑም ፡ አእኰተከ ፡ አባ ፡ እግዚአ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ብሎ ፡ እንዳመሰገነ ፡ ይሴብሕዎ ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ በበግዑ ፡ ምስጋና ፡ የማንከ ፡ እግዚአ ፡ ተሰብሐ ፡ በኀይል ፡ ብሎ ፡ እንዳመሰገነ ፡ ይሴብሕዎ ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ ንሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስቡሐ ፡ ዘተሰብሐ ፡ ብሎ ፡ እንዳመሰገነ ፡ ይሴብሕዎ ፡ በስብሐተ ፡ በግዑ ፡ በበጉ ፡ ምስጋና ፡ የማንከ ፡ እግዚአ ፡ ተሰብሐ ፡ በኀይል ፡ መንክር ፡ ስብሐቲከ ፡ ዘትገብር ፡ መድምመ ፡ ብለው ፡ ይሴብሕዎ ፡ ያመሰግኑታል ።

ወይብሉ ፡ ዐቢይ ፡ ወመድምም ፡ ግብርከ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ተመልከ ፡

ሁሉን ፡ የምትገዛ ፡ በሁሉ ፡ አድረህ ፡ የምትኖር ፡ አቤቱ ፡ ሥራህ ፡ ድንቅ ፡ ነው፡ እያሉ ፡ ያመሰግኑታል ፡

ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ፍናዊከ ።

ፍርድህ ፡ ጽድቅ ፡ ርትዕ ፡ ነው ፡ ጽድቅ ፡ ለጻድቁ ፡ ፈርዶ ፡ የሚሰጠው ፡ ዋጋ ፡ ርትዕ ፡ በኃጥኡ ፡ ፈርዶ ፡ የሚያመጣው ፡ ፍዳ ፡ ፍናዊከ ፡ የወል ፡ ነው ፡

ዘነገሥከ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ።

በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሠልጥነህ ፡ የምትኖር ፡ ዘፀአ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፻፵፭ ፡ ፲፯ ። ም ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ።

፬ ፤ ወመኑ፡ ዘኢይፈርሀከ ፡ ወኢይሴብሐ ፡ ለስምከ ፡

የማይፈራህ ፡ የማያመልክህ ፡ ማነው ፡ ለስምህስ ፡ ምስጋና ፡ የማያቀርብ ፡ ማነው ፡

እስመ ፡ ባሕቲትከ ፡ ጻድቅ፡ አንተ ፡ ወሥሉጥ ፡ አንተ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ፡

አንተ ፡ ብቻ ፡ ጻድቀ ፡ ባሕርይ ፡ ነህና ፡ በአሕዛብም ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለህ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡ ስምህን ፡ የማያመሰግን ፡ ማነው ፡

ወይሰግዱ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሉ ፡ ተግባርከ ፡

አቤቱ ፡ ፍጥረቶችህ ፡ ሁሉ ፡ ላንተ ፡ ይሰግዳሉ ፡ አለ ፡ ላንተ ፡ ይገዛሉ ፡

እስመ ፡ አስተርአየ ፡ ኵነኔከ ።

ፍርድህ ፡ ታውቋልና ፡ መዝ ፡ ፹፯ ፡ ፱ ።

፭ ፤ ወእምድኅረዝ፡ ተርኅወ ፡ መቅደስ ፡ ዘደብተራ፡ ስምዕ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡ መቅደስ ፡ ተከፈተ ፡ ሐተታ ፡ በሰማይ ፡ መከፈት ፡ መዘጋት ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፡ የተዘጋ ፡ ቤት ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ያልታየ ፡ ዕቃ ፡

እንዲታይ ፡ ያልተገለጠ ፡ ምስጢር ፡ ተገ
ለጠ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡
ነው ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ መሠረቷ ፡ በሰ
ማያዊት ፡ ደብተራ ፡ ብርሃን ፡ አምሳል ፡
ነውና ፡ ምሳሌዋን ፡ ሲያይ ፡ ዘደብተራ ፡
ስምዕ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ።

፮። ወወፅኡ ፡ እልክቱ ፡ ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡
ይጸውሩ ፡ ሰብዐተ ፡ መቅሠፍተ ፡ እምነ ፡ መቅደሱ ፡

ሰባት ፡ ማሠሬ ፡ ሰባት ፡ ጨንገሬ ፡ የያዙ ፡
አለ ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ የታዘዙ ፡ ሰባት ፡
መላእክት ፡ ሲወጡ ፡ አየሁ ፡

ወይለብሱ ፡ አልባሰ ፡ ንጹሐ ፡ ወብሩሀ ፡

ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ፡ አለ ፡ ጸጋቸ
ውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወቅኑታን ፡ እሙንቱ ፡ በቅናተ ፡ ወርቅ ፡ እንተ ፡ መን
ገለ ፡ እንግድአቲሆሙ ፡

በደረታቸው ፡ የወርቅ ፡ ዝናር ፡ ታጥቀ
ዋል ፡ አለ ፡ እስከ ፡ ደረታቸው ፡ እንደ ፡
ድግ ፡ መተው ፡ ያይዋቸዋል ፡ ተገዥ
ዎች ፡ ነን ፡ ሲሉ ። አንድም ፡ እንደ ፡ ተቋ
ጠረ ፡ አቅማዳ ፡ ሁነው ፡ ያይዋቸዋል ፡
ያ ፡ የላዩ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የታቹ ፡ ወደ ፡ ላይ፡
እንዳይተላለፍ ፡ ባሕርይህን ፡ መተላለፍ ፡
አይቻለንም ፡ ሲሉ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።

፯። ወአሐዱ፡ እምነ፡ እልክቱ ፡ አርባዕቱ እንስሳሁ፡
ካራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ አንዱ ፡

መጠዎሙ፡ ለእልክቱ፡ሰብዐቱ ፡ መላእክት፡ ሰብዐተ፡
ጽዋዐተ ፡ ወርቅ ፡ ምሉዓነ ፡ መዓቱ፡ ለእግዚአብሔር፡
ዘሕያው ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለሰባቱ ፡ መላእክት ፡ የዘለዓለም ፡ ሕያ
ው ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መዓቱ ፡
የተመላበትን ፡ ሰባት ፡ የወርቅ ፡ ጽዋዕ ፡
ሰጣቸው ፡ አለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መዓቱ፡
የሚፈጸምበትን ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ አዘዛ
ቸው ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፯—፰ ። ም ፡ ፲፩ ፡ ፲ ።

፰። ወእምዝ ፡ መልአ ፡ መቅደሱ ፡ ጢሰ ፡ መዓቱ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ እምስብሐቲሁ ፡ ወእምኀይሉ ፡

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከጌትነቱ ፡ ከከሃሊነቱ ፡
የተነሣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የመዓቱ፡ ጢስ፡
በመቅደሱ ፡ መላ ፡ አለ ፡ በዓለመ ፡ መላ
እክት ፡ ምሕረት ፡ ተከለከለ ፡

ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ በዊአ ፡ ውስተ ፡ መቅደሱ ፡

ከከሃሊነቱ ፡ ከጌትነቱ ፡ የተነሣ ፡ ከመላ
እክት፡ ወገን፡ ማማለድ፡ የተቻለው፡የለም፡

እስከ ፡ ኀልቀ ፡ ሰብዐቱ ፡ መቅሠፍት ፡ ዘሰብዐቱ ፡
መላእክት፡

ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ የሚሠሩት ፡ ሰባት ፡
ሥራ፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፡ ዘፀአ፡ ፴ ፡ ፴፩።
ነገሥ ፡ ፰ ፡ ፲ ። ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩ ። ሕዝ ፡ ፵፬፡፩፡

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩። ወይቤሎሙ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ እምነ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ለእልክቱ ፡ ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡

በሰማይ ፡ካለ ፡ ከዓለመ ፡ መላእክት ፡ ቃ
ል፡ ሰባቱን፡መላእክት፡ እንዲህ፡ አላቸው ፡

ሑሩ ፡ ወከዐዉ ፡ ጽዋዐ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ውስተ ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡

ሂዳችሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የመዓቱን ፡
ጽዋዕ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ አፍስሱ ፡ አላ
ቸው ፡ አለ ፡ መዓቱ ፡ የሚፈጸምበትን ፡
ሥራ ፡ ሥሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡
ም ፡ ፲፭ ፡ ፯ ።

፪። ወሖረ ፡ መልአክ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወከዐወ ፡ ጽዋዖ ፡
ውስተ ፡ ምድር ፡

መዠመሪያው ፡ መልአክ ፡ ሂዶ ፡ በም
ድር ፡ ጽዋዑን ፡ አፈሰሰ ፡ አለ ፡ በየብስ ፡
ሥራውን ፡ ሠራ ፡





መላእክት ፡ ከመቅደሱ ፡ እየወጡ ፡ የመዓቱን ፡ ጽዋዕ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳፈሰሱ ።

ወመጽአ ፡ ላዕለ ፡ እልክቱ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ጸሐፉ ፡ ትእ
ምርቶ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ወሰገዱ ፡ ለምስሉ ።

የሐሳዌ ፡ መሢሕን ፡ ምልክት ፡ ዘመር ፡
ዘመስ ፡ ብለው ፡ በጻፉ ፡ በእሱ ፡ ለተሣ
ለው ፡ ሥዕል ፡ ለተመሰለው ፡ ምስል ፡
በሰገዱ ፡

መጽአ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ጸልዕ ፡ እኩይ ፡

መጽአና፡መጽአ፡ አንድ፡ወገን፡ነው፡ ክፉ ፡
ቍስል ፡ መጣባቸው ፡ ዋጣ ፡ ቂጥኝ፡ ችፌ፡
ኀርምጥ ፡ ቍስለ ፡ ሥጋ ፡ ነው ። አንድም፡
ብቻ ፡ ኃላፍያትን ፡ አያሳየውም ፡ መጻእ
ያትንም ፡ ያሳየዋል ፡ ብሎ ፡ በሽሕ ፡ ቢ

www.ethiopianorthodox.org

መጡ ፡ ቀዳማዊ ፡ መልአክ ፡ ሙሴ ፡ ነው ፡ ሐመደ፡ ዕቶኑን፡ ዘግኖ ፡ በግብፅ ፡ በበተ ነው ፡ ጊዜ ፡ በግብፃውያን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ታዘዘባቸው ፡ ዘፀአ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።

፫ ፤ ወከዐወ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ጽዋዖ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ።

በሁለተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሁለተኛው ፡ መልአክ ፡ በባሕር ፡ ጽዋዑን ፡ አፈሰሰ ፡ አለ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

ወኮነት ፡ ባሕር ፡ ደመ ።

ባሕር ፡ ደም ፡ ሆነች ፡

ወሞተ ፡ ኵሉ ፡ ነፍስ ፡ ሕይወት ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ።

በባሕር ፡ ተፈጥሮ ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕይ ወት ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሞተ ፡ አለ ፡ ጠፋ ፡ ምግብ ፡ ቢለወ ጥበት ፡ በፅምዕ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ ኢያሱ ፡ ነው ፡ በኢያሪኮ ፡ ሥራ ውን ፡ ሠራ ፡ አሕዛብ ፡ ጠፉ ፡ ዘፀአ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።

፬ ፤ ወከዐወ ፡ ሣልስ ፡ መልአክ ፡ ጽዋዖ ፡ ውስተ ፡ አፍላግ ፡ ወውስተ ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት ፡

በሦስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሦስተኛው ፡ መ ልአክ ፡ በአፍላግ ፡ በአንቅዕት ፡ ጽዋዑን ፡ አፈሰሰ ፡ አለ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ አፍ ላግ ፡ አንቅዕት ፡ ሐተታ ፡ እንደ ፡ ቀደ መው ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፲ ።

ወኮኑ ፡ ደመ ፡ ኵሉ ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት ።

አንቅዕትም ፡ ሁሉ ፡ ደም ፡ ሆኑ ፡ ዘፀአ ፡ ፯ ፡ ፲፱—፳፩ ።

፭ ፤ ወይቤ ፡ መልአከ ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት ፡ ጻድቅ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወራትዕ ፡

መጋቤ ፡ ማያት ፡ መልአክ ፡ ነው ፡ ፈታ ሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ የምት ሆን ፡ አቤቱ ፡ ዕውነትን ፡ የምትፈርድ ፡ ዕውነተኛ ፡ አቤቱ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ዘሀለውከ ፡

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበርህ ፡

ወትሄሉ ፡

ዓለሙን ፡ አሳልፈህ ፡ የምትኖር ፡

ከመዝ ፡ ኰነንከ ።

እንዲህ ፡ ፈረድህ ፡ እንዲህ ፡ ፈረድህን ፡ እንዲህ ፡ ፈረድህ ፡ አለ ።

፮ ፤ እስመ ፡ ከዐዉ ፡ ደመ፡ ቅዱሳኒከ ፡ ወነቢያቲከ ፡

የወዳጆችህ ፡ የነቢያት ፡ የሐዋርያትን ፡ ደም ፡ አፍስሰዋልና ፡

ወአስተይካሆሙ ፡ ደሞሙ ፡

ፍዳቸውን ፡ አመጣህባቸው ፡

እስመ ፡ ይደልዎሙ ።

የሚገባቸው፡ ስለ ፡ ሆነ። አንድም፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ ሣልስ ፡ መልአክ ፡ ሳሙኤል ፡ ነው ፡ በእስራኤል ፡ በልዑላኑ ፡ በትሑ ታኑ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ (ወኮኑ) ፡ እስራ ኤል ፡ ጠፉ ፡ (ወይቤ) ፡ መጋቤ ፡ እስራ ኤል ፡ ኤሊ ፡ ነው ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነ በርህ ፡ ዓለሙን ፡ አሳልፈህ ፡ የምትኖር ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ አቤቱ ፡ እንዲህ ፡ ፈረድህ ፡ (እስመ ፡ ከ ዐዉ ፡ ደመ) ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ በቅ ተው ፡ የሚሠውትን ፡ መሥዋዕት ፡ ሳይ በቁ ፡ ሰውተዋልና ። አንድም ፡ የነቢያት ፡ የሐዋርያት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ ደመ ፡ አባግዕን ፡ ሰውተዋልና ።

፯ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዘይቤ ፡ በውስተ ፡ ምሥዋዕ፡

በዓለመ ፡ መላእክት ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡

እወ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ትመልክ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ኵነኔከ ።

ሁሉን ፡ ፈጥረህ ፡ የምትገዛ ፡ በሁሉ ፡ አድ ረህ ፡ የምትኖር ፡ አቤቱ ፡ ፍርድህ ፡ ጽድ ቅ ፡ ርትዕ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፪ ።

፰ ፤ ወከዐወ ፡ ራብዕ ፡ መልአክ ፡ ጽዋዖ ፡ ውስተ ፡ ፀሓይ ፡

በራተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አራተኛው ፡ መል አክ ፡ በፀሓይ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡

ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ሐሩር ፡ ከመ ፡ ያውዕዮ ፡ ለሰብእ ፡ በእሳት ።

ሰውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥለው ፡ ዘንድ ፡ ሐሩር ፡ ተሰጠው ፡ የተሰጠውስ ፡ በተፈ ጥሮ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ በፅምዕ ፡ ይፈ ጀው ፡ ዘንድ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ ዋ ዕዩ ፡ ጮራው ፡ ተለክቶ ፡ ተለክቶ ፡ ተመ ጥኖ ፡ ተመጥኖ ፡ የሚወጣበት ፡ እንደ ፡ ጽንሐሕ ፡ እንደ ፡ ግርግራ ፡ እንደ፡ አልጋ፡ መለበምያ ፡ ያለ ፡ አለ ፡ ባራተኛው ፡ መን ፈቅ ፡ የማይሠራ ፡ ሥራ ፡ የለም ፡ መል አኩ ፡ ያን ፡ ሰብሮ ፡ ይጥለዋል ፡ ዋዕየ ፡ ፀሓይ ፡ ይጸናል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በፅምዕ ፡ ያልቃልና ።

፱ ፤ ወውዕየ ፡ ሰብእ ፡ በዐቢይ ፡ ሐሩር ፡

ሰው ፡ ሁሉ ፡ በፅምዕ ፡ አለቀ ፡

እስከ ፡ ይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘው እቱ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ እልክቱ ፡ መቅሠፍታት ።

ይህን ፡ መቅሠፍት ፡ ማምጣት ፡ የሚቻ ለው ፡ መሐሪ ፡ መስተሣሕል ፡ የሚባል ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጽኑዕ ፡ ጨካኝ ፡ ብለው ፡ እስኪሰድቡ ፡ ድረስ ፡

ወኢነስሑ ፡ ከመ ፡ ያእኵትዎ ።

ያምኑበት ፡ ዘንድ ፡ አልተመለሱም ። አን ድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ፡ በኤልያስ ፡ ጊዜ፡ የሆነውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ቀኍ ፡ ፳፩ ። ም ፡ ፱ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።

፲ ፤ ወከዐወ ፡ ኃምስ ፡ መልአክ ፡ ጽዋዖ ፡ ላዕለ ፡ መንበሩ ፡ ወላዕለ ፡ መንግሥቱ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡

ባምስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ አምስተኛው ፡ መልአክ ፡ በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ በግዛቱ ፡ በከተማው ፡ ጽዋዑን ፡ አፈሰሰ ፡ አለ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ።

ወጸልመት ፡ መንግሥቱ ፡

መንግሥቱ ፡ እጠፋ ፡ እጠፋ ፡ አለች ፡

እስከ ፡ ይሜጽሩ ፡ ልሳናቲሆሙ ፡ ሰብእ ፡ በሕማም ።

ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ሰዎች ፡ ምላሳቸውን ፡ እስኪያላምጡ ፡ ድረስ ፡ (ጥቅ) ፡ እለ ፡ ሥርወ፡ ዕፅ ፡ ይሜጽሩ ፡ እን ዲል ፡ ዘፀአ፡ ፲፡ ፳፩ ። ኢሳ፡ ፰ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

፲፩ ፤ ወእስከ ፡ ይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአ ፡ ሰማይ ፡ እምነ ፡ ሕማመ ፡ አጽልዕቲሆሙ ፡

ከመከራውም ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ሰማ ዩን ፡ ምድሩን ፡ የብሱን ፡ ባሕሩን ፡ የፈ ጠረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጨካኝ ፡ ብለው ፡ እስኪሰድቡ ፡ ድረስ ፡ (በሰማይ ፡ በምድር፡ ያለ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡

ወኢነስሑ ፡ እምነ ፡ ግብሮሙ ፡

ከክፉ ፡ ሥራቸውም ፡ አልተመለሱም ። አንድም ፡ በሽሕ ፡ ቢመጡ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነው ፡ በምናሴ ፡ በግዛቱ ፡ በከተማው ፡ ሥራውን ፡ ሠራ ፡ የምናሴ ፡ መንግሥቱ ፡ ጠፉች ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፳ ።

፲፪ ፤ ወከዐወ ፡ ሳድስ ፡ መልአክ ፡ ጽዋዖ ፡ ውስተ ፡ ፈለግ ፡ ዐቢይ ፡ ዘኤፍራጥስ ፡

በስድስተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ስድስተኛው ፡ መልአክ ፡ በታላቁ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ፡ ጽዋዑን ፡ አፈሰሰ ፡ አለ ፡ ሥራውን ፡ ሠራ፤ በሠራ ፡ ጊዜ ።

ወየብሰ ፡ ማዩ ፡ ከመ ፡ ትደሎ ፡ ፍኖቶሙ ፡ ለነገሥት ፡ እለ ፡ እምነ ፡ ምሥራቀ ፡ ፀሓይ ።

ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚመጡ፡ ነገሥታት፡ ጐዳናቸው ፡ ጥርጊያ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ውኃው ፡ ደረቀ ፡ ማለት ፡ ተከፈለ፡ ደቂቀ፡
ኬሬቢ ፡ ናቸው ፡ ታሪክ ፡ ሥጋ ፡ ከመብ
ላት ፡ ጠጅ ፡ ከመጠጣት ፡ ተከልክለው ፡
ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ዩዋዩ ፡ ቢደርስ ፡ ጌታ ፡
ኤርምያስን ፡ ጠርቶ ፡ ደቂቀ ፡ ኬሬቢን ፡
ለይልኝ ፡ አለው ፡ ለየለት ፡ በደመና ፡ አፋ
ፍሶ ፡ ወስዶ ፡ ብሔረ ፡ አዛፍ ፡ ጥሏቸ
ዋል ፡ ብሔረ ፡ ዕረፍት ፡ ማለት ፡ ነው ፡
ብሔረ ፡ ብፁዓን ፡ ነው ፡ ከዘጠኙ ፡ ነገ
ድ ፡ ተከልም ፡ ተወጣጥተው ፡ ሚጠት ፡
በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ምንት ፡ ኃጢአቱ ፡ ለይ
ሁዳ፡ አኮኑ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወምንት፡ ጌጋዩ፡
ለእስራኤል ፡ አኮኑ ፡ ሰማርያ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
እንጅ፡ የደረሰብን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደግ፡ አገ
ር ፡ናት ፡ እህሉን ፡ ተክሉን ፡ ታበቅላለች ፡
ያበቀለችውን ፡ እህል ፡ ተክል ፡ በልተን ፡
ከጥጋባችን፡ የተነሣ፡ ኃጢአት ፡ ብንሠራ ፡
አይደለምን፡ እንግዲህ፡ ከዚያ፡አገር፡አንመ
ለስም፡ ብለው፡እግራቸው፡እንዳወጣቸው፡
ሲሄዱ፡ከምውት፡ባሕር፡ደርሰዋል፡ሣር፡የዶ
ሮ፡ላባ፡ቢጥሉበት፡ የሚያሠጥም፡ነው፡ ተከ
ፍሎላቸው፡ተሻግረው፡ ብሔረ፡ አዛፍ፡ ገብ
ተዋል ፡ ብሔረ ፡ ዕረፍት ፡ ማለት ፡ ነው ፡
ዕድሜያቸው ፡ አንድ፡ሺሕ ፡ ዘመን ፡ነው ፡
በሺሕ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ከምሽቶቻቸው ፡
የሚገናኙ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ነው ፡ በሦስት ፡
ቀን፡ ሩካቤ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ይወልዳሉ ፡
አንዱን፡ ለቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ይሰጣሉ ፡
ሁለቱን ፡ ለዘርዕ ፡ ይተዋሉ ፡ በሚሞቱ
በትም ፡ ጊዜ ፡ መቃብራቸውን ፡ ቈፍረው፡
ዘመዶቻቸውን ፡ ተሰነባብተው ፡ ይሞታ
ሉ፡ ጌታ፡ እሑድ፡ እሑድ፡ እየገባ፡ ያስተም
ራቸው ፡ ነበር ፡ ኋላም ፡ ማቴዎስ ፡ ገብቶ ፡
አስተምሯቸዋል ፡ ኋላም ፡ ዞሲማስ ፡ ከዳ
ርና ፡ ከዳር ፡ ዛፍ ፡ ገጥሞለት ፡ ገብቶ ፡
አይቷቸው ፡ ወጥቷል ፡ ስፍራ ፡ ሁለት ፡
የሚለላኩ ፡ ብላቴናዎችም ፡ ጨምረው ፡
ሰጥተውታል ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ መጥ
ተው ፡ ንገሩልን ፡ አሉ ፡ ገብተው ፡ ነገ
ሩት ፡ ሥራ፡ ይዞ ፡ ነበረና፡ ተኝቷል ፡ በሉ፡
አላቸው ፡ ወጥተው ፡ ተኝቻለሁ ፡ ይላል ፡
አሏቸው ፡ በሀገራቸው ፡ ሐሰት ፡ አልተ
ለመደም ፡ ነበረና ፡ በሀገራችን ፡ ጠልተ
ነው ፡ የመጣነውን ፡ ሐሰት ፡ ሊያስተምር
ብን ፡ ነውን ፡ ውጣልን ፡ አሉት ፡ ወጥቶ ፡
ሲሄድ ፡ ፍቅር ፡ ኀሎበታልና ፡ ዛፉ ፡ የማ
ይገጥምለት ፡ ሆነ ፡ ተመልሶ ፡ ማሩኝ ፡
ብሎ ፡ ከእግራቸው ፡ ወድቆ ፡ ቢሄድ ፡ ገጥ
ሞለት ፡ ወጥቶ ፡ ሂዷል ፡ በስድስተኛው ፡
መንፈቅ ፡ ተከፍሎላቸው ፡ ወጥተው ፡
በኢየሩሳሌም፡ በሰማዕትነት፡ ይሞታሉና ፡
ትደሎ፡ ፍኖቶሙ፡ አለ። አንድም ፡ በሺሕ ፡
ቢመጡ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ነው ፡ በፈለገ ፡
ኮቦር ፡ ሥራውን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ሙስና ፡
መቃብር ፡ ጠፋ ፡ የነፍሳት ፡ ጐዳናቸው ፡
ጥርጊያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ (ሐተታ) ፡ በፀጋ
ማዊት፡ኀኑ ፡ ተኝቶ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ጹሞ ፡ ከስ
ድስት ፡መቶ ፡ የሚበዙ ፡ ሙታን ፡ አስ
ነሥቷል ፡ኢሳ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።

፲፫ ፤ ወእምዝ ፡ ወፅኡ ፡ እምነ ፡ አፉሁ ፡ ለዝክቱ ፡
አርዌ ፡ ቀዳማዊ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዲያብሎስ ፡ ሥልጣን ፡

ወእምአፉሁ ፡ ለሐሳዌ ፡ ነቢይ ፡ ሠለስቱ ፡ አጋንንት ፡
ርኵሳን ፡

በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ትእዛዝ ፡ በሐሳዌ ፡
ኤልያስ ፡ ሥልጣን ፡ ሦስት ፡ አጋንንት ፡
ወጡ ፡ ርኵሳን ፡ ልዩ ፡ የሚሆኑ ፡ አጋ
ንንት ፡

ወከመ ፡ ቈርነናዓት ፡ እሙንቱ መንፈስ፡ አጋንንት ።

ተሳቦ ፡ ቀንዳም ፡ ትል ፡ ዛጎል ፡ ል
ብሱ ፡ ጓጉንቸር፡ ይመስላሉ፡ (መንፈስ ፡
አጋንንት) ፡ አጋንንት ፡ ናቸው ፡ ቢሉ ፡



ባሕርየ ፡ አጋንንት ፡ አላቸው ፡ (አካለ ፡
አጋንንት ፡ ቢሉ ፡ ይሆናል) ፡ ሰዎች ፡
ናቸው ፡ ቢሉ ፡ ሀብተ ፡ አጋንንት ፡ አድ
ሮባቸዋል ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፲ ። ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።
ም፡፲፫፡፲፩።ዘፀአ፡፳፡፺።፩፡ነገሥ፡፳፪ ፡ ፳፩።

፲፬ ፤ ወይገብሩ ፡ ተአምራተ ፡

የምትሐት ፡ ታምራት ፡ ያደርጋሉ ፡

ወይወፅኡ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ነገሥት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡
ኵሉ ፡ ዓለም ፡

ባራቱ፡ መዓዝን፡ ወዳሉ ፡ ነገሥታት ፡ ይወ
ጣሉ ፡

ወያስተጋብእዎሙ ፡ ይትቃተሉ ፡ በዕለት ፡ ዐባይ ፡
እንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ።

ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ ይመልዕ ፡
ቢል ፡ በሁሉ ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በሚፈርድባት ፡ በቍርዕ ፡
ፍርድ ፡ ቀን ፡ ይዋጉ ፡ ዘንድ ፡ ይሰበስ
ቧቸዋል ፡ (ይሰበስቧቸው ፡ ዘንድ ፡ ይወ
ፅኡ ፡ ይሄዳሉ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡
ም ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ።

፲፭ ፤ ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ግብተ ፡ ከመ ፡ ሰራቂ ፡
ወብፁዕ ፡ ዘይትጌሀ ፡ ወየዐቅብ ፡ አልባሲሁ ፡ ከመ ፡
ኢይሑር ፡ ዕራቆ ፡ ወኢያስተርኢ ፡ ኀፍረቱ ።

ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ግብተ ፡ ከመ ፡ ሰራቂ ፡
ብሏልና ፡ ተግቶ ፡ ልብሱን ፡ የሚጠብቅ ፡
ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ (ከመ ፡ ኢይ
ሑር ፡ ዕራቆ) ፡ ዕራቁቱን ፡ እንዳይሄድ ፡
(ወኢያስተርኢ) ፡ ዕርቃኑ ፡ እንዳይገለጽ።
አንድም ፡ ሰውነቱን ፡ ተግቶ ፡ ከኃጢአት፡
የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡
ከክብር ፡ ባዶ ፡ እንዳይሆን ፡ ክብር ፡ እን
ዳያጣ ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፭ ፡ ፪ ። ም ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፮ ፤ ወያስተጋብእዎሙ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘስሙ ፡
አርማርጌዶን ፡ በዕብራይስጥ ፡

(ያስተጋብእሙ ፡ ቢል) ፡ በዕብራይስጥ ፡
አርማጌዶን ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፡ ይሰበስባ
ቸዋል ፡ አለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ያስተጋብእ
ዎሙ ፡ ሠለስቱ ፡ አጋንንት ፡ ያላቸው ፡
ይሰበስቧቸዋል ፡ አርማጌዶን ፡ ማለት ፡
መካነ፡ ድምሳሴ፡ መካነ ፡ ሥራዌ፡ ማለት፡
ነው ፡ መሳ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ፴፩ ። ፪ ፡ ነገሥ ፡
፱ ፡ ፳፯ና ፡ ፳፫ ፡፳፱ ። ዘካ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ።

፲፯ ፤ ወከዐወ ፡ ሳብዕ ፡ መልአክ ፡ ጽዋዖ ፡ ውስተ ፡
ነፋስ ፡

በሰባተኛው ፡ መንፈቅ ፡ ሰባተኛው ፡ መል
አክ፡ በነፋስ፡ ሥራውን፡ ሠራ፡ በሠራ፡ጊዜ፡

ወወፅአ ፡ ቃል ፡ ዐቢይ ፡ እምነ ፡ መቅደሱ ፡ ወእም
ኀበ ፡ መንበሩ ፡ ዘይብል ፡ ኀልቀ ።

ከዓለመ ፡ መላእክት ፡ ከመንበሩ ፡ ሰባቱ ፡
መላእክት ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ደረሰ ፡
ተፈጸመ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተሰማ ።

፲፰ ፤ ወእምዝ፡ ኮነ ፡ መብረቅ፡ ወቃለ ፡ ነጐድጓድ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መብረቅ ፡ ነጐድጓድ፡ ሆነ፡
አለ ፡ ኀልፈተ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ፡

ወመጽአ ፡ ዐቢይ ፡ ድልቅልቅ ፡ ዘኢኮነ ፡ ከማሁ ፡
እምአመ ፡ ተፈጥረ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ውስተ ፡
ምድር፡ ወኢይከውንሂ፡ ዘከማሁ፡ ድልቅልቅ፡ ዐቢይ።

ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ሆኖ ፡ የማያ
ውቅ ፡ ከእንግዲህም፡ የማይሆን፡ ፍጹም ፡
መነዋወጥ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ ኀልፈተ ፡ ዓለም ፡
ሆነ ።በሺሕ፡ ቢመጡ፡ ሳብዕ፡መልአክ፡ዮሐ
ንስ ፡ መጥምቅ፡ ነው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ሥራውን፡ ሠራ፡ (ወወፅአ፡ ቃል)፡ አካላዊ ፡
ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ ተወልዶ ፡ አም
ስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ የነ
በረ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ ጠፋ ፡ እያለ ፡ ሲያ
ስተምር ፡ ተሰማ ፡ (ወእምዝ ፡ ኮነ) ፡ ከዚ
ህ ፡ በኋላ ፡ ስብከተ ፡ ሐዋርያት ፡ ተደረገ ፡
(ወመጽአ ፡ ዐቢይ ፡ ድልቅልቅ) ፡ ዓለም ፡
ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ሁኖ ፡ የማያውቅ ፡
ከእንግዴህም፡ ወዲህ፡ የማይሆን፡ ስብከት፡

www.ethiopianorthodox.org

ሆነ ፡ አለ ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፰ና ፡ ፫ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ።

፲፱ ፤ ወኮነት ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡ ሠለስተ ፡ መክፈልተ ፡

ደጊቱ ፡ ሀገር ፡ ባቢሎን ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለች ፡ አለ ፡ መከራው ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ መጣባት ፡ አባር ፡ ቸነፈር ፡ ጦር ። አንድም ፡ ሦስት ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ሰፈሩባት ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አሕዛብ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ምእመናን ፡ አንድ ፡ ወገን ። አንድም ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡ ገሃነም ፡ ናት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለች ፡ አለ ፡ ሦስት ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ ስለ ፡ ሰፈሩባት ፡ አጋንንት ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ መናፍቃን ፡ መናፍቃንስ ፡ ዘውእቶሙ ፡ እለ ፡ ያጣዕዉ ፡ ይላቸዋል ፡ ብሎ ፡ መናፍቃንና ፡ መምለክያነ፡ ጣዖት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኃጥአን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ ስለሚሠፍሩባት ፡

ወአህጉረ ፡ አሕዛብኒ ፡ ወድቃ ፡

የአሕዛብም ፡ ሀገሮች ፡ ተፈቱ ፡

ወለባቢሎንኒ ፡ ዐባይ ፡ ተዘከርዋ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይመጥውዋ ፡ ጽዋዐ ፡ ሕምዘ ፡ ወይነ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ደጊቱ ፡ ሀገር ፡ ባቢሎን ፡ ከሁሉ ፡ ተለይታ ፡ እንዴት ፡ በሽታ ፡ ትሙት ፡ ብለው፡ ጠጅ ፡ መዓቱን ፡ ያቀምሷት ፡ ዘንድ ፡ ፍትሖ ፡ ርትዕ ፡ ሥላሴ ፡ በመዓት ፡ አሰብዋት ፡ አዘከርዋ ፡ ቢል ፡ መላእክት ፡ አሳሰብዋት ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፫ ። ም ፡ ፲፬ ፡ ፲ ፡

፳ ፤ ወጠፍአ ፡ ኵሎን ፡ ደስያት ፡ ወአድባርኒ ፡ ኢተረክቡ ።

ደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ጠፉ ፡ አድባርም ፡ ሁሉ ፡ ቀንተው ፡ አልተገኙም ፡ ም፡ ፮ ፡ ፲፬ና ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።

፳፩ ፤ ወወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ ዐቢይ ፡ በረድ ፡ ዘመጠነ ፡ መክልይ ፡

ጉልቻ ፡ ጉልቻ ፡ የሚያህል፡ በረድ ፡ ከሰማይ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ወርዷልና ፡ ኢተረክቡ ፡ ላለው ፡ መድሎቱ ፡ ይላል ፡ ሚዛኑ ፡ መክሊት ፡ የሚያነሣ ፡ በረድ ፡ ወርዷልና ፡

ወፀረፉ ፡ ሰብእ ፡ ላዕለ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ መቅሠፍተ ፡ በረድ ፡

ስለ፡ በረዱ ፡ መቅሠፍትነት፡ ስለ ፡ በረዱ ፡ መቅሠፍት ፡ ሰዎች ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ የተባለ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጽኑ ፡ ጨካኝ ፡ አሉ ፡

እስመ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ጥቀ ።

መቅሠፍቱ ፡ መቅሠፍትነቱ፡ ጽኑ ፡ ነውና፡ ዘፀአ ፡ ፱ ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡

፩ ፤ ወመጽአ ፡ አሐዱ ፡ እምነ ፡ እልክቱ ፡ ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ይጸውሩ ፡ ሰብዐተ ፡ ጽዋዓተ ፡

ሰባት ፡ ጽዋ ፡ ከያዙ ፡ ከሰባቱ ፡ መላእክት፡ አንድ ፡ መልአክ ፡ መጣ ፡ አለ ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ ከታዘዙ ፡ ከሰባቱ ፡ መላእክት ፡ አንድ ፡ መልአክ ፡ መጣ ፡

ወይቤለኒ ፡ ነዓ ፡ አርኢከ ፡ ደይና ፡ ለእንታክቲ ፡ ዘማ ፡ ዐባይ ፡ እንተ ፡ ትነብር ፡ ውስተ ፡ ማያት ፡ ብዙኅ ።

በብዙ ፡ ውኃ ፡ ላይ ፡ በተቀመጠች ፡ በዚያች ፡ ታላቅ ፡ ዘማ ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፩ ፡



፪ ፤ እንተ ፡ ምስሌሃ ፡ ዘመዉ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ፡

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ከሷ ፡ ጋራ ፡ እንደሷ ፡ የሴሰኑ ፡ አለ ፡ እሷን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ኃጢአት ፡ በሠሩ ።

ወሰክሩ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምነ ፡ ወይነ፡ ዝሙታ ።

አበርትታ ፡ ጥላ ፡ ካጠጣቻቸው ፡ ጠጅ ፡ የተነሣ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ አእምሯቸውን ፡ ያጡ ፡ አለ ፡ አብነት ፡ ሆና ፡ ካሠራቻቸው ፡ ኃጢአት ፡ የተነሣ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ በፍዳ ፡ በተያዙ ፡ በዚያች ፡ በቤተ ፡ አይሁድ ፡ የሚፈርድባትን ፡ ፍርድ ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፰ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፯ ።

፫ ፤ ወእምዝ ፡ ወሰደኒ ፡ መንፈስ ፡ ገዳመ ፡

ከዚህ፡ በኋላ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አነሳሥቶ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ወሰደኝ ፡ (የራእይ ፡ ነው) ፡

ወርኢኩ ፡ ብእሲተ ፡ ትጼዐን ፡ ላዕለ ፡ አርዌ ፡ ቀይሕ፡ ዘምሉእ ፡ አስማተ ፡ ፅርፈት ፡ ዘሰብዐቱ ፡ አርእስቲሁ ፡ ወዐሠርቱ ፡ አቅርንቲሁ ።

አንዲት ፡ ሴት ፡ የስድብ ፡ ስም ፡ በተመላበት፡ ሰባት ፡ ራሶች፡ ዐሥር ፡ ቀንዶች ፡ ባሉት ፡ በቀይ ፡ አውሬ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ አየሁ ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ናት ፡ በሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ሠልጥና ፡ አየሁ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።

፬ ፤ ወትለብስ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ልብሰ ፡ ወርቅ ፡ ዘቦ ፡ ሜላት ፡

ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ያለበት፡ ነጭ፡ ሐር ፡ ግምጃ ፡ ለብሳለች ፡

ወዘቦ ፡ ለይ ፡ ወዕንቍ ፡ ክቡር ፡ ወባሕርያት ፡

የዕንቍ ፡ የሉል ፡ ፈርዕ ፡ ያለበት ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ለብሳለች ፡ ሐተታ ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ከብዕላቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ አራት ፡ ኅብር ፡ አምስተኛ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ፡ ይለብሳሉና ፡

ወትጸውር ፡ ውስተ ፡ እዴሃ፡ ጽዋዐ፡ ወርቅ ፡ ዘምሉእ፡ ርኵሰ ፡ ወግማኔ ፡ ዝሙታ ።

በእጅዋም ፡ ኃጢአት ፡ ዝሙት ፡ የተመላበት ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ይዛለች ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ከብዕላቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ በወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ይጠጣሉና ፡ ሐተታ፡ ያነኑን ፡ በዐስበ ፡ ደነስ ፡ በማግለጃ፡ ያመጡታልና፡ በዐስበ ፡ ደነስ ፡ በማግለጃ ፡ ያመጡትን ፡ ይበሉበታል ፡ ይጠጡበታልና ፡ ዘምሉእ ፡ ርኵሰ ፡ ወግማኔ ፡ አለ ፡ ሕዝ ፡ ፳፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፯ ።

፭ ፤ ወጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ፍጽማ ፡ አስማተ ፡ ምሥጢራ ፡ ለባቢሎን ፡ ዐባይ ፡

የባቢሎን ፡ ኅቡዕ ፡ ስሟ ፡ በግምባሯ ፡ ተጽፏል ፡

ዘይብል ፡ እሞን ፡ ለዘማት ፡ ወዘርኵሳ ፡ ለምድር ።

የኃጥአን ፡ እናታቸው ፡ የኃጣውእ ፡ ነቃቸው ፡ የምትሆን ፡ የባቢሎን ፡ ኅቡዕ ፡ ስሟ ፡ በግንባሯ ፡ ተጽፏል ። አንድም ፡ የኃጥአን ፡ እናታቸው ፡ የኃጣውእ ፡ ነቃቸው ፡ ናት ፡ የሚል ፡ ኅቡዕ ፡ ስሟ ፡ ተጽፏል ፡ ፪፡ ተሰ ፡ ፪፡ ፯ ። ራእ፡ ፲፬ ፡ ፰ና ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ዳን ፡ ፬ ፡ ፳፯ ።

፮ ፤ ወስክርት ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ እምደሞሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወእምደሞሙ ፡ ለጻድቃኒሁ ፡ ለኢየሱስ ።

በቅዱሳን ፡ ደም ፡ ሰክራለች ፡ አለ ፡ በሰማዕትነት ፡ በሞቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ጻድቃን ፡ ደም ፡ በመጣ ፡ ፍዳ ፡ ተይዛለች ፡

ወአንከርክዋ ፡ ሶበ ፡ ርኢክዋ ፡ ዐቢየ ፡ ተደመምኩ ።

ባየኋትም ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አደነቅሁ ፡ ወሶበ ፡ ርኢክዋ ፡ አንከርክዋ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፳፬ ።

፯ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዝኩቱ ፡ መልአክ ፡ ምንተ ፡ ታነክር ፡

ያም፡ መልአክ፡ ምን ፡ ታደንቃለህ፡ አለኝ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አነ ፡ እነግረከ ፡ ምሥጢራ ፡ ለዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ወለ ዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ዘይጸውራ ፡ ወሰብዐቱ ፡ አርእስቲሁ ፡ ወዐሠርቱ ፡ አቅርንቲሁ ።

የዚያችን ፡ ሴት ፡ ትርጓሜ ፡ የተሸከማትንም ፡ አውሬ ፡ የሰባቱንም ፡ አርእስት ፡ ያሥሩንም ፡ ቀንዶች ፡ ትርጓሜ ፡ እኔ ፡ እነግርሃለሁ ።

፰ ፤ ወዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ዘርኢከ ፡ ሀለወ ፡ ወኢ ሀለወ ፡

ያ ፡ ያየኸው ፡ አውሬ ፡ በገናንነት ፡ አለ ፡ በገናንነት ፡ የለም ፡

ወሀለዎ ፡ ይዕርግ ፡ እምነ ፡ ቀላይ ፡

ከከተማ ፡ ነግሦ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ አለው ና ፡ ሀለወ ፡ ላለው ፡

ወየሐውር ፡ ለሙስና ፡

ፈጥኖ ፡ ይጠፋልና ፡ ኢሀለወ ፡ ላለው ፡

ወይደመሙ ፡ በእንቲአሁ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ያምኑበታል ፡

እለ ፡ ኢኮነ ፡ ጽሑፈ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ መጽ ሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ዘእምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡

ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ስማቸው ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፈ ፡ አለ ፡ ስማቸው ፡ በልበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለበ ጎው ፡ ነገር ፡ ያልታወቀ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ያምኑበታል ፡

ሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡ ከመ ፡ ሀለወ፡ ወኢ ሀለወ ፡ እንዘ ፡ ሀለወ ።

በገናንነት ፡ ሳለ ፡ በገናንነት ፡ የሌለ ፡ እሱ ፡ በገናንነት ፡ እንዳለ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ያምኑ በታል ። አንድም ፡ በልበ ፡ መናፍቃን ፡ ሳለ ፡ በልበ ፡ ምእመናን ፡ የሌለ ፡ እሱ ፡ በልበ ፡ መናፍቃን ፡ እንዳለ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ያምኑበታል ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ም፡ ፲፫ ፡ ፫ ። ም ፡ ፫ ፡ ፳ ።

፱ ፤ ወዘበ ፡ ልብ ፡ ወጥበብ ፡ የአምሮ ፡ ለዝንቱ ፡

አእምሮ ፡ ያለው ፡ (ወጥበብ) ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ይህን ፡ ያስተውለዋል ፡

ወለዝንቱሰ ፡ አርዌ ፡ ወሰብዐቱ ፡ አርእስቲሁ ።

ያየኸው ፡ አውሬ ፡ ትርጓሜ ፡ የሰባቱም ፡ አርእስት ፡ ትርጓሜያቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡

ሰብዐቱ ፡ አርእስት ፡ ሰብዐቱ ፡ አድባር ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ዲቤሆሙ ፡ ትነብር ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ።

ሰባቱ ፡ አርእስት ፡ ሰባቱ ፡ አድባር ፡ ናቸው ፡ ያች ፡ ሴት ፡ በላያቸው ፡ የተቀመጠችባ ቸው ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፰ ። ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።

፲ ፤ ወሰብዐቱ ፡ አድባር ፡ ሰብዐቱ ፡ ነገሥት ፡ እሙ ንቱ ።

ሰባቱ ፡ አድባርም ፡ ሰባቱ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፡

ወኀምስቱ ፡ ወድቁ ።

አምስቱ ፡ አልፈዋል ፡ አለ ፡ ያልታወቁ ፡

ወአሐዱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ሀለወ ፡

አንዱ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ያልታወቀ ፡

ወአሐዱ ፡ ኢመጽአ ፡ ዓዲ ፡

አንዱ ፡ ገና ፡ አልመጣም ፡ አለ ፡ ያልታ ወቀ ።

ወሶበ ፡ መጽአ ፡ ይነብር ፡ ኀዳጠ ፡ መዋዕለ ።

በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ይቀመጣል ። አንድም ፡ አምስቱ ፡ አልፈዋል ፡ ፈርዖን ፡ ጺሩጻይዳ፡ናቡከደነፆር፡ሰናክሬም፡ዲዮቅል ጥያኖስ ፡ ናቸው ፡ ፈርዖን ፡ ለእግዚአብ ሔርኒ ፡ ኢየአምሮ ፡ ወለእስራኤልኒ ፡ ገብ ርየ ፡ ኢይፌንዎ ፡ ብሏል ፡ ጺሩጻይዳ ፡ አነ ፡ አሠርቅ ፡ ፀሐየ ፡ ብሏል ፡ ናቡከደ ነፆር ፡ ስግዱ ፡ ለምስል ፡ ዘወርቅ ፡ ብሏል ፡ ሰናክሬም ፡ ቦኑ ፡ ግልፎ ፡ ዘያድኅን ፡ በኢ የሩሳሌም ፡ ብሏል ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ረትዐት ፡ መለኮትየ ፡ ብሏል ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ አለ ፡ መንግሥተ ፡ ሮም ፡ አ ንዱ ፡ ገና ፡ አልመጣም ፡ አለ ፡ መንግሥ ተ ፡ ተንባላት ፡ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ይቀመጣል ፡ ሐተታ ፡ ምነው ፡ ዛሬስ ፡ እንኳ ፡ ገና ፡ እንጅ ፡ ያይደለ ፡ ስለ ምን ፡ ኀዳጠ ፡ ይነብር ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ጥን ቱን ፡ የተሰጠው ፡ ስድስት ፡ መቶ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ በሰው ፡ ኃጢአት ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ተጨምሮለታል ፡ እንጅ ።

፲፩ ፤ ወዝክቱ፤ ፡ አርዌ ፡ ዘሀለወ ፡ ወኢሀለወ፡ ሳም ኖሙ ፡ ውእቱ ፡

አለ ፡ የለም ፡ ያልሁትም ፡ አውሬ ፡ ስምን ተኛቸው ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ነው ፡

ወምስለ፡ እሉ፡ ሰብዐቱ ፡ ውእቱ፡የሐውር፡ ለሙስና ።

ከሊህ ፡ ከሰባቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይሄዳል ። አንድም ፡ አምስቱ ፡ መክስም ያኖስ ፡ ዳኬዎስ ፡ ክስሪ ፡ መርቅያን ፡ ዱድ ያኖስ ፡ አልፈዋል ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ አለ ፡ ከመንግሥተ፡ ሮምና፡ ከመንግሥተ ፡ ተንባላት ፡ አንዱ ፡ አንዱ ፡ ገና ፡ አልመ ጣም ፡ አለ ፡ መንግሥተ ፡ ሐሳዌ ፡ መሢ ሕ ፡ በመጣም፡ ጊዜ፡ ጥቂት፡ ይቀመጣል ፡ አለ ፡ የተመቸ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመን ፈቅ ፡ አለ ፡ የለም ፡ ያልሁትም ፡ አውሬ ፡ ስምንተኛቸው ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ ከሊ ህ ፡ ከሰባቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይሄ ዳል ፡ ቀ ፡ ፰ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፲፪ ፤ ወእሉሰ ፡ ዐሠርቱ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ዘርኢከ ፡ ዐሠርቱ ፡ ነገሥት ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ዓዲ ፡ ኢጸንዐት ፡ መንግሥቶሙ ።

ዐሥሩ፡ አቅርንት፡ ዐሥሩ፡ ነገሥታት፡ ናቸ ው፡መንግሥታቸው፡ገና፡ ያልተደላደለች ፡

ወባሕቱ ፡ ከመ ፡ ነገሥት ፡ ሥልጣን፡ቦሙ፡ ለአሐቲ ፡ ሰዓት፡

ነገሥታት ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ ለጥ ቂት ፡ ሰዓት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፤



ወይትነሥኡ ፡ ምስለ ፡ ዝኩ ፡ አርዌ ፡

ከሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ጋራ ፡ ይናገሣሉ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። ዳን ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፳፬ ።

፲፫ ፤ ወአሐዱ ፡ ምክሮሙ ፡

በምክር ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡

ወኀይሎሙ ፡

በገናንነት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡

ወሥልጣኖሙ ፡

በሥልጣን ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡

አግብኡ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ።

ኀይላቸውን ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ለሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ያበረክታሉ ።

፲፬ ፤ ወይፃብኡ ፡ ምስለ ፡ በግዑ ፡ ወይመውዖሙ ፤

ከበጉ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋሉ ፡ በጉ ፡ ድል ፡ ይነ ሣቸዋል ፡

እስመ ፡ እግዚአ ፡ አጋእዝት ፡ ውእቱ ፡ ወንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ውእቱ ፡

እግዚአ ፡ አጋዕዝት ፡ ነውና ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥትም ፡ ነውና ፡

ወእለ ፡ ምስሌሁኒ ፡ ስሙያን ፡ ወኅሩያን ፡ ወመሃይ ምናን ፡ እሙንቱ ።

ከሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ስሙ፡ጽር ፡ ደጋግ፡ የታመኑ ፡ ናቸውና ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፬ ።

፲፭ ፤ ወዝንቱ ፡ ማያት ፡ ዘርኢከ ፡ ዘኀቤሆሙ ፡ ትነ ብር ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘማ ፡ አሕዛብ ፡ ወሕዝብ ፡

ያች ፡ ሴት ፡ ተቀምጣባቸው ፡ ያየሃቸው ፡ ውኃዎችም ፡ አሕዛብ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡

ወበሐውርት ፡ ወሰብእ ፡ እሙንቱ ።

ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ሰብእ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ውን ፡ በሐውርት ፡ ብሎ፡ ደገመው ፡ ቀ ፡ ፩ ። ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፯ ። ኤር ፡ ፵፯ ፡ ፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፮ ፤ ወዝንቱ ፡ ዐሠርቱ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ወዝንቱ ፡ አርዌ ፡ ዘርኢከ ።

ያየኻቸው፡ ዐሥሩ፡አቅርንት፡ያየኸውም ፡ አውሬ ፡

ይጸንሕዋ ፡ እሙንቱ ፡ ለዛቲ ፡ ዘማ ፡ ወያማስንዋ ፡ ወያዐርቅዋ ፡ ወይበልዕዋ ፡ ሥጋሃ ።

በቤተ ፡ አይሁድ ፡ ይሸምቁባታል ፡ ያጠ ፏታል ፡ ይዘርፏታል ፡ ገንዘቧን ፡ ይበሉ ባታል ፡ (ጥቅ) ፡ ኤፍሬም ፡ ይበልዖ ፡ ለም ናሴ፡ወምናሴ፡ይበልዖ፡ለኤፍሬም፡እንዲል፡

ወኪያሃሰ ፡ ያውዕይዋ ፡ በእሳት ።

በእሳት ፡ ያቃጥሏታል ። አንድም ፡ በጦር፡ ያጠፏታል ፡ ቍ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፲፰ ፡ ፰ ።

፲፯ ፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደየ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ ከመ ፡ ይኀበሩ ፡ በአሐዱ ፡ ምክር ፡

እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ፡ እንዳንድ፡ ቃል፡ ተናጋሪ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕውቀቱን ፡ ጥበቡን ፡ ገልጾላቸዋልና ፡

ወያገብኡ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለዝንቱ ፡ አርዌ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸም ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለሐሳዌ ፡ መ ሢሕ ፡ ያበረክታሉ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከ መንፈቅ ፡ ነው ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፯ ።

፲፰ ፤ ወዛቲ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ርኢካ ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ትነግሥ ፡ ላዕለ ፡ መንግሥታተ ፡ ምድር ፡

ያችም ፡ ያየኻት ፡ ሴት፡ ደጊቱ ፡ አገር ፡ ባ ቢሎን ፡ ናት ፡ አለ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ባሉ ፡ ነገሥታት ፡ ሠልጥና ፡ ያለች ፡ ቤተ፡ አይሁድ ፡ ናት ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፲ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡

፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ወረደ ፡ ካልዕ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ። አንድም ፡ ምክንያተ ፡ ሕይወት ፡ ጌታ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ፡

ወቦ ፡ ዐቢይ ፡ ሥልጣን ፡

ጽኑ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡

ወበርሀት ፡ ምድር ፡ እምብርሃኑ ፡ ገጹ ፡ ወእምስብሐቲሁ ።

ከፊቱ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ (ወእምስብሐ ቲሁ) ፡ ከልብሱ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ም ድር፡ብርሃን፡ሆነች፡ ም፡ ፲፡ ፲፩ ። ሕዝ፡፵፫።

፪ ፤ ወጸርኀ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ወይቤ ፡ ወድቀት ፡ ባቢሎን ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፤

ደጊቱ ፡ ሀገር ፡ ባቢሎን ፡ ተፈታች ፡ እያለ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮኸ ፡

ወኮነት ፡ ማኅደረ ፡ ለአጋንንት ፡ ኅበ ፡ ይነብር ፡ ኵሉ፡ ጋኔን ፡ ርኩስ፡

የአጋንንት ፡ የርኩስ ፡ ጋኔን ፡ ማደሪያ ፡ ሆነች ፡ እያለ ፡ ሐተታ ፡ አገር ፡ ሲፈታ ፡ ደባስ ፡ የሚባል ፡ ጋኔን ፡ ያድርበታልና ፡

ወምንባረ ፡ ኵሉ ፡ ዖፍ ፡ ርኩስ ፡ ወጽሉእ ፡

የቍራ፡ የጕጉት፡ ማደሪያ ፡ ሆነች ፡ እያለ ፡ ሐተታ ፡ አገር፡ ሲፈታ ፡ የቍራ፡ የጕጉት ፡ ማደሪያ ፡ ይሆናልና ። አንድም ፡ ዲያብ ሎስን ፡ በግብሩ ፡ ዖፍ ፡ ርኩስ ፡ ወጽሉእ ፡ አለው ፡

ወምንባረ ፡ ኵሉ ፡ አርዌ ፡ ርኩስ ።

የጅብ ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ ሆነች ፡ እያለ ፡ ሐተታ ፡ አገር ፡ ሲፈታ፡ የጅብ ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ ይሆናልና ። አንድም ፡ ዲያብ ሎስን ፡ በግብሩ ፡ አርዌ ፡ ርኩስ ፡ አለው ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፰ ። ኢሳ ፡ ፳፩፡ ፱ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፰ ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፳፩ና ፡ ፴፬ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ። ኤር ፡ ፶ ፡ ፫ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ።

፫ ፤ እስመ ፡ እምነ ፡ ሕምዘ ፡ ወይኑ ፡ ዝሙታ ፡ ወድቁ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡

አበርትታ ፡ ጥላ ፡ ካጠጣቻቸው ፡ አለ ፡ አብነት ፡ ሆና ፡ ካሠራቻቸው ፡ ኃጢአት ፡ የተነሣ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍተዋልና ፡

ወነገሥተ ፡ ምድርኒ ፡ እለ ፡ ዘመዉ ፡ ምስሌሃ ፡

ከእሷ፡ ጋራ፡ እንደእሷ፡የሴሰኑ፡አለ፡ እሷን፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ኃጢአት ፡ የሠሩ ፡ ነገሥታቱም ፡ ጠፍተዋልና ፡

ወሠየጠ ፡ ምድርኒ ፡ እለ ፡ በልዑ ፡ እምነ ፡ ኀይለ ፡ ነፈርዐጺ ።

ምድሩን ፡ ለወርቅ ፡ ለብር ፡ የሚሸጡ ፡ የሚለውጡ፡ ነጋድያንም፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከሰበሰበችው ፡ ገንዘብ ፡ በልተው ፡ ጠጥ ተው ፡ የሚኖሩ ። አንድም ፡ እለ ፡ ብዕሉ ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከሰበሰበችው ፡ ገንዘብ ፡ ከብረው ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍተዋልና ፡ ሐተታ ፡ እምነ ፡ ኀይለ ፡ ነፈርዐጺ ፡ አለ፡ እ ንደ ፡ ከተማ፡ ቅሬ ፡ የከተማ፡ ቅሬ፡ ቤቷን ፡ ጠርጋ ፡ አንጥፋ ፡ ጎዝጕዛ ፡ የወጣ ፡ የወረ ደውን ፡ እያሳደረች ፡ ገንዘብ ፡ እንድትቀ በል ፡ ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፯ ። ናሆ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፬ ፤ ወመጽአ ፡ ካልእ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ።

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተሰማ ፡

ዘይብል ፡ ፃኡ ፡ ሕዝብየ ፡ እምኔሃ ፡

ወገኖቼ፡ከእሷ፡ተለዩ፡የሚል፡ቃል፡ተሰማ ፡

ከመ ፡ ኢትትካፈልዋ ፡ኃጢአታ ፡

ኃጢአቷን ፡ እንዳትካፈሉ ፡ አለ፡ በእሷ ፡ ኃጢአት ፡ በመጣ፡ ፍዳ ፡ ከእሷ፡ ጋራ ፡ አ ንድ ፡ እንዳትሆኑ ፡

ወኢይርከብክሙ ፡ መቅሠፍታ ።

ፍዳዋ ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፳ና ፡ ፶፪ ፡ ፲፩ ። ኤር ፡ ፶ ፡ ፰ና ፡ ፶፩ ፡ ፮ ፡ ፵፭ ።

፭ ፤ እስመ ፡ ተለዋ ፡ ኃጣውኢሃ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡

ኃጢአቷ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሶ ፡ ተከት ሏታልና ፡ አለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ አስፈርዶባታልና ፡

ወተዘከረ ፡ ላቲ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐመፃሃ ።

እግዚአብሔርም ፡ ኃጢአቷን ፡ አስቦ ፡ ፈ ርዶባታልና ፡ ዘፍጥ፡ ፲፰ ፡ ፳ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፱ ።

፮ ፤ ወተበቀልዋ ፡ በከመ ፡ ይእቲ ፡ ተበቀለት ፡ ካዕበተ ፡ ምክዕቢት ፡ ዘከመ ፡ ገብረት ።

እሷ ፡ እንዳደረገች ፡ እንደ ፡ ተበቀለች ፡ ፍትሑ፡ ርቱዕ፡ ሥላሴ ፡ ዕፅፍ፡ ድርብ፡ አድርገው ፡ ተበቅለው ፡ ፈርደውባታልና ፡

ወበጽዋዕ ፡ ዘቀድሐት ፡ ቀድሑ ፡ ላቲ ፡ ካዕበቶ ።

እሷ ፡ ቀድታ ፡ ባጠጣችበት፡ ጽዋዕ፡ መላ ልሰው ፡ አጠጥተዋታልና ፡ አለ ፡ በፈረደ ችው ፡ ፍርድ ፡ ፈርደውባታልና ፡ መዝ ፡ ፻፴፯ ፡ ፰ ። ኤር ፡ ፶ ፡ ፲፭ ፡ ፳፱ ።

፯ ፤ ወአምጣነ ፡ ገፍዐት ፡ ወፈግዐት ፡

የበደለችውን ፡ ያህል ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያደረገችውን ፡ ያህል ፡

ከማሁ ፡ ሣቀይዋ ፡ ወአልሕውዋ ።

የበደለችውን ፡ ያህል ፡ ሥቃይ ፡ አጸኑ ባት ፡ (ወአልሐውዋ) ። ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያደረገችውን ፡ ያህል ፡ አሳዘኗት፡

እስመ ፡ ትቤ ፡ በልባ ፡ እነግሥ ፡ ለዝሉፉ ፡

ለዘላለሙ ፡ ሠልጥኜ ፡ እኖራለሁ ፡ ብላ ፡ ነበርና ፡

ወኢይከውን ፡ መበለተ ፡

ድሀ ፡ አልሆንም ፡ ብላ ፡ ነበርና ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወኢይሬኢ ፡ ላሀ ።

ልቅሶ፡ (ኀዘን ፡ ቢል፡ አንድ ፡ ነው) ፡ አያ
ገኘኝም ፡ ብላ ፡ ነበረና ፡ ኤር ፡ ፶፡ ፳፱ ።
ኢሳ ፡ ፵፯ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

፰ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ በአሐቲ ፡ ሰዓት ፡ ይመ
ጽእ ፡ ላዕሌሃ ፡ መቅሠፍታ ፡ ሞት ፡ ወላሀኒ ፡ ወረ
ኃብኒ ፡

ስለዚህ ፡ መቅሠፍቷ ፡ ሞት ፡ ይመጣባ
ታል ፡ አለ ፡ እነግሥ ፡ ላለው ፡ ልቅሶ ፡
ይመጣባታል ፡ አለ ፡ ኢይሬኢ ፡ ላሀ ፡
ላለው ፡ ረኃብ ፡ ይመጣባታል ፡ አለ ፡
ኢይከውን ፡ መበለተ ፡ ላለው ፡

ወያውዕይዋ ፡ በእሳት ፡

በጦር ፡ ያጠፏታል ፡

እስመ ፡ ጽኑዕ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይትቤቀላ።

የሚፈርድባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽኑዕ ፡
ከሃሊ ፡ ነውና ፡ ኢሳ ፡ ፵፯ ፡ ፱ ። ኤር ፡
፶ ፡ ፴፩ ። ራእ ፡ ፲፯ ፡ ፲፮ ።

፱ ፤ ወይበክዩ ፡ ላዕሌሃ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ፡

የምድር፡ነገሥታትም፡ሁሉ፡ያለቅሱላታል፡

ወይሬእይዋ ፡ እለ ፡ ዘመዉ ፡ ወፈግዑ ፡ ምስሌሃ ።

ከእሷ ፡ ጋራ ፡ ተድላ፡ ደስታ ፡ ያደረጉ ፡
አለ ፡ እሷን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ኃጢ
አት ፡ የሠሩ ፡ ሁሉ ፡ ባይዋት ፡ ጊዜ ፡ ያለ
ቅሱላታል ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፪ ።

፲ ፤ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ጢሰ ፡ እሳታ፡ እምርሑቅ፡ ቆሙ፡
በእንተ ፡ ፍርሀተ ፡ ሥቃያ ።

ያውዕይዋ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ወሶበ ፡ ርእዩ፡
ጢሰ ፡ እሳታ ፡ አለ ፡ ዜና ፡ ጥፋቷን ፡ በ
ሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እሷን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡
ብለው ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ይቀራሉ ፡

ወይቤሉ ፡ አሌ፡ ላ ፡ አሌ፡ ላ፡ ለሀገር፡ ባቢሎን፡ ዐባይ ፡
ለሀገር ፡ ጽንዕት ።

ለደጊቱ ፡ አገር ፡ ለባቢሎን ፡ ወዮላት ፡
ወዮ ፡ ሊሉላት ፡ ይገባል ፡

እስመ ፡ በጽሐት ፡ ሰዓተ ፡ ደይና ።

የሚፈረድባት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡ ም ፡
፲፬ ፡ ፰ ። ኢሳ ፡ ፳፩ ፡ ፱ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፰ ።

፲፩ ፤ ወይበክይዋ ፡ ሠየጠ ፡ ምድርኒ ፡ ወይላህውዋ።

ምድሩን ፡ ለወርቅ ፡ ለብር ፡ የሚሸጡ ፡
የሚለውጡ፡ ባለጸጎችም ፡ ያዝኑላታል ፡
ያለቅሱላታል ፡

እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ዘይሣየጥ ፡ ገራውሂሆሙ ።

እርሻቸውን ፡ የሚገዛቸው ፡ አጥተዋልና ፤

ቀ ፡ ፲፰ ። ሕዝ ፡ ፳፯ ፡ ፴፮ ።

፲፪ ፤ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡

ወርቅ ፡ ብር ፡ ሰጥቶ ፡

ወዕንቈ ፡ ክቡረ ፡

ዕንቍ ፡ ሰጥቶ ፡

ወባሕርየ ፡

ሉል ፡ ሰጥቶ ፡

ወሜላተ ፡

ነጭ ፡ ሐር ፡ ሰጥቶ ፡

ወአዝመረ ፡

አረንጓዴ ፡ ሐር ፡ ሰጥቶ ።

ወለየ ።

ቀይ ፡ ሐር ፡ ሰጥቶ ።

ወሰንሰሪቄተ ።

ቢጫ ፡ ሐር ፡ ሰጥቶ ፡

ወኵሎ ፡ ዕፀ ፡ ሕቍ ፡

ዞጲ ፡ ሰጥቶ ፡

ወኵሎ ፡ ንዋየ ፡ ዘቀርነ ፡ ነጌ ፡

የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ሰጥቶ ፡

ወኵሎ ፡ ሠርጐ ፡ ዘቦ ፡ ዕንቍ ፡ ክቡር ፡

አራት ፡ ኀብር ፡ አምስተኛ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡
የተሠራ ፡ የዕንቍ ፡ ፈርጽ ፡ ያለበት ፡ ጌ
ጠኛ ፡ ልብስ ፡ ሰጥቶ ፡



ወብርተ ፡ ወኀጺነ ፡ ወባላቀ ፡ ወሩካመ ።

ብርት ፡ ብረት ፡ ዕብነ ፡ በረድ ፡ ሰጥቶ ፡
ሕዝ ፡ ፳፯ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፳፪ ።

፲፫ ፤ ወቀናንሞ ፡ ወአበሞ ፡

ሽቱ ፡ ሰጥቶ ፡

ወዕጣነ ፡

ዕጣን ፡ ሰጥቶ ፡

ወሜሮነ ፡

ሜሮን ፡ ሰጥቶ ፡

ወስኂነ ፡

ዕጣነ ፡ ወስኂነ ፡ ነጭ ፡ ዕጣን ፡ ጥቁር ፡
ዕጣን ፡ አለና ፡

ወወይነ ፡

ወይን ፡ ሰጥቶ ፡

ወቅብዐ ፡

ዘይት ፡ ሰጥቶ ፡

ወስንዳሌ ፡

ሥንዴ ፡ ሰጥቶ ፡ ልጦ ፡ ጕርዶ ፡ የወ
ጣውን ፡ ወይነ ፡ ወስንዳሌ ፡ ብለህ ፡
ግጠም ፡

ወሥርናየ ፡

ልጦ ፡ ጕርዶ ፡ ያልወጣውን፡ ተርታውን ፡
(አባሪሙን), ፡ ሰጥቶ ፡

ወእንስሳ ፡

ላም ፡ በሬ ፡ ሰጥቶ ፡

ወአባግዐ ፡

በግ ፡ ፍየል ፡ ሰጥቶ ፡

ወአፍራሰ ፡

ፈረስ ፡ ሰጥቶ ፡

ወሪዶነ ፡

በቅሎ ፡ ሰጥቶ ፡ ወራድ ፡ እንዲሉ ። አን
ድም ፡ ወአፍራሰ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ ሰጥቶ ፡

ወሪዶነ ፡ የግመል ፡ ወሳብሬ ፡ ሰጥቶ ፡
መንኰራኵር ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ፡

ወጼዋ ፡ ነፍሰ ፡ ሰብእ ፡

ባሪያ ፡ ሰጥቶ። አንድም ፡ ወጼዋ ፡ ምርኮ ፡
ሰጥቶ ፡ ወነፍሰ ፡ ሰብእ ፡ ባሪያ ፡ ሰጥቶ ፡

የሚገዛላቸው ፡ አላገኙምና ፡

፲፬ ፤ ወአቅማሕትኪ ፡ ተኀደገ ፡ እምኔኪ ፡

ብዕልሽ ፡ ሁሉ ፡ ከአንቺ ፡ ቀረ ፡

ወኵሉ ፡ ስብሐትኪ ፡ ወብርሃንኪ ፡ ደመነ ፡

ተድላ ፡ ደስታሽ ፡ ከአንቺ ፡ ጠፋ ፡

ወኢይረክብዎ ፡ እንከ ፡ ሠየጥኪ ፡ ለዝንቱ ፡ በውስ
ቴትኪ ።

ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወርቁን ፡ ለብር ፡
ብሩን ፡ ለወርቅ ፡ የሚለውጡ ፡ ባለጸጎች ፡
ይህን ፡ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ አያገኙትምና ።
አንድም ፡ (ወይበክዋ) ፡ ለቤተ ፡ አይሁድ ፡
መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ለምእመናን ፡ የሚ
ዋጁ ፡ ሐዋርያት ፡ ያዝኑላታል ፡ ያለቅሱ
ላታል ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የሚገባላ
ቸው ፡ አላገኙምና ፡ (ወርቀ ፡ ወብሩረ) ፡
ንጽሐ ፡ ነፍስን ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋን ፡ ይዞ ፡
(ወዕንቈ) ፡ ንጽሐ ፡ ልቡናን ፡ ይዞ ፡ (ወባ
ሕርየ) ፡ በክርስቶስ ፡ አምኖ ፡ (ወአዝመረ፡
ወሜላተ ፡ አፍአዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ አእም
ሮን ፡ ይዞ ፡ (ወለየ) ፡ ደሙን ፡ አፍስሶ ፡
(ወሰንሰሪቄተ) ፡ ተዋልጦተ ፡ ገድልን ፡
ይዞ ፡ (ወኵሎ ፡ ዕፀ ፡ ሕቍ) ፡ በመስቀል ፡
ተሰቅሎ ፡ (ወኵሎ ፡ ንዋየ) ፡ ምግባረ ፡
አብርሃምን ፡ ይዞ ፡ (ወኵሎ ፡ ሠርጐ) ፡
በፍቅሩ ፡ ተሰውራ ፡ ያለች ፡ ፍቅርን ፡
ይዞ ፡ (ወብርተ ፡ ወኀጺነ) ፡ አፍአዊ ፡
ውሳጣዊ ፡ ትዕግሥትን ፡ ይዞ ፡ (ወባላቀ ፡
ወሩካመ ፡ )አፍአዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ አርም
ሞን ፡ ይዞ ፡ (ወቀናንሞ ፡ ወአበሞ) ፡ አፍ
አዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ ትሕትናን ፡ ይዞ ፡ (ወሜ

www.ethiopianorthodox.org

ሮን) ፡ ሜሮን ፡ ተቀብቶ፡ (ወስኂን)፡ ዕጣን፡
ወስኂን ፡ አፍኣዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ ጸሎትን ፡
ይዞ ፡ (ወወይን) ፡ ወይን ፡ ወስንዳሌ ፡ ሥጋ
ውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብሎ ፡ (ወቅብዐ) ፡
ልጅነትን ፡ ተቀብሎ ፡ (ወሥርናየ) ፡ በቅ
ተውም ፡ ሳይበቁም ፡ የሚቀበሉት ፡ አለና፡
(ወእንስሳ) ፡ ተገዢ ፡ ሆኖ ፡ (ወአባግዐ) ፡
መሥዋዕት ፡ ሆኖ ፡ (ወአፍራሰ) ፡ መም
ህር ፡ ሆኖ ፡ አስተምሮ ፡ (ወሪዶነ) ፡ ደቀ ፡
መዝሙር ፡ ሆኖ ፡ ተምሮ ፡ (ወ፪ዋ) ፡ መ
ጥዎተ ፡ ርእስን ፡ ይዞ ፡ የሚገባላቸው ፡
አላገኙምና ፡ (ወአቅማሐትኪ)፡ አቅማሐ፡
ገድልሽ ፡ ሁሉ ፡ ካንቺ ፡ ቀረ ፡ ክብርሽ ፡
ሁሉ ፡ ካንች ፡ ቀረ ፡ (ወኢይረክብዎ) ፡
መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ለምእመናን ፡ የሚ
ዋጁ ፡ ሐዋርያት ፡ ይህን ፡ ባንቺ ፡ አያገ
ኙትምና ።

፲፭ ፤ ወይቀውሙ ፡ እምርሒቅ ፡ በእንተ ፡ ፍርሃተ ፡
ሥቃይኪ ፡

ሥቃይዋን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ርቀው ፡ ይቆ
ማሉ ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ይቀራሉ ፡

ወይበክዩኪ ፡ ወይላሕዉኪ ።

ያዝኑላታል ፡ ያለቅሱላታል ፡ ሕዝ ፡ ፳፯ ፡
፳፯ ፡ ፴ ፡ ፴፮ ።

፲፮ ፤ ወይብሉ፡ አሌ፡ ላ፡ አሌ፡ ላ ፡ ለሀገር፡ ዐባይ ፡
እንተ ፡ ትለብስ ፡ ሜላተ ፡ ወአዝመረ ፡ ወለየ ፡ እንተ ፡
ተገብረት ፡ በወርቅ ፡ ወበዕንቍ ፡ ክቡር ፡ ወበባ
ሕርይ ፡

አራት ፡ ኅብር ፡ አምስተኛ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡
የተሠራ ፡ የዕንቍ ፡ ፈርዕ ፡ ያለበት ፡ ልብ
ስ ፡ ለምትለብስ ፡ ለደጊቱ ፡ አገር ፡ ለባቢ
ሎን ፡ ወዮላት ፡ ወዮ ፡ ሊሉላት ፡ ይገባል ፡
እያሉ ፡ ያዝኑላታል ፡ ያለቅሱላታል ፡

እስመ ፡ በአሐቲ ፡ ሰዓት ፡ ትማስን ፡ ብዕላ ።

ባንድ ፡ ሰዓት፡ ብዕሏ ፡ ጠፍቷልና ፡ ማሰነ፡
ሲል፡ ነው ፡ ም፡ ፲፯፡ ፬ ። ኢሳ፡ ፳፫ ፡ ፲፬ ።

፲፯ ፤ ወኵሉ ፡ ዘሐዳፍ ፡

ቀዛፊ ፡ ሁሉ ፡

ወኵሉ ፡ ኪነተ ፡ አሕማር ፡

መርከብ ፡ ሠሪ ፡

ወኖትያ ፡

ዋናተኛ ፡

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትቀነዩ ፡ በውስተ ፡ ባሕር ፡ እም
ርሑቅ ፡ ቆሙ ፡

በባሕር ፡ የሚነግዱ ፡ ሁሉ ፡ ርቀው ፡ ይቆ
ማሉ፡ አለ፡ እሷን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ብለ
ው ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ይቀራሉ ፡ ሕዝ ፡ ፳፯ ፡
፳፯—፴፮ ።

፲፰ ፤ ወጸርኁ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ውዕየተ ፡ ሀገራ ፡

ዜና ፡ ጥፋቷን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ።

ወይቤሉ ፡ መኑ ፡ ይመስላ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡

ደጊቱ ፡ ሀገር ፡ ባቢሎንን ፡ ማን ፡ ይመስ
ላታል ፡ ማን ፡ ይመስላት ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡
ይጮሃሉ ፡ ኢሳ ፡ ፴፬ ፡ ፲ ።

፲፱ ፤ ወወደዩ ፡ መሬተ ፡ ውስተ ፡ አርእስቲሆሙ ።

በራሳቸውም ፡ ትቢያ ፡ እየነሰነሱ ፡ ይጮ
ሃሉ ፡ (ትእምርተ ፡ ኀዘን ፡ ነው) ፡

ወይጸርኁ ፡ ወይበክይዋ ፡ ወይላሕውዋ ፡ ወይብሉ ፡
አሌ፡ላ ፡ አሌ፡ ላ ፡ ለሀገር ፡ ዐባይ፡ እንተ፡ እምኔሃ ፡
ብዕሉ ፡

ከእሷ ፡ የተነሣ፡ ከብረው ፡ የሚኖሩ፡ ሁሉ፡
ለደጊቱ ፡ አገር ፡ ለባቢሎን ፡ ወዮላት ፡
ወዮ ፡ ሊሉላት ፡ ይገባል ፡ እያሉ ፡ እየ
ጮሁ ፡ ያዝኑላታል ፡ ያለቅሱላታል ፡

ኵሎሙ፡ እለ፡ ቦሙ፡ አሕማር ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ እምነ ፡
ክብራ ፡

ከክብሯ ፡ ብዛት፡ የተነሣ ፡ በባሕር፡ መር
ከብ፡ የሚያኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ያዝኑላታል ፡ ያ
ለቅሱላታል ፡ ሐተታ ፡ ሰሎሞን ፡ በጋ
ስዮን ፡ ጋቤር ፡ ለማስነገድ ፡ መርከብ ፡
አስቀምጦ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡

www.ethiopianorthodox.org



እስመ ፡ በአሐቲ ፡ ሰዓት ፡ ማሰነት ፡

ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ጠፍታለችና ፡ ሕዝ ፡ ፳፯ ፡
፳፬ ፡ ፴ ።

፳ ፤ ለይትፌሣሕ ፡ ላዕሌሃ ፡ ሰማይ ፡ ወቅዱሳን ፡ ነቢ
ያት ፡ ወሐዋርያት ።

መላእክት ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ደስ ፡
ይበላችሁ ፡

እስመ ፡ ተበቀለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀለክሙ ።

እግዚአብሔር ፡ ተበቅሎ ፡ ፈርዶላችኋ
ልና ፡ ኢሳ ፡ ፵፬ ፡ ፳፫ ። ኤር ፡ ፶፩ ፡ ፵፰ ።

፳፩ ፤ ወነሥአ ፡ አሐዱ ፡ መልአክ ፡ ኀያል ፡ ወጾ
ኑዐ ፡ ዕብነ ፡ ዐቢየ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ማኅረጽ ፡ ወወገረ፡
ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወይቤ ፡ ከመዝ ፡ ትትገደፍ ፡ባቢ
ሎን ሀገር ፡ ዐባይ ፡

ኀያል ፡ ጽኑ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ መል
አክ ፡ ወፍጮ ፡ የሚያህል ፡ ታላቅ፯፡፯ደን
ጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ከባሕር ፡ ጥሎ ፡ ደጊቱ ፡
አገር፡ ባቢሎን፡ እንዲህ፡ ትጠፋለች ፡አለ ፡

ወኢትትረከብ ፡ እንከ ።

እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ቀንታ ፡ አትገኝም ፡
ለዲያብሎስ ፡ ሐረስ ፡ የሚባል፡ ብላቴን ፡
ጌታ ፡ አለው ፡ እሱን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡
አለቃውም ፡ ዲያብሎስ ፡ እንዲህ ፡ ድል ፡
ይነሣል ፡ አለ ፡ ኀይል ፡ በተፈጥሮ ፡ ጽንዕ፡
በሥራ ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ነው ፡ ኤር ፡
፶፩ ፡ ፷፫ ፡ ፷፬ ።

፳፪ ፤ ወኢይሰማዕ ፡ በውስቴታ ፡ ቃለ ፡ መሰናቁት ፡
ወዕንዚራ ። ወማኅሌት ፡

በውስጥዋ ፡ የዘፈን ፡ የእንዚራ ፡ የመሰ
ንቆ ፡ ቃል ፡ (ድምፅ) ፡ አይሰማባትም ፡

ወቃለ ፡ ቀርን ፡ ኢይሰማዕ ፡ በውስቴታ ፡

የነጋሪትም ፡ ድምፅ ፡ አይሰማባትም ፡

ወኵሉ፡ ኬንያ፡ ዘኵሉ፡ ኪን፡ኢይትረከብ፡በውስቴታ ፡

የሥጋ ፡ ጥበብ ፡ ጥበበኛ ፡ ሁሉ ፡ አይገኝ
ባትም ፡ ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፰ ። ሕዝ ፡ ፳፮ ፡ ፲፫ ።

፳፫ ፤ ወኢብርሃነ ፡ ማኅቶት ።

አብራ ፡ ቅዳ ፡ ማለት ፡ አይገኝባትም ።

ወኢቃለ፡መርዓዊ፡ወመርዓት፡ኢይሰማዕ፡በውስቴታ ።

እገሌ፡ እገሊትን፡ ያግባ፡ እገሊት ፡ እገሌን ፡
ታግባ ፡ ማለት ፡ አይሰማባትም ፡

፳፬ ፤ እስመ ፡ ሠየጥኪ ፡ መሣፍንተ ፡ ምድር ፡ እለ ፡
አስሐትኪዮሙ ፡ በሥራያትኪ ፡ ለኵሉ ፡ አሕዛበ ፡
ምድር ።

ምድሩን ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ ለአሕዛብ ፡
የሚለውጡ ፡ ባለጸጎችን ፡ በሥራይሽ ፡
ያሳትሻቸው ፡ ነሽና ። አንድም ፡ ሤጥኪ ፡
በሥራይሽ ፡ ያሳትሻቸው ፡ ባለጸጎችን ፡
ለአሕዛብ ፡ አሳልፈሽ ፡ ሰጥተሻቸዋልና ።
አንድም ፡ (ወኢይሰማዕ) ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
መንፈሳዊ ፡ ምስጋና ፡ አይሰማባትም ።
(ወቃለ ፡ ቀርን) ፡ ዮሐንስ ፡ ሲያስተምር ፡
አይሰማባትም ። (ወኵሉ ፡ ኬንያ) ፡ የመ
ንፈሳዊ፡ ጥበብ፡ ጥበበኛም፡ አይገኝባትም፡
(ወኢብርሃነ ፡ ማኅቶት) ፡ መንፈሳዊ ፡
አእምሮ ፡ አይገኝባትም ፡ (ወኢቃለ ፡ መ
ርዓዊ) ፡ መምህራን ፡ ሲያስተምሩ ፡ ምእ
መናን ፡ ሲማሩ ፡ አይሰሙባትም ፡ (እስ
መ ፡ ሠየጥኪ) ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡
ለምእመናን ፡ የሚዋጁ ፡ ሐዋርያትን ፡
አብዳን ፡ ዝንጉአን ፡ ስሑታን ፡ ጊጉያን ፡
ያልሻቸው ፡ ነሽና ። አንድም ፡ አብዳን ፡
ዝንጉአን ፡ ስሑታን ፡ ጊጉያን ፡ ያልሻ
ቸው፡ ሐዋርያትን፡ ሤጥኪ፡ ለአሕዛብ፡ አሳ
ልፈሽ ፡ ሰጥተሻቸዋልና ። ኤር ፡ ፯፡ ፴፬ና፡
፲፮ ፡ ፱ና ፡ ፳፭ ፡ ፲ ። ኢሳ ፡ ፳፫ ፡ ፰ ።

፳፭ ፤ ወተረከበ ፡ በላዕሌኪ ፡ ደመ ፡ ነቢያት ፡ ወዘ
ቅዱሳን ፡ ወዘኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተቀትሉ ፡ በውስተ ፡
ምድር ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለክርስቶስ ።

በነቢያት ፡ በሐዋርያት ፡ ደም ፡ የመጣ ፡
ፍዳ ፡ ባንቺ ፡ ደረሰ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡
ስላመኑ ፡ ስሙን ፡ ስላስተማሩ ፡ በስሙ ፡

ስለ ፡ ተጠሩ ፡ በሰማዕትነት ፡ በሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ የመጣ ፡ ፍዳ ፡ ባንቺ ፡ ደረሰ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፲ ። ም ፡ ፲፯ ፡ ፮ና ፡ ፲፱ ፡ ፪ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡

፩ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተሰምዐ ፡ ቃል ፡ ዐቢይ ፡ እምሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሰማይ ፡ ቃል ፡ ተሰማ ፡

ከመ ፡ ዘብዙኅ ፡ ሰብእ ፡

እንደ ፡ ገበያተኛ ፡ እንደ ፡ ሠርገኛ ፡ እንደ፡ ልቅሶኛ ፡ እንደ ፡ ድሎተኛ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ተሰማ ፡

ወይብሉ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡

ስብሓት ፡ ለዘሀሎ ፡ ስብሓት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ሰብሐ ፡ እግዚአ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግናሉ ፡

እስመ ፡ ስብሓት ፡ ወፍርቃን ፡ ወኀይል ፡ ለአምላክነ ።

ኀይል ፡ ሥልጣን ፡ ምስጋና ፡ ለፈጣሪያችን ፡ የሚገባ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ።

፪ ፤ እስመ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ኵነኔሁ ፡

ፍርዱ ፡ ጽድቅ ፡ ርትዕ ፡ ነውና ፡

እስመ ፡ ኰነና ፡ ለዐባይ ፡ ዘማ ፡ እንተ ፡ አማሰነት ፡ ምድረ ፡ በዝሙታ ፡

አብነት ፡ ሆና ፡ ሌላውን ፡ ኃጢአት ፡ ባሠራች ፡ በቤተ ፡ አይሁድ ፡ ፈርዶባታልና ፡

ወተበቀለ ፡ ደመ ፡ ኵሎሙ፡ አግብርቲሁ፡ እምእዴሃ ፡

(ተቀበለ ፡ ይላል) ፡ የወዳጆቹን ፡ ደም ፡ ከእጅዋ፡ ተቀብሎ፡ አፍሷልና ። አንድም ፡ ተበቀለም፡ ይላል፡ በእጅዋ፡ የፈሰሰ፡ የወዳጆቹን ፡ ደም ፡ አስቦ ፡ ፈርዶባታልና ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፮ ። ም ፡ ፮ ፡ ፲ ። ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፵፫ ።

፫ ፤ ወይብሉ ፡ ዳግመ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡

ዳግመኛም፡ ስብሓት፡ ለዘሀሎ፡ ስብሓት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ሰብሐ ፡ እግዚአ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግናሉ ፡

ወዐርገ ፡ ጢስ ፡ ዘለዓለመ ፡ ዓለም ።

የዘለዓለም ፡ ጢስ ፡ ወጣ ፡ አለ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ እየተመዘዘ ፡ ሲወጣ ፡ ያየዋል ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ በሐልዮ ፡ በሠሩት ፡ እንደ ፡ ተፈረደባቸው ፡ ለማጠየቅ ፡ ኢሳ ፡ ፴፬ ፡ ፲ ።

፬ ፤ ወሰገዱ ፡ እልክቱ ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሊቃናት ፡ ወእልክቱኒ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ቅዱስ ፡

ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሊቃናት ፡ አራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ላለ ። አንድም ፡ በጌትነት ፡ ላለ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ይብጅ፡ ያድርግ፡ ብለው፡ ሰገዱለት ፡

ወይብሉ ፡ አሜን ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

አሜን ፡ እያሉ ፡ ስብሓት ፡ ለዘሀሎ ፡ ስብሓት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ሰብሐ ፡ እግዚአ ፡ እያሉ ፡ ሰገዱለት ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፻፮ ፡ ፵፰ ።

፭ ፤ ወወፅአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ እምውስተ ፡ መንበሩ ፡ ዘይብል ፡ ሰብሑ ፡ ለአምላክነ ፡ ኵልክሙ ፡ አግብርቲሁ ፡ ወእለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ንኡስክሙ ፡ ወዐቢይክሙ ።

በሰማይ ፡ ካለ ፡ ከመንበሩ ፡ ወዳጆቹ ፡ ሁላችሁም ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተሰማ ።

፮ ፤ ወእምዝ ፡ ሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ከመ ፡ ዘብዙኅ ፡ ሰብእ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሠርገኛ ፡ እንደ ፡ ዱለተኛ ፡ እንደ ፡ ልቅሶኛ ፡



ወከመ ፡ ቃለ ፡ ማይ ፡ ዐቢይ ፡

እንደ ፡ መጣያ ፡ ውኃም ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፤

እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡

ስብሓት ፡ ለዘሀሎ ፡ ስብሓት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ሰብሐ ፡ እግዚአ ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ሰማሁ ፡

እስመ ፡ ነግሠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ።

ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ (ይመልዕ) ፡ በሁሉ ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራን ፡ ሠርቷልና ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ።

፯ ፤ ለንትፈሣሕ ፡ ወንትሐሠይ ፡ ወነሀብ ፡ሎቱ ፡ ስብሐተ ፡

ደስ ፡ ይበለን ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ ለእሱ ፡ ምስጋናን ፡ እናቅርብ ፡

እስመ ፡ በጽሐ ፡ መርዓ ፡ በግዑ፡ ወብእሲትኒ፡ ድሉት፡ ይእቲ ።

በግዑ ፡ ምእመንን ፡ የሚዋሐድበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡ ምእመንም፡ ለተዋሕዶ፡ በቅታ ፡ ተገኝታለችና ፡ መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፳፬ ። ም ፡ ፳፩ ፡ ፱ ።

፰ ፤ ወተውህባ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ትልበስ ፡ ሜላተ ፡ ብርሃን ፡ ንጹሐ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሜላት ፡ ጽድቆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡

ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ትለብስ ፡ ዘንድ ፡ ተሰጣት ፡ ይኸውም ፡ ቅዱሳን ፡ በሠሩት፡ ሥራ፡ የሚወርሱት ፡ ክብር ፡ ነው ፡ ሜላት ፡ ያለውን ፡ ተረጎመ ፡ መዝ ፡ ፵፭ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፲ ።

፱ ፤ ወይቤለኒ ፡ ጸሐፍ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተጸውዑ ፡ ውስተ ፡ በዓለ ፡ መርዓ ፡ በግዑ ፡

በግዑ ፡ ለተዋሐዳት ፡ ለምእመን፡ ዕረፍት፡ በቅተው ፡ የተገኙ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ፡

እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ።

ይህ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነገር ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር ፡ ነውና ። አንድም ፡ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ዕውነተኛ ፡ ነውና ። አንድም ፡ ዕውነተኛ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ ሉቃ፡ ፲፬፡፲፭ ፡

፲ ፤ ወወደቀ ፡ ኀበ ፡ እገሪሁ ፡ ወሰገድኩ ፡ ሎቱ ፡

ከግእሩ ፡ ወድቄ ፡ ሰገድሁለት ፡

ወይቤለኒ ፡ ዑቅ ፡ ዮጊ ፡ ኢትስግድ ፡ ሊተ ፡

ለኔ ፡ እንዳትሰግድ ፡ ዕወቅ ፡ አለኝ ።

እስመ ፡ አነሂ ፡ ገብር ፡ ዘከማከ ፡ ወዘምስሌከ ፡ ወምስለ፡ አኀዊከ፡ ነቢያት ፡ እለ፡ የዐቅቡ፡ ሕጎ፡ ለኢየሱስ፡

ያንተ ፡ ባልደረባ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ እንዳንተ ፡ ያለሁ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና ፡ የወንድሞችህ ፡ የነቢያት ፡ ባልደረባ ፡ የምሆን ፡ እንደ ፡ ወንድሞችህ ፡ ያለሁ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሕግ ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ባልደረባ ፡ የምሆን፡ እንደ፡ እሳቸው ፡ ያለሁ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና፡ (ዑቅ ፡ ኢትስግድ ፡ ሊተ) ፡ ለእኔ ፡ እንዳትሰግድ፡ ዕወቅ ፡ አለኝ ፡

ወባሕቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንስግድ ፡ ኵልነ ፡

እኔም ፡ አንተም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንስገድ ፡ እንጅ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔም ፡ አንተም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንስገድ ፡

እስመ ፡ ሕጉ ፡ ለኢየሱስ ፡ መንፈስ ፡ ተነብዮ ።

መጻእያትን ፡ የሚነግር ፡ መልአኩን ፡ ባልደረባ ፡ መስጠት ፡ ለኢየሱስ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ። አንድም ፡ መጻእያትን ፡ የሚገልጥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ማሳደር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ወባሕቱ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንስግድ ፡ ዑቅ ፡ ኢትስግድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፰ ። የሐዋ ፡ ፲ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩ ፤ ወእምዝ ፡ ተርኅወ ፡ ሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ፡ ሐተታ ፡ በሰማይ ፡ መከፈት ፡ መዘጋት ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ የተዘጋ ፡ ቤት ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ያልታየ ፡ ዕቃ ፡ እንዲታይ ፡ ያልተ ገለጸ ፡ ምሥጢር ፡ ተገለጸ ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወወፅአ ፡ ፈረስ ፡ ጸዓዳ ፡

አምበላይ ፡ ፈረስ ፡ ወጣ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡

ወዘይጼዐኖ ፡ ስሙ ፡ መሃይምን ፡ ወጻድቅ ፡

የተቀመጠበትም ፡ ስሙ ፡ መሃይምን ፡ ጻድቅ ፡ ይባላል ፡

ወዘበጽድቅ ፡ ይኴንን ፡ ወይፀብእ ።

በዕውነተኛ ፡ ፈርዶ ፡ ፍርድ ፡ የሚያጠፋ፡ ነው ፡ ም፡ ፯ ፡ ፱ ። ም፡ ፩ ፡ ፳ና ፡ ፫ ፡ ፲፬ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፲፪ ፤ ወአዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡

ዐይኖቹ ፡ እንደ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ ናቸው ፡ አለ ፡ ትእምርተ ፡ በቀል ፡

ወዲበ ፡ ርእሱ ፡ አክሊል ፡

በራሱ ፡ ላይ ፡ አክሊል ፡ ደፍቷል ፡ አለ ፡ ለምእመናን ፡ የሚሰጣቸው ፡ ክብር ፡ የባ ሕርዩ፡ነው ፡

ወጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ቀጸላሁ ፡ አስማት ፡ ዘአልቦ ፡ ዘየአምሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ።

በቀጸላውም ፡ ከእሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ፡ የሚያ ውቀው ፡ የሌለ ፡ ስም ፡ ተጽፏል ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፬ና ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። ም ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፲፫ ፤ ወይለብስ ፡ ልብሰ ፡ ዘንዙሕ ፡ በደም ፡

ደም ፡ የተረጨ ፡ ልብስ ፡ ለብሷል ፡ አለ ፡ ትስብእትን ፡ ተዋሕዷል ፡

ወሰመዩ ፡ ስሞ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

ስሙንም ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ይሉታል ፡ ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፩ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፲፬ ፤ ወሐራ ፡ ሰማይ ፡ ይተልውዎ ፡ በአፍራስ ፡ ጸዓድው ፡

መላእክት ፡ ባምበላይ ፡ ፈረስ ፡ ሆነው ፡ ተከትለውታል ፡ አለ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወይለብሱ ፡ ሜላተ ፡ ብርሃን ፡ ንጹሐ ።

ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ፡ አለ ፡ ጸጋቸ ውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ።

፲፭ ፤ ወይወፅእ ፡ እምነ ፡ አፉሁ ፡ ሰይፍ ፡ በሊሕ ፡ ዘቦቱ ፡ ይቀሥፎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡

አሕዛብን ፡ የሚያጠፋበት ፡ መቅሠፍት ፡ በቃሉ ፡ ይታዘዛል ፡

ወውእቱ ፡ ይርዕዮሙ ፡ በበትረ ፡ ኀጺን ፡

በኅ ፡ በኅዎቹን ፡ በተወደደ ፡ ሥልጣን ፡ ይጠብቃቸዋል ፡

ወውእቱ ፡ ይከይዳ ፡ ለምክያደ ፡ ወይነ ፡ ሕምዘ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ።

ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ የእግዚአብሔ ር ፡ መዓቱ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አደባባይ ፡ ተረግጧል ፡ አለ ፡ መዓቱ ፡ የሚፈጸምበ ትን ፡ ሥልጣን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ም ፡ ፲፬፡፲፱። ኢሳ፡ ፷፫ ፡ ፫ ።

፲፮ ፤ ወጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ልብሱ ፡ ወውስተ ፡ ገቦሁ፡ ስም ፡ ዘይብል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወእግዚአ ፡ አጋ እዝት ።

በልብሱም ፡ ውስጥ ፡ በጎኑ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እግዚአ ፡ አጋእዝት ፡ የሚል ፡ ተጽፏል ፡ (ዕርቅ) ፡ በቀጸላው ፡ የተጻፈ ውን ፡ አልቦ ፡ ዘየአምሮ ፡ አለ ፡ በልብሱ ፡ ውስጥ ፡ በጎኑ ፡ የተጻፈውን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እግዚአ ፡ አጋእዝት ፡ የሚል ፡ ነው ፡ አለ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የተ ሠወረውን ፡ የምገልጽ ፡ የተገለጸውን ፡ የምሠውር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲል ። አንድም ፡ ውሳጣዊ ፡ አፍአዊ ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲል፡ ነው፡ ም፡ ፲፮፡ ፲፬። ፩፡ ጢሞ፡ ፮፡ ፲፭።

፲፯ ፤ ወእምዝ፡መቆ፡አሐዱ፡መልአክ፡ውስተ፡ፀሓይ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ መልአክ ፡ በፀሓይ፡ ቆመ፡አለ፡በምድር፡ሥራውን፡ሠራ፡ (ጥቅ)፡ መራጉተ ፡ አወፍዮ ፡ ለፀሐይ ፡ እንዲል ፡

ወይጸርኅ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ወይቤ ፡ ለኵሉ ፡ አዕ ዋፍ ፡ ዘይሠርር ፡ ውስተ ፡ ማእከለ ፡ ሰማይ ፡ ንዑ ፡ ተጋብኡ ፡ ውስተ ፡ በዓሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዐቢይ ።

በታላቅ ፡ ቃል ፡ ይጮሃል ፡ በሕዋ ፡ የሚ በሩ ፡ አዕዋፍን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ኑ ፡ ተሰብሰቡ ፡ እያለ ፡ ሕዝ ፡ ፴፱ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።

፲፰ ፤ ከመ ፡ ትብልዑ ፡ ሥጋ ፡ ነገሥት ፡

የነገሥታቱን ፡ ሥጋ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡

ወሥጋ ፡ መላእክት ፡

ያለቆችንም ፡ ሥጋ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡

ወሥጋ ፡ ጽኑዓን ፡

የአርበኞችንም ፡ ሥጋ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡

ወሥጋ ፡ አፍራስ ፡

የፈረሶችንም ፡ ሥጋ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡

ወዘእለ ፡ ይጼዐንዎሙ ፡

የተቀመጡባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሥጋ ፡ ትበ ሉ ፡ ዘንድ ፡

ወሥጋ ፡ ኵሉ ፡ አግዓዚ ፡ ወገብር ፡

የተገዙንም፡የገዙንም፡ሥጋ፡ትበሉ፡ዘንድ፡

ወዘንኡስ ፡ ወዘዐቢይ ።

የታላቁንም፡ የታናሹንም፡ሥጋ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡

፲፱ ፤ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ ዝክቱ ፡ አርዌ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ተነሣ ፡

ወነገሥተ ፡ ምድር ፡ ወሠራዊቶሙ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሁ ፡

የምድር ፡ ነገሥታትም ፡ ሠራዊታቸውም፡ ከሱ፡ ጋራ፡ ተሰበሰቡ፡ አለ፡ አንድ፡ ሆኑ ፡

ከመ ፡ ይዕብእዎ ፡ ለውእቱ ፡ ዘይጼዐን ፡ ላዕለ ፡ ፈረስ ፡ ጸዓዳ ፡

ባምበላይ ፡ ፈረስ ፡ ላይ፡ ጉቀምጦ፡ ያለ፡ ጌ ታን ፡ ይጣሉት ፡ ዘንድ ፡

ወለሠራዊቱ ።

ምእመናንንም፡ ይጣሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ። ም ፡ ፲፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፮ ።

፳ ፤ ወእምዝ ፡ አኀዝዎ ፡ ለዝኩ ፡ አርዌ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕን፡ ያዙት፡

ወለሐሳዌ ፡ ነቢዩ ፡ ዘገብረ ፡ ተአምራተ ፡ በቅድሜሁ፡

በዲያብሎስ፡ሥልጣን፡ በሐሳዌ፡ መሢሕ ፊት ፡ የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ ያደረገ ፡

በዘያስሕቶሙ ፡ ለእለ ፡ ጸሐፉ ፡ ማኅተመ ፡ ስሙ ፡ ለውእቱ ፡ አርዌ ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ወለምስሉ ፡

ዘመር፡ዘመስ፡ብለው፡ የሐሳዌ፡ መሢሕን ፡ የስሙን፡ ምልክት፡ የጻፉትን፡ለሱ፡ የሰገዱ ትን፡ለምስሉም፡የሰገዱትን፡ ሰዎች፡ በሚያ ስታቸው፡ገንዘብ፡የምትሓት፡ ተአምራት ፡ የሚያደርግ ፡ ሐሳዌ ፡ ኤልያስን ፡ ይዘው ፡

ወወደይዎሙ ፡ ሕያዋኒሆሙ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅተ ፡ እሳት ፡ ዘይነድድ ፡ በተይ ።

ከነሥጋቸው ። አንድም ፡ አለን ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ ጽኑ፡ ሥቃይ ፡ ባለበት ፡ በገሃነመ ፡ እሳት ፡ ጣሏቸው ፡ ም፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፲፫፡ ፲፩ ። ም ፡ ፳ ፡ ፲ ። ዳን፡ ፯ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ።

፳፩ ፤ ወለእለሰ ፡ ተርፉ ፡ ቀተልዎሙ ፡ በሰይፈ ፡ ዝክቱ ፡ ዘይጼዐን ፡ ላዕለ ፡ ፈረስ ፡ ጸዓዳ ፡

የቀሩትን ፡ ግን ፡ ባንበላይ ፡ ፈረስ ፡ ተቀ ምጦ ፡ ባለ ፡ በሱ ፡ ሥልጣን ፡ አጠፏቸው፡ በሰይፈ፡ዝክቱ፡አርዌ፡ይላል፡በክፉው፡ የሚ ከፋበት፡ ስለ፡ ሆነ፡ (ጥቅ)፡አነ ፡እከውኖ ፡ ከመ ፡ ነምር ፡ ለቤተ፡ኤፍሬም፡ ወከመ ፡ አንበሳ ፡ ለቤተ ፡ ይሁዳ ፡ እንዲል ፡



www.ethiopianorthodox.org

እንተ ፡ ትወፅእ ፡ እምአፉሁ ፡

ከቃሉ ፡ በምትታዘዝ ፡ ሥልጣን ፡ አጠ ፏቸው ፡

ወጸግቡ ፡ ኵሉ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ እምነ ፡ ሥጋሆሙ

ኑ፡ ተሰብሰቡ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ ሥጋቸውን ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ወረደ ፡ ካልእ ፡ መልአክ ፡ እም ሰማይ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ፡

ወይጸውር ፡ መራኁተ ፡ ዐሐይ ።

የምድርን ፡ መክፈቻ ፡ ይዟል ፡ (ጥቅ) ፡ መራኁተ ፡ አወፍዮ ፡ ለፀሐይ ፡ እንዲል ፡

ወዐበይት ፡ መዋቅሕት ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።

ታላቅ ፡ ዛንገርር ፡ በጁ ፡ ተይዟል ፡ ም ፡ ፱፡ ፩ ፡ ፪ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፬ ። ይሁዳ ፡ ቍ ፡ ፮ ።

፪ ፤ ወአኀዞ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ዘውእቱ፡ ቀዳማዊ፡

ቀዳማዊ ፡ የሚሆን ፡ ዲያብሎስን ፡ ይዞ ፡

ወውእቱ ፡ ጋኔን ፡ ሰይጣን ፡

ይኸውም ፡ ጋኔን ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ ጋኔን ፡ ማለት ፡ ዕሩቅ ፡ ውዱቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሰይጣን ፡ ማለት ፡ መስተቃርን ፡ መስተ ፃርር ፡ ባላጋራ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ዲያብሎ ስ ፡ ማለት ፡ ያፍ ፡ ሠራሪ ፡ ነድ ፡ ውዑይ ፡ ፈታዊ ፡ አምላክና ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወአሠሮ ፡ ዐሠርተ ፡ ምእተ ፡ ዓመተ ።

ሺሕ ፡ ዘመን ፡ አጋዘው ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፱ ።

፫ ፤ ወአውደቆ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቅ ፡ ወዐጸወ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ በማኅተም ፡

በጥልቅ ፡ ቦታ ፡ ጣለው ፡ ቦታ ፡ ወሰነበት ፡

ከመ ፡ ኢያስሕት ፡ አሕዛበ ፡ እስከ ፡ ይትፌጸም ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ዓመት ፡

ሺሕ ፡ ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ወ ጥቶ ፡ አሕዛብን ፡ እንዳያስት ፡ በምጽ

አት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ እስከ ፡ ነው ፡ ከምጽአት ፡ አስቀድሞ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የተመቸ ፡

ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ሀለዎ፡ይትፈታሕ፡ኅዳጠ፡መዋዕለ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ ፪ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

፬ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ መናብርተ ፡ ወነበረ ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወንበር ፡ ተዘርግቶ ፡ አየሁ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ተቀምጧል ፡ ሐተታ ፡ መናብርት ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡ እንደ ፡ አፍንርጅ ፡ ወንበር ፡ እር ከን ፡ ያለው ፡ ነውና ። አንድም ፡ የንጉሥ ፡ ወንበር ፡ በተዘረጋ ፡ ጊዜ ፡ የአቡን ፡ የእ ጨጌ ፡ ወንበር ፡ ተዘርግቶ ፡ እንዲታይ ፡ ይታየዋልና ፡ መናብርት ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡

ወአግብአ ፡ ሎሙ ፡ ፍትሐ ፡ በእንተ ፡ ነፍሰሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡

በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ስላመኑ ፡ ስሙን ፡ ስላስተማሩ ፡ በስሙ ፡ ስለ ፡ ተጠ ሩ ፡ በሰማዕትነት ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ ይፈርድላቸዋልና ፡

ወበእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

በአካላዊ ፡ ቃል ፡ ስላመኑ ፡ ፈረደላችው ።

ወእለሰ ፡ ኢሰገዱ ፡ ለዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ወኢለምስሉ ፡ ወኢጸሐፉ ፡ ትእምርቶ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሞሙ ፡ ወኢ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡

ለሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ያልሰገዱ ፡ በሐሣዊ ፡ መሢሕ፡ለተሣለው፡ሥዕል፡ ለተመሰለው፡ ምስል ፡ ያልሰገዱ ፡



ዘመር ፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ በግንባራቸው ፡ ያልጻፉ ፡ በጃቸው ፡ ያልተከተቡ ፡

እሙንቱ ፡ የሐይዉ ፡

ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ ይነሣሉ ፡

ወይነግሡ ፡ ምስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐሠርተ ፡ ምእተ ፡ ዓመተ ።

ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ነግ ሠው ፡ ይኖራሉ ፡ ዘመኑ ፡ ሥጋዌ ፡ ነው ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ፳፪ ፡ ፳፯ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፴ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፪ ።

፭ ፤ ወባዕዳንሰ ፡ ምውታን ፡ ኢይትነሥኡ ፡

ሌሎቹ ፡ ምውታን ፡ ግን ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡ ና ፡ አይነሡም ፡

እስከ፡ አመ፡ ይትፌጸም፡ ዝንቱ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ዓመት ፡

ሺሕ ፡ ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡

ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሚት ፡ ሕይወት ።

መዠመሪያዪቱ ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ ይህ ች፡ ናት፡ ፩፡ ቆሮ፡፲፭፡ ፳፫። ፩፡ተሰ፡፬፡፲፮ ።

፮ ፤ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ ውእቱ ፡ ዘረከበ ፡ ክፍለ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ትቀድም ፡ መጺአ ፡

ከትንሣኤ፡ ሥጋ፡አስቀድማ፡ በምትሆን፡ በ ትንሣኤ፡ ልቡና፡ዕድል፡ፈንታ፡ ጽዋ፡ተራ፡ ያገኘ፡ ሰው፡ ንዑድ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ (ለሥጋ ው፡ለደሙ፡ በቅቶ፡ የተገኘ፡ ማለት ፡ነው) ፡

እስመ ፡ አልቦ ፡ እንከ ፡ ዳግመ ፡ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ ላዕለ ፡ እሉ ፡

ዳግመኛ ፡ ሞት ፡ አይሠለጥንባቸውምና ፡

እስመ ፡ ይከውኑ ፡ ካህናቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወለ ክርስቶስ፡ ወይነግሡም፡ ስሌሁ ፡ ፲ተ፡ ፻ተ ፡ዓመተ ።

የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ስለ፡ ሆኑ ፡ ሺሕ፡ዘመን፡ከእሱ፡ጋራ፡ተዋሕደው፡ይኖራ ሉና።አንድም፡(ወእለሰ)፡በሐሳዌ፡መሢሕ፡ ለተመሰለው ፡ ምስል ፡ ያልሰገዱ ፡ ዘመር፡ ዘመስ ፡ ብለው ፡ በግምባራቸው ፡ ያልጻፉ፡

በጃቸው፡ ያልተከተቡ፡ትንሣኤ፡ሥጋ፡ ይነ ሣሉ፡(ወይነግሡ)፡ተነሥተው፡ከክርስቶስ፡ ጋራ፡ተዋሕደው፡ሺሕ፡ዘመን፡ ሠልጥነው ፡ ይኖራሉ ፡ በፍጹም፡ ቍጥር ፡ (ወባዕዳንሰ)፡ ሌሎቹ ፡ ምውታን ፡ ግን ፡ ትንሣኤ ፡ ሥጋ፡ አይነሡም ፡ ትንሣኤያቸው ፡ ዘለሐሳር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ እስከ ፡ ነው ፡ (ወዛቲ ፡ ይእቲ) ፡ ደገኛዪቱ ፡ ትንሣኤ ፡ ሥጋ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ (ብፁዕ ፡ ወቅዱስ) ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አስቀድማ ፡ በም ትሆን ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጕባኤ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ጽዋ ፡ ተራ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ንዑድ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ (ለተዋሕዶ ፡ በቅቶ ፡ የተ ገኘ ፡ ማለት ፡ ነው) ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በሊህ ፡ ላይ ፡ ለሞት ፡ ሥልጣን ፡ የለው ምና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የክርስቶስም ፡ ባለሟሎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ (ወይነግሡ ፡ ምስሌሁ) ፡ ከሱ ፡ ጋራ፡፡ ተዋሕደው፡ ሺሕ፡ ዘመን፡ነግሠው ፡ ይኖራሉ፡ ከምጽአት፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ በፍጹም ፡ ቍጥር ፡ ከምጽአት ፡ አስቀ ድሞ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የተመቸ ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ ነው ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፲ ።

፯ ፤ ወሶበ ፡ ኀልቀ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ዓመት ፡ ይትፈታሕ ፡ ሰይጣን ፡ እምነ ፡ ሞቅሑ ፡

ሺሕ ፡ ዘመን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን፡ ከሥራቱ ፡ ይለቀቃል ።

፰ ፤ ወይወፅእ ፡ ያስሕቶሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ አርባዕቱ ፡ መዓዝኒሃ ፡ ለምድር ፡

ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ ያስታቸው ፡ ዘንድ ፡ ይወጣል ፡

ወያስተጋብአሙ ፡ ለጎግ ፡ ወለማጎግ ፡ ከመ ፡ ያስተ ቃትሎሙ ፡

ያዋጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ጎግ ፡ ማጎግን ፡ ይሰበ ስባቸዋል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኍልቆሙሰ ፡ ከመ ፡ ኆፃ ፡ ባሕር ፡

ቍጥራቸውም ፡ ብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው፡ ሕዝ፡ ፴፰፡ ፪ ። ሕዝ፡ ፴፰ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።

፱ ፤ ወዐርጉ ፡ ውስተ ፡ ስፍሐ ፡ ለምድር ፡

ምድርን ፡ ያላብሷታል ፡

ወዐገትዋ ፡ ለትዕይንቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወለሀገር ፡ ቅድስት ፡

የቅዱሳን ፡ ሀገር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከበዋት ፡ ይሠፍራሉ ፡

ወእምዝ ፡ ወረደት ፡ እሳት ፡ እምሰማይ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበልዐቶሙ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መቅሠፍት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዛ ፡ ታጠፋቸዋለች ። ሕዝ ፡ ፴፰ ፡ ፳፪ና፡ ፴፱ ፡ ፮ ። ዘካ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ፡

፲ ፤ ወለዝኩቱኒ፡ ሰይጣን፡ ዘያስሕቶሙ ፡ ወደይዎ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅተ ፡ እሳት ፡ ወተይ ፡

የሚያስታቸውንም ፡ ሰይጣን ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ባለበት ፡ በገሃነም ፡ ይጥሉታል ፡

ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ዝክቱ ፡ አርዌ ፡ ወሐሳዌ ፡ ነቢይ ፡ ከመ ፡ ይደየኑ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ባለበት ፡ ሐሳዌ ፡ ኤልያስም ፡ ባለበት ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ፍዳቸውን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ። የገሃነመ፡ እሳት፡ መደበኛዋ፡ ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ ነውና ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ም ፡ ፲፬ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።

፲፩ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ መንበረ፡ ዐቢየ፡ ወጸዓዳ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብሩህ ፡ ታላቅ ፡ መንበርን ፡ አየሁ ፡

ወእምዘ ፡ ይነብር ፡ ዲቤሁ ፡ ጐዩ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡

በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ካለው ፡ ከሱ ፡ ከፊቱ፡ መገለጽ፡ የተነሣ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ሸሹ ፡ አለ ፡ አለፉ ፡

ወኀጥኡ ፡ መካነ ።

ቦታ ፡ ቦታነት ፡ አላገኙም ፡ ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ መጽኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ምውታን ፡ ዐቢያን ፡ ወንኡሳን ፡ ወቆሙ ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ሙታን ፡ ተነሥተው ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፡ (ይህ ፡ ይቀድማል) ፡

ወከሠቱ ፡ ኵሎ ፡ መጻሕፍተ ፡

መጻሕፍተ ፡ ብሉያት ፡ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳት ፡ ተነገሩ ፡ ተመረመሩ ፡ ሐተታ ፡ እሊህ ፡ ባሉት ፡ የጸና ፡ መዳኑን ፡ እሊህ ፡ ባሉት ፡ ያልጸና ፡ አለመዳኑን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወለመጽሐፈ፡ ሕይወትሰ፡ እንተ፡ ባሕቲታ፡ ከሠትዋ፡

መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ ለብቻዋ ፡ ተነገረች ፡ አለ ፡ ድኅነት ፡ ማሰጠቷን ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ (ወከሠቱ)፡ ምግባረ ፡ ኃጥአን፡ ተነገረች ፡ ተመረመረች ፡ አለ ፡ ዋጋ ፡ አለማሰጠቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወለመጽሐፈ ፡ ሕይወትሰ) ፡ ምግባረ ፡ ጻድቃን ፡ ግን ፡ ለብቻዋ ፡ ተነገረች ፡ አለ ፡ ዋጋ ፡ ማሰጠቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወተኰነኑ ፡ እልክቱ ፡ ምውታን ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ፡ ተጻፈ ፡ ሙታን፡ ተፈረደባቸው ፡ ተፈረደላቸው ፡

በከመ ፡ ገብሩ ።

እንደ ፡ ሠሩ ፡ እንደ ፡ ሠሩት ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፲፡ ፳፪። ም፡ ፫፡ ፭። ፊል፡ ፬፡ ፭። ሮሜ፡፪፡፮።

፲፫ ፤ ወአግብአት ፡ ባሕርኒ ፡ ኵሎ ፡ ምውታነ ፡ እለ ፡ ውስቴታ ፡

ባሕርም ፡ በውስጧ ፡ ያሉ ፡ ሙታንን ፡ መለሰች ፡





ጌታ ፡ በምጽአት ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ለጻድቃን ፡ እንደ ፡ ፈረደላቸው ፡ በኃጥአን ፡ እንደ ፡ ፈረደባቸው ።

ወአግብኡ ፡ ሲኦል ፡ ወሞት ፡ ዘኀቤሆሙ ፡ ምውታነ ፡

ሞትም ፡ መቃብርም ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ ሙታንን ፡ መለሱ ፡

ወአግብአት፡ምድርኒ፡እለ፡ሀለዉ፡ውስቴታ፡ምውታነ፡

ምድርም ፡ በውስጧ ፡ ያሉ ፡ ሙታንን ፡ ሁሉ ፡ መለሰች ፡ እንደ ፡ ፈንጠር ፡ ሳይ ቀበሩ፡ ወድቀው፡ ወድቀው፡ የቀሩ፡ናቸው፡

ወተኰነኑ ፡ ኵሎሙ ፡ በከመ ፡ ምግባሮሙ ።

ሁሉም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራቸው፡ ተፈረደባቸው ፡ ተፈረደላቸው ።

፲፬ ፤ ወወደይዎሙ ፡ ለሲኦል ፡ ወለሞት ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅተ ፡ እሳት ፡ ዘምልዕት ፡ ተየ ፡

ሞትንና፡ መቃብርንም፡ ጽኑ፡ ሥቃይ፡ ባለ

www.ethiopianorthodox.org

በት ፡ በገሃነም ፡ ጣሏቸው ፡ አለ ፡ ሞት ፡ መግደሉን ፡ መቃብር ፡ መቀበሉን ፡ መተዋቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ዘምል ዕት ፡ ተየ ፡ ዘምልዕተ ፡ ተይ ፡ ይላል ፡

ወሞትሰ ፡ ዳግም ፡ ገሃነም ፡ ዘእሳት ፡ ውእቱ ።

ሁለተኛ ፡ ሞትም፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ነው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ፡ ፶፬ ፡ ፶፭ ።

፲፭ ፤ ወኵሉ ፡ ዘኢይትረከብ፡ ጽሑፈ፡ ውስተ፡ መጽሐፈ፡ ሕይወት፡ ይወድይዎ፡ ውስተ፡ ገሃነም፡ዘእሳት ።

በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ አለ ፡ በልበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ያልታወቀውን ፡ ሁሉ ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ባለበት ፡ በገሃነም ፡ ይጥሉታል ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵፩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩ ፤ ወእምዝ፡ ርኢኩ፡ሰማየ፡ሐዲሰ፡ወምድረ፡ሐዳሰ፡

ከዚህም፡ በኋላ፡ ሐዲስ ፡ ሰማይ ፡ ሐዲስ ፡ ምድር ፡ አየሁ ፡

እስመ ፡ ሰሰለ ፡ ሰማይ ፡ ቀዳማዊ ፡

የቀደመው ፡ ሰማይ ፡ አልፏልና ፡

ወምድርኒ ፡ ቀዳሚት ፡

የቀደመችው፡ ምድርም፡ አልፋለችና፡መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ተሰጠች ፡ ማለቱ ፡ ነው፡ ሐተታ ፡ ሰማይ ፡ አላት ፡ ሰማይ ፡ አልፋ ፡ እሷ ፡ የምትተካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰማያውያን ፡ መላእክት ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምድር ፡ አላት ፡ ምድር ፡ አልፋ ፡ እሷ ፡ የምትተካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በምድር ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ የምትወረስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምድራውያን ፡ ጻድቃን ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በምድር ፡ ተድላ ፡ ሥጋ ፡ ይፈጸማል ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይም ፡ ተድላ ፡ ነፍስ ፡ ይፈጸማልና ፡ ሐዲስ ፡ አላት ፡ በተሐድሶ ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከመታየት ፡ እንግዳ ፡ ናትና፡ ታድሰው፡ የሚወርሷት፡ ስለ፡ሆነ ፡

ወባሕርኒ ፡ ተሥዕረት ፡ እንከ ።

ውቅያኖስም ፡ አለፈች ፡ ኢሳ፡ ፷፭፡ ፲፯። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።

፪ ፤ ወሀገርኒ ፡ ቅድስት ፡ ሐዳስ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ርኢክዋ ፡ ወረደት ፡ እምሰማይ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር፡

ሀገር ፡ ቅድስት፡ ኢየሩሳሌምም፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተሰጠች ፡ ስትሰጥ ፡ አየሁ ፡

ወድሉት ፡ ይእቲ ፡ ከመ ፡ መርዓት ፡ ሥርጕት ፡ ለምታ ።

ሴት ፡ ለባሏ ፡ ያጌጠች ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ በጣዕም ፡ በመዓዛ ፡ በብርሃን ፡ በስን ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ። ገላት ፡ ፬ ፡ ፳፮ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

፫ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዐቢየ ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብልዎ ፡ ናሁ ፡ ቅድሳቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ኀደረት ፡ ምስሌሆሙ ፡

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ታላቅ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ለምእመናን ፡ ተሰጠች ፡ የሚል ። አንድም ፡ (ወእምዝ) ፡ ሐዲስ ፡ መለኮትና ፡ ሐዲስ ፡ ትስብእት ፡ ተዋሕደው ፡ አየሁ ፡ የሥጋ ፡ አምላክ ፡ መሆን ፡ የአምላክ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ እንግዳ ፡ ነውና ፡ ሐዲስ ፡ አለ ፡ (ሰሰለ) ፡ መለያየት ፡ ጠፍቷልና ፡ (ወባሕርኒ) ፡ ኀልፈተ ፡ ምኵራብ ፡ ሆነ ፡ (ሀገር) ፡ እመቤታችን ፡ ለምእመናን ፡ ተሰጠች ፡ ሴት ፡ ለባሏ ፡ ያጌጠች ፡ እንደ ፡ ሆ



ነች ፡ እመቤታችንም ፡ በንጽሐ፡ ሥጋ ፡ በ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ በንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡ (ቅድሳቱ) ፡ እመቤታችን ፡ ለምእመናን ፡ ተሰጠች ። አንድም ፡ ሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌል ፡ ተሠርቶ ፡ አየሁ ፡ ብሉይ ፡ ሕግ ፡ አልፏልና ፡ ጥምቀተ ፡ አይሁድ ፡ አለፈች ፡ (ሀገር ፡ ቅድስት) ፡ መምህራን ፡ ለምእመናን፡ ሲሰጡ፡ አየሁ ፡ ሴት ፡ ለባሏ ፡ ያጌጠች ፡ እንደሆነች ፡ መምህራን ፡ በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ ያጌጡ ፡ ናቸው ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃልን ፡ ሰማሁ ፡ መምህራን፡ ለምእመናን፡ ተሰጡ፡ በማስተማር ፡ ነው፡ ቅድስቱ፡ ይላል፡ቅድስቱ፡ ወልድ፡በምእመናን፡ አደረች፡

ወእሙንቱኒ ፡ ይከውንዎ ፡ ሕዝቦ ፡

እሳቸውም ፡ ልጆቹ ፡ ይሆናሉ ፡

ወውእቱኒ ፡ ይከውኖሙ ፡ አምላኮሙ ፡

እሱም ፡ አባት ፡ ይሆናቸዋል ፡

ወይሄሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሆሙ ፡

እግዚአብሔር ፡ አድሮባቸው ፡ ይኖራል ፡

፬ ፤ ወያሴስል ፡ አንብዐ ፡ እምአዕይንቲሆሙ ፡

እንባን ፡ ከዐይናቸው ፡ ያርቃል ፡ አለ ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ። አንድም ፡ ዕሤተ ፡ አንብዕን ፡ ይሰጣቸዋል ።

ወአልቦ ፡ እንከ ፡ ሞት ፡ ወኢላሕ ፡ ወኢገዐር ፡ ወኢሕማም ፡ አልቦ ፡ እንከ ፡

ከዚያ፡ በኋላ፡ ሞት፡ ኀዘን፡ ልቅሶ፡ መከራ፡ የለባቸውም ፡

እስመ፡ኀለፈ፡ዘቀዳሚ፡ሥርዐት፡ወናሁ፡ተሐደሰ፡ኵሉ።

ብሉይ ፡ ግብር ፡ አልፏልና ፡ እነሆ ፡ ሁሉም ፡ ታድሷል ፡ ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፲ ።

፭ ፤ ወይቤ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ናሁ ፡ እገብር ፡ ኵሎ ፡ ሐዲሰ ፡

በመንበሩ፡ላይ፡ያለው። አንድም፡በጌትነት፡ ያለው፡እሱ፡ሁሉን፡ አድሰዋለሁ፡ ብሏልና፡

ወይቤለኒ ፡ ጸሐፍ ፡

ጻፍ ፡ አለኝ ፡

እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ እሙን ፡ ዘበጽድቅ ፡ ይከውን።

በዕውነት፡የሚደረግ፡ይህ፡ቃል፡ የታመነ፡ነውና።ጻፍ፡አለኝ። አንድም፡ የታመነ፡ይህ ፡ ቃል፡ በዕውነት፡ የሚደረግ፡ነውና ። አንድም ፡ የታመነ ፡ በዕውነት ፡ የሚደረግ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፪ ፡ ፲፱ና ፡ ፭ ፡ ፩ ።፪፡ ቆሮ፡ ፭ ፡ ፲፯፡ ፳፩ ።

፮ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ አልፋ ፡ ወአ ፡ ወአነ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወአነ ፡ ደኃራዊ ፡

አልፋ፡አ፡እኔ፡ ነኝ፡አለ፡ አንድነት፡ ሦስትነት፡ ገንዘቤ፡ የሚሆን፡ እኔ፡ ነኝ። አንድም ፡ አልፋ፡ ቀዳማዊ፡አ፡ ደኃራዊ፡ ማለት፡ነው ፡ ቀዳማዊ፡ ደኅራዊ ፡ የምሆን ፡ እኔ፡ ነኝ፡ አልፋ፡ ያለውን ፡ ቀዳማዊ ፡ አ፡ ያለውን ፡ ደኃራዊ ፡ ብሎ ፡ ተረጕመው ፡

ወአንሰ ፡ ለዘጸምዐ ፡ እሁቦ ፡ ይስተይ ፡ እምነቅዐ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ በከንቱ ።

ለሻ ፡ ሳይጽር ፡ ሳይግር ፡ ከነቅዐ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ እሰጠዋለሁ ፡ አለ ፡ ልጅነትን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ም ፡ ፩፡፰።

፯ ፤ ወዘሰ ፡ ሞዐ ፡ ይወርሶ ፡ ለዝንቱ ፡

ክህደትን ፡ በሃይማኖት ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ ይህን ፡ ይወርሰዋል ፡

ወእከውኖ፡ሎቱ፡አምላከ፡ወውእቱኒ፡ይከውነኒ፡ወልደ።

አባት ፡ እሆነዋለሁ ፡ እሱም ፡ ልጅ ፡ ይሆነኛል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፯ ። ዘካ ፡ ፰ ፡ ፰ ።

፰ ፤ ወእለሰ ፡ ይፈርህዎ ፡ እንዘ ፡ የአምኑ ፡ ወያጌምኑ ፡ ርእሶሙ ፡

ኢየአምኑ፡ሲል፡ነው፡ሳያምኑ፡ምግባር፡ትሩፋት፡የሚሠሩ። አንድም፡እንዘ፡ የአምኑ፡ አምነው፡ምግባር፡ትሩፋት፡የማይሠሩ፡ሰውነታቸውን ፡ በኃጢአት ፡ የሚያሳድፉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይቀትሉ ፡ ወይዜምዉ ፡ ወይገብሩ ፡ ሥራየ ፡ ወያ
መልኩ ፡ አማልክተ ።

ነፍስ ፡ የሚገሉ ፡ የሚሴስኑ ፡ ሥራይ ፡ የሚያደርጉ ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልኩ ፡

ወኵሎ ፡ ሐሰተ ፡

ሐሰትን ፡ ሁሉ ፡ የሚሠሩ ።

ይከውን ፡ ምንዳቤሆሙ ፡ ገሃነም ፡ ዘእሳት ፡ ወተይ ፡

ፍዳቸው ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ያለበት ፡ ገሃነም ፡ ይሆናል ፡

ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዳግም ፡ ሞት ።

ሁለተኛም ፡ ሞት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ዕብ ፡ ፲ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ። ም ፡ ፳፪ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፳ ፡ ፲፬ ።

፱ ፤ ወመጽአ ፡ አሐዱ ፡ እምነ ፡ እልክቱ ፡ ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ይጸውሩ ፡ ሰብዐተ ፡ ጽዋዐተ ፡ እለ ፡ ምሉዐን ፡ ሰብዓተ ፡ መቅሠፍተ ፡ ደኃርያተ ፡ ወተናገረ ፡ ምስሌየ ፡

ሰባት ፡ መቅሠፍት ፡ የሚፈጸምባቸውን ፡ ሰባት ፡ ሥራ ፡ ከታዘዙ ፡ ከሰባቱ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ደኃርያት ፡ አለ ፡ ሰባተኛው ፡ መጥቅዕ ፡ ሲፈጸም ፡ ነውና ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተነጋገረ ፡

ወይቤለኒ ፡ ነዐ ፡ አርኢከሃ ፡ ለመርዓት ፡ ለብእሲተ ፡ በግዑ ።

በግዑ ፡ ለተዋሐዳት ፡ ለምእመን ፡ የተሰጠች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ና ፡ ላሳይህ ፡ አለኝ ። አንድም ፡ ለና ፡ ለ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ በግዑ ፡ የተዋሐዳት ፡ ምእመንን ፡ ላሳይህ ፡ ና ፡ አለኝ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ፯ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፯ ።

፲ ፤ ወወሰደኒ ፡ መንፈስ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ዐቢይ ፡ ወነዋኅ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወደ ፡ ረዥም ፡ ተራራ ፡ አወጣኝ ፡ የራእይ ፡ ነው ፤

ወአርአየኒሃ ፡ ለሀገር ፡ ቅድስት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንተ ፡ ትወርድ ፡ እምሰማይ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከወደ ፡ ሰማይ ፡ የምትሰጥ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ አሳየኝ ፡

ወስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሃ ።

ብርሃን ፡ ሰፍሮባታል ፡ ሕዝ ፡ ፵ ፡ ፪ ።

፲፩ ፤ ወከዋክብቲሃኒ ፡ ይመስሉ ፡ ከመ ፡ ዕንቍ ፡ ክቡር ፡

ሰማይ ፡ ብሏት ፡ ነበረና ፡ ከዋክብቲሃ ፡ አለ ፡ የሚወርሷት ፡ ጻድቃንም ፡ ዕንቍ ፡ ይመስላሉ ፡ አለ ፡ ለሰማዕታት ፡ ለምእመናን ፡ ንጽሕናቸውን ፡ ክብራቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፤

ወጽዕዱት ፡ ይእቲ ፡ ከመ ፡ ባሕርይ ።

ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ጽርየቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ቈ ፡ ፳፫ ። ሕዝ ፡ ፵፰ ፡ ፴፩ ።

፲፪ ፤ ወዐባይ ፡ አረፍታ ፡ ወነዋኅ ፡ ጥቅማ ፡

ዕርከኗ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ቁመቷም ፡ ረዥም ፡ ነው ፡ አለ ፡ ጽናቷን ፡ ረድኤቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡

ወባቲ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አናቅጽ ፡

ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ በር ፡ አላት ፡ አለ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ መዓርግ ፡ ትወረሳለች ፡

ወውስተ ፡ አናቅጺሃ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ መላእክት ፡

በደጅ ፡ አፏ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መላእክት ፡ ቆመዋል ፡ አለ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሥዩማን ፡ ሥልጣን ፡ ትወረሳለች ፡

ወጽሑፋን ፡ አስማት ፡ ዘዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ።

በውስጣቸውም ፡ ያሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ስም ፡ ተጽፏል ፡ አለ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ተጽፈዋል ፡ ሕዝ ፡ ፵፰ ፡ ፴፩ ።

፲፫ ፤ ወውስተ ፡ አናቅጽ ፡ ጽባሐውያን ፡ ሠለስቱ ፡

በምሥራቅ ፡ ሦስቱ ፡ ሰፍረዋል ፡ ሮቤል ፡ ስምዖን ፡ ጋድ ፡

ወውስተ ፡ አናቅጽ ፡ ዐረባውያን ፡ ሠለስቱ ፡

በምዕራብ ፡ ሦስቱ ፡ ሰፍረዋል ፡ ይሁዳ ፡ ይሳኮር ፡ ዛብሎን ፡

ወውስተ ፡ አናቅጽ ፡ ሰሜናውያን ፡ ሠለስቱ ፡

በሰሜን ፡ ሦስቱ ፡ ሰፍረዋል ፡ ኤፍሬም ፡ ብንያም ፡ ምናሴ ፡

ወውስተ ፡ አናቅጽ ፡ ደቡባውያን ፡ ሠለስቱ ፡

በደቡብ ፡ ሦስቱ ፡ ሰፍረዋል ፡ አሴር ፡ ዳን ፡ ንፍታሌም ።

፲፬ ፤ ወዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ መሠረታቲሃ ፡ ለአረፍተ ፡ ሀገራ ።

በሯ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ነው ፡ አለ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ መዓርግ ፡ ትወረሳለች ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትን ፡ ከበው ፡ በሰፈሩት ፡ አምሳል ፡ ተናገረ ፡

ወጽሑፍ ፡ ውስቴቶን ፡ አስማተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሐዋርያተ ፡ በግዑ ።

በውስጧም ፡ ያሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ስም ፡ ተጽፏል ፡ በግዑ ፡ የሾማቸው ፡ ሐተታ ፡ ሐዋርያት ፡ ገቦችም ፡ አግቦችም ፡ ናቸውና ፡ ደገማቸው ።

፲፭ ፤ ወዘክቱ ፡ ዘይትናገር ፡ ምስሌየ ፡ ይጸውር ፡ ሕለተ ፡ ወርቅ ፡ በዘቦቱ ፡ ይሜጥና ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡

ለእኔ ፡ የሚነግረኝ ፡ ያ ፡ መልአክ ፡ ያችን ፡ ሀገር ፡ በሚሠፍራት ፡ ገንዘብ ፡ የሚሠፍርበት ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ይዟል ፡ አለ ፤ ያችን ፡ ሀገር ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅበትን ፡ ጽሩይ ፡ አእምሮ ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፡

ወለአናቅጺሃ ፡ ወለአረፋቲሃ ።

ዕርከኗን ፡ በሯን ፡ የሚሠፍርበት ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ይዟል ፡ ክብሯን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ወርብዕት ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡

ያችም ፡ ሀገር ፡ ምዕዙን ፡ ናት ፡ አለ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ ይወርሷታል ፡

በአምጣነ ፡ ኑኃ ፡ ወግድማ ።

ወርዷ ፡ በቁመቷ ፡ ልክ ፡ ነው ፡ አለ ፡ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ተካክለው ፡ ይወርሷታል ፡

ወመጠና ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡ በውእቱ ፡ ሕለት ።

ያችን ፡ ሀገር ፡ በወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ሰፈራት ፤ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ አወቃት ፡ መረመራት ።

ወኮነ ፡ አምጣኒሃ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ምእተ ፡

መጠኗ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ባሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ ትወረሳለች ፡ ሥዩማን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ።

ኑኃ ፡ ወግድማ ፡ ወቆማኒ ፡ ዕሩይ ።

ርዝመቷ ፡ ሞላልነቷ ፡ ቁመቷ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ አለ ፡ በኪዳነ ፡ አብርሃም ፡ በኪዳነ ፡ ይስሐቅ ፡ በኪዳነ ፡ ያዕቆብ ፡ ትወረሳለች ፡ በወጣኒነት ፡ በማዕከላዊነት ፡ በፍጹምነት ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሕዝ ፡ ፵፰ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።

፲፯ ፤ ወእምዝ ፡ መጠነ ፡ አረፋቲሃ ፡ ምእት ፡ ወአርብዓ ፡ ወአርባዕቱ ፡ በእመተ ፡ ሰብእ ፡

የዕርከኗ ፡ መጠን ፡ በሰው ፡ ክንድ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነው ፡

ዘውእቱ ፡ አሐዱ ፡ በእመተ ፡ መልአክ ።

ይኸውም ፡ በመልአኩ ፡ ክንድ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ መቶው ፡ አምሳ ፡ አርባው ፡ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሁለት ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ይሆናል ፡ የሰባ ፡ ሁለቱ ፡ አርድእት ፡ ምሳሌ ፡ በ፸፪ቱ ፡ አርድእት ፡ ስብከት ፡ ትወረሳለች ፡ አለ ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ አንድ ፡ መሆናቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፲፰ ፤ ወውስተ ፡ ርእሰ ፡ አረፍታ ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡ በዕንቈ ፡ ኢያስጲድ ፡ ወያክንት ፡

ክባቧም ፡ ኢያስጲድ ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠ ፡ ነው ፡ ያክንትም ፡ በሚባል ፡ ዕን



www.ethiopianorthodox.org

ቀ ፡ ያጌጠ ፡ ነው ፡ አለ ፡ በንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ትወረሳለች ፡ መረግድን፡ ይጨምራል ፡ በንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ በንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ትወረሳለች ፡ የላይኛውን ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡ ነፍ ስ ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህነን፡ኪዳነ፡ አብርሃም፡ ኪዳነ፡ ይስሐቅ፡ ኪዳነ ፡ ያዕቆብ ፡ ማለት፡ ነው፡ ይህነን ፡ ን ጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ንጽሐ ፡ ል ቡና ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ያነን ፡ ኪዳነ ፡ አብርሃም ፡ ኪዳነ ፡ ይስሐቅ ፡ ኪዳነ ፡ ያ ዕቆብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡

ወትመስል ፡ ሀገራ ፡ ከመ ፡ ዘበወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ ግብ ረታ ።

ሀገርነቷም ፡ በጠራ ፡ ወርቅ ፡ የተሠራች ፡ ትመስላለች ፡ አለ ፡ የወርቅ ፡ አሸዋ ፡ ፈሶ ባታል ፡ ክብርዋን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፲፱ ፤ ወመሠረተ ፡ አረፍተ ፡ ሀገራ ፡ ከመ ፡ ማህው ፡ ጸዓዳ ፤

ደረጃዋም ፡ እንደ ፡ ሞ ፡ ጸዓዳ ፡ ነው ፡ አለ፡ የሞ ፡ አሸዋ ፡ ፈሶባታል ፡ ጽርየቷን ፡ መ ናገር ፡ ነው ፡

ሥርጉት ፡ በኵሉ ፡ ዕንቍ ፡ ክቡር ፡

በክቡር ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡ አለ ፡ በፍጹም ፡ ክብር ፡ ትወረሳለች ፡

ወቀዳሚት ፡ መሠረት ፡ በኢያሰጲድ ፡

አሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ መሠረታቲሃ ፡ ለአ ረፍተ ፡ ሀገራ ፡ ብሎ ፡ ሥርጉት ፡ ይእቲ ፡ በኵሉ ፡ ዕንቍ ፡ ክቡር ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ቀዳሚት ፡ መሠረት ፡ በኢያሰጲድ ፡ አለ ፡ መዠመሪያዪቱ ፡ መሠረት ፡ ኢያሰጲድ ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወካልዕት ፡ በሰንፔር ፡

ሁለተኛዪቱም ፡ መሠረት ፡ ሰንፔር ፡ በሚ ባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወሣልስት ፡ በኬልቄዶን ፡

ሦስተኛዪቱም ፡ መሠረት ፡ ኬልቄዶን ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወራብዕት ፡ በዘመረግድ ።

አራተኛዪቱም፡መሠረት፡መረግድ፡ በሚባ ል፡ዕንቍ፡ያጌጠች፡ ናት፡ ኢሳ፡ ፶፬፡፲፩፡፲፪።

፳ ፤ ወኃምስት ፡ በሰርዶንክስ ፡

አምስተኛዪቱ ፡ መሠረት ፡ ሰርዶንክስ ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወሳድስት ፡ በሰርድዮን ፡

ስድስተኛዪቱም ፡ መሠረት ፡ ሰርድዮን ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወሳብዕት ፡ በክርስቲሎቤ ፡

ሰባተኛዪቱም ፡ መሠረት ፡ ክርስቲሎቤ ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ።

ወሳምንት ፡ በቢረሌ ፡

ስምንተኛዪቱም፡ መሠረት፡ ቢረሌ ፡ በሚ ባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወታስዕት ፡ በወራውሬ ፡

ዘጠነኛዪቱም፡ መሠረት፡ወራውሬ ፡ በሚ ባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወዐሥርት ፡ በክርስጵራስስ ፡

አሥረኛዪቱም፡ መሠረት፡ ክርስጵራስስ ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡

ወእንተ ፡ ዐሥሩ ፡ ወአሐቲ ፡ በያክንት ፡

አሥራ ፡ አንደኛዪቱ ፡ መሠረት ፡ ያክንት፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠች ፡ ናት፡

ወእንተ ፡ ዐሥሩ ፡ ወክልኤ ፡ በአሜቴስጢኖስ ።

ዐሥራ፡ ሁለተኛዪቱም፡መሠረት፡አሜቴስ ጢኖስ፡ በሚባል፡ ዕንቍ፡ ያጌጠች፡ ናት ።

፳፩ ፤ ወዴዴያቲሃኒ ፡ ዐሥሩ ፡ ወክልኤ ፡ በዐሥሩ፡ ወክልኤ ፡ ባሕርይ ፡

ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በር ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ዕርከን ፡ ባሥራ ፡ሁለቱ ፡ አዕናቍ፡ ያጌጡ፡ ናቸው ፡ ወለለአሐቲ ፡ ዴዴ ፡ አሐቲ ፡ ባሕርይ ፡ እያንዳንዱ ፡ ዕርከን ፡ እያንዳ ንዱ ፡ በር ፡ ጌጡ ፡ አንዳንድ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ባንዳንድ ፡ ዕንቍ ፡ ያጌጠ ፡ ነው ፡

ወጽጕ ፡ ሀገራ ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ ንጹሕ ፡

አደባባይዋ ፡ እንደ ፡ ጠራ ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ አለ ፡ የወርቅ ፡ አሸዋ ፡ ፈሶባታል ፡

ወያጸድል ፡ እንተ ፡ ውስጣ ፡ ከመ ፡ ማህው ።

ውስጧም ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ያበራል፡ አለ፡ ጽርየቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፪ ።

፳፪ ፤ ወኢርኢኩ ፡ ጽርሐ ፡ ዘከማሃ ፡

እንዲህ ፡ ያለች ፡ አዳራሽ ፡ አላየሁም፡ ርኢ ኩ፡ ይላል፡ እንዲህ፡ ያለች፡ አዳራሽ፡አየሁ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ ውእቱ ፡ ጽርሐ ።

ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳራሿ ፡ ነውና ፡

ወበግዑ ።

በግዑም ፡ ነውና ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ ይላል፡ አድሮባት ፡ ይኖራልና ፡ (ወበግዑ) ፡ በግ ዑም ፡ አድሮባት ፡ ይኖራልና ።

፳፫ ፤ ወሀገራሰ ፡ ኢትፈቅድ ፡ ፀሓየ ፡ ወወርኀ ፡ ከመ ፡ ያብርሁ ፡ ላቲ ፡

ሀገርነቷም ፡ ያበሩላት ፡ ዘንድ ፡ በመዓ ልት ፡ ፀሓይን ፡ በሌሊት ፡ ጨረቃን ፡ አትሻም ፡

እስመ ፡ ብርሃነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያበርህ ፡ ላቲ ፡

እግዚአብሔር ፡ ያበራላታልና ፡ አለ ፡ ብርሃኗ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡

ወማኅቶታ ፡ ውእቱ ፡ በግዑ ።

መብራቷም ፡ በግዑ ፡ ነውና ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፭ ። ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፳፫ና ፡ ፷ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፳፬ ፤ ወየሐውሩ ፡ አሕዛብ ፡ በብርሃነ ፡ ዚአሃ ፡

አሕዛብ ፡ በብርሃኗ ፡ ይሄዳሉ ፡ አለ ፡ ዜና ዋን ፡ ሰምተው ፡ መንነው ፡ ይሄዳሉ ፡ ጣ ዕመ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ምረረ ፡ ገሃነመ ፡ እሳትን ፡ እየሰሙ ፡ ሂደዋልና ፡

ወነገሥተ ፡ ምድርኒ ፡ ያመጽኡ ፡ አምኃ ፡ እምክብ ሮሙ ፡ ውስቴታ ።

ነገሥታቱም ፡ ዘውዳቸውን ፡ እየሰበሩ ፡ ይመጸውታሉ ፡ ኢሳ ፡ ፷ ፡ ፫ ፡ ፭ ።

፳፭ ፤ ወኢይትዐጸዉ፡አናቅጺሃ፡መዓልተ፡ወሌሊተ፡

በመዓልትም ፡ በሌሊትም፡በሮችዋ፡ አይዘ ጉም፡ አለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የሚገባ ፡ ከተገኘ ፡ አለመከልከሏን ፡ መናገር፡ ነው ፡

እስመ ፡ አልባቲ ፡ ሌሊት ።

ጨለማ ፡ የለምና ፡ አለ ፡ መከልከል ፡ የለ ምና ፡ ኢሳ ፡ ፷ ፡ ፲፩ ። ዘካ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ። ራእ ፡ ፳፪ ፡ ፭ ።

፳፮ ፤ ወያመጽኡ ፡ ክብሮሙ ፡ ወስብሐቲሆሙ ፡ አሕዛብ ፡ ውስቴታ ።

አሕዛብም፡ዘውዳቸውን፡ወርቃቸውን፡ብራ ቸው፡ንይመጸውታሉ።አንድም፡(ቀዳሚት፡ መሠረት፡በኢያሰጲድ)፡ኢያሰጲድ፡ኅብሩ፡ ጸሊም ፡ ወጸዓዳ ፡ ነው ፡ ሦስት ፡ ኅርወት ፡ አለበት ፡ በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡ የሮቤል ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ጸሊም ፡ ወጸዓዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፊት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷል ፡ ከአባቱ ፡ ዕቁባት ፡ ደርሷል፡ (ጥቅ) ፡ ሮ ቤል ፡ ወልድየ ፡ ርእሰ ፡ ጥብዓንየ ፡ ፀነ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ጊዜ ፡ ሰቀየተ ፡ ምድር ፡ ወባሕቱ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኅድር ፡ ላዕሌሁ ፡ እስመ ፡ ገብረ ፡ ምሕረተ ፡ ላዕለ፡ ዮሴፍ ፡ ወልድየ ፡ እንዲል ፡ በኋላ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷል ፡ ዮሴፍን ፡ ከወንድሞቹ ፡ አድኗል ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ አፅመ ፡ አበውን ፡ ከግብፅ ፡ ይዞ ፡ ሲወጣ፡ አፅሙ፡



www.ethiopianorthodox.org

ጠቁሮ ፡ አግኝቶታል ፡ ኋላ ፡ ጸልዮ ፡ መ
ልሶ ፡ አድኖታልና ፡ ሦስት ፡ ኅርወት ፡
እንዳለበት ፡ ሦስት ፡ ሥርዐት ፡ አፍር
ሷል ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከን ፡ ኢት
ክሥት ፡ ኃፍረተ ፡ ብእሲተ ፡ አቡከን ፡
ኢትዘሙን ፡ በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከሮ
ቤል ፡ ቤት ፡ የተወለደ፡ የጴጥሮስ ፡ ዕንቍ፡
ነው ፡ ጸሊም ፡ ወጸዓዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወሐይወ ፡ በመንፈስ ፡
እያለ ፡ ይጽፋልና ፡ ሦስት ፡ ኅርወት ፡ እን
ዳለበት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ክዶታልና ። አን
ድም ፡ ለመጻሕፍቱ ፡ በሦስቱ ፡ ስም ፡
አርእስት ፡ ሰጥቷልና ። አንድም፡ ረዐይኬ፡
ብሎ፡ሦስት፡ጊዜ፡መላልሶ፡ ሹሞታልና፡ ቢ
ል፡ይሆናል ። ሰንፔር፡ ኅብሩ፡ፍሕም፡ ይመ
ስላል ፡ በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡ የስምዖን ፡
ዕንቍ ፡ ነው ፡ ተናዶ ፡ ጠላቶቹን ፡ አጥፍ
ቷልና፡(ጥቅ)፡ ስምዖን፡ ወሌዊ፡ ፈጸምዋ፡ ለ
ዐመፃ ፡ በቅንዓቶሙ ፡ ወበቃሕዎሙ ፡ እን
ዲል ። በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከቤተ ፡ ስም
ዖን ፡ የተወለደ ፡ የእንድርያስ ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ ተባዕ ፡ ለመስቀል ፡ በኰረ ፡ ሐዋር
ያት፡ይለዋልና፡በአባት ፡ ከሮቤል፡ በእናት፣
ከስምዖን ፡ ይወለዳሉና ። ከአባት፡ ወገን ፡
ጴጥሮስን ፡ ከእናት ፡ ወገን፡እንድርያስን ፡
አመጣ ፡ ኬልቄዶን ፡ ኅብሩ ፡ ሐመል
ሚል ፡ ነው ፡ ብቃያ ፡ ይመስላል ፡ በብ
ሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡ የይሳኮር ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ በተገብሮ፡ ኗሪ፡ ነውና፡ (ጥቅ)፡ ይሳ
ኮር፡ ፈተዋ፡ ለሠናይት፡ ወአትሐተ ፡ መት
ከፎ ፡ ከመ ፡ ይትቀነያ ፡ ለምድር ፡ እን
ዲል ፡ በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከሳይኮር ፡
ቤት ፡ የተወለደ ፡ የማቴዎስ ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ምሳሌ ፡ ዘርዕን፡
አብዝቶ ፡ ጽፏልና ፡ መረግድ ፡ ኅብሩ ፡
ጸዓዳ ፡ ወቀይሕ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ አፈ ፡

ሰይፍ ፡ ያለ ፡ መውጊያ ፡ አለበት ፡ በብ
ሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡ የይሁዳ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡
ጸዓዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጸዓዳ ፡ ስነኒሁ ፡ ከመ
ሐሊብ ፡ ወፍሡሐት ፡ አዕይንቲሁ ፡ እም
ወይን ፡ ይለዋልና ። ቀይሕ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡
የጠላቶቹን ፡ ደም ፡ ያፈሳልና ፡ እንደ ፡
አፈ ፡ ሰይፍ ፡ ያለ ፡ መውጊያ ፡ አለበት ፡
ይሁዳ ፡ እዴከ ፡ ዲበ ፡ ዘባኖሙ ፡ ለፀርከ ፡
ይለዋልና ። በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከይ
ሁዳ ፡ ቤት ፡ የተወለደ ፡ የዮሐንስ ፡ ወልደ፡
ዘብዴዎስ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ጸዓዳ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ዮሐንስ ፡ ማለት ፡ ፍሥሐ ፡ ወሐ
ሤት ፡ ርኅራኄ፡ ወሣህል ፡ ማለት ፡ ነውና፡
ቀይሕ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደማችሁን ፡ አፍ
ስሱ ፡ የምትል ፡ ሕገ ፡ ተስፋ ፡ ወንጌልን ፡
ጽፏልና ። አንድም ፡ ከጌታ ፡ ጎን ፡ ትኩስ፡
ደም ፡ ጥሩ ፡ ውኃ ፡ ሲፈስ ፡ አይቷልና ፡
እንደ ፡ አፈ ፡ ሰይፍ ፡ ያለ ፡ መውጊያ ፡
እንደ ፡ አለበት ፡ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ ያላት ፡
መናፍቃንን ፡ አጋንንትን፡ እንደ፡ እሳት ፡
ታቃጥላቸዋለች ፡ እንደ ፡ መዶሻ ፡ ትቀጠ
ቅጣቸዋለች ፡ እንደ ፡ ሰይፍ ፡ ትቆራርጣ
ቸዋለችና ። ሰርዶንክስ ፡ ኅብሩ ፡ ደም ፡
ይመስላል ፡ ጽዕዳዌ፡ ዘይኄይሎ፡ ይላል ፡
ሰማያዊ ፡ ነው ፡ በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡
የሌዊ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ የሰማያዊ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ ደመ ፡ አባግዕን ፡
ያፈሳልና ። በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከሌዊ ፡
ቤት ፡ የተወለደ ፡ የያዕቆብ ፡ ወልደ ፡ ዘብ
ዴዎስ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ የሰማያዊ ፡ ክር
ስቶስን ፡ ነገር ፡ ሲያስተምር ፡ ሄሮድስ ፡
በሰይፍ ፡ አስመትቶ ፡ ገድሎታልና ። በአ
ባት፡ከቤተ፡ ይሁዳ፡በእናት ፡ ከቤተ፡ ሌዊ፡
ይወለዳሉና፡ ከአባት፡ ወገን፡ ዮሐንስን፡ ከ
እናት፡ወገን፡ያዕቆብን፡አመጣ። ሰርድዮን ፡
ኅብሩ፡ ወርቅ፡ ይመስላል ፡ በብሉይ፡ ዕንቍ



ነቱ ፡ የጋድ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ጽኑይ ፡
ፍርድን ፡ ይፈርዳልና፡ በጽኑይ ፡ ፍርድ ፡
ይኖራሉና ፡ (ጥቅ) ፡ ለጋድ ፡ ፈየትዎ ፡
ፈያት ፡ ወውእቱኒ ፡ ተሊዎ ፡ ዐሠሮሙ ፡
ፈየቶሙ ፡ እንዲል ፡ በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡
ከጋድ ፡ ወገን ፡ የተወለደ ፡ የያዕቆብ ፡
ወልደ ፡ እልፍዮስ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ጽኑይ፡
ትምህርቱ ፡ ለእለ ፡ ይትዌከፍዎ ፡ ይለዋ
ልና ። ክርስቲሎቤ፡ ኅብሩ፡ ሐመልሚል ፡
ነው ፡ ብጫ ፡ ይመስላል ፡ በብሉይ ፡ ዕን
ቍነቱ ፡ የንፍታሌም ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ንፍ
ታሌምን ፡ በቀልት ፡ ይለዋል ፡ ይህ፡ በቀ
ልት ፡ ብጫ ፡ ይመስላልና ፡ በሐዲስ፡ ዕን
ቍነቱ ፡ ከንፍታሌም ፡ ቤት ፡ የተወለደ ፡
የበርተሎሜዎስ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ወይን ፡
ተክሎ ፡ ዕለቱን ፡ ለመሥዋዕት ፡ አድርሷ
ልና ። አንድም ፡ አዋልደ ፡ ክርስቶስ ፡
ሥርግዋት ፡ እያለ ፡ ያስተምራልና ። ቢ
ረሌ ፡ ኅብሩ ፡ በረድ ፡ ይመስላል ፡ አጥፌ
ነት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡
የዛብሎን ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ጠላቶቹን ፡ ለማ
ጥፋት ፡ ጫማውን ፡ አዝቦ ፡ ይኖራልና ፡
(ጥቅ) ፡ ዛብሎን ፡ ስዑኖ ፡ የኀድር ፡ ከመ ፡
መርሶ ፡ ለአሕማር ፡ እንዲል ፡ በሐዲስ ፡
ዕንቍነቱ ፡ ከዛብሎን ፡ የተወለደ ፡ የፊል
ጶስ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ የመናፍቃንን ፡ ትም
ህርት ፡ ለማጥፋት ፡ ጫማ ፡ ትምህርቱን ፡
አዝቦ ፡ ይኖራልና ። አንድም ፡ በብሔረ ፡
ጽልመት ፡ በአፍራቅያ ፡ ብርሃን ፡ ትም
ህርቱን ፡ ገልጿልና ። ወራውሬ ፡ ኅብሩ ፡
ማይ ፡ ይመስላል ፡ በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡
የብንያም ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ (ታሪክ) ፡ እስራ
ኤል ፡ ከግብፅ፡ ሲወጡ ፡ የሚጓዙ ፡ እንደ ፡
ትውልዳቸው፡ ነው፡ ሙሴ፡ኤርትራን፡ከሦ
ስት ፡ ካራት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ ተሻገሩ ፡ አላ
ቸው ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ የቆመ ፡

ውኃ ፡ ተንዶ ፡ ቢጫኑንሳ ፡ ብለው ፡ ፈር
ተው ፡ ከዳር፡ቆሙ፡ ሳለ፡ ብንያም፡ በኋላ ፡
ቢደርስ ፡ ቆመው ፡ አግኝቷቸዋል ፡ ምነ
ው ፡ ከዚህ ፡ ቆማችኋል ፡ አላቸው ፡ ይህ ፡
እንደ ፡ ዕንጨት ፡ የቆመ ፡ ውኃ ፡ ተንዶ ፡
ይጫነናል ፡ ብለን ፡ ፈርተን ፡ አሉት ፤
የአባቶቻችን ፡ ፈጣሪ ፡ በግብፅ ፡ ዘጠኝ ፡
መቅሠፍት ፡ ዐሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵር ፡
አድርጎ ፡ ያወጣኝ ፡ ባሕር ፡ ከፍሎ ፡ ተሻ
ገር ፡ ቢለኝ ፡ እጠራጠረዋለሁ ፡ ብሎ ፡
በፊት ፡ እሱ ፡ ቀድሞ ፡ ተሻግሯል ፡ ህየ ፡
ብንያም ፡ ወሬዛ ፡ በኃይሉ ፡ ያሰኘበት ፡
ቅሉ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድ
ርገው ፡ ሁሉም ፡ ተሻግረዋል ፡ በሐዲስ ፡
ዕንቍነቱ ፡ ከብንያም ፡ ቤት ፡ የተወለደ ፡
የናትናኤል ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ከሁሉ ፡ ይል
ቅ ፡ አብዝቶ ፡ አጠመቀ ፡ ይለዋልና ።
ክርስጵራስስ ፡ ኅብሩ ፡ ድብ ፡ ያለ ፡
ነው ፡ እየቆየ፡ እየፈጋ፡ ይሄዳል፡ በብሉይ ፡
ዕንቍነቱ ፡ የአሴር ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ድብ ፡
ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሴርን ፡ ጽጉበ ፡ ዕክ
ል ፡ ይለዋል ፡ ባለጸጋ ፡ ድብ ፡ ያለው ፡
ነውና ፡ እየቆየ ፡ እየፈጋ ፡ እንዲሄድ ፡ ኑሮ፡
ኑሮ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠላቱን ፡
ሳያጠፋ ፡ አይመለስምና ፡ አሴር ፡ ዘእ
ገሪሁ ፡ ኀጺን ፡ ወአሣዕኒሁ ፡ ዘብርት ፡
ይለዋልና ፡ በሐዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከአ
ሴር ፡ ቤት ፡ የተወለደ ፡ የቶማስ ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ ድብ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትንሣ
ኤውን ፡ ከማመን ፡ ዘግይቷል ፡ እየቆየ ፡
እየፈጋ ፡ እንዲሄድ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላ
ኪየ ፡ ብሏል ፡ ይህንም ፡ ሊቁ ፡ አንተ ፡
ዘቀዳሚ ፡ ወአንተ ፡ ዘይእዜ ፡ ብሎ ፡ ወስ
ዶታል ። አንድም ፡ በብሔረ ፡ ጽልመት ፡
በህንደኬ ፡ ብርሃን ፡ ትምህርቱን ፡ ገል
ጾአልና ። ያክንት፡ ኅብሩ፡ ሰማያዊ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡ የዮሴፍ ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ ለሰማያዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ምሳሌ ፡
ሆኖ ፡ ለሠላሳ ፡ ብር ፡ ተሸጧልና ፡ በሐ
ዲስ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ከዮሴፍ ፡ ቤት ፡ የተወ
ለደ ፡ የታዴዎስ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ ዘማን ፡
በነፋስ ፡ ሰቅሏልና ። አንድም ፡ ስንዴ ፡
ዘርቶ ፡ ዕለቱን ፡ ለመሥዋዕት ፡ አድርሷ
ልና ። አሜቴስጢኖስ፡ ኅብሩ ፡ ብር ፡ ይመ
ስላል ፡ በብሉይ ፡ ዕንቍነቱ ፡ ምሽቱ ፡ ለ
መቶ ፡ ብር ፡ የሸጠችው ፡ ሶምሶን ፡ ከሱ ፡
የተወለደ፡ የዳን፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ (ቅርሽ ፡ ይ
ላል)፡ በሐዲስ፡ዕንቍነቱ፡ መምህሩን፡ ለሠ
ላሳ ፡ ብር ፡ በሸጠ ፡ በይሁዳ ፡ እግር ፡ የገባ፡
የማትያስ ፡ ዕንቍ፡ ነው ። ዐሥራ፡ ሁለቱ፡
ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ባሥ
ራ ፡ ሁለቱ ፡ አዕናቍ ፡ ይመሰላሉ ፡ እያንዳ
ንዱ ፡ ነገድ ፡ እያንዳንዱ፡ ሐዋርያ፡ ባንድ፡
አንድ ፡ ዕንቍ ፡ ይመሰላል ፡ ምሳሌው ፡
አንድ ፡ አንድ ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡
አዕሡ ፡ ውሉድ ፡ በምሳሌ ፡ ተካክለው ፡
ተገኝተዋል፡ (ጥቅ)፡ ውእተ፡ አሚረ፡ይትራ
ከብ ፡ ዘርዕ ፡ ምስለ ፡ ማእረር ፡ ወዮኀብር፡
ሠርፅ ፡ ምስለ ፡ ቀሥም ፡ እንዲል ፡ ገቢ
ዎም ፡ መግቢያዋም ፡ የዕንቍ ፡ ቤት ፡
አሳይቶታል ፡ ሐዋርያት ፡ ገቢዎችም ፡
አግቢዎችም ፡ ናቸውና ። አንድም ፡ ኢያ
ሰጲድ ፡ በፀሓይም ፡ በእሳትም ፡ አይቀል
ጥም ፡ በአረር ፡ ውኃ ፡ እያቀለጡ ፡ እየሰ
ፉ ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ ጨምረው ፡ ቀ
ለበት ፡ አሠርተው ፡ የያዙት ፡ እንደ ፡
ሆነ፡ካለፈውም፡ ከሚመጣውም፡ ሥራይ ፡
ይጠብቃል ፡ ኢያሰጲድ ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡
ነው ፡ በፀሓይ ፡ በእሳት ፡ እንዳይቀልጥ ፡
ብግድ፡ ሰው ፡ አልሆነም ፡ በአረር ፡ ውኃ፡
እንዲቀልጥ ፡ በፈቃዱ ፡ ሰው ፡ ሆኗል ፡
የሰው ፡ ሥጋ ፡ ጨምረው ፡ አሠርተው ፡

የያዙት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከሚመጣውም ፡ ካለ
ፈውም ፡ ሥራይ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ሥጋን ፡
ተዋሕዶ ፡ ያመኑበት ፡ ምእመናንን ፡ ካለ
ፈውም ፡ ከሚመጣውም ፡ ፍዳ ፡ አድኗ
ልና ። ሰንፔር ፡ እባብ ፡ ለነደፈው ፡ በጥቶ፡
የቀበሩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርዙን ፡ መጥ
ምጦ ፡ ያወጣዋል ፡ ዕንቍ ፡ ይጠቁራል ፡
ወስደው ፡ ከባሕር ፡ ይጥሉታል ፡ ሦስት ፡
መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ ባሕ
ር፡ አድሮ፡ወደ፡ቀደመ፡ኅብሩ፡ይመለሳል።ሰ
ንፔር፡የተባለ፡ጌታ፡ነው፡ ሰንጴር፡ እባብ፡ለ
ነደፈው፡በጥቶ፡ የቀበሩት፡እንደ፡ሆነ ፡ መር
ዙን፡መጥምጦ፡እንዲያወጣው፡ ዲያብሎስ፡
በሥጋ ፡ ከይሲ ፡ ተሠውሮ ፡ ቢያስት ፡
ጌታ ፡ ዲያብሎስ ፡ ያሳተበትን ፡ ሥጋ ፡
ተዋሕዶ፡ አድኖበታልና።(ጥቅ)፡ወበከመ ፡
ኮነ ፡ ተኀብአ ፡ ሰይጣን ፡ በጕሕሉት ፡ ው
ስተ ፡ ሥጋ ፡ ከይሲ ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ድኅ
ነትነ ፡ በተሰውሮተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በዘመድነ ፡ ወኀበ ፡ አርዌ ፡ ምድር፡
ቄዐ ፡ ኀምዞ ፡ በኢሰሚዕ ፡ ህየ ፡ ቃል ፡
በዊዖ ፡ በሰሚዕ ፡ አሕየወ ፡ እንዲል ፡ እን
ዲጠቁር ፡ በአዳም ፡ የተፈረደውን ፡ ጸዋት
ወ፡መከራ፡ተቀብሏል፡ (ጥቅ)፡ እንተ፡ ባቲ ፡
አመከረነ ፡ ጸላኢ ፡ ነሥአ ፡ ደዌነ ፡ ወጾረ ፡
ሕማመነ ፡ እንዲል ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡
ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ ባሕር ፡ አድሮ፡
ወደቀደመ ፡ ኅብሩ ፡ እንዲመለስ ፡ እሱም፡
በከርሠ ፡ መቃብር ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡
ሦስት ፡ ሌሊት ፡ አድሮ ፡ ውስና ፡ መቃ
ብርን ፡ አጥፍቶ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁኖ ፡
ለመነሣቱ ፡ ምሳሌ ፡ (ጥቅ) ፡ ወኀደገ ፡
ንዴተ ፡ ህላዌ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ተመይጠ ፡
ወገብአ ፡ ኀበ ፡ ስብሓቲሁ ፡ ወክብሩ ፡
እንዲል ፡ ኬልቄዶን ፡ ድምፀ ፡ መልካም ፡
ነው ፡ ምፅ ፡ የሚጸናባት ፡ ያፍ ፡ አለች ፡

www.ethiopianorthodox.org



ድምፁን ፡ የሰማች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምፅ ፡
ሳይሰማት ፡ ትወልዳለች ፡ ኬልቄዶን ፡
የተባለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ በሕማም ፡ ለዲ ፡
ያለውን ፡ መርገም ፡ አጥፍቶ ፡ ተወልዷ
ልና ። አንድም፡ በእሱ ፡ ባመኑ ፡ ምእመ
ናን ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ የለባቸውምና ።
መረግድ ፡ ይዘውት ፡ ወፋ፡ የወጡ፡ እንደ፡
ሆነ ፡ ድል ፡ አያስነሳም ፡ መረግድ ፡ የተ
ባለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ በእሱ ፡ ያመኑ፡ምእመ
ናንን ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡ አይነሷቸው
ምና ። ሰርዶንክስ ፡ የነጋድያን ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ ይዘውት ፡ በመርከብ ፡ የተጫኑ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ አይነሳባ
ቸውም ፡ ሰርዶንክስ ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡
ነው ፡ በእሱ ፡ ባመኑ፡ምእመናን ፡ ማዕበለ፡
ኃጢአት ፡ ሞገደ ፡ ኃጢአት ፡ ማዕበለ ፡ ክ
ህደት ፡ ሞገደ ፡ ክህደት ፡ አይነሣባቸው
ምና ። አንድም ፡ ገሠጸ ፡ ባሕረ ፡ ወነፋ
ሳተ ፡ ይለዋልና ። ሰርድዮን ፡ እንደ ፡ ጃን፡
ተከል ፡ ያኖሩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነፍጥ ፡
አያስተኩስም ፡ ጦር ፡ አያስወረውርም ፡
ሰርድዮን ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡ ነው፡ በእሱ ፡
ባመኑ ፡ ምእመናን ፡ ፀብአ ፡ አጋንንት ፡
አይበረታባቸውምና ። ክርስቲሎቤ ፡ በፀ
ሓይም ፡ በእሳትም ፡ አይቀልጥም ፡ በአ
ረር ፡ ውኃ ፡ እያቀለጡ ፡ ለንዋያት፡ ሁሉ ፡
ጌጥ ፡ ያደርጉታል ፡ ክርስቲሎቤ ፡ የተባለ፡
ጌታ ፡ ነው ፡ ምሳሌው ፡ እንደ ፡ ኢያስ
ጲድ ፡ ነው ፡ ለንዋያት ፡ ሁሉ ፡ ጌጥ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ጌታም ፡ ሠርጕ፡ ምእመናን ፡
ነውና ፡ ቢረሌ ፡ በአንጻር ፡ ያሳዩት ፡ እንደ፡
ሆነ ፡ የተቀበረውን ፡ ወርቅ ፡ እያፈናጠረ ፡
የሚያወጣ ፡ ነው ፡ ቢረሌ ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡
ነው ፡ እምከመ ፡ ተለዐልኩ ፡ እምድር ፡
እስሕብ ፡ ኵሎ ፡ ኀቤየ ፡ ብሏልና ፡ ወራ
ውሬ ፡ ደንጊያውን ፡ ሰብስቦ ፡ ያሳዩት ፡

እንደ ፡ ሆነ ፡ አቅልጦ ፡ አንድ ፡ ያደርገ
ዋል ፡ ወራውሬ ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡
ሕዝብንና፡ አሕዛብን፡ ነፍስንና፡ ሥጋን ፡
ሰውንና ፡ መላእክትን ፡ሰውንና ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ አስታርቋልና፡
ክርስጵራስስ ፡ ፃዕር ፡ በጸናበት፡ወስደው ፡
ከላዩ ፡ ላይ ፡ ያኖሩት ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ፃዕር ፡
ሳይሰማው ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ትለያ
ለች ፡ ዕንቍው ፡ ይጠቁራል ፡ ወስደው ፡
ከባሕር ፡ ይጥሉታል ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡
ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ ባሕር ፡ አድሮ ፡
ወደ ፡ ቀደመ ፡ ኅብሩ ፡ ይመለሳል ፡ ክርስ
ጵራስስ ፡ የተባለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ በእሱ ፡
ባመኑ ፡ ምእመናን ፡ ፃዕር ፡ የለባቸው
ምና ። አንድም ፡ ፃዕረ ፡ ዘሞት ፡ ፈትሐ ፡
ይለዋልና ። ያክንት ፡ አክባሪ ፡ ዕንቍ ፡
ነው ፡ ክብረ ፡ ነገሥታት ፡ ነው ፡ ሰሎ
ሞን ፡ ሐሩራኤል ፡ ጭልዋቅ ፡ የሚል ፡
የጌታን ፡ ኅቡዕ ፡ ስም ፡ ቀለበት ፡ አሠ
ርቶ ፡ ጽፎ ፡ ይዞ ፡ ነበረ ፡ ያክንት ፡ የተ
ባለ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ክብረ ፡ ምእመናን፡ነው
ና ። አሜቴስጢኖስ ፡ ደም ፡ ቃታ ፡ ለያ
ዘው ፡ ይበጃል ፡ ኮሶ ፡ ለጠመመው ፡ ይበ
ጃል፡ እሱም፡ ጕሕቍትን፡ ቅብውን፡ እንተ
ደም ፡ ይውኅዛን ፡ አድኗልና ። አሥራ ፡ ሁ
ለቱ ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡
ያመኑበት ፡ ጌታ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ፡
አሥራ ፡ ሁለቱ፡ ሐዋርያት ፡ በተመሰሉ
ባቸው ፡ በ፲፪ቱ ፡ አዕናቍ ፡ ይመሰላል ፡
እያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሐዋርያ ፡
ያመነበት ፡ ጌታ ፡ እያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ እያ
ዳንዱ ፡ ሐዋርያ ፡ በተመሰለበት ፡ ዕንቍ ፡
ይመሰላል ፡ ምሳሌው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡
ዕንቍ ፡ ነው ። (ወሀገራሰ) ፡ እመቤ
ታችን ፡ በመዓልት ፡ ፀሐይን ፡ በሌ
ሊት ፡ ጨረቃን ፡ አትሻም ፡ አለ ፡ ፀሓይ ፡

ጨረቃ ፡ ምሳሌዋ ፡ ሊሆኑ ፡ አትሻም ፡ ምሳሌዋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ በግ ዑም ፡ ነውና ፡ አሕዛብ ፡ በሷ ፡ ተስፋ ፡ በእሷ፡ ኪዳን ፡ አምነው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራ ሉ፡ (ጥቅ)፡ ለምንት፡ የሐውር፡ ወልደ፡ ብእ ሲት ፡ ምስለ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ወእለ ፡ አምሰጡ ፡ የሐውሩ ፡ ባቲ ፡ እንዲል ። አን ድም ፡ በልጅዋ ፡ አምነው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ነገሥተ ፡ እስራኤልም ፡ ዘው ዳቸውን ፡ እየሰበሩ ፡ በእሷ ፡ ስም ፡ ይመ ጸውታሉ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በሯ ፡ አይዘጋም ፡ ሌሊት ፡ የለምና ፡ አለ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ሰአሊ ፡ ለነ ፡ ቅድስት ፡ ሳይላት ፡ የሚውል ፡ የለምና ፡ እሷን ፡ ከማ መስገን ፡ ማቋረጥ ፡ የለም ። አሕዛብ ፡ በሷ ፡ ስም ፡ ዘውዳቸውን ፡ እየሰበሩ ፡ ይመ ጸውታሉ ። አንድም ፡ (ወሀገራሰ ፡ ኢትፈ ቅድ) ፡ መምህራን ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ምሳ ሌያቸው ፡ ሊሆኑ ፡ አይሹም ፡ አለ ፡ ሊያ ስተምሯቸው ፡ አይሹም ፡ ዕውቀታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ በግዑም፡ ነውና ፡ ምእመናን ፡ በበግዑ ፡ ትምህርት ፡ ጸን ተው ፡ ይኖራሉ ፡ ነገሥታቱም ፡ ለመም ህራን፡ አሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ ይሰጣሉ ፤ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ትምህርት ፡ አይፈታም ፡ (እስመ ፡ አልባቲ) ፡ ድንቁ ርና ፡ ርቋልና ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ለመ ምህራን፡አሥራቱን፡ በኵራቱን፡ይሰጣሉ ።

፳፯ ፤ ወኢይበውእ ፡ ውስቴታ ፡ ኵሉ ፡ ዘርኵስ ፡ ወዘይገብር ፡ ግማኔ ፡ ወሐሰተ ፡

ኃጢአትን ፡ የሚሠራ ፡ ሐሰትንም ፡ የሚ ናገር ፡ ሁሉ ፡ አይወርሳትም ፡

ወዘኢኮነ ፡ ጽሑፈ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ዘበግዑ ።

በበግዑ፡ ልቡና፡ ያልተጻፈ፡ አለ፡ ለበጎው፡ ነገር ፡ በልበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልታወቀ፡ ሁሉ ፡ አይወርሳትም ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፲፭። ፊል ፡ ፬ ፡ ፫ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ ፤ ወአርአየኒ ፡ ፈለገ ፡ ዘማየ ፡ ሕይወት ፡ ጸዓዳ ፡ ከመ ፡ በረድ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ የጠራ ፡ የሕይወት ፡ ውኃ ፡የሚፈስበትን ፡ ወንዝ ፡ አሳየኝ ፡ አለ ፡ ልጅነት ፡ የሚሰጥበትን ፡ ግብር ፡ ገለጠልኝ ፡

ወይወፅእ ፡ እምነ ፡ መንበሩ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ከእግዚአብሔር ፡ ከመንበሩ ፡ እግር ፡ ይወ ጣል ፡ አለ ፡ ከጌትነቱ ፡ ይሠጣል ፡

ወሥልጣነ ፡ በግዑ ።

ከበግዑም ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣል ። አን ድም ፡ በበግዑ ፡ ሥልጣን ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ከጌትነቱ ፡ ይሰጣል ፡ ሕዝ ፡ ፵፯ ፡ ፲፪ ። ዘካ ፡ ፲፬ ፡ ፰ ።

፪ ፤ ወይውኅዝ ፡ ማእከለ ፡ መርሕባ ፡

ባደባባይዋ፡ በዝቶ፡ ይፈሳል፡ አለ፡ በመንግ ሥት ፡ ሰማይ ፡ በዝቶ ፡ ይሰጣል ፡

ወኑምለፌኒ ፡ ውእቱ ፡ ፈለግ ፡

ከመንበሩ ፡ ወዲህ ፡ ወንዝ ፡ አለ ፡

ወእምከሓሁኒ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡

ከመንበሩም ፡ ወዲያ ፡ ዕፀ፡ ሕይወት፡ አለ ፡ መንበር፡በመካከል፡ነው፡ከምጽአት፡ አስቀ ድሞ ፡ ልጅነት ፡ አለ ፡ ከምጽአትም ፡ በ ኋላ ፡ ትንሣኤ ፡ አለ ። አንድም ፡ ከዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ወዲህ ፡ ወንዝ ፡ አለ ፡ ከወን ዙም ፡ ወዲያ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ከት ንሣኤ ፡ አስቀድሞ ፡ ልጅነት ፡ አለ ፡ ከል ጅነት ፡ በኋላ ፡ ትንሣኤ ፡ አለ ። አንድም ፡ እምለፌ ፡ ውእቱ ፡ ፈለግ ፡ ከወዲያኛው ፡ ወንዝ ፡ ወዲህ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ከወንዙም ፡ ወዲያ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ከደገኛው ፡ ክብር ፡ አስቀድሞ ፡ የዓረቦኑ ፡ ክብር ፡ አለ ፡ ከዐረቦኑም ፡ ክብር ፡ በኋላ ፡ ደገኛው ፡ ክብር ፡ አለ ፡

ወይገብር ፡ ፍሬ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ለለአሐዱ ፡ ወርኅ ።

ለያንዳንዱ ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ፍሬ ፡

ያፈራል ፡ አለ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋር ያት ፡ ስብከት ፡ ይወረሳል ፡ (በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሥዩማን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡

ወቈጽለ ፡ ዕፁኒ ፡ ፈውስ ፡ ለሕይወተ ፡ አሕዛብ ።

ቅጠሉም ፡ ለአሕዛብ ፡ ሰውነት ፡ ፈውስ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ተስፋነቱ ፡ ለአሕዛብ ፡ ሰው ነት፡ ነው ፡ ም፡ ፳፩፡ ፳፩ ። ሕዝ፡ ፵፯፡ ፲፪ ።

፫ ፤ ወአልቦ ፡ እንከ ፡ ርኩስ ፡ ወኢምንትኒ ።

ኃጥእ፡ ግን፡ ምንም፡ ምን፡ አይወርሳትም ።

ወሀለወ ፡ ውስቴታ ፡ መንበረ ፡ እግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ጌትነቱ ፡ ታውቆባት ፡ ይኖራል ፡

ወበግዑ ፡

የበግዑም፡ጌትነቱ፡ ታውቆባት፡ ይኖራል ፡

ወኢይከውን ፡ መዓት ፡ ላዕለ ፡ አግብርቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እለ ፡ ያመልክዎ ፡

እግዚአብሔርን ፡ በሚያመልኩ ፡ በምእ መናን ፡ ላይ ፡ ቁጣ ፡ የለም ፡ አለ ፡ ሐሩ ፡ መባል ፡ አያገኛቸውም ። አንድም ፡ ክህ ደት ፡ የለም ፡ አለ ፡ ምእመናን ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ አይክዱትም ፡ (ጥቅ)፡ መዓተ ፡ አርዮስ ፡ እንዲል ፡

አላ ፡ ያመልክዎ ፡ ይላል ።

ሲያመልኩት፡ይኖራሉ፡እንጅ፡ዘካ፡፲፬፡፲፩።

፬ ፤ ወይሬእዩ ፡ ገጾ ፡

ፊቱን ፡ ያያሉ ፡ አለ ፡ ባለሟሎች ፡ ይሆ ናሉ ፡

ወስሙ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሞሙ ።

ስሙም ፡ በግምባራቸው ፡ ተጽፍዋል ፡ አለ፡ በገጸ ፡ ልቡናቸው ፡ ተጽፏል ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፫ ። ም ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፭ ፤ ወአልቦ ፡ እንከ ፡ ሌሊት ፡

እንግዲህ ፡ ሌሊት ፡ የለም ፡ አለ ፡ ድንቁ ርና ፡ የለም ፡

ወኢይፈቅዱ ፡ ብርሃነ ፡ ማኅቶት ፡ ወብርሃነ ፡ ፀሐይ ፡

የመብራትን ፡ ብርሃን ፡ የፀሐይንም ፡ ብር ሃን ፡ አይሹም ፡ አለ ፡ ከሰው ፡ የሚገኘ ውን ፡ ዕውቀት ፡ አይሹም ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያበርህ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

ዕውቀታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡

ወይነግሡ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ ነግሠው ፡ ይኖራሉ ፡ ም ፡ ፳፩፡ ፳፭ ። ም ፡ ፭ ፡ ፲። ዳን ፡ ፯ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ።

፮ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዝክቱ ፡ ቃለ፡ ጽድቅ፡ ወመሃይምን፡ እግዚእነ ፡

የታመነ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ጌታችን ፡

ወእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡

ወመንፈሰ ፡ ነቢያት ፡ ዘፈነወ ፡ መልአኮ ፡ ከመ ፡ ያርእዮሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ ዘሀለወ ፡ ይኩን ፡ ፍጡነ ።

በነቢያት ፡ አድሮ ፡ ነቢያትን ፡ የሚያና ግር ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ውን ፡ ለባለሟሎቹ ፡ ይነግራቸው ፡ ዘ ንድ ፡ መልአኩን ፡ የሰደደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፯ ፤ ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡

ይቤለኒ ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡ ፈጥኜ ፡ እመ



www.ethiopianorthodox.org

ጣለሁ፡ አለኝ። ወብፁዕ፡ ማንሻ። አንድም፡ አንድ፡ ወገን ፡ ጌታችን፡ የታመነ፡ አካላዊ ፡ ቃል፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢያት፡ አድሮ፡ ነቢያትን ፡ የሚያናግር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ለባለሚሎቹ ፡ ይነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ መልአኩን ፡ የሰደደ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቤለኒ ፡ እመጽእ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣለሁ ፡ አለኝ ፡

ወብፁዕ ፡ ዘየዐቅብ ፡ ቃለ ፡ ተነብዮቱ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ።

በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ የተነገረውን ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ ደግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከሆነ ፡ በዠመረበት ፡ መጨረስ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ብፁዕ ፡ ዘየዐቅብ ፡ አለ ፡ ቍ ፡ ፱ ፡፳ ። ም ፡ ፫ ፡ ፲፩ና ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፰ ፤ ወአነ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘርኢኩ ፡ ወዘሰማዕኩ ፡ ዘንተ ፡ ሰገድኩ ፡ ቅድመ ፡ እገሪሁ ፡ ለውእቱ ፡ መልአክ ፡ ዘአርአየንዮ ፡ ለዝንቱ ።

ይህን ፡ ያየሁ ፡ የሰማሁ ፡ እኔ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰገድኩ ፡ ቅድመ ፡ እገሪሁ ፡ ይህን ፡ ለነገረኝ ፡ ለዚያ ፡ መልአክ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወድቄ ፡ ሰገድሁ ፡ (ለገለጸልኝ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፲ ።

፱ ፤ ወይቤለኒ ፡ ኢትስግድ ፡ ሊተ ፡ ዑቅ ፡ የጊ ፡

መቸም ፡ መች ፡ ለኔ ፡ እንዳትሰግድ ፡ ዕወቅ ፡ አለኝ ፡

ገብረ ፡ አኃእዝቲከ ፡ አነ ፡

የጌቶችህ ፡ የሥላሴ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና።

ወዘአኀዊከ ፡ ነቢያት ፡

የወንድሞችህ ፡ የነቢያት ፡ የሐዋርያት ፡ ጌቶች ፡ የሚሆኑ ፡ የሥላሴ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና ፡

ወዘእለ ፡ የዐቅቡ ፡ ቃለ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡

በዚህ ፡ መጽሐፍ፡ የተነገረውንም፡የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ጌቶች ፡ የሚሆኑ ፡ የሥላሴ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና ። አንድም ፡ የወንድሞችህ ፡ የነቢያት ፡ የሐዋርያት ፡ ባልደረባ ፡ የምሆን ፡ የሥላሴ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተነገረውንም ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ባልደረባ ፡ የምሆን ፡ የሥላሴ ፡ ተገዥ ፡ ነኝና ፡ ዑቅ ፡ ኢትስግድ ፡ ላለው ።

ወአንተሰ ፡ ለእግዚአወሔር ፡ ስግድ ።

ለእግዚአብሔር ፡ ስገድ ፡ እንጅ ፡ ዑቅ ፡ ኢትስግድ ፡ ላለው ።

፲ ፤ ወኢትኅትም ፡ ቃለ ፡ ተነብዮቱ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡

በዚህ ፡ መጽሐፍ፡ የተነገረውንም፡ ነገር ፡ አትሠውር ፡

እስመ ፡ በጽሐ ፡ ዘመኑ ።

የሚገለጥበት ፡ ዘመኑ ፡ ደርሷልና ።

፲፩ ፤ ወለዘገፍዐኒ ፡ ይገፍዕዎ ፡ እንከ ፡

የበደለን ፡ የሚበድሉበት ፡

ወለዘረስሐኒ ፡ ያረስሕዎ ፡ እንከ ፡

ኃጥእንም ፡ ኃጥእ ፡ የሚሉበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡

ወጻድቅ ፡ ለይጸደቅ ፡

ጻድቁ ፡ ዐስበ ፡ ጽድቁን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡

ወንጹሕኒ ፡ ለይንጻሕ ፡

ንጹሑም ፡ ዐስበ፡ ንጹሑን፡ ያገኝ፡ ዘንድ ፡ ዘመኑ ፡ ቀርቧልና ። አንድም ፡ የበደለን ፡ እንጅ ፡ ይበድሉታል ፡ ኃጥእንም ፡ እንጅ ፡ ኃጥእ ፡ ነህ ፡ ይሉታል ፡ ጻድቁ ፡ ዐስበ ፡ ጽድቁን ፡ ያግኝ ፡ ብለው ። ንጹሑም ፡ ዐስበ ፡ ንጽሑን ፡ ያግኝ ፡ ብለው ።



፲፪ ፤ ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡

እነሆ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣለሁ ፡

ወዕሤትየኒ ፡ ምስሌየ ፡ ውእቱ ፡

ለምእመናን፡ የምሰጣቸውም፡ ዋጋ፡ የባሕርዬ ፡ ነው ፡

ከመ ፡ እፍድዮ ፡ ለለአሐዱ ፡

(ግጥም) ፡ እመጽእ ፡ ከመ ፡ እፍድዮ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ ዋጋውን ፡ እከፍለው፣ ዘንድ ፡

ወእኩንኖ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ።

እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ አለ ፡ በክፉው ፡ እፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ ለበጎው ፡ እፈርድለት ፡ ዘንድ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ም ፡ ፫ ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፮ ፡ ፲፩ ።

፲፫ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ አልፋ ፡ ወአ ፡

አልፋ ፡ አ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ አ ፡ አብ ፡ ል ፡ ወልድ ፡ ፋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አ ፡ አንድነት ፡ አንድነት፡ ሦስትነት፡ ገንዘቤ ፡ የሚሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡

አነ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወአነ ፡ ደኃራዊ ፡

አልፋ ፡ ያለውን ፡ ቀዳማዊ ፡ አ ፡ ያለውን ፡ ደኃራዊ ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡

ርእስ ፡ ወማኅለቅት ።

ጥንት ፡ ፍጻሜ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ቀዳማዊ ፡ ያለውን፡ ርእስ ፡ ደኃራዊ፡ ያለውን፡ ማኅለቅት፡ ብሎ፡ ደገመው፡ ም ፡ ፩፡ ፬፡ ፳፡

፲፬ ፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ አንጽሑ ፡ አልባሲሆሙ ፡

ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ የለዩ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡

ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥልጣኖሙ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡

በልጅነት ፡ በሚገኝ ፡ ክብር ፡ ሠልጥነው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡

ወይበውእዋ ፡ እንተ ፡ አናቅጺሃ ፡ ለዛ ፡ ሀገር ።

እለ ፡ አንጽሑ ፡ ወእለ ፡ ይበውእዋ ፡ (ግጥም) ፡ ሥራዋን ፡ ሠርተው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ የሚወርሷት ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። አንድም ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ወከመ ፡ ይባእዋ ፡ በልጅነት ፡ በሚገኝ ፡ ክብር ፡ ሠልጥነው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ሥራዋንም ፡ ሠርተው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ይወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ሰውነታቸውን፡ ከኃጢአት ፡ የለዩ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፯ ።

፲፭ ፤ ወይወፅኡ ፡ አፍአ ፡ ኅምስቱ ፡ አክላብ ፡

አምስቱ ፡ አክላብ ፡ ግን ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አፍአ ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ይወጣሉ ፡

እለ ፡ ሥራይ ፡

ሥራይን ፡ የሚያደርጉ ፡

ወዘማውያን ፡

ሴሰኞች ።

ወቀታልያን ፡

ነፍሰ ፡ ገዳዮች ፡

ወእለ ፡ ያመልኩ ፡ አማልክተ ፡

ጣዖትን ፡ የሚያመልኩ ፡

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ግብረ ፡ ሐሰት ።

የሐሰትን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ሁሉ ፡ ይወፅኡ ፡ አፍአ ፡ ላለው ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፳፡፳፯ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ፲ ።


፲፮ ፤ አነ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈነውኩ ፡ መልአክየ ፡ ያስምዕ ፡ ለክሙ ፡ ዘንተ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

ይህን፡ለናንተ፡ለምእመናንይነግራችሁ፡ዘንድ፡መልአኩን፡የሰደድሁ፡እኔ፡ኢየሱስ፡ነኝ፡

አነ ፡ ውእቱ ፡ ሥርው ፡ ዘእምዘመደ ፡ ዳዊት ፡

ከዳዊት፡ ወገን፡ የምሆን፡ይቀውም፡ሥርወ፡ ዕሴይ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረልኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡

www.ethiopianorthodox.org



አምስቱ ፡ አክላብ ፡ ወደገሃነም ፡ ሲጓዙ ።

ቅከበ ፡ ብርሃን ፡ ጽባሐዊ ።

ኮከብ፡ ይሰርቅ ፡ እምያዕቆብ፡ ተብሎ፡ የተነገረልኝ፡ እኔ ፡ ነኝ፡ ም፡ ፩ ፡ ፩ ። ም፡ ፩፡ ፪። ኢሳ ፡ ፲፩፡ ፲። ራእ፡ ፳፡ ፳። ሉቃ፡ ፩፡ ፸፰ ።

፲፯ ፤ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘመርዔት ፡

በምእመናን፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ መንፈስ፡ ቅዱስም፡ ገንዘቤ፡ የሚሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡

ወይቤሉ ፡ ለይምጻእ ፡

ዘመርኤት ፡ ወዘይቤሉ ፡ ምእመናን ፡ ለይምጻእ ፡ ያሉት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገንዘቤ ፡ የሚሆን ፡ እኔ ፡ ነኝ ። አንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገንዘቤ ፡ የሚሆን ፡ (ወዘይቤሉኒ) ፡ ምእመናንም ፡ ለይምጻእ ፡ ያሉኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡



ወዘጸምአኒ ፡ ለይምጻእ ፡

የተጠማ ፡ ይምጣ ፡

ወዘይፈቅድ ፡ ለይንሣእ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ በከንቱ ።

የሻም ፡ ያለዋጋ ፡ ማየ ፡ ሕይወትን ፡ ይውሰድ ፡ አለ ፡ የሻ ፡ በኔ ፡ ይመን ፡ ሳይፅር ፡ ሳይግር ፡ ልጅነትን ፡ ያግኝ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፫ ። ም ፡ ፳፩ ፡ ፮ ።ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፩። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፴፯ ።

፲፰ ፤ ወአነ ፡ ስምዑ ፡ ለኵሉ ፡ ዘይሰምዕ ፡ ቃለ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተነገረውን ፡ ሰምቶ ፡ የሚያስተውል ፡

እመ ፡ ወሰከ ፡ ዲቤሁ ፡ ይዌስክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሁ ፡ መቅሠፍተ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ።

ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ያየው ፡ ብዙ ፡ ነበረ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ከፍሎታል ፡ ብሎ፡ ቢጨምር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ መቅሠፍት ፡ ይጨምርበታል ፡ እንዲጨምርበት ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፮—፳ ።

፲፱ ፤ ወእመኒ፡ አሰሰለ፡እምውስተ፡ቃለ፡ዝንቱ፡ መጽሐፍ፡ያሴስል፡እግዚአብሔር፡ክፍሎ፡እምዕፀ፡ሕይወት፡

ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ፡ ያየው፡ ጥቂት፡ ነበረ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ፡ ወርቅ፡ ጨምሮበታል ፡ እንጅ ፡ ብሎ ፡ ቢከፍል ፡ እግዚአብሔር ፡ በልጅነት ፡ ከሚገኝ ፡ ክብር ፡ ዕድል ፡ ፈንታውን ፡ ጽዋ ፡ ተራውን ፡ ይከፍልበታል ፡ እንዲከፍልበት ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ። አንድም ፡ (ወአነ ፡ ስምዑ) ፡ ዮሐንስ ፡አፈ ወርቅ ፡ ያገኘው ፡ ብዙ ፡ ነበረ ፡ የኋላ ፡ ሰዎች ፡ ከፍለውታል ፡ ብሎ ፡ ቢጨምር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ መቅሠፍት ፡ ይጨምርበታል ፡ እንዲጨምርበት ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ። [illegible] ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ያገኘው ፡ ጥቂት ፡ ነበረ ፡ የኋላ ፡ ሰዎች ፡ ጨምረውበታል ፡ ብሎ ፡ ቢከፍል ፡ እግዚአብሔር ፡ በልጅነት ፡ ከሚገኘው ፡ ክብር ፡ እድል ፡ ፈንታውን ፡ ጽዋ ፡ ተራውን ፡ ይከፍልበታል ፡ እንዲከፍልበት ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ፡

ወእምነ ፡ ሀገር ፡ ቅድስት ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ፡ መጽሐፍ ።

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በተጻፈች ፡ በመንግሥተ፡ ሰማይ ፡ ከሚገኝ ፡ ክብር ፡ ዕድል ፡ ፈንታውን ፡ ጽዋ ፡ ተራውን ፡ ይከፍልበታል ፡ እንዲከፍልበት ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ፡ ዘዳግ፡ ፬፡ ፪ና፡ ፲፪፡ ፴፪ ። ፊል፡ ፬፡ ፫ ።

፳ ፤ ወይበል ፡ ዘሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ እወ ፡

ይህን ፡ የሰማ ፡ አዎን ፡ ይከፍልበታል ፡ አዎን ፡ ይጨምርበታል ፡ ይበል ፡

እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡ አሜን ፡

ፈጥኜ ፡ እመጣለሁና ፡ (ይበል ፡ አሜን) ፡ አሜን ፡ ይጨምርበት ፡ አሜን ፡ ይክፈልበት ፡ ይበል ፡

ነዓ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ።

እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡ ቢለው ፡ የናፍቆት ፡ አነጋገር ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ና ፡ ይላል ። አንድም ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ይበል ፡ አሜን ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይሁን ፡ ና ፡ ይላል ።

፳፩ ፤ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ፡

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ይደረግላችሁ ።

አሜን ።

ይሁን ።

በዝየ ፡ ተፈጸመ ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ አቡቀለምሲስ ፡

ዮሐንስ፡ ያየው፡ ራእይ፡ ደረሰ፡ተፈጸመ ፡


www.ethiopianorthodox.org

ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ ዘርእየ ፡ በሕይወቱ ፡ ራእየ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

አቡቀለምሲስ ፡ ማለት፡ ይኸውም ፡ በሕይ ወቱ ፡ ያየው፡ ራእይ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ራእ ይን፡ ያየ፡ ማለት፡ ነው፡ ቢሉም፡ ይሆናል)፡ አስገሮምሮ ፡ ላስፈጸመን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ይግባው ።

አሜን ።

# የጎንደሩ ፡ ሊቅ ፡ ታላቁ ፡ አለቃ ፡ ጎሩይ ።



አለቃ ፡ ጎሩይ ።

የታላቁ ፡ ሊቅ ፡ የአለቃ ፡ ጎሩይን ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንገልጸለን ።

ታላቁ ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ጎሩይ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳትንና ፡ መጻሕፍተ ፡ ሊቃውንትን ፡ የዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ አድርገው ፡ በጉባኤ ፡ ሲያስተምሩ ፡ አርባ ፡ ዘመን ፡ ያህል ፡ ቆይተዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዕድሚያቸው ፡ እየገፋ ፡ ድካም ፡ ስለ ፡ ተሰማቸው ፡ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳትን ፡ በማስተማር ፡ እስከ ፡ ርደተ ፡ መቃብር ፡ ድረስ ፡ ቆይተዋል ፤ በዚህም ፡ ድካማቸው ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎችን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ተክተዋል ።

፩ኛ ፤ አለቃ ፡ አየለን ፡

፪ኛ ፤ አባ ፡ ዘካርያስን ፡

፫ኛ ፤ ንቡረ ፡ እድ ፡ መኰሪያን ፡

፬ኛ ፤ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ መሐሪን ፡

፭ኛ ፤ መምህር ፡ ወንድማገኘሁን ፡

፮ኛ ፤ አባ ፡ ጌዴዎንን ፡

፯ኛ ፤ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ወልድን ፡

፰ኛ ፤ አባ ፡ ገብረ ፡ አምላክን ፡

እሊህም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ዛሬውኑ ፡ በማስተማር ፡ ይገኛሉ ።

አለቃ ፡ ጎሩይ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ የራቁ ፡ በመሆናቸው ፡ ከቶ ፡ አንድ ፡ ጥሪት ፡ አልነበራቸውም ።

አለቃ ፡ ጎሩይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ የጠበቁ ፡ ዕውነተኛ ፡ መምህር ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ጣርማዊነታቸው ፡ ከዕልፍኞቻቸው ፡ አስቀምጠው ፡ በሚያስፈልጋቸው ፡ ሁሉ ፡ እየረዱ ፡ በየዕለቱ ፡ ይጎ

www.ethiopianorthodox.org

በኙዋቸው ፡ ነበረ ። አለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ በሚያዩበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ከፍቅራቸው ፡ ጽን ዓት ፡ የተነሣ ፡ ደዌያቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይዘነጉት ፡ ነበር ።

አለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ዕሜተ ፡ አንብዕ ፡ የተሰጣቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ አጠገብ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በሰጧቸው ፡ ቤት ፡ ሳሉ ፡ ትሕትና ፡ ገንዘባቸው ፡ የሚሆን ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ሊጠ ይቋቸው ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ለመንገር ፡ በሩ ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ዕንባቸው ፡ በሚጸልይዋት ፡ አርጋኖን ፡ ላይ ፡ ሲንጠበጠብ ፡ ታይቷል ።

እንደ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ሊቃውንቱን ፡ የሚከባከቡ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እኒህን ፡ ሊቅ ፡ እንደ ፡ ዐይናቸው ፡ ብሌን ፡ ይከባከቧቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አስታመው ፡ አማውተው ፡ እስከ ፡ መቃብር ፡ ሸኙተው ፡ ተመልሰዋል ፤ የመምህራን ፡ አምላክ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ይጠብቅልን ፤ የአለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ሞት ፡ ሞት ፡ አ ይባልም ፡ ከልባቸው ፡ ፈልቶ ፡ የአርድእትን ፡ ልቡና ፡ ያረካው ፡ ትርጓሜያቸው ፡ አካል ፡ ገዝቶ ፡ ስለ፡ ተ ገኘላቸው ፡ ነው ።

አለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ከትዕግሥታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የሐረሩ ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ አብ ፡ ዲያብሎስ ፡ ቅሉ ፡ ድል ፡ ሊነሣቸው ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ነገር ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ። አለቃ ፡ ኀሩይ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ በአዲስ ፡ ዓለም ፡ ማርያም ፡ የነበሩት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ በየዕለቱ ፡ ሊጠይቋቸው ፡ ሲመጡ ፡ የነበረ ፡ ፍቅር ፡ ልክ ፡ አልነበረውም ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ አረፉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ጉባኤውን ፡ አጥፈው ፡ በኀዘን ፡ ቆይተው ፡ የፍቅራቸው ፡ ብዛት ፡ ሊታወቅ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ በአረፉ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ አለቃ ፡ ኀሩይ ፡ አርፈው ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተቀበሩ ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሊህን ፡ የሁለቱን ፡ ሊቃውንት ፡ ነፍሳት ፡ በዕረፍት ፡ ቦታ ፡ እንዲያሳርፍልን ፡ እንጸል ያለን ።

የሐረር ፡ ሥላሴ ፡ አለቃ ፤ አለቃ ፡ ለማም ፡ ከአለቃ ፡ አየለ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበውን ፡ ለመስማ ት ፡ ዘወትር ፡ ከአለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ጉባኤ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ። የዲማው ፡ ሊቅ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱም ፡ ዘወትር ፡ ከጉባኤያቸው ፡ እየተገኙ ፡ የተሠወረውን ፡ ምሥጢር ፡ የምሥጢር ፡ ባለቤት ፡ ከሆኑት ፡ ከአ ለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ይረዱ ፡ ነበር ። የአለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ነበር ። ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ በዚህ ፡ መጽሐ ፍ ፡ ገልጸነዋል ።

## የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ።



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ የመጻሕፍተ ፡ ሐዲሳትና ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የአቡሻሕር ፡ መምህር ፡ ሊቅ ፡ መሆናቸውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታውቅላቸው ፡ ስለሆነ ፡ በሰፊው ፡ መግለጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ባለመሆኑ ፤ ትተነዋል ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕድለ ፡ መልካም ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በጉባኤ ፡ የወለዷቸው ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ ከነዚህም ፡ ብዙዎች ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ዛሬ ፡ ለመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መንፈሳውያን ፡ አባት ፡ የሆኑ ፡ ይገኛሉ ። እሊህም ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ያዕቆብ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ታዴዎስ ፡ ናቸው ። ከመልካም ፡ ግንድ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ እንዲገኝ ፡ ከታላቁ ፡ አባታችን ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ የተገኙትም ፡ መምህራኖች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ መልካም ፡ አገልግሎትን ፡ እንዲያስገኙላት ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተዉላት ፡ ቅርስ ፡ ለዘ ለዓለም ፡ የማይረሳ ፡ ስለሆነ ፡ ለኋላ ፡ ትውልድ ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲሆን ፡ ፎቶግራፋቸውን ፡ በዚህ ፡ መጽ ሐፍ ፡ እናያለን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማረሚያ ።

| ገጽ ፡ | ዐምድ ፡ | መሥመር ፡ | ስሕተትና ፡ ግድፈት ። | የታረመ ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ፲፩ | | ፮ | ሕገ ፡ | ሕግ ፡ |
| » | | » | ሕገ ፡ | ሕግ ፡ |
| ፲፮ | ፩ | ፱ | | በአርብዓ ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ ያስተርእዮሙ ፡ |
| ፳፬ | ፪ | ፲፰ | | ወፎናጦስ ፡ |
| ፳፮ | ፩ | ፴ | | ራእየ ፡ ይሬእዩ ፡ |
| ፴፮ | ፩ | ፲፬ | | ያዋሐዶው ፡ |
| ፺፩ | ፩ | ፳፰ | ይጼሊ ፡ | ይሄሊ ፡ |
| ፻፸፩ | ፪ | ፮ | ወሀዉሉ ፡ | ወሀለዉ ፡ |
| ፪፻፳ | ፪ | ፪ | | አላ ፡ ለሊነ ፡ ርኢነ ፡ ዕበዮ ፡ |
| ፫፻፳፱ | ፪ | ፳፰ | ታስተሰናሉ ፡ | ታስተሰናኡ ፡ |
| ፫፻፴ | ፪ | ፳፬ | | ከመ ፡ ተሀቡ ፡ |
| ፫፻፵፪ | ፪ | ፰ | ወተመጠውዋ ፡ | ወተመጠዋ ፡ |
| ፫፻፷፮ | ፪ | ፯ | | ወይዘምዉ ፡ |
| ፫፻፹፮ | ፪ | ፩ | | ወበጊዜሃ ፡ ኮንኩ ፡ በመንፈስ ፡ |
| ፬፻ | ፪ | ፰ | ወሶበ ፡ አውረደ ፡ | ወአውረደ ፡ |
| ፬፻፵፫ | ፪ | ፳፩ | | ወእምአፉሁ ፡ ለአንበሳ ፡ |

www.ethiopianorthodox.org